# ትርጓሜ መኃልየ ፲ቱ ወ፭ቱ ነቢያት
# አንድምታ
# ወምቅናየ ነቢያት ሐተታ።

ከቀድሞ ሊቃውንት አባቶች ጀምሮ ሲወርድ
ሲዋረድ የመጣው
ንባቡና ትርጓሜው (በአንድምታ)

አዘጋጅ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል።

፲፱፻፺ ዓ.ም
አዲስ አበባ

**መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው**

ያለ አዘጋጁ ፈቃድ መለወጥም ሆነ በከፊል ማሳተም
በሕግ የተከለከለ ነው::

አዘጋጅ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባዩበል

**ረዳት አዘጋጆች**
ተማሪ ደረጀ ዓለም ወሰኑ
እና
ተማሪ ዘውድነሽ አዳነ

## ምስጋና

፩ ከገጸ ንባብ እስከ ትርጉም መርምረው አቃንተው ለኅትመት እንዲበቃ ጊዜያቸዉን መሥዋዕት አድርገው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለረዱኝ በጎንደር የአራቱ ጉባኤያት መምህርና የትርጓሜ መጻሕፍት ምስክር ለሆኑት እንዲሁም የመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ለታላቁ ሊቅ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ::
በተጨማሪም ለትርጓሜ መጻሕፍት ተማሪዎቻቸው ለመምህር ፍቅረ ማርያም ጌትነት እና ለመምህር ኃይለ እግዚእ አሰፋ::

፪ በምሥራቅ ጎጃም ርእሰ አድባራት መርጡለ ማርያም ለቅኔ መምህሩ ለመሪጌታ ዲበ ኩሉ ዳምጤ

፫. ለቤተ መዛግብትና ለቤተ መጻሕፍት ድርጅት በኢትዮጵያ ጥናትና ጥናታዊ ሥነ-ጽሑፍ የጥንታውያን ጽሑፎች ክፍል ባለሙያዎች::

### የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ

፩ በጎንደር ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ የአቋቋም ምስክር ለነበሩት ለታላቁ ሊቅ መጋቤ አዕላፍ ሄኖክ ወልደ ሚካኤል::

፪ ለታላቁ ሊቅ ለመምህር ዲበ ኩሉ እምባዬ የፈለገ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፍኖተ ሰላም:

፫ ለመምህር ጎሩደ ገብረ ሥላሴ የመጽሐፍ መምህር ጥጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዲሁም ለትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ይሁንልኝ::




ምስለ ፍቁር ወልዳ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ



ከ ፲፱፻፲፱ - ፲፱፻፺፯ ዓ.ም
የቤተ ክርስቲያን ዓይን የሆኑት የአቋቋም ምስክር
ታላቁ ሊቅ መጋቤ አዕላፍ ሄኖክ ወልደሚካኤል እኒህ
ነበሩ



አዘጋጅ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል

## ማውጫ

ገጽ


1. የ፲፭ቱ ነቢያት ማኃልይ የአርእስት ታሪክ.........1-14
2. ጸሎተ ሙሴ ..........................................14-21
3. ጸሎተ ሙሴ ዘዳግም ..................................21-31
4. ጸሎተ ሙሴ ዘሣልስ ..................................31-42
5. ጸሎተ ሐና እመ: ሳሙኤል ነቢይ ...................42-52
6. ጸሎተ ሕዝቅያስ ......................................52-57
7. ጸሎተ ምናሴ .........................................57-61
8. ጸሎተ ዮናስ..........................................61-65
9. ጸሎተ ዳንኤል .......................................65-77
10. ጸሎተ ፫ቱ ደቂቅ ....................................77-83
11. ጸሎተ ዕንባቆም ......................................83-95
12. ጸሎተ ኢሳይያስ ....................................95-103
13. ጸሎተ እግዝእትነ: ማርያም .......................103-117
14. ጸሎተ ዘካርያስ ካህን ...............................117-127
15. ጸሎተ ስምዖን ነቢይ................................127-129


## የአንድምታ ትርጉም ጥቅሶችና መገኛቸው

## ከገጽ 129-133

## ማውጫ

## የክፍል ሁለት: የነቢያት ቃል ሐተታ

ገጽ


1. ስለ መኃልይ ትርጉም ..........................135-136
2. ስለ ነቢይ ትርጉም ...................................136
3. ስለ ጸሎት ..............................................137
4. ስለ ሙሴ የልደት ዘመንና የግብጽ ተልዕኮ ....137-139
5. ስለ እስራኤል ከግብጽ አወጣጥ .......................139
6. ስለ ባሕረ ኤርትራ ....................................139
7. ከአብርሃም እስከ እስራኤል ነፃ መውጣት ድረስ
   ያሉት የሦስቱ ፈርዖኖች ልዩ ስም ...................140
8. ስለ ሰማይ .........................................140-141
9. ስለ ምድር ...............................................141
10. የአራቱ ወንዞች ስምና መነሻ መድረሻ .......141-143
11. ስለ እሳትና ባሕርይው ................................143
12. ስለ ሲኦል ...............................................144
13. ስለ ኦሪት አጻጻፍ .....................................144
14. ስለ ሙሴ አገልግሎትና ዕረፍት .......................145
15. ስለነቢይት ሐና የልደት ዘመን .......................145
16. ስለ ስእለት ..............................................146
17. ስለ ሕዝቅያስ የትውልድ ዘመን ................146-147

18. ስለ ንጉሡ ምናሴ የትውልድ ዘመንና ንስሓ ......147
19. ስለ ውቅያኖስ ..............................148
20. ስለ ብሔሞት ..............................148
21. ስለ ንስሓ ትርጉም ..............................148
22. ስለ ነቢዩ ዮናስ የትውልድ ዘመን ..................148
23. ስለ ዐንበሪ..............................148
24. ስለ መልሕቅ ..............................149
25. ስለ ነነዌ..............................149
26. ስለ ነቢዩ ዳንኤል እና የትንቢቱ ፍጻሜ ....149-150
27. ስለ ኢየሩሳሌም ጥንታዊ ስም ..............150-151
28. ስለ እናንያ አዛርያ ሚሳኤል ዘላለማዊ ምስጋና እና ስሞቻቸው ..............................151-156
29. ስለ ዕንባቆም የትውልድ ዘመንና ዕረፍት ..156-157
30. ስለ ቴማን ትርጉም ..............................157
31. ስለ ፋራን ..............................157
32. ስለ መብረቅ ..............................157-158
33. ስለ ኢሳይያስ የትውልድ ዘመንና ትንቢቱ..158-159
34. ስለ ድንግል ማርያም ዘመንና ምስጋናዋ.........159
35. ስለ ካህኑ ዘካርያስ የልደት ዘመንና የልጁ ዮሐንስ ልደት ..............................159-160
36. ስለ ዘካርያስ እረፍትና የደሙ ጩኸት ....160-161
37. ስለ ካህኑ ስምዖን የትውልድ ዘመንና ዕረፍቱ...162

# መቅድም

የመጽሐፉ ስም መክሥተ ነቢያት ወምቅናየ ነቢያት በሚል ስያሜ ተሰይሟል።

## መክሥት

፩. **መክሥት፡-** ማለት የሚገልጽ ገላጭ ማሰት ሲሆን ነቢያትንና ሥራዎቻቸውን /ትንቢቶቻቸውን/ የሚገልጽ ማስት ነው። በተጨማሪም ነቢያትና ሥራዎቻቸው /ትንቢቶቻቸው / የሚገለጹበትና የሚታወቁበት ማለት ነው።

፪. **ምቅናይ፡-** ማለት በትርጉም መግዣ ማስገዣ ማለት ሲሆን በምሥጢር ነቢያት የሚቃኙበት የሚዳሰሱበት ታሪካቸውም የሚገለጽበት ማለት ነው።
ስለዚህ ምቅናየ ነቢያት ተባለ። ወ፡ በመክሥትና በምቅናይ መካከል የገባ አጫፋሪና አገናኝ ቃል ነው።
ከዚህ በመቀጠል ከየአንድ አንዱ ነቢይ የኃይለ ቃል ጥቅስን እናቀርባለን።
ዘአቅደመ ነጊረ በእፈነቢያቲሁ ወበመጻሕፍቲሁ። በነቢያቱ አፍና በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋን የተናገረ ነው። ሮሜ ፩÷፪
ዳግመኛም አቅዲሙ ነገረ በኦሪት ከመ ይመጽእ ወልድ በስብሐት እንዲል ቅዱስ ያሬድ ። በእነዚህ በ፪ቱ ጥቅሶች ፲፩ ቱ ሁሉ ይቃኛሉ /ይገለጻሉ/።

፫. **በሊቀ ነቢያት ሙሴ፡-** ወይቤ እብጻሕ ፡ዘ፡ ራእየ ዐቢየ እፎ ኢትውዒ ዛ ዕፀት። ሙሴም ይህች እንጨት እንዴት እትቃጠልም? ይህን ደግ ራእይ ከዚህ ደርሼ ልይ አለ። ዘጸ ፫÷፫ ዘዳ ፴፫÷፲፮

ይህ ማለት በምሥጢር ሙሴ በአምሳለ ዕፀ ጳጦስ ድንግል ማርያም እንደሆነች በመጀመሪያ አስቀድሞ ተናግሯል::

፪. **በነቢይት ሐና**:- ወተፈሥሕኩ በአድኅኖትከ::
ስጊዜው ልመናዋን ስለሰማት: በትድግናህ /በማዳንህ/ ደስ አለኝ አለች እንጂ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን እንደሚያድን ተገልጸላት ትንቢትን ስትናገር ነው:: ፩ኛ ሳሙ ፪:፩

፫. **በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ**:- ወአንሣእካ ለነፍስየ::
ነፍሴን ከሞት አዳንካት የሚለው ለጊዜው ለእርሱ ቢሆንም ፍጻሜው ግን የሰሎተ ዓርብንና የዕለተ ትንሣኤን ትንቢት ያመለክታል::

፬. **በንጉሡ ምናሴ**:- እስመ አኮ ለጻድቅ ዘገበርከ ለንስሓ አላ ተመየጥ ንስሓ ዚአየ ለኃጥእ:: ንስሓን የሠራሃው ለጻድቅ ሰው አይደለም የእኔን የኃጥእን ንስሓ ወደማየት ተመለስ /ይቅር በል/ እንጂ:: ፪ኛ ዜና መዋ በግእዙ ፴፫፥፰ የሚለው ቃል ከሐዲስ ቃል ጋር የሚስማማ በመሆኑ::
ለዚህ ማስረጃ ኢመጻእኩ እጸውእ ጻድቃን አላ ለንስሓ ኃጥአን:: ኃጢአተኞችን ወደ ንስሓ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም:: ማቴ ፱፥፲፫

፭. **በነቢዩ ዮናስ**:- ዮናስ የራሱ የክርስቶስ ምሳሌ ስመሆኑ ፫ ቀን በከርሠ ዐንበሪ ማደርና ከባሕር መውጣት የክርስቶስ ፫ ቀን በከርሠ መቃብር አድሮ መነሣት በቂ ማስረጃ ነው:: ዮናስ ፪፥፪ ማቴ፲፪፥፴፱-፵፪

፮ **በነቢዩ ዳንኤል**:- ወትትሐነጽ ኢየሩሳሌም እስከ ክርስቶስ ንጉሥ::
ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ሆና ትሠራለች:: ስማያዊ እምላክም በሐዲስ ክርስቶስ እንዲባል ገልጿል:: ዳን ፱፥፳፭ ማቴ ፩፥፲፮ .



፯. **<u>በ፫ቱ ደቂቅ</u>**:- ለፈጣሪያቸው በጸለዩት ጸሎት ውስጥ ፴፫ ቃላትን መናገራቸው ክርስቶስ በዚች ምድር ላይ ለ፴፫ ዓመት ያህል እንደሚመላለስ ተገልጾላቸው ትንቢትን በመናገራቸው::

፰.**<u>በነቢዩ ዕንባቆም</u>**:- በማዕከለ ፪ቱ እንስሳ ርኢኩከ: ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አእምረከ: ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ አስ.በወከ:: በሁለቱ እንስሳዎች /አድግና ላሕም/ መካከል አየሁህ በመት እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ:: ጊዜውም እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ ብሎ የክርስቶስን ልደቱን ስቅለቱን ትንሣኤውን በመተንበዩ:: ዕንባ ፫፥፪::

፱. **<u>በነቢዩ ኢሳይያስ</u>**:- ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ::
እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ብሎ ደረቅ ትንቢትን ስለተናገረ:: ኢሳ ፯፥፲፬

፲. **<u>በቅድስት ድንግል ማርያም</u>**:-ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኩሉ ትውልድ::
እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል በማለት ድንቅ ሥራንም ሠርቶልኛልና ስሙ ቅዱስ ነው ስትል: የጻነሰችውም የንስም ፈጣሪ መሆኑን ይህንንም ክብር የሰጣት እርሱ መሆኑን ገልጻ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል አለች:: ትንቢቱም የተፈጸመላት አማናዊት ድንግል እርሷ ናትና:: ሉቃ ፩፥፵፰ ዘፍ ፫፥፩

፲፩ **<u>በካህኑና በነቢዩ ዘካርያስ</u>**:- አንሥአ ለነ ቀርነ መድኃኒትነ እምቤተ ዳዊት ገብሩ:: ከባለሟሉ ከዳዊት ወገን የድኅነታችን ቀርን ክርስቶስን ያስነሳልን ብሎ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለሙን ማዳኑን ተናግሯል::
በሣህሉ ወበምሕረቱ ለእምላክነ: ለዘሐወጸነ እምእርያም:: ከስማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በፍጹም ይቅርታውና በቸርነቱ

## መቅድም

ለጎበኘን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል ብሎ ተናግሮአልና:: ሉቃ ፩፥፷፰-፸፱

፲፪. በነቢዩና በካህኑ ስምዖን፦ የነቢዩ ኢሳይያስን ትንቢት:: ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ የሚለውን አማናዊ ትንቢት በሚጽፍበት ጊዜ ትንቢቱ ተፈጽሞ ጌታችን ተወልዶ በ፵ ቀኑ ቤተመቅደስ ገብቶ እንደሚታቀፈው በመንፈስ ቅዱስ የተነገረው ምስጢር ተፈጽሞለት እስመ ርእያ አዕይንትየ አድኅኖተከ: ዘአስተዳሎከ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ:: ከሁሉ አስቀድሞ ያዘጋጀኸው ትድግናህን ወይም ማዳንህን ዓይኖቼ አይተዋልና ብሎ ያየውን ነገር መስክሮ በዕለተ ዐርብም እንደሚሰቀልና ዓለምን እንደሚያድን የተናገረው ትንቢት የነቢያትን ትንቢት ሁሉ አጠቃሎ ስለሚገልጽና ለትንቢቶቻቸው መጨረሻና መደምደሚያ የሚሆነውን ትንቢት በመተንበዩ::
እኛም በዚሁ ከሙሴ እስከ ስምዖን በአሉት በ፲፭ቱ ነቢያት ውስጥ ያለውን የመክሥተ ቃላት መግለጫን እናጠቃልላለን::

ከዚህ በመቀጠል መጀመሪያ ወደተነሣንበት ስንመለስ ይህን መጽሐፍ ከዋናው አንድምታ ትርጉም ጎን ለጎን እንዲዘጋጅ ያደረግንበት ምክንያት ትንቢት ከትንቢት: ምስጋና ከምስጋና: ታሪክ ከታሪክ: ትርጉም ከትርጉም ምሥጢር ከምሥጢር ጋራ ነውና::

፩ ለዚህም አንድ አንድ ማስረጃዎችን እናቀርባለን::
ከመዝሙረ ዳዊት: መዝሙረ ክርስቶስ
፪ ከትንቢተ ኢሳይያስ ዕርገተ ኢሳይያስ /ብሉይ አዋልድ/
፫ ከትንቢተ ኤርምያስ: ሰቆቃው
፬ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት: ሄርማ
፭ ከቅዱስ ኤፍሬም ድርሰት /ውዳሴ ማርያም/ መልክአ ውዳሴ: እንደተውጣጣ ሁሉ በዚህ መጽሐፍም ውስጥ እንደዚሁ የነቢያትን ኃይለ ቃልና ታሪክ እንቃኛለን::

## ማብራሪያ

፩ኛ. ከዘወትር ምስጋና /ስብሐተ ነግህ/ የተለመደው ምስጋና ከተደረሰ /ከተፈጸመ/ በኋላ ምቅናይ ተብሎ የመጀመሪያው መደበኛ ድርሰትን መስሎ በውስጡ ስርዋጽ እየጠቀሰ ይሄዳል:: ስርዋጽ ማለት ማቅኛ ማስረጃ ማስታወቂያ በነገር መካከል የሚገባ ነው:: ይህም ምቅናይ ይባላል::

፪ኛ. በዐቢይ ጾም እንደዚሁ በምቅናይ ውስጥ ስርዋጽ ይገኛል::

፫ኛ. በዘመነ ጽጌ:

፬ኛ. በዕለተ ሰንበት:

፭ኛ. በዘመነ ስብከት::

ስለዚህ ይህም ምቅናየ ነቢያት ተብሎ ከዋናው አንድምታ ትርጉም ቀጥሎ ኃይለ ቃሉን እየተረጉመና ታሪኩን እስከ ዘመኑ እየቃኘ በግልጽ የሚያስረዳ በመሆኑ መክሥተ ነቢያት ወምቅናየ ነቢያት በሚል ስም ተሰይሞ ቀርቧል::

ከዚህ በመቀጠል በምዕራፍ ሳይሆን በአንቀጽ በአንቀጽ ተከፍሎ /ተዘጋጅቶ/ የቀረበ መሆኑንም ለአንባብያን እናሳስባለን::

## የመግቢያ ማሳሰቢያ

አንቀጽ ማለት በር መውጫ መግቢያ ማለት ሲሆን ሌሎች ትርጉሞችም አሉት በተከታታይ ዝርዝሩን እናቀርባለን።

፩ ቤትና ባለቤት፦ የመውጫና የመግቢያ በር ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ ለቤቱም መልክና ውበት የሚሰጠው ለበሩ መውጫና መግቢያ ሲኖረው ነው። ባለቤቱም በቤቱ ውስጥ እንግዳን የሚቀበልና የሚያስተናግድ መውጫና መግቢያውን አልፎ ነው። እንግዳውም ግቢውን አልፎ ወደ በሩና ወደ ቤት ገብቶ ይስተናገዳል። ይህም የመጽሐፍ ክፍል የአንዱን ነቢይ ወይም የአንዱን ኃይለ ቃል ትርጉም ከተረጉመ በኋላ ወደዋናው ቋሚ ታሪክ ምሥጢርና ሐተታ ገብቶ ከመነሻው እስከ መድረሻው ያለውን ታሪክና ምሥጢር ያስረዳል።

፪ አንቀጽ፦ ማለት የመጽሐፍ ክፍል ምዕራፍ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ አንቀጽና ምዕራፍ የተለያዩ አለመሆናቸውን ከዚህ ትርጉም መረዳት እንችላለን።

፫. አንቀጽ፦ ማለት የዘማች ቃል ማሠሪያ ማለት ነው። ይህም ክፍል የተፈላጊውን ኃይለ ቃል ዘርዝሮ በመጨረሻ በቡቱ ማስረጃ ለታሪኩ መነሻና መድረሻ ማሠሪያና መደምደሚያ ሰጥቶ ዝርዝሩን ይጨርሳል።

፬. አንቀጽ ፦ ማለት የዜማ ስረይ ማለት ነው። ለሌላ ዜማ ምልክት የሚሆን አብነት ማለት ሲሆን የዜማው ጠባይ ብዙ ዓይነትና ብዙ መንገድ /ድርብ/ ሲኖረውና ከአንድ በላይ የሚሆንበት ሲገኝ አንቀጽ ይባላል።

የመጽሐፉም አዘገጃጀትና መንገድ ተደራራቢ ትርጉም ምሥጢርና ታሪክ ያለው ስለሆነ።

፭. አንቀጽ፦ ሃሌታ ተብሎ በኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ድርሰት የተወሰነ ስያሜ አለ። ሃሌ /ሃሌታ/ ማለት ደግሞ አዲስ ምስጋና፡ መዝሙር፡ ቅኔ፡ ግናይ አገልግሎት ማለት ነው። አይኑ ግናይ ወአይኑ አኰቴት። ምን መገዛት ነው ምን ምስጋና ነው እንዳለ ዮሐንስ ወልደ ነጕድጓድ በመጽሐፈ ቅዳሴ።



በዚህም ሳይ መዝሙር በሃሌ
ነገር በምሳሌ
ጠጅ በብርሌ እንዲሉ። ስለዚህ ሃሌታና አልልታ /መንፈሳዊውን/ አንድ እንደሆነ ሁሉ የአንድምታ ትርጉሙን ተከትሎ የተዘጋጀው ይህ የመጽሐፍ ክፍል ለአንድምታው የትርጉም ልጅ ነው። ልጅ ከአባትና ከእናቱ እንደሚገኝ ሁሉ ይህም ክፍል መከረተ ነቢያት ወምቅናየ ነቢያት የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። በመጀመሪያው መቅድም ላይና በዚህ የመግቢያ ማሳሰቢያ ክፍል ያቀረብናቸውን ማስረጃዎችንና ማስገንዘቢያዎችን በዚህ አጠናቀን ወደ ዋናው የነቢያት መኃልይ አንድምታ ትርጉም ገብተን እንመለከታለን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።*

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::**

መኃልየ ነቢያት ወጸሎቱ ለሙሴ:: ሙሴ ማለት ምልክአም ማለት ነው:: ምልክእምም ማለት መልአክ እግዚአብሔር ማለት ነው:: ኋላ ግን ተርሙት ወለተ ፈርዖን ከውሃ ስላገኘችው ዕጓለ ማይ ተብሏል:: እማይ ዘአውጻእክዎ እማይ ዘረከብክዎ ስትል::

ታሪክ

ሴሩህ የሚባል ሰው ነበረ:: ብኑ/ብህኑ/ የሚባል ልጅ ነበረው::

ወእንዘ በቆዑ ተመስጠ ሕፃኑ: ወእንዘ ቆዑም ያላል:: ገና በሕፃንነቱ ሳለ ሞተበት:: ኀዘን ጸናበት ኀዘን ሲጸናበት አይተው ዘመዶቹ እንጨት ጠርበው ዘይት ቀብተው ልብሱን አልብሰው ልጅህ ብኑ ይኸውልህ አሉት:: ልጄ ብኑ ነህ? አለው:: ሲያከናውኑት /ሲያጥቡት ሲገንዙት/ ሰይጣን ከውስጡ አድሮ እ አለው:: አምላክ ቢሆን ነው እንጂ አምላክ ካልሆነ ይናገራል? ብለው ሲያመልኩት ኖሩ::

ሴሩህ ናኮርን ናኮር ታራን ታራ አብርሃምን አራንን ናኮርን ይወልዳል:: ይህ አብርሃም አባቱ ታራ ጣዖት እየጠረበ እየሰጠው እሱ እየሸጠ ይመለሳል:: ከዕለታት አንድ ቀን ረክሶበት /የሚገዛው አጥቶ/ ሲመለስ ከዋዕየ ፀሐይ የተነሣ ደክሞት ከዛፍ ጥላ ሥር አርፎ ሳለ አምላክ አይደለህምን? ራበኝ አብላኝ አለው:: ዝም አለው:: ባይሆንም የደከመው ሰው ሲያጫውቱት ይጸናልና አጫውተኝ አለው:: የማይመልስለት ሆነ እንኪያ ደንጊያ ተሸክሜ እሄዳለሁ? ብሎ ያን ቀጥቅጦ ጥሎ ጊዜው ቀትር ነበርና አቅንቶ ቢያይ ፀሐይ መልታ ሰፍታ ስታበራ አይቶ አምላክስ ይቺ ናት አለ:: ቀጥሎ ሲያስብ ደፈር ጠፈር ሲከለክላት አየ ይቺ ስትገባ ማን ይገዛል ብሎ አምላክ ፀሐይ ተናበበኒ ፀሐይን የፈጠርክ አምላክ ተገለጽልኝ አለ::

ያን ጊዜ ጌታ አብርሃም አብርሃም ነዐ ጸእ እምብሔርከ ወተፈለጥ እምአዝማዲከ ብሎ ፳፪ቱን ሥነ-ፍጥረት ነገረው:: ሄዶ አባቱ ሰማዩን ምድሩን ባሕሩን የብሱን የፈጠረ አምላክ አለሳ?



ወዲያውስ ምንት ውእቱ ዘንረክብ እምኀቤሁ ተድላ ወረድኤተ::

ከጣዖቱ የምናገኘው ጥቅም ምንድር ነው አለው:: ልጄ ፈጣሪስ እንዳይደለ አውቃለሁ እንደሀገሩ ይናገሩ እንደወንዙ ይሻገሩ ብዬ ነው እንጂ:: ነገር ግን የዚህ አገር ሰዎች ልቡናቸው በፍቅረ ጣዖት ተመስጧል: ይገድሉሃል ዝም በል አለው: እሺ ያለ መስሎ ሄዶ ቤተ ጣዖቱን አቃጠለው::

ወሠረረ አራን ይላል:: ጣዖቱን ሲያመጣ ገባ እሳት ተሻምቶ አስቀርቶታል:: ለማዕተ ጣዖት ሆኗል:: ያን ጊዜ አባቱን የወንድሙ ልጅ ሎጥን ይዞ ካራን ወጣ:: ከዚያ ፳፱ ዓመት ኖረ:: አባቱ ሞተ አባቱን ቀብሮ ከካራን ወጣ:: ብሔረ ከነዓንን ከዚህ እስከዚህ አወርስሃለሁ ብሎ በዓይነ ሥጋ አሳየው በእግረ ሥጋ አስረገጠው:: ብሔረ እስራኤልስ ሰፊ ናት ብሎ ቅርብ ቅርቡን በዓይነ ሥጋ አሳየው በእግረ ሥጋ አስረገጠው:: ሩቅ ሩቁን በዓይነ ኅሊና አሳየው በእግረ ኅሊና አስረገጠው:: ከዚያ ሲኖር ለወንድሙ ልጅ ለሎጥ የአባትህን ክብት ውሰድ ብሎ ከፍሎ ሰጠው:: ከብታቸው በዛ ኖሎተ አብርሃምና ኖሎተ ሎጥ /የአብርሃምና የሎጥ እረኞች/ በሣር በውሃ ምክንያት ይጣሉ ጀመር::

ለምንት ንጻባዕ እንበ አኀው ንሕነ ተፈለጥ የማነ አው ፀጋመ:: ቀኝ ግራ ብለህ ተለይ አለው::

ወርእየ አሕቃላቲሃ ለዮርዳኖስ ይላል:: አሻግሮ ቢያይ ያች ሰዶም እምሳሲሃ ለገነት ይላታል:: እጅግ ልምልምት ነበረች ሄዶ ከዚያች ተቀመጠ:: ፭ቱ ነገሥተ ሰዶም ለ፬ቱ ነገሥተ ኮሎዶጎሞር ፲፪ ዓመት ሲገብሩ ኖሩ:: በ፲፫ተኛው ዓመት በሰማይ የለ ዱር በሰዶም የለ ግብር ብለው ግብር አቀለጡ /ከለከሉ/:: መጥተው ገጠሟቸው ፭ቱ ነገሥተ ሰዶም ድል ሆኑ ሎጥ ተማረከ ኸረ የወንድምህ ልጅ ሎጥ ተማረከ ብለው ለአብርሃም ነገሩት:: ቤተሰቡን ቢያወጣ /ቢያስቆጥር/ ፫፻፲፰ ጭፍራ አገኘ:: ኤስኮል መምሬ የሚባሉ አርበኞች ነበሩ:: እነዚያን እርዱኝ ብሎ በቆላተ ሴዊ::

እንተ ይእቲ ባሕረ ጼው ይላታል:: ግዳይ /ምርኮ/ ሲያስጥል አደጋ ጥሎ ወንድሙን መልሷል:: ይህ ምሳሌ ነው:

አብርሃም የወለደ እግዚአብሔር፡ ሎጥ የሃይማኖት፡ ፫፻፲፰ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ምሳሌ፡ ከ፭ቱ ነገሥተ ሰዶም ፬ቱ ሞተው አንዱ ቀርቶ ነበር፡፡ ቀረብ ብሎ ገንዘብ አልልህም አገር ያለ ሰው እንዳይለማ ታውቃለህ ሰውን ስጠኝ አለው፡፡

አሌዕል አደውየ ውስተ ሰማይ ከመ ኢይነሥእ እምንዋይከ ኢ ፈትለ ወኢ ቶታነ አሣዕን ከመ ኢትበል አነ አብዐልክዎ ለአብርሃም አለው፡፡

ባሕቱ ይንሥኡ መክፈልቶሙ ኤስኬል ወመምሬ አለው፡፡

አዘዘብን እንዳይሉ ጌታ ገንዘብ በመጥፋቱ ደስ አለው፡፡

አብርሃም ብዙኀ ዐስብክ በንቤየ አለው፡፡ ምንት ይበቊዐኒ አኮኑ ኢያቡር ወልደ ዘመድየ ዘይወርሰኒ አለው፡፡ አኮ ኢያቡር ዘይወርሰከ ንዋየከ አላ ወልድከ ዘይወጽእ እምሐቌከ ውእቱ ይወርስከ ንዋየከ አለው፡፡ ሌሊት ከተራራ አውጥቶ ኍልቊ ከዋክብተ ሰማይ አለው፡፡

አኈለ ኢይክል ኍልቆቶሙ አለው፡፡ ከማሁ ኢይትኌለቊ ዘርዕከ /ኢይትኌለቁ ደቂቅከ/ አለው፡፡ ልጅህ የልጅ ልጅህ እንዲህ አይቆጠርም/ አይቆጠሩም/ ብሎታል፡፡ በከዋክብት የተመሰሉ እስራኤል ልጆቹ፡ በአሸዋ የተመሰሉ አሕዛብ ልጆቹ ናቸው፡፡ አንድም በከዋክብት የተመሰሉ በሥጋም በሃይማኖትም የሚወልዳቸው፡ በአሸዋ የተመሰሉ በሥጋ ብቻ የሚወልዳቸው፡ አንድም በከዋክብት የተመሰሉ ጻድቃን ልጆቹ፡ በአሸዋ የተመሰሉ ኃጥአን ልጆቹ ናቸው፡፡ ይህስ የሚወርሱበት ምን ጊዜ ነው አለው፡፡

አምጽእ ላህመ ዘ፫ቱ ዓመቱ፡ ወአጣሌ ዘ፫ቱ ዓመቱ፡ ወበግዐ ዘ፫ቱ ዓመቱ፡ ርግበ ወማዕነቀ አለው፡፡ ይህን ሰውተህ አንብር ዘተመትረ በአንጻረ ቢጹ፡፡ ከሁለት ከሁለት ክፍለህ በአንጻር በአንጻሩ አኑረው፡፡ ሰአዕዋፍሰ ኢትምትሮን አዕዋፍን ግን ገዝግዘህ ተዋቸው አትቁረጣቸው አለው፡፡ እንዳለው አደረገ፡፡ ወመጽአ ድንጋጼ ለአብራም ይላል፡፡ እንደ እንቅልፍ ወጅብ አደረገው በሥጋው ላይ እሳት ነፋስ ጨለማ ሲመላለስ አዕዋፍ እንበላሰን ብለው ሲመጡ በዘንግ ሲከለክላቸው ያያል፡፡ ይህም ምሳሌ ነው፡፡ እሳት ነፋስ ጨለማ የመከራቸው፡ ሥጋ የእስራኤል፡ አዕዋፍ የአሕዛብ፡ ዘንግ የኪዳነ አብርሃም፡፡ አዕዋፍ እንበላሰን ሲሉ በዘንግ



ሲከለክላቸው ማየቱ አሕዛብ እስራኤልን እናጠፋሰን ሲሉ በኪዳነ አብርሃም ተጠብቀው የመኖራቸው ምሳሌ፡፡ ከ፪ ከፈለው ማለቱ ፪፻፲፭ ዘመን በከነዓን ፪፻፲፭ ዘመን በግብፅ የመኖራቸው፡፡ በአንጻር አኑረው ማለቱ መከራው በጽርዕ በሜዶን በፋርስ በባቢሎን ተበትነው እንደተቀበሉት አይደለም፡፡ በአንድ በግብጽ ሁነው ተቀብለውታልና፡፡ ከዚያውም ዘንድ በምድረ ጌሴም፡፡ ዘ፫ቱ፡ ዓመቱ ማለቱ በ፫ኛው ትውልድ በያዕቆብ ግብጽ የመውረዳቸው፡፡ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብን በላም መስላቸው፡፡ ላም ከሁለ ትበረታለች በመጀመሪያው ፈርዖን በርትተው የመገዛታቸው /የመኖራቸው/ በፍየል መስላቸው ፍየል ከላም ትደክማለች ከበግ ትበረታለች በሁለተኛው ፈርዖን እጅግም ሳይበረቱ እጅግም ሳይደክሙ የመኖራቸው በበግ መስላቸው፡፡ በግ ከሁሉ ትደክማለች በሦስተኛው ፈርዖን ፈጽመው የመድከማቸው፡፡ ርግብ የሙሴ ስለ የዋህነቱ፡፡ ማዕነቅ የአሮን፡፡ አንድም ርግብ የአሮን ርግብ ከተማ እንዳትለቅ አሮንም በዘመዶቹ መካከል ይኖራልና፡፡ ዋኖስ መሥዋዕት እንድትሆን አሮንም መሥዋዕት ያቀርባልና፡፡ የአሮን ማዕነቅ የሙሴ ኑሮዋ በረሃ ነው፡፡ ተሰዶ ምድረ ምድያም የመሄዱ መገዝገዛቸው በእስራኤል መከራ የማዘናቸው አለመቆረጣቸው ሙሴን አሮንን ፈጽሞ መከራ እንደ እስራኤል አላገኛቸውም፡፡ ላህም የጌታ፡ ጠሊ የሐዋርያት፡ በግዕ የአርድእት፡፡ አንድም ስለማዕረጋቸው፡ ጠሊ የአርድእት፡ በግዕ የሐዋርያት፡ ርግብ የእመቤታችን፡ ማዕነቅ የዮሐንስ፡ ወልደ ነጐድጓድ፡፡ መገዝገዛቸው በጌታ ሞት የማዘናቸው አለመቆረጣቸው እመቤታችን ዮሐንስ በሰማዕትነት አልሞቱም፡፡ አንድም ዘ፫ቱ ዓመቱ፡ ማለቱ ሦስት ላም ሦስት ፍየል ሦስት በግ ሲል ነው ብሎ አንድ ወገን የመሥዋዕትነቱ ምሳሌ፡፡ ይህን ከሁለት ሲከፍሉት ፲፰ ይሆናል፡፡ ርግብና ዋኖስ ባሉበት /ሲጨመሩ/ ፳ ይሆናል፡፡ ተስፋውን ለአብርሃም በነገረው በሁለት ሺህ ዘመን ጌታ ከቤተ አብርሃም ሰው የመሆኑ፡ ሥጋ የመልበሱ ምሳሌ፡፡ በሦስተኛው ፈርዖን በጣም ጨርሰው የደከሙበት እንደምን ነው ቢሉ መምክሮን መሚክሮን የሚባሉ የከነዓን ነገሥታት ነበሩ፡፡ እየወረዱ

ግብጻውያንን ይወጓቸው ነበር:: ዛሬስ ባሮቻችን እስራኤል ይርዱን ብለው አስለፏቸው ግብጻውያን እንደልማዳቸው ድል ሆኑ:: እስራኤል ባሉብት ድል አድርገው ይዘፍኑ ያጨበጭቡ ጀመር:: የአሕዛብ ምን ድንበር አለው ደርበህ በለው ብለው ወግተዋቸዋል አምቻችን አፈኛ ቢመለስ ወደእኛ ወይ እኛ ወይ እኛ ባመጣነው እዳ ሆን አሣሪኛ ያለው እንጂ በእኛ ይደርሳል እንግዲህማ መውጫ መግቢያውን አውቀውታል ከጠላቶቻችን ጋራ ሆነው ወግተውን ሲኼዱ አይደለምን? ንዑ ንጠበብ ቦሙ ኖራ አናስወግጣቸው ጡብ /ጡብና/ እናስረግጣቸው ብለው ራምሴ ጋምሴ በሚባል ቦታ አንፈቶን /ፊቶም/ የሚባል ግንብ አሠርተዋቸዋል:: እንዲህ ማድረጋቸው ሲደክሙ ሲውሉ አይገናኙም ካልተገናኙ አይባዙም ብለው ነበር:: እነሱ ግን በጥበበ እግዚአብሔር እየበዙ ሔዱ:: ፸ህ ሲፖራ የሚባሉ ዐቀብተ መወልዳት ሾሙ:: እናዋልዳለን እያላችሁ እየቀረባችሁ ወንድ ወንድ ሲወለድ ገርዎ ውስተ ባሕረ ተከዚ እያነቃችሁ ከባሕር ጣሉት አሏቸው::

ታሪክ በዚያ ወራት ጌታ ሙሴን ሊያድነው ቢወድ በፊቱ ብርሃን ተሰሎበት ተወለደ:: ወተሰብሐ ኅብረ ገጹ ለሙሴ እንዲል ወተራኅርኃ እልክቱ መወልዳት ይላል:: ያህንስ የፈጠረው ፈጣሪ ይግደለው ብለው ራርተው ትተውት ወተሐፅነ ፫ተ አውራኀ ውስተ ቤተ አቡሁ ይላል:: በ፫ ወሩ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ሲያለቅስ ሲአነጥስ ይታወቃል ንጉሥ የሰማ እንደሆነ ለእናንተም ለእኛም መልካም አይደለም ለዚህ ነገር ብልሀት ፈልጉለት አሏቸው:: አባቱ እንበረም ሣጥን ጠርቦ አፍሮዲጡ በሚባል የውሃ አረፋ ለብጦ ወስዶ ከጅብጅባ ስር ጣለው:: ሌሊት ሌሊት እናቱ ዮካብድ እየወረደች ስታጠባው ታድራለች:: ቀን ቀን ማርያም እኅቱ ስትጠብቀው ትውላለች:: እንጨት የምትሰብር ውሃ የምትቀዳ እየመሰለች:: ከምን ትጠብቀዋለች ቢሉ አነዳሰበር የሚባል አሞራ አለ:: እሱ ሽቅብ ሣጥኑን ይዞ ወጥቶ ከድንጋይ ላይ ይጥለዋል አጥንቱ ይከስከሳል ደሙ ይፈስሳል ሥጋውን በልቶ ደሙን ጠጥቶ ይሄዳል፡ ከዚያ ትጠብቀው ነበር::



በ፳ተኛው ቀን ወወረደት ተርሙት ወለተ ፈርዖን ትትሐጸብ በማይ ይላል:: ከባሕር ለምን ሔደች ቢሉ ኮብሽ የሚባል ደዌ ይዟት ነበርና ለመታጠብ፡ አንድም መንግሥት በጕርጕራ ባለ የነገሥታት የአፄ መለክ ስገድ ልጆች ይዋኙ እንደነበር ለመዋኘት:: አንድም ባሕር ታመልክ ነበርና ለማሚረት፡ አንድም ዓሣ ዐንበሪ እዞ ጕማሬ ታመልክ ነበርና ለማሚረት ሔዳ:: አንድም ደንገጥሮችዋ እየተመላለሱ ሲጫወቱ አይታ፡ አንድም ነጋዴ ወዳጅ ነበራት ለመገናኘት:: በማናቸውም ምክንያት ከወረደች ዘንድ እሻግራ ዓይታ የነጋድያን እቃ /ወርቅ/ ማዕበል ሞገድ አስቀርቶባቸው /ያመጣው/ ይሆናል እምጡት ብላ አስመጥታ ከፍታ ብታይ መልከ መልካም እንደ ፀሐይ የሚያበራ ልጅ አገኘች:: ከዚህ በኋላ ዕብራውያን ፈርተው ጥለውታል ልጅ ይሆነኛል አሳድገዋለሁ ሞግዚት ፈልጉልኝ አለች ማርያም እኅቱ ቀረብ ብላ ካልሽስ ትናንትና ልጇ የሞተባት ዕብራዊት ሴት አለች ብላ እናቱን ወሰደችለት እናቱ ሞግዚት እኅቱ የሞግዚት ደንገጥር ሆነው አሳድገውታል:: አባቱ እንበረምም የሞግዚት ባል ሆኖ ቀረበ:: እናቱ ዜና አበውን አባቱ ተሰፋ አበውን እየነገሩት አደገ:: ፳ ዓመት ሆነው፡ አንድም በ፳ ዓመቱ ቀስት ነፍጥ መጠረቅ መታጠቅ መፍታትን ይማር ተብሎ ከአያቱ ከፈርዖን ቤት ገባ:: ፳ ዓመት ተቀመጠ:: ፵ ዘመን ሆነው በ፵ ዘመኑ እስኪ በምድረ ጌሴም ያሉ ዘመዶቼን ጠይቄ ልምጣ ብሎ ሄደ:: ሲኼድ ዕብራዊና ግብጻዊ ተጣልተው አገኘ ጠቡ /የጠቡ ምክንያት/ ፩ኛ. ዕብራዊ በጠበጠው እንጾድ ግብጻዊ ልጠብ ብሎ፡ ፪ኛ. በዕብራዊ ፈንታ ግብጻዊ ላጠጣ ብሎ ፫ኛ. ዕብራዊ ያወጣውን ዓሣ ግብጻዊ ልውሰድ ብሎ:: ምነው አንተ እንዲህ አድርገህ ትገደረዋለህን /ትበድለዋለህን? አለው አንተ በገዛ ባሪያዬ ገላውን እንደ ቆርበት /ቆርበቱን እንደ ጀንዲ/ ሥጋውን እንደ እንጾድ ደሙን እንደውሃ አጥንቱን እንደ እሰት አድርጌ ባጥብበት ታድነዋለህ? ብሎታል:: ወነጸረ ሙሴ ለፌ ወለፌ ይላል:: ቀኝ ግራ ብሎ አይቶ ይህ መምለኬ ጣዖት መምለኬ እግዚአብሔርን ይገደረዋልን ብሎ ክቡደ መዝራዕት ነውና አንድ ጊዜ በጡጫ ቢለው አረፈ:: ወደፈኖ ውስተ ኆፃ ይላል:: አሸዋ ጭሮ አልብሶት ሄዷል:: ይህም ምሳሌ

ነው:: ሙሴ የጌታ: ዕብራዊ የአዳም: ግብጻዊ የዲያብሎስ: ኖባ የሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ:: እንድም ኖባ የመስቀል ከፎቱ በአንዱ ድል እንደነሳው:: ጌታም በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ቢመጣበት በሦስቱ አርእስተ ምግባራት ድል ነስቶታል:: ከዚያ ጠይቆ ሲመለስ ዕብራዊና ዕብራዊ ተጣልተው አገኘ ጠቡ እንደዚሁ ነው:: ወፈቀደ ይዕርቆሙ ይላል:: ሲያስታርቃቸው ወዶ ለምንት ትጻብዑ እንዘ አኀው አንትሙ አላቸው:: ይልቁንም በደለኛውን አይቶ አንተ ወንድምህን እንዲህ አድርገህ ለምን ትገፋዋለህ አለው:: መኑ ሤመከ መልአከ ወመኰንነ:: በእኛ አለቃ ዳኛ አድርጎ ማን ሾሞሀል ወሚመ ትፈቅድኑ ትቅትለኒ በከመ ቀተልኮ ትማልም ለግብጻዊ አለው:: ምነው አሁን ወነጸረ ሙሴ ለፌ ወለፌ አላልነም ነበር ቢሉ እሱ አላየም አልን /አለ/ እንጂ ሌላ አላየውም አላለም:: በዱር በገደል ተጠግቶ ያለ በቅጠል ቀዳዳ ሲመለከተው የነበረ ነው:: አንድም ዛሬ ወንድሜ ሙሴ ባይኖር ያ ግብጻዊ ሲገለኝ ነበር ብሎ አመሰገኝ አማሳኝ እንዲሉ: ሙሴ ያዳነው ሰው ነው ባለጌን ካሳደገ ያነቀ ጸደቀ እንዲሉ: ዮሐንስ አፈወርቅ ግን ወንድሜ ሙሴ ባይኖር /ባይሆን/ ብሎ የተናገረው በትረ ፈሪ ጎሮ ወዳጅ /ብትር ፈሪ ጠብ ወዳጅ/ እንዲሉ: ያዳነው ሰው ያው ነው ብሏል:: ወኮነ ዝንቱ ነገር ክሡተ ቅድመ አዕይንቲሁ ለፈርዖን ይላል:: ይህ ነገር በፈርዖን ፊት ታውቆ ቢሆንማ ከታች ባቴን ከላይ አንገቴን አይሠራኝም አይቀጣኝም? ብሎ ተሰዶ ምድረ ምድያም ሔደ በጎዳነኛ ልማድ ከውሃ ዳር ተቀምጦ ሳለ የካህን ምድያም የዮቶር ፯ ሴቶች ልጆች ነበሩት በግ ሲያለቃቅሙ ዓይቶ ምነው እናንተ አታጠጡም አላቸው:: ይህ ደንጊያ የሚከፈት ለሃምሳ ለስልሳ ነው ዘላኖች /እረኞች/ መጥተው አጠጥተው እኛስ የምናጠጣ በመጨረሻ ነው አሉት:: ያንን ከፍቶ እየቀዳ ሲያጠጣላቸው ዘላኖች መጡ:: ምነው እናንተ ወትሮን ዛሬ ከኛ ፊት ማጠጣታችሁ አሏቸው:: ምነው ውሃ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ /ምርኮ ለጀመረ/ አይደለም? ብሏቸዋል:: ፍትሐ ሙሴ ያሰኘው ይህ ነው:: ይኸውም ጸንቶለት ይኖራል:: አጠጥቶላቸው ሄዱ ዮቶር ዮምሰ አፍጠንክን መጺአ አዋልድየ:: ልጆቼ ዛሬስ ፈጥናችሁ መጣችሁ አላቸው:: አባታችን እንዲህ ያለ ሰው



አጠማጠሙ ግብፃዊ እነጋገሩ ዕብራዊ አግኝተን እርሱ አጠጥቶልን ነው አሉት:: እንዲህ ያለ ሰው ስታዩ ለምን ትታችሁ መጣችሁ አላቸው:: ሲፓራ ይላታል ሚስቱ የምትሆን ናትና አሁንም አሳጣውም ብላ ሄዳ ይዛው መጣች:: ራት በልተው ሲተሳሰቡ አድረዋል በነገው ሲጨዋወቱ ነገድህስ ከማን ነው ነገርህስ እንደምን ነው አለው:: ነገዴም ዕብራዊ ነኝ ነገሬም እንዲህ ያለ ነው አለው:: ጎዳና ቢኼዱት ቢኼዱቱ ውሃ ቢቀዱት ቢቀዱት ያልቃል? ከልጆቼ አንዲቱን አግብተህ በጎቼን እየጠበቅህ አትኖርም አለው ሲፓራን አግብቶ ፵ ዘመን በግ እየጠበቀ ኖሯል:: ኤልዛር ጌርሳም የሚባሉ ልጆች ወልዷል:: ኤልዛር ማለት ረዳኢ ረድኤተ እግዚአብሔር ማለት ነው:: ጌርሣም ማለት ነግድ ወፈላሲ ዘወልድክዎ በስደትየ ማለት ነው:: ኤልዛር በአባቱ ሥርዓት ተገዘረ ጌርሳም በእናቱ ሥርዓት ሳይገዘር ቀረ በአርባ ዘመኑ በጎቹን በደብረ ኮሬብ አሰማርቶ ሲአበላ /ሲጠብቅ/ በደብረ ሲና ነበልባሉ ከሐመልማሉ ሐመልማሉ ከነበልባሉ ተዋሕዶ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው አይቶ ወቀርበ ያጠይቆ ይላል:: ይህንስ ቀርቦ ሲረዱት ይገባል ብሎ በጎቹን አንድ ወገን ከፈረሰ ግንብ አግብቶ /አስጠግቶ/ ዘለሳ /እጥር/ ጥሉባቸው ከአፈረ ነደልም ቢሉ አስጠግቷቸው ይሄዳል:: ስጊዜው ሳልረዳው እመለሳለሁ ብሎ ነው:: ለኋላ ግን ምሳሌ ነው:: ሙሴ የመናንያን: ምነና ሲኼዱ ገንዘብን ሰጥቶ መጽውቶ ሕዋሳትን ጠቅሎ መሄድ ይገባል ሲል ከእግረ ደብር ሲደርስ ፵ ክንድ ሲቀረው ሙሴ ሙሴ ፍታሕ ቶታነ አሣዕኒከ እምእገሪከ እስመ ዘትከያዳ ምድር ቅድስት ይእቲ የምትቆምባት ደብረ ሲና ክብርት ናትና ጫማህን አውልቅ አለው:: ለጊዜው ስንኳን ከሰማያዊ ንጉሥ ሲቀርቡ /ሲገናኙ/ ከምድራዊ ንጉሥ ሲገናኙ /ሲቀርቡ/ ጫማን አውልቆ ባጭር ታጥቆ መገናኘት ይገባል ሲል ነው:: ለኋላ ግን ምሳሌ ነው:: ደብረ ሲና የቤተክርስቲያን አምሳል: ቤተክርስቲያን ሲገቡ ጫማን ፈትቶ በአጭር ታጥቶ መግባት ይገባል ሲል:: እንድም የምትሄድባት ግብጽ ጽንዕት ናትና አሣዕነ ፍርሐትን /የልብ ፍርሐትህን/ ተው ሲል ነው:: እንድም ፋል የሚባል ጥንቆላ ተምሮ ነበርና ያንን ተው ሲል

/ሲሰው/ ነው። <u>ኢንድም</u> ልጆቼን ማን ይመግብልኛል ማለትን ተው ሲል ነው። አንድም ከግብጽ ስትመለስ በደብረ ሲና የምሠራልህ ሕግ ጽንዕት ናትና ልማደ ዮቶርን ተው ሲለው ነው። ይህም ምሳሌ ነው። ሐመልማል የእስራኤል፡ ነበልባል የመከራቸው፡ ሐመልማሉ ነበልባሉን እንዳላጠፋው እስራኤልም በኀዘን መከራውን አላራቁትም፡ ነበልባሉ ሐመልማሉን አለማቃጠሉ መከራውም ጨርሶ አላጠፋቸውም ጨርሶማ ካጠፋቸው ከሴት ከሕፃን ሌላ ስድስት መቶ ሺህ አጋር ይገኛል? ነዐ እፈኑከ ኀበ ፈርዖን ብሎ ለፈርዖን አለው። ፈንዎሙአ ለሕዝብየ ይግበሩ በዓልየ በሐቅል አለህ በለው አለው። ማን አለኝ ልበለው አለው አኸያ ሸራኸያ ኤልሻዳይ። አኸያ አምላክ ዕብራውያን፡ ሸራኸያ አምላክ ተስፋ፡ ኤልሻዳይ ዘሀሎ ወይሄሉ ማለት ነው። ምን ምልክት ይዠሀል ቢለኝላ አለው። ምን ይዠሀል አለው ለማናገር ቢሻ ነው። ብትር አለው ጣለው አለው ቢጥለው እባብ ሆነ ሙሴ ሸሸ ተመልሰህ አንሳው አለው። ተመልሶ ቢያነሳው በትር ሆነ ይኸውም ምሳሌ ነው። ብትር የእስራኤል፡ እባብ መሆኑ የመከራቸው፡ መጣሉ ግብፅ የመውረዳቸው፡ ሙሴ መሸሹ ተሰዶ ምድረ ምድያም የመሄዱ፡ ተመልሶ ማንሳቱ ተመልሶ እስራኤልን የማውጣቱ፡ እባብ ተመልሶ ብትር መሆኑ እስራኤል የመዳናቸው ። ድገመኝ አለው። እጅህን ከብብትህ አግባው አለው። አገባው አውጣው አለው አወጣው ቢያወጣው ለምፅ ሆነ መልሰህ አግባው አለው አገባው አውጣው አለው ቢያወጣው ደኅና ሆኗል ወርቁ አይለወጥም። ዳግም ከቤተ መንግሥት የሚላክ አስናውኖ የሚናገር ነው። እኔ ምላሰ ዲዳ እፈ ለንባዳ ነኝ አለው። ጸያፍ እ እ የሚል ነው ዲዳ ረን ለ የሚል ነው። አሮን እኁከ ያኩንከ ነቢየ አፈም ይላል። አሮን ከራምሴ /ከጋምሴ/ ከደብረ ሲና ሙሴ፡ ተራከቡ በደብረ እግዚአብሔር /በደብረ ሥላሴ/ ይላል። ነገረ እግዚአብሔር ስለተነገረባት ደብረ እግዚአብሔር አላት።

<u>ቷሪክ</u> ለዚህ ያበቃቸው ምክንያት ምንድነው ቢሉ በግብፅ ሳሉ ራሔል የምትባል ሴት ነበረች ባልዋ (ምናሴ/ሮቤል) ይባላል።

መድኃኒት ጠጥቶ ታሞ ይላሉ። በባሏ ተተክታ ኖራ ልትረግጥ ሄደች። ስትረግጥም ምጥ ተሰማት ለሹሙ ወጥቼ



ልውሰድ አለችው የንጉሥ ሥራ ይፈታ የለም? ብሎ ጀርባዋን በዘንግ ቢመታት መንታ ጸንላ ነበርና ወጥተው ወጥተው ወደቁ። ባይሆንም አውጥቼ ልቅበር አለችው የሰው ደም ማሸጋ /ጡብ ግንብ/ ያፀናል እንጂ ምን ይጎዳል ምን ይል ብለሽ ነው? አርገጭ ብሎ ጨምሮ /አብሮ/ አስረግጧታል። ያን ጊዜ ደሟን ከእንባዋ ጋራ ቀላቅላ ኢህሎኑ በዝ ሰማይ አምላክ እስራኤል አዳናይ ብላ ወደሰማይ ብትረጨው ቅድመ እግዚአብሔር ደርሷል /ደርሶላታል/ አብርሃምም በነፍስ ተካሷል። ከጭቃ ተለውሰው ከናስ ተንለው ከቀሩማ አበዝኅ ዘርዐከ ያልከው ወዴት ነው ብሏል። ከዚህ በኋላ ሙሴ ሚስቱን ልጆቹን ይዞ ተነሳ ስለምን ቢሉ ተጠራጥሮ። <u>ኢንድም</u> እስከዚያ የሚመግባቸው የለም ብሎ መልአኩ ሰይፉን መዞ ለሚስቱ ታየት ደመ ግዝሮሁ /ግዝረቱ/ ለወልድየ ይኩን ቤዛ ምትየ ብላ ያልተገረዘውን ጌርሳምን ገዘረችው። ከዚህ በኋላ ያሉትን ይዘህ ትሄዳለህ አለው እስከዚያው የሚመግባቸው የለም ብዬ ነው እንጂ አለው። ከአጠገቡ ባሕር አለ እጅህን ከባሕሩ አግባው አለው አገባው ያገኘኸውን ይዘህ ውጣ አለው ድንጋይ ይዞ ወጣ ከድንጊያው ምታው አለው ቢመታው ውስጠ ግብ /ውስጠ ክፍት/ ሆኖ መንታ ሠርዶ በቅላ ትል አንዲቱን ወገን ሲመገብ አንዲቱ ወገን ስትለመልምለት ደግሞ አንዲቱን ወገን ሲመገብ አንዲቱ ስትለመልምለት አሣይቶ ይህን የመገበ የአንተን ልጆች አይመግብም? ብሎት ትቷቸው ሄዷል። አሮን ከራምሴ ከደብረ ሲና ሙሴ ተራከቡ። በደብረ እግዚአብሔር /ሥላሴ/ ይላል። እዕሩገ እስራኤልን ሰብስብልኝ አለው። ተሰበሰቡ ሳወጣችሁ መጥቻለሁ አላቸው። ምን ምልክት ይዠሀል አሉት በትሩን ጥሎ ብትሩን እባብ አድርጎ አሳያቸው እውነት ነው ታወጣናለህ? አሉት አሮንና ሙሴ ከፈርዖን ቤት ገብተው ፈንዎሙአ ለሕዝብየ ይግበሩ በዓልየ በሐቅል አለህ አሉት። ማን ላላችሁ አላቸው አኸያ ሸራኸያ ኤልሻዳይ አሉት። ምን ምልክት ይዛችኋል አላቸው። በትሩን ጥሎ እባብ አድርጎ እባቡን በትር አድርጎ አሳየው። ይህንስ የኔም ጠበብቶች ያደርጋሉ አለ። ኢያኔስ ኢያንብሬስ የሚባሉ ጠቢባን ነበሩት። ተጠርተው መጡ እናንተ ሙሴና አሮን ያደረጉትን

ማድረግ አይቻላችሁም? አላቸው። በትሩን በምትሐት እባብ አደረጉት እባቡን ግን በትር ማድረግ አልተቻላቸውም። የሙሴ በትር የእነሱን በትር ውጣ ወደ ባለቤቶች ገሠገሠች በትራችን አንሷት እኛን ልትደርበን ነው እያሉ ወጉዩ በስላቅ ይላል እየተዘባበቱ ሄደዋል። ይህ ፈርዖን ምንም እባቡን በትር ማድረግ ቢሳናቸው በትሩን እባብ በማድረጋቸው ልቡ ፀና። ከዚህ ሁሉ እንጂ እንውጣን ያስቡበት አገዛዝ ብታቀሉላቸው አይደለም? በሉ እያባደሩችሁ ግዚቸው አለ። መከራ አጸኑባቸው ሙሴ አሮን ወደ አደባባይ ሲያልፉ አይተው አዬ ሙሴ አሮን ሳታወጡን እናወጣለን ብላችሁ እንደ ሽቱ ተወደን እንኖርበት በነበረ አገር መከራ ታጸኑብን እያሉ ይላቀሱ ጀመር። ሙሴ ወደ ጌታ አመለከተ። ለምንት ትጸርሕ ኀቤየ ኵሎ ጊዜ አንሰ አከብድ ልቦ ለፈርዖን ብሎ ዝብጣ ለባሕር አለው። ውሃውን በብትሩ ቢነካው ተለውጦ ደም ሆኗል። ዘጠኝ መቅሰፍት አሥረኛ ሞተ በኵር አውርዶ ይፈጽማቸው ጀመር። እምበኵረ ፈርዖን ንጉሥ ዘይነብር ዲበ መንበረ መንግሥት እስከ በኵረ ዓመት ፂውውት ዘትነብር ዲበ ማሕረፅ ያላል። ፈርዖን በኵር ነው /ነበርና/። የግብጽ ሰዎች አንተ በኵር ሚስትህ ልጅህ በኵር እናንተ ካለቃችሁ መንግሥቱ ለማን ይሆናል አትስጧቸውምን ብለዋቸዋል። ሙሴ አሮንን ሌሊት አስጠርቶ ያዛችሁልኝ ውጡ አላቸው። ያን ጊዜ ጌታ ሙሴን ለይትወሀስ ኀር እምኀሩ ወዓመት እምእግዝእታ ወገብር እምእግዚኡ ብለህ አዋጅ ንገር አለው። ፫ ቀን በዓል አድርገን እንመጣለን መሳሪያችሁን አውሱን አሏቸው ገንዘብ ያስወድዳቸው የነበረ ሰይጣንን አሰረው ሴቲቱ ድሪዋን ቀለበቷን ወንዱ ቢትዋውን ጨፋውን /ጋሻውን የራስ ባርኔጣ ጌጡን/ ሳይቀር አውሰዋቸዋል። ይኸውም እዳ እንዳልሆንባቸው ሀየንተ ዘተቀንዩ ተቀንዮ ወሀየንተ ዘገብሩ ግንፋለ። ፬፻፴ ዘመን ያለ ደመወዝ ስለተገዙ ስለ ደመወዝ ሆኗቸዋል። በ፫ኛው ቀን ሰይጣንን ፈታው እስራኤል እንጂ ሲመለሱ አልሄዱም ወይ ከገንዘባችን ወይ ከባሮቻችን አልሆን አለ። ምታ ነኃሪት ክተት ሠራዊት ብሎ ተከተላቸው። ሦስት ቀን የተጓዙትን በአንድ ቀን ገስግሶ



ደረሰባቸው። እነዚያ ልጅ ከብት ጓዝ ይዘው ነው። እሱ ግን ደረቅ ጦር /አርበኛ ብቻ/ ሆኖ ነው ዞረው /ዘወር/ ብለው ቢያዩ ደርሶባቸው አዬ ሙሴ አሮን ሳተወጡን እናወጣለን ብላችሁ ከዚህ ከምድረ በዳ እንደሻሽ አንጥፋችሁ እንደቅጠል አርግፋችሁ ታስቀሩን ብለው ይላቀሱ ጀመር። ሙሴ ወደ ጌታ አመለከተ። በሉሙ ለእስራኤል ይንድኡ እንስሳቲሆሙ ንዱ በላቸው አለው። ከዚህ ቀደም በዓይነ ሥጋ እንደተያያችሁ ከእንግዲህ ወዲህ በዓይነ ሥጋ አትተያዩም ብሎ በፊታቸው የሚሄድ ደመና ነበር አዙሮ ጋርዷቸዋል። ግብፃውያንና እስራኤላውያን ሳይተያዩ ከአንድ ዛፍ ፈረስ በቅሏቸውን አስረው አድረዋል። ከዚህ በኋላ ኤርትራ ደረሱ ዝብጣ ለባሕር አለው። ከሦስት ተከፍላለች ያሉ እንደሆነ አራት አራት እየሆኑ ከአራት ተከፍላለች ያሉ እንደሆነ ሦስት ሦስት እየሆኑ ተሻግረዋል። በቀኝ እንደግድግዳ በግራ እንደግድግዳ በላይ እንደጠፈር እንደመስኮት ታቹ የለፋ መስክ ሆኖላቸው ፈረስ በቅሏቸውን እያበሉ ተሻግረዋል። ፈርዖን ቢደርስ ተከፍላ የአገሬ ውሃ እነሱን የሰደደች እኔን የምትከለክለኝ ናት? ብሎ ፈሪው እንዳይቀር ለኮ ለለኮ አያይዞ ገባ። እስራኤል ጨርሰው ሲወጡ ግብፃውያን ጨርሰው ሲገቡ ዝብጣ ለባሕር አለው። ከወደፊታቸው ነፋስ ያገናኘው ጀመር። እናንተ እስራኤል እንጂ ፈጣሪያቸው ይረዳቸዋል እንመለስ አሉ። ከወደኋላቸው /ከኋላ/ ተገጥሞባቸዋል። ያን ጊዜ ሙሴ አሮን የወንዶች አቀንቃኝ፡ ማርያም እኅተ ሙሴ የሴቶች አቀንቃኝ፡ ሆነው ወባረኩ ዘ ቡራኬ በኀብረተ ቃል ይላል። ቃለ ሽካራ ቃለ ኍሀና ሳይኖር በርትዓት ቃል ዲዳዎች ረትቶላቸው በፍትሐተ ቃል ሕፃናት ፈትቶላቸው አመስግነዋል። ለዝክረ ነገር ምድሪቱ ሣር ሳታበቅል ትኖራለች ይህም ምሳሌ ነው። ኤርትራ የገሃነም፡ ሙሴ የጌታ፤ ፈርዖን የዲያብሎስ፡ በትር የመስቀል፡ እስራኤል የነፍሳት፡ እስራኤል ወዲያው ወጥተው ምድረ ርስት አልገቡም ፵ ዘመን በምድረ በዳ ኖረዋል። ነፍሳትም ከሲኦል ወጥተው መንግሥተ ሰማያት አልገቡም በገነት የመኖራቸው ምሳሌ። አንድም ግብፅ የኃጢአት፡ ኤርትራ የጥምቀት፡ ደመና የመንፈስ ቅዱስ፡ ሙሴ የቀሳውስት፡ እስራኤል የምእመናን፡ እስራኤል ፊት ደብተራ አሪትን ኋላ

ቤተመቅደስን ሠርተው እንደኖሩ ምእመናንም በዚህ ዓለም ቤተ እግዚአብሔር /ቤተክርስቲያን/ ሠርተው የመኖራቸው:: ፵ ዘመን መና ከደመና እያወረደላቸው ውሃ ከድንጊያ እያፈለቀላቸው እንደተመገቡ ምእመናንም ሥጋውን ደሙን ተቀብለው የመኖራቸው ምሳሌ:: ማንሻ መኃልየ ነቢያት ይላቸዋል:: መላው እስራኤልን ወላድያነ ነቢያት ናቸውና መጻእያትን ይናገራሉና:: አንድም ደጎች ሲል ወይጼሊ ሰከ እስመ ከመ ነቢይ ውእቱ እንዲል::

ወጸሎቱ ለሙሴ ሙሴ የተናገረው ይህ ነው:: አንድም መኃልየ ነቢያት የሚላቸው ከሐና እስከ ስምዖን:: ወጸሎቱ ለሙሴ ንሴብሖ ብሎ እስመ እሳት እስኪል ድረስ ነው:: ይህን ፲፱ ንሴብሖን ከኦሪት ዘጸአት: አጽምዕ ሰማይን እስመ እሳትን ከኦሪት ዘዳግም: ሐናን ከመጽሐፈ ነገሥት /ሳሙኤል/ ሕዝቅያስን በሴሲትን ከመጽሐፈ ኢሳይያስ: ምናሴን ከሕጹጻን: /ዜና መዋዕል/ ዮናስን ዕንባቆምን ከደቂቀ ነቢያት: ስብሐት ዘአምአዛርያን ፲ቱ ደቂቅን ኀበ ባረኩን ከመጽሐፈ ዳንኤል: ጸሎተ ማርያምን ዘካርያስን ስምዖንን ከሉቃስ ወንጌል: አምጥተው ጠርዘውልናል /ሰጥተውናል/:: ይህ አርእስት ነው:: ፲ቱ፱ ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሲሰጡ ለዚህም አርእስት ሰጥተዋል:: እሱ ግን ነገሩን ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ብሎ ያመጣዋል::



## ጸሎተ ሙሴ ነቢይ ፩

፩. ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ:: ምስጉን ሆኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: ምስጉን የተመሰገነ አለ:: ሰው በሐሰት ሆኖ ይመሰገናል:: ንፋጉ ለጋስ: ደካማው ኃያል: ደሀው ባለጸጋ ተብሎ:: እሱ ግን በለጋስነቱ ንፍገት በኃያልነቱ ደካማነት በባለጸግነቱ ድህነት የለበትም:: ስቡሐ: ቅድመ ዓለም የተመሰገነ:: ወዘተሰብሐ:: ዛሬም በኤርትራ ግብጻውያንን አጥፍቶ እስራኤልን አድኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን::
ፈረሰ ወመስተፅዐነ ወረወ ውስተ ባሕር:: ፈረሱን በፈረስ የተቀመጠውን በባሕር አሰጠመ:: አንድም ሠራዊተ አጋንንትን ሲቃነ አጋንንትን በባሕረ ገሃነም አሰጠመ::

፪. ረዳኤ ወመሠውረ ኮነኒ ለአድኅኖትየ:: እኔን ለመርዳት /ለማዳን/:: ረዳኤ:: በደመ በግዕ:: ወመሠውረ: በደመና:: አንድም ረዳኤ:: በደሙ:: መወሠወረ በመንፈስቅዱስ:: ረዳት ሆነኝ::
ውእቱ አምላኪየ ወአምላከ አቡየ እሴብሖ ወአሌዕሎ:: ፈጣሪዬ ያባቶቼ ፈጣሪ ነው:: አገነዋለሁ አከብረዋለሁ:: አሁን ፍጡር ፈጣሪውን የሚያገን የሚያከብር ሆኖ አይደለም:: ልዕልናውን እናገራለሁ ሲል ነው::
ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ ብሎ እንዲያመጣው::

፫. እግዚአብሔር ይቀጠቅጥ ፀብአ ወእግዚአብሔር ስሙ:: ፀባኤ ይላል:: አርበኛ ፈርዖንን ያጠፋዋል ስሙ እግዚአብሔር ሲባል ይኖራል:: አንድም ዲያብሎስን በመስቀል ድል ይነሣዋል:: ስሙ አምላክ ወሰብእ ሲባል ይኖራል::

፬. ሠረገላቲሁ ለፈርዖን ወሠራዊቶ ወረወ ውስተ ባሕር:: የፈርዖንን ሠረገላውን ሠራዊቱን በባሕር አሰጠመ:: አንድም ሠራዊተ አጋንንትን ሲቃነ አጋንንትን በባሕረ ገሃነም አሠጠመ:: ኀሩያን:: ለሹመት ለምክር የተመረጡትን:: ወመስተቀፅዐናነ በመሥልስት:: ሦስት ወገን ሆነው የተሰለፉትን:: ባንድ___ሠረገላ ቀስተኛ ጋሻኛ ነፍጠኛ ይቀመጣሉና:: አንድም በመካከል ሠረገላ ቀኝና ግራ ፈረስ

ይሄዳልና። እንድም ከሦስት በተከፈለች በኤርትራ አሠጠመ። እንድም ሦስት ወገን ሆነው ስመሰለፍ የተመረጡትን ድር እግር ሠረገላ አሠጠመ። /ድር ትንሽ ጓዝና ትንሽ ሰው የሚይዝ እግር በእግር ብቻ የሚሄድ/ እንድም ኀሩያን። በኢየሩሳሌም ስማያዊት ሊኖሩ የተመረጡትን እጋንንት። ወመስተፅዕናነ በሦስት ወገን የሰፈሩ አጋንንትን በዓየር በዚህ ዓለም በመሠረተ ምድር። ፀ ዘወድቀ ውስተ አየር ወፀ ዘወድቀ ውስተ ምድር ወፀ ዘወድቀ ውስተ እንጦርጦስ /እንጦርጦስ/ ዘውእቱ መትሕተ ታሕቲት እንዲል። እንድም በነፍስ በሥጋ በልቡና ያደሩትን። እንድም በደቂቀ ሴም በደቂቀ ያፌት በደቂቀ ካም ያደሩትን አሠጠመ።

ወተሰጥሙ ውስተ ባሕረ ኤርትራ። በባሕረ ኤርትራ ተሰጠሙ /ሠጠሙ/ እንድም በባሕረ ገሃነም ተሰጠሙ /ሠጠሙ/።

፭. ወደፈኖሙ ማዕበል። ማዕበለ ኤርትራ ቀበራቸው። እንድም ማዕበለ ገሃነም ቀበራቸው።

ወተሰጥሙ ውስተ ቀላይ ከመ እብን። ደንጊያ ሲጥሉት እንዲሰጥም ሰጠሙ።

፮. የማንከ እግዚኦ ተሰብሐ በኃይል። አቤቱ የማንህ ሙሴ ኃይል አድርጎ ተመሰገነ። እንድም አቤቱ ሥልጣንህ ኃይል አድርጎ ተመሰገነ። እንድም አቤቱ አብ! ልጅህ ኃይል አድርጎ ተመሰገነ። እንድም አቤቱ ወልድ! ሥልጣንህ ኃይል አድርጎ ተመሰገነ።

የማን እዴከ እግዚኦ ሠረወቶሙ ለፀር። ለፀር ሠረወቶሙ ስማለት ደገመው።

፯. ወበብዝኀ ስብሐቲከ ቀጥቀጥከሙ ለጸላእትከ። በብዙ ታምራትህ ጠላቶችህ ግብጻውያንን ጠላቶችህ አጋንንትን አጠፋሀቸው።

ፈኖከ መዓተከ ወበልዖሙ ከመ ብርዕ። መዓትህን ላክህ እሳት ብርዓን እንዲበላ በላቸው።

፰. ወበመንፈሰ መዓትከ ቆመ ማይ። መዓትህን በምትፈጽምበት በነፋስ ውሃው ተከፍሎ ጸና። እንድም በረቂቅ ሥልጣንህ



ውሃው ተከፍሎ ጸና። እንድም በቅዱስ ሚካኤል ውሃው ተከፍሎ ጸና። እንድም በረቂቅ ሥልጣንህ ገሃነም ተከፍሎ ጸና።

ወጠግዐ ከመ ዓረፍት ማይ። ውሃው ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ጸና። እንድም ገሃነም ተከፍሎ እንደ ግድግዳ ጸና።

ወረግዐ ማዕበል በማእከለ ባሕር። በባሕሩ መካከል ማዕበሉ ረጋ። እንድም በባሕረ ገሃነም መካከል ማዕበለ ገሃነም ረጋ።

፱. ወይቤ ጸላዒ ዴግኖ እእኅዞሙ። ጠላት ፈርዖን ተከትዬ እይዛቸዋለሁ ብሎ ነበር።

እትካፈል ምሕርካ ወእጸግባ ለነፍስየ። ምርኮውን እካፈላለሁ ስውነቴን አጠግባታለሁ ብሎ ነበር።

እቀትል በመጥባሕትየ ወእኴንን በእዴየ። ወንድ ወንዱን እገድላለሁ ሴት ሴቱን እገዛለሁ ብሎ ነበር። እንድም እንቢ ያለኝን እገድላለሁ እሺ ያለኝን እገዛለሁ ብሎ ነበር። ምንም ቢሆን ነገር ያነቁ ናቸውና ሙሴ አሮንን እገድላለሁ ሠራዊቱን እገዛለሁ ብሎ ነበር።

እንድም ወይቤ ጸላዒ ዴግኖ እእኅዞሙ ጠላት ዲያብሎስ ግብራቸውን ተከትዬ ዕቄራኛቸዋለሁ ብሎ ነበር።

እትካፈል ምሕርካ ወእጸግባ ለነፍስየ። ምህርካ ነፍስን እካፈላለሁ ለባሕርዬ አጠግባታለሁ ብሎ ነበር።

እቀትል በመጥባሕትየ ወእኴንን በእዴየ። በሥልጣኔ ነፍስን ከሥጋ እለያለሁ ተቆራኝቼ እኖራለሁ ብሎ ነበር።

፲. ፈኖከ መንፈሰከ ወደፈኖሙ ባሕር። ነፋስን ላክህ ባሕረ ኤርትራ ቀበራቸው። ፊትም የከፈለው ኋላም ያገናኘው ነፋስ ነው። እንድም ረቂቅ ሥልጣንህን ገለጽክ ኤርትራ ቀበራቸው። እንድም ቅዱስ ሚካኤልን ላክህ ባሕረ ኤርትራ ቀበራቸው። እንድም ረቂቅ ሥልጣንህን ላክህ ኤርትራ ቀበራቸው።

ወተሰጥሙ ከመ ዐረር ውስተማይ ብዙኅ። እርሳስ ዕሙቅ ሰፊሕ በሆነ ውሃ ውስጥ ቢጥሉት እንዲሠጥም ሠጠሙ።

፲፩. መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚኦ:: አቤቱ በስም አማልክት ከሚባሉ ከጣዖታት አንተን የሚመስልህ ማነው::
ወመኑ ከማከ ስቡሕ በውስተ ቅዱሳን:: በቅዱሳን በነቢያት በካህናት ዘንድ እንዳንተ ክቡር ምስጉን ማነው::
መንክር በብሐቲከ ዘትገብር መድምመ:: ድንቅ ሥራ የምትሠራ አቤቱ ታምራትህ ድንቅ ነው:: አንድም ታምራትህ ድንቅ ነው::
ወትገብር መድምመ:: ከእንግዲህ ወዲህም ድንቅ ሥራ ትሠራለህ::

፲፪. ሰፋሕከ የማነከ ወውኀጦሙ ምድር:: ሙሴን ላክህ ኤርትራ ቀበረቻቸው:: ምድር ይላታል በኋላ ግብሯ:: አንድም ረቂቅ ሥልጣንህን ገለጽክ ኤርትራ ቀበረቻቸው አንድም ልጅህን ላክህ ገሃነም ቀበራቸው::

፲፫. ወመራሕኮሙ ለሕዝብከ ለእለ ቤዘውከ:: በደመ በግዕ የተቤዠሐቻውን በደመና መርተህ አወጣሀቻው:: አንድም በደምህ የተቤዠሐቻውን በመንፈስቅዱስ መርተህ አወጣሀቻው::
ወአስተፍሣሕከ በኃይልከ ተረፈ መቅደስከ:: የአብርሃምን ልጆች ደስ አሰኘህቻው:: አንድም በዚህ ዓለም ቤተእግዚአብሔር ሠርተው የሚኖሩ ምእመናንን ደስ አሰኘ ህቻው::

፲፬. ሰምዑ አሕዛብ ወተምዑ:: አሕዛብ ይህን ሰምተው ተበሳጩ:: አንድም አጋንንት ይህን ሰምተው ተበሳጩ::
ወአኀዞሙ ማሕምም ለእለ ይነብሩ ፍልስጥኤም:: በፍልስጥኤም የሚኖሩ ሰዎችን ምጥ ያዛቸው:: አንድም አጋንንትን ምጥ ያዛቸው::



፲፭. ወውእተ አሚረ መምዑ መሳፍንተ ኤዶም:: በዚያ ወራት የኤዶም መሳፍንት ተሸበሩ:: በኤዶም የነበሩ አጋንንት ተሸበሩ::

፲፮. ወአኀዞሙ ረዓድ ለመላእክተ ሞአብ:: የሞአብ አለቆችን ረዓድ እንቅጥቅጥ ያዛቸው:: አንድም በሞዓብ ያሉ አጋንንትን ረዓድ እንቅጥቅጥ ያዛቸው::
ወተመስዉ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ከነዓን:: በከነዓን የሚኖሩ ሰዎች እንደ ሰም ቀለጡ:: አንድም በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሊኖሩ ተፈጥረው የነበሩ አጋንንት እንደ ሰም ቀለጡ::
ወአኀዞሙ ፍርሐት ወረዓድ:: ፍርሐት ረዓድ ያዛቸው::
ኀይለ መዝራዕትከ ፀነዐ እምኵኵሕ:: በሥልጣንህ ኃይል የተፈጠረው ውሃ ተከፍሎ ከደንጊያ ይልቅ ጸና:: አንድም በኃይለ መዝራዕትከ:: በሥልጣንህ ኃይል ውሃው ተከፍሎ ከድንጊያ ይልቅ ጸና::
አንድም ኃይለ መዝራእትከ ጸንዐ በኵኵሕ:: የሥልጣንህ ኃይል በፈርዖን ላይ ጸናበት:: ኵኩሕ አለው ፈርዖንን ስለ ጽናቱ አንድም ኃይለ መዝራዕትከ የልጅህ ኃይል ገሃነምን

በመክፈል ከደንጊያ ይልቅ ጸና። <u>ኢንድም</u> ኃይለ መዝራዕትከ ጸንዐ በኲኲሕ። የልጅህ ኃይል በዲያብሎስ ጸናበት።
እስከ የኀልፉ ሕዝብከ እግዚኦ። አቤቱ ወገኖችህ እስኪያልፉ ድረስ። እስከ የኀልፉ ሕዝብከ ዝንቱ ዘቤዘውከ። በደመ በግዕ። በደምህ የተቤዠሃቸው ወገኖችህ ምእመናን እስኪያልፉ ድረስ።

፲፯. ወሰድኮሙ ወተከልኮሙ ውስተደብረመቅደስከ። ወስደህ በምስጋናህ ማደሪያ በኢየሩሳሌም በገነት/በመንግሥተ ሰማያት አኖርሃቸው።
ውስተ ድልው ማኅደርከ እግዚኦ ዘገበርከ። በተዘጋጀች በፈጠርሃት።
ቅዱስ እግዚአብሔር ዘአስተዳሰዋ አደዊከ። ክቡር እግዚአብሔር አጆችህ ባዘጋጇት ሥልጣንህ በፈጠራት ሥልጣኑማ ያልፈጠረውን አለ? ብሎ በአዝርዕት በአትክልት ባዘጋጀሃት በዚህ ዓለም። አንድም ለአብርሃም ከዚህ እስከዚህ አወርስሐሰሁ ብለህ ባዘጋጀሃት /ባዘጋጀህለት/ በከነዓን። አንድም ልጅህ ሕይወትህ መንፈስቅዱስ በጣዕም በመዓዛ በብርሃን ባዘጋጃት በገነት በመንግሥተ ሰማያት አኖርሃቸው።

፲፰. ይነግሥ እግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም እንዲህ አድርጎ አጥፊ ለጥፋት የሚለው የለም። ለዘላለሙ ነግሦ /ጸንቶ/ ይኖራል። ወዓዲ ቢል ዘልፈ ያላል። ዘወትር ማለት ነው።

፲፱. እስመ ቦአ ሠረገላቲሁ ለፈርዖን ምስለ አፍራሲሁ ወመስተፅዕናን ውስተ ባሕር። የፈርዖን ሠረገላው ከፈረሱ ጋር በፈረስ ከተቀመጡት ጋር ወደ ባሕር ገብተዋልና።
ወአስተጋብአ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ ማየ ባሕር። ዋዌውን ጥሶ ውሃውን አጠራቀመባቸው።አንድም አጠራቅሞባቸዋልና። ይነግሥ።
ወደቂቀ እስራኤልሰ ኀለፉ እንተ የብስ ማዕከለ ባሕር። እስራኤል ግን በባሕር መካከል በደረቅ አለፉ።
ማይሰ ሎሙ ዐረፍት በይምን ወዐረፍት በጽግም። ማይኒ። ውሃውም በቀኝ እንደግድግዳ ሆኖ ጸናላቸው። አ<u>ንድም</u>



ማይስ። ውሃውስ ትለኝ እንደሆነ ውሃውስ በቅኝ እንደ ግድግዳ በግራ እንደ ግድግዳ ሆኖ ጸናላቸው።
ሰፋሕከ የማነከ ካሰውና እግዚኦ ተሰብሐ ባሰው ሐዲስ ተርጉም የቀረውን ሳይተረጉሙ የመጡ እንደሆነ ይመስሏል። ሙሴ የጌታ፡ ፈርዖን የዲያብሎስ፡ እስራኤል የነፍሳት። ኤርትራ የገሃነም ምሳሌ።

## ጸሎተ ሙሴ ዘዳግም

ዳግም ሕግ የተራ /ሰተራ/ ያሉ እንደሆነ ሰአሪት ዘኍልቍ ለ፴ተኛው ብሔር ለ፳ተኛው ዳግም አሰ። በምሥጢር /ሰምበጢር/ ያሉ እንደሆነ ለአሪት ዘጸአት ሰ፪ተኛው ብሔር ፳ተኛውን ዳግም አሰ። እንድም ሰንሴብሖ ዳግም አሰ ሙሴ ፪ተኛ የተናገረው ይህ ነው።

፩. አፅምዕ ሰማይ ወእንግርከ። ሰማይ አድምጥ ልንገርህ። ወትስማዕ ምድር ቃለ እፉየ። ምድር ከአንደበቴ የወጣ ቃልን ትስማ። የሰማይ የምድር መስማት እንደምን ነው ቢሉ ጌታ ሰውን በተጣላበት ወራት ሰማይን ዝናም ሰዘር ጠል ሰመከር አትስጥ ይሰዋል። ምድርንም የዘሩብሽን አታብቅዪ የተከሉብሽን አታጽድቂ ይላታል። ይህን ማድረግ መስማት ነውና። እንድም ልዑላን መላእክት ትሑታን ደቂቀ አዳምን አታማልዱ ይላል።

፪. ወትስፈዎ ከመ ዝናም ለነገርየ። ምድር ዝናምን እንድትቀበል ነገሬን ትቀበለው።
ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ። ነቢብን ነቢቦትየ ይላል። ጠል ከመስከ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬ ከሰው ልቡና ይስማማ።
ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት። ልዝብ ዝናም ከእርሻ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬ ከሰው ልቡና ይስማማ።
ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር። ጠል ከመስከ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬ በሰው ልቡና ይስማማ። ወፈውስ ኵሉ ፍጡር ጊሜ እንዲል።

፫. እስመ ስመ እግዚአብሔር ጸዋዕኩ። የእግዚአብሔን ስም ጠርቼ ነግሬያቸዋለሁና። <u>እንድም</u> አጽምዕ ሰማይ። ገብርኤል አድምጥ ልንገርህ። ወትስማዕ። ማርያም በአንተ አድሬ የምነግራትን ቃል ትስማ።
ወትስፈዎ ከመ ዝናም ሰነገርየ። ምድር ዝናምን እንድትቀበል ማርያም ነገሬን ትቀበለው።
ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ። ጠል ከሰማይ እንዲወርድ አካላዊ ቃል ሳይሰማ ሰው ይሁን። ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት።



የቢዘን ዝናም ሳይሰማ እንዲወርድ አካላዊ ቃል ሳይሰማ ሰው ይሁን።
**ወከመ ጊሜ** ውስተ ፀምር። ጠል ሳይሰማ እንዲወርድ አካላዊ ቃል **ሳይሰማ** ሰው ይሁን። ሰው የሆነበትን ጊዜ ያወቀው የለምና። **መልአክኒ** ኢያእመረ ዕለተ ትስብእቱ ለቃል ወእልቦ ዘአእመረ እምእለ ሀለዉ ውስተ አርያም ዕሰተ ምጽአቱ ለቃል ወሥርዓተ ዘገብሮ እግዚእ እንዲል።
እንድም ወከመ ዝናም ውስተገራህት። ዝናም ምሳሌው እንደመሆኑ ገራህት ምሳሌዋ በሆነች /በምትሆን/ በማሕፀነ ማርያም ሰው ይሁን። ዝናም ምሳሌው እንደመሆኑ ገራህት ምበሌዋ በሆነች /በምትሆን/ በማሕፀነ ማርያም ሰው ይሁን። አንቲ ውእቱ ገራህቱ ሰአብርሃም እንዲል።
ወከመ ጊሜ ውሰተ ፀምር። ጠል ምሳሌው እንደመሆኑ ፀምር ምሳሌዋ በሆነች በማሕፀነ ማርያም ሰው ይሁን። ፀምር ዘጌዴዎን እንዲል። ፀምር ዘጌዴዎን ያሰኘው እንደምን ነው ቢሉ
ታሪክ የምድያም ሰዎች ፳ኤልን ፯ዓመት አገዛዝ አጽንተው ገዟቸው በዘር በመከር ጊዜ እየመጡ ይወጓቸው ነበር። ከዕለታት ባንድ ቀን ይህ ጌዴዎን ስንዴ ደርሶለት እየለበረ ሲያሻሽ መልአኩ መጥቶ ኦ ፅኑዓ ኃይል እግዚአብሔር ምስሌከ። ፅኑዓ ኃይል ጌዴዎን እግዚአብሔር በረድኤት ካንተ ጋር አለ አለው። ባባቶቻችን ዘመን ነበረ እንጂ በኛስ የሰም በረድኤትማ ካሰ የምድያም ሰዎች እንዲህ አድርገው አገዛዝ ሲያፀኑብን መቼ ይተወን ነበር አሰው። አይዞህ ባንተ አድሬ አጠፋቸዋለሁ ብሎሃል አለው። ምን ምልክት ታሳየኛለህ አሰው በግ ሠውተህ ሥጋውን ባገልግል /በቅርጫት/ ደሙን በመንቀል አድርገህ አምጣ አሰው አመጣ። ካጠገቡ ንጽፍ ደንጊያ አለ ሥጋውን ከዚያ ላይ አኑረው ደሙን በላይ አፍስስበት አለው። እንዳለው አደረገ። መልአኩ ዘንግ ይዞ ነበር። ያን ደንጊያ በዘንግ ቢመታው ከደንጊያው እሳት ወጥቶ ሲበላው አይቷል /ያያል/ ይህ ምሳሌ ነው። እሳት የሥልጣነ እግዚአብሔር፡ ዘንግ የኵናተ ጌዴዎን። ሥጋ የእሕዛብ

ምሳሌ፡ ሄዶ ቤተጣዖቱን አቃጠለው ተሰብስበው መጥተው ዮአስ አሉት የጌዴዎንን አባት ልጅህ አምላካችንን ተበቅሎብናልና አምጣው እንበቀለዋለን ለጣዖቱ እንሠዋዋለን አሉት፡፡ ለአምላካችሁ እናንተ ትበቀሉለታላችሁ? እሱ ተበቅሎ ያጥፋው እንጂ ብሎ ዘበተባቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ፯ ዓመት እንደገዟቸው ለማጠየቅ ሰባት ዓመት የሆነው ወይፈን ነበረው ያን ሠዋ፡፡ ፀምር ልዘርጋ በፀምሩ ላይ ጠል ይውረድ /ይውረድበት/ በዳሩ በዳሩ ላይ አይውረድ /አይውረድበት/ አለ እንዳለው ተደረገ፡፡ ቢጠምቀው ወመልዐ አይገነ ይላል፡፡ መንቀል/ትንሽ የውሃ እንስራ /ማድጋ/ ሙሉ ሆኗል /ሆነ/፡፡ ጠጥቶታል፡፡ ኃይል ቅሉ የሆነው ይህ ነው፡፡ ተፈታተነኝ አትበል፡፡ ሁለተኛ ልዘርጋ በዳር በዳሩ ይውረድ በፀምሩ ላይ አይውረድ አለ እንዳለው ተደርጓል፡፡ ይህ ምሳሌ ነው ፀምር የእስራኤል፡ ጠል የረድኤተ እግዚአብሔር፡ በፀምሩ ላይ መውረዱ በዳር በዳር አለመውረዱ ረድኤተ እግዚአብሔር ለእስራኤል የመሰጠቱ ለአሕዛብ አለመሰጠቱ፡፡

## በ፪ተኛ አማርኛ

ጠል የመዓተ እግዚአብሔር፡ በዳር በዳር መውረዱ በፀምሩ ላይ አለመውረዱ መዓተ እግዚአብሔር በአሕዛብ የመታዘዙ፡ በእስራኤል አለመታዘዙ፡ አንድም ፀምር የእመቤታችን፡ ጠል የጌታ፡ በፀምሩ ላይ መውረዱ ጌታ ከእመቤታችን ሰው የመሆኑ ሥጋ የመልበሱ፡ በዳር በዳር አለመውረዱ ጌታ ከሌሎች ሴቶች ሰው ያለመሆኑ ሥጋ ያለመልበሱ፡፡

## በ፫ኛ አማርኛ

ጠል የዘርዐ ብእሲ፡ በዳር በዳር መውረዱ ሌሎች ሴቶች በዘር በሩካቤ የመውለዳቸው፡ በፀምሩ ላይ አለመውረዱ እመቤታችንን ዘርዐ ብእሲ ሩካቤ ብእሲ አላገኛትም፡፡

እስመ ስመ እግዚአብሔር ጸዋዕኩ፡፡ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቼ እነግራቸዋለሁና /ነግሬያቸዋለሁና/፡፡



ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ፡፡ ለፈጣሪያችን ዕበይ ስጡ አለ ዐቢይ እያላችሁ አመስግኑ፡፡

፬. እግዚአብሔር ጻድቅ በምግባሩ፡፡ እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ እውነተኛ ነው፡፡
ወርቱዕ ኵሉ ፍናዊሁ፡፡ ሥራው ሁሉ የቀና ነው፡፡
እግዚአብሔር ጻድቅ ወአልቦ ዓመፃ፡፡ እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ሐሰት የለበትም ቸር ነው ግፍ የለበትም፡፡
ጻድቅ ወኄር እግዚአብሔር፡፡ እግዚአብሔር ቸር ነው እውነተኛ ነው፡፡ ሰው ቸር ቢሆን እውነተኛ እውነተኛ ቢሆን ቸር አይሆንም፡፡

፭. አበሱ ወአኮ ሎቱ ትውልድ ርኩሳን፡፡ ርኩሳን ትውልድ /ትውልደ ርኩሳን/ ይላል፡፡ በደሉ የሱ ወገኖች አይደሉም እሱን የጎዱ አይደለም ለሱ ምላሹ አይደለም፡፡ መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከደንጊያ አፍልቆ ለሚገበ ለሱ፡፡ ትውልድ ዕሉት ወግፍትዕት፡፡ አሉተኛ ግፍትዕት ወረተኛ ትውልድ አንድ ጊዜ ወደሕገ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ወደሕገ ጣዖት የምትል፡፡
ከመዝኑ ተዐሥይዎ ለእግዚአብሔር፡፡ ለእግዚአብሔር እንዲህ ያለ ወረታ ትመልሱለታላችሁ? መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከደንጊያ አፍልቆ ለመገበ፡፡

፮. ዝ ሕዝብ ዓብድ ወአኮ ጠቢብ፡፡ ዘአልቦ ጥበብ /ወአልቦ ጥበብ/፡፡ ይህ ወገን ጥበብ የሌለው ሰነፍ ነው፡፡ አንድም ወአልቦ ጥበብ ይህ ወገን ሰነፍ ነው፡፡ ወአኮ ጠቢብ ብልህ አይባልም፡፡
አኮኑ ዝንቱ አብ ፈጠረከ፡፡ ፈጣሪህን ትክድ ለጣዖት ትሰግድ ዘንድማ የፈጠረህ እግዚአብሔር አይደለምን?
ፈጠረከኒ ወገብረከ፡፡ ፈጠረከኒ፡፡ በነፍስ ወገብረከ በሥጋ፡፡ አንድም ፈጠረከኒ በነፍስ በሥጋ፡፡ ወገብረከ ወገን ያደረገህ አይደለምን?

፯. ወተዘከር መዋዕለ ትካት፡፡ ይህንስ ማሰብ ትተህ የቀደመ ዘመንን አስብ አለ፡፡ የኖኅን ዘመን አስብ፡፡

ወኀሲ ዓመተ ለትውልደ ትውልድ:: ለልጅ ልጅ የሚሆን የኖኅን ዘመን አስብ::
ተሰአሎ ለእቡከ ወይነግረከ:: አንተም ባታውቅ አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል::
ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ:: ሽማግሌዎቹን ጠይቅ ይነግሩሃል::

፰. አመ ከፈሎሙ ልዑል ለአሕዛብ:: ደቂቀ ኖኅን በቦታ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል::
ወዘከመ ዘርዖሙ ለደቂቀ አዳም:: ደቂቀ አዳምን በቦታ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል::
ሠርዖሙ ለአሕዛብ በበደወሎሙ:: በየአውራጃቸው እንደሠራራቸው:
ወበበኍልቆሙ ለመላእክተ እግዚአብሔር:: በመላእክተ ዑቃቢያቸው ቍጥር እንደሠራራቸው::

፱. ወኮነ ያዕቆብ መክፈልተ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር:: ያን ጊዜ ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ወገንነት ያለው እድል ሆነ:: ወእስራኤልኒ ሐብለ ርስቱ:: እስራኤልም በርስቱ በኢየሩሳሌም የሚኖር ሆነ:: ከማየ ዓይኅ በኋላ ኖኅን ሽማግሌ መልእኩን ዳኛ አድርጎ አካፍሏቸዋል:: ያን ጊዜ ቀኝ ቀኙ ለያፌት ግራ ግራው ለካም መካከሉ ለሴም ደርሷል:: ኋላ እስ ደብረ ዘይት እስ ቀራንዮ እስ ደብረ ታቦር ጌታ ሥራውን የሚሠራባቸው አህጉር ላንተ እንዲደርሱህ ማድረጉ ቢወድህ አይደለም? እሉን ትተህ ለምን ጣዖት ታመልካለህ ለማለት:: እንድም ተዘከር መዋዕለ ትካት:: የቀደመውን ዘመን አስብ እስ የናምሩድን:: ወኀሲ ዓመተ ለትውልደ ትውልድ:: የልጅ ልጅ የሚሆን የናምሩድን ዘመን አስብ::



ተሰአሎ ለእቡከ ወይነግረከ:: አንተ ባታውቅ አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ:: ሽማግሌዎችን ጠይቅ ይነግሩሃል::
አመ ከፈሎሙ ልዑል ለአሕዛብ:: ደቂቀ ናምሩድን በቋንቋ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል::
ወዘከመ ዘርዖሙ ለደቂቀ አዳም:: ደቂቀ አዳምን በቋንቋ በለያያቸው ጊዜ ያደረገውን ነገር እንደለያያቸው ይነግሩሃል::
ሠርዖሙ ለአሕዛብ በበደወሎሙ:: በየአውራጃቸው እንደሠራራቸው ወበበኍልቆሙ ለመላእክተ እግዚአብሔር::

በአለቆቻቸው ቀጥር እንደሠራራቸው ይነግሩሃል:: ወከነ ያዕቆብ ትርጓሜ እንዳለፈው አይሰወጥም::
ወእስራኤልኒ ሐብለ ርስቱ:: እስራኤልም በርስቱ በዕብራይስጥ ቋንቋ የሚናገር ሆነ::
ታሪክ እነዚህ ደቂቀ ናምሩድ አንድ ሁነው ወደምሥራቅ ሲጓዙ ሠናዖር ከምትባል ሜዳ ደረሱ:: ከዚያ ላይ ሆኖ የውሃ ሻሻቱ እየሰደደ የሚያጠፋቸው ያባቶቻችንን ጠላት እናጥፋ ብለው ግንብ ይሰሩ ጀመር:: ፲፫ ምዕራፍ አድርገው ጀምረዋል:: ዐቢይ ምዕራፍ ያሉ እንደሆነ ፰ ገመል ከነሳቢው /ከነመሳቢያው/ ሰኮ አተርትሮ የሚያቆም የሴትና የወንድ መልክ /አካሄድ/ የሚለይበት፡ የፈረስ አፍታ የሚደክምበት፡ ንዑስ ምዕራፍ ያሉ እንደሆነ የወንጭፍ ደንጊያ የሚደርስበት፡ የፈተና ደንጊያ ተሸክሞ የሚያደርስበት፡ አርበኛ ፍላፃ ወርውሮ የሚያደርስበት ያህል አርቀው ጀምረዋል:: አሠራታ ፸፪ አለቆች ሹመዋል ጡቡ አቆልቋዩ ፲ ክንድ ወርዱ ፫ ክንድ ፭ሺ ከ፭፻፴፫ ክንድ ከ፪ ስንዝር ሠርተው ወጡ:: ከዚያ ላይ ሆነው ፍላጻቸውን ሽቅብ ይወረውራሉ በአየር ያሉ አጋንንት በምትሐት ደም እየቀቡ ይሰዱላቸዋል:: እኔ ንጉሡን ወጋሁት እኔ ቢትወደዱን ወጋሁት እያሉ ሲዘብቱ /ይዘባበቱ/ ጀመር:: ሥላሴ ንዑ ንረድ ወንክዐሙ ነገሮሙ ለከሰዳውያን በነገርን ብለው፡ ባንድ ቋንቋ ይናገሩ የነበረ ፸፩ ቋንቋ ጨመሩባቸው:: ጭቃ ሲሰው ደንጊያ ደንጊያ ሲሰው ጭቃ እያመጣ የማይስማሙ ሆነው ወርደዋል:: ይህንንም እንዳያመልኩት በነፋስ በትኖታል:: ያንጊዜ ፲፫ ለሴም ፳፭ ለያፌት ፴፪ ለካም ደርሷል:: ዕብራይስጥ ቋንቋ ለሴም ደርሷል:: ፊትም ዓለምን የፈጠረበት ኋላም ዓለሙን የሚያሳልፍበት እንዲደርስህ ማድረጉ ቢወድህ አይደለምን? እሱን ትተህ ለምን ጣዖትን.ታመልካለህ ለማለት::

፲. ወአጽገቦሙ በምድረ ገዳም:: በምድረ በዳ አጠገባቸው መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከደንጊያ አፍልቆ::



በብሔረ ጽምዕ ወሐፍ በብሔረ በድው:: ጽምዕ ሐፍ ባለበት ቦታ አጠገባቸው::
አንድም በብሔረ ሐሩል በብሔረ ፋሉል ይላል ጥፉ::
መገቦሙ ወመርሖሙ:: <u>መገባቸው</u> መርቶ አወጣቸው::
ወዐቀቦሙ ከመ ብንተ ዓይን:: እንደ ዓይን ብሌን ጠብቃቸው የዓይን ብሌን በሽፋሽፍት እንድትጠበቅ እርሷም ሕዋሳቷን እንድትጠብቅ::

፲፩. ወከመ ንስር ዘያስተጋብእ እጐሊሁ በታሕተ ክነፊሁ:፥ ንስር ልጆቹን በክንፉ ውስጥ እንዲሠውር ሠወራቸው::
ወከመ የሐቅፍ እጐሊሁ በገበዋቲሁ:: በጎኑ እንዲያቅፍ አቀፋቸው:: ወሐዘሎሙ በክነፊሁ:: በክንፈ ረድ<u>ኤቱ</u> <u>አጸናቸው /አዘላቸው/</u>
ወጾሮሙ በእንግድዓሁ በረድኤቱ አጸናቸው::

፲፪ እግዚአብሔር ባሕቲቱ መርሖሙ:: እግዚአብሔር ብቻውን መርቶ አወጣቸው::
ወአልቦ ምስሌሆሙ አምላክ ነኪር:: ከነርሳቸው ጋር ጣዖት አልነበረም::

፲፫. ወአዕረጎሙ ዲበ ኃይለ ምድር፡ ኀበ ብዕለ ምድር ይላል:: አወጣቸው ወሴሰዮሙ እክለ ገራውህ:: እህሉን መገባቸው በታነጸ ግንባቸው በደረሰ እዝመራ መከራቸው ገብተዋልና::
ወሐፀኖሙ በመዓር እምኰኵሕ:: ከደበቅና ከማጓ /ከዋሻና ከእንጨት/ ውስጥ የተገኘውን ከዳቦ ቆሎ ከድንጊያ ይልቅ የጸናውን ወግሩን /ግግሩን/ ማር እየመገበ አሳደጋቸው::
በቅብዕ እምእብን ፅንዕት:: ከድንጊያ ይልቅ የጸናውን ቅቤ እየመገበ አሳደጋቸው የደጋ ላም ጦስኝ የሚባል ሣር /ቅጠል/ ትበላለች ያ ቅቤው ፅኑ ነውና::

፲፬. በቅብዐ እጕልት ወበሐሊበ በግዕ:: የጊደሩን ቅቤ የበጉን ወተት እየመገበ አሳደጋቸው::
ምስለ መቍዓለ ጠሊ ወላሕም:: ከፍየሉ ከላሙ ወረሞ /ጮማ/ ጋራ::

ዕጉለ አልሕምት ወአባግዕ:: የላሙን ጊደር የበጉን ጠቦት እየመገበ አሳደጋቸው:: ምስለ ቄቅሐ ሥርናይ:: ልጦ ጉርዶ ከወጣው ስንዴ ጋር /ከተፈተገና ከተጣራ/ ወደመ አስካለ ወይን ሰተዩ:: የወይኑን የዘለላውን ደም ጠምቀው /ጨምቀው/ ጠጡ:: አንድም ወደመ አስካል ሰትዩ ወይነ:: የዘለላውን ወይን ደም ጠጅ አድርገው ጠጡ::

፲፭. በልዐ ያዕቆብ ወጸገበ:: ያዕቆብ ያን በልቶ ጠገበ::
ከረየ ጽጋብ ለምንዝሩት፡ ፍቁር ይላል:: ድልድል ቅምጥል ያዕቆብን ጥጋብ አቀናጣው::
ሰብሐ ወገዝፈ ወርኅበ:: ሰብሐ የወርድ:: ወገዝፈ የቁመት:: ወርኅበ የወል:: ኀደጎ ለእግዚአብሔር ፈጣሪሁ:: ፈጣሪው እግዚአብሔርን ተለየው:: አንድም ፈጣሪው እግዚአብሔር ተለየው::
ወርኀቀ እምእግዚአብሔር ሕይወቱ:: ከሕይወቱ ከእግዚአብሔር ራቀ:: አንድም ሕይወቱ ከእግዚአብሔር ራቀ::

፲፮. ወዐሀኩኒ በዝ ነኪር፡ ሆኩኒ ይላል:: በጣዖታቸው አወኩኝ ቅሠፈን ቅሠፈን አሉኝ:: አሁን ቅሠፈን ቅሠፈን ብለው አይደለም:: ኃጢአት ሠርቶ ንስሓ አለመግባት ቅሠፈኝ ቅሠፈኝ ማለት ነውና::
ወአምረሩኒ በርኩሶሙ:: በኃጢአታቸው አሳዛኑኝ በርኩሶሙ በጣዖታቸው አሳዘኑኝ::

፲፯. ሦዑ ለአጋንንት ወአኮ ለእግዚአብሔር:: ለአጋንንት ሠዉ ለእግዚአብሔር የሠዉ አይደለም ለሱ ምላሹ አይደለም:: መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከድንጊያ አፍልቆ ለመገበ ለሱ ለአማልክት እለ ኢየአምሩ:: ለማያውቋቸው ለጣዖታት፡ ለአማልክተ ግብት እለ ኢይበቍዑ:: ለማይረቡ ለማይጠቅሙ ድንገት ለተገኙ ለጣዖታት ሠዉ
ወእለ ኢየአምሩ አበዊሆሙ:: አባቶቻቸው ለማያውቋቸው አባቶቻቸውን ለማያውቁ:: ጌታ የሆነ እንደሆነ እነ ውእቱ



አምላከ አበዊከ አምላከ አብርሃም አምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ ይላል::

፲፰. ኀደጎ ለእግዚአብሔር ዘወለደከ:: በሃይማኖት የወለደህን እግዚአብሔን ተለየኸው::
ወረሳዕኮ ለእግዚአብሔር ዘሐፀነከ:: በሕግ መጽሐፋዊ ያሳደገህን እግዚአብሔርን ዘነጋኸው::
አንድም ሐደጎ ለእግዚአብሔር ዘወለደከ:: ወልድየ ዘበኩርየ ብሎ በሐዲስ ተፈጥሮ የፈጠረህ እግዚአብሔርን ተለየኸው::
ወረሳዕኮ:: መና ከደመና አወርዶ ውሃ ከድንጊያ አፍልቆ የመገበህ እግዚአብሔርን ዘነጋኸው::

፲፱. ወርእየ እግዚአብሔር ወቀንዐ:: እግዚአብሔር ይህን አይቶ ቀና::
ወተምዐ መዓተ ሳዕለ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ:: በወንዶች በሴቶች ልጆቻቸው ፈጽሞ ፈረደባቸው::

፳. ወይቤ አመይጥ ገጽየ እምኔሆሙ:: ገጸ ረድኤቴን ከነሳቸው እመልሳለሁ አለ::
ወእሬእዮሙ ዘይከውኑ በደኃሪቶሙ:: በኋላ ዘመን የሚሆኑትን እያለሁ አለ:: እስመ ውሉድ ዓላውያን እሙንቱ:: ከዳተኞች ልጆች ናቸውና:: ውሉደ ዓላውያን ይላል:: የከዳተኞች ልጆች ናቸውና::
ውሉድ እለ አልቦሙ ሃይማኖት:: ሃይማኖት የሌላቸው ናቸውና::

፳፩. እሙንቱሰ አቅንዑኒ በዘኢኮነ አምላክ:: አምላክ ባይደለ በጣዖት አስቀኑኝ:: አንድም ባይደለ አምላክ አስቀኑኝ::
ወአምዕዑኒ በአማልክቲሆሙ:: በጣዖታቸው /በጣዖቶቻቸው/ አሳዘኑኝ::
ወአነ አቀንዖሙ በዘኢኮነ ሕዝብ:: እኔም ባይደለ ወገን አስቀናቸዋለሁ
በዘኢኮነ ሕዝብ፡ ሕዝበ እግዚአብሔር ባይደለ በአሕዛብ አድሬ አስቀናቸዋለሁ::

ወእምዕየሙ በሕዝብ በዘኢይሌብዉ:: ሕዝቡን ሕገ እግዚአብሔርን ልብ በማያደርጉ በአሕዛብ አስቆናቸዋለሁ /አሳዝናቸዋለሁ/ አለ አስማርኬ:: አንድም በሕዝብ በዘኢይሌብዉ በና በ የተደራረበ ነው:: በሄኖን በቅሩበ ሳሌም እንዲል:: አንድም ይገዛናል ብለው ልብ በማያደርጉ ወገን አሳዝናቸዋለሁ አለ:: ተርታ ወገን አሰነሰቼ::

አንድም ለሕዝብ በዘኢይሌብዉ:: አይሁድን ሕገ እግዚአብሔርን ልብ በማያደርጉ በአሕዛብ አሳዝናቸዋለሁ አለ:: ሊቃ ጳጳስ ጳጳስ አድርጌ ሹሜ:: እንክስ ብኩርና ለነ ወእኮ ለአይሁድ እያሉ ወሰደውባቸዋልና::

<u>፫ ጸሎተ ሙሴ ዘሣልስ</u>

ሣልስ ለንሴብሖ ነው:: ሙሴ ሦስተኛ የተናገረው ይህ ነው::

፳፪. እስመ እሳት ትነድድ አመዓትየ:: ከመዓቴ የተነሣ እሳት ትነዳለችና ወአምዕየሙ ላለው /ባለው/:: አንድም ከመዓቴ የተነሣ እሳት ትነዳለች እኮን:: እሳት አባር ቸነፈር ጦር:: ወታውዓ እስከ ሲኦል ታሕተ:: ሲኦል:: ታሕተ አንድ ወገን:: አባር:: እስከ ታሕተ መሠረተ ምድር ታቃጥላለች:: ወትበልዓ ለምድር ወለኵሉ ፍሬሃ:: የምድርን ፍሬዋን ሁሉ ትበላለች:: <u>አንድም</u> ወታውዓ እስከ ሲኦልታሕተ:: ቸነፈር ሲኦል እናት አባት፡ ታሕት እያት ቅድመ እያት ታጠፋለች::

ወትበልዓ ለምድር ወለኵሉ ፍሬሃ:: ምድር እናት አባትን:: ወለኵሉ ፍሬሃ ልጅ የልጅ ልጅን ታጠፋለች::

ወያድለቀልቅ ኵሉ መሠረታተ አድባር:: የተራሮች መሠረት በአባር ይነዋወጣል:: <u>አንድም</u> የልዑላኑ መሠረት በሞት ይነዋወጣል::

፳፫. ወእስተጋብእ ላዕሌሆሙ እኩየ::መቅሰፍትን እሰበስብባቸዋለሁ::



ወእኀልቅ እሕፃየ በላዕሌሆሙ:: እሕፃ መዓቴን እፈጽምባቸዋለሁ::

ወየኀልቁ በረኀብ:: እሕፃ ካለው /ካላቸው/ አንዱን አመጣ በረኀብ ያልቃሉ::

ወይከውኑ መብልዐ ለአዕዋፈ ሰማይ:: ለአዕዋፍ ምግብ ያሆናሉ:: በዘመነ ረኀብ አዕዋፍ ይሠለጥናሉ::

፳፬. ወይደክም ፅንዖሙ:: ጉልበታቸው ይደክማል:: አንድም አርበኞቸው ይደክማል::

ወእፌንው ላዕሌሆሙ ስነነ አራዊተ ምድር ምስለ ኀምዝ:: መርዝ ያላቸው አራዊትን እሰድባቸዋለሁ /እሰዳለሁ/:: በዘመነ ረኀብ አራዊት ይሠለጥናሉና:: አንድም ከሠራዊቱ ጋራ ነገሥታቱን እሰዳለሁ:: ዘነኪር ኀምዙ እንዲል::

ከመ ይትየዩ እምድር:: ከዚህ ዓለም በሞት ይርቁ /ይለዩ ዘንድ/::

፳፭. በአፍኣ ያጸምቶሙ መጥባሕት ለውሉዶሙ:: ልጆቻቸውን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል:: ጸምታ /ጸሚታ/ እንዲል ትግሬ::

ወውስተ እብያቲሆሙ ድንጋጼ በቤታቸው ልቅሶ ይሰማል:: ለወራዙቶሙ ምስለ ደናግሊሆሙ ከቆነጃጅቱ ጋር ጎልማሶችን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል::

ለሕፃናቲሆሙ ምስለ አዕሩጊሆሙ:: ከሽማግሎች ጋራ ሕፃናቱን በቤት ልቅሶ ያገኛቸዋል:: አንድም ለወራዙቶሙ ምስለ ደናግሊሆሙ:: ከቆነጃጅቱ ጋር ጎልማሶቹን በቤት ልቅሶ ያገኛቸዋል አለ:: የማይዘምት ጎበዝ የማትዘምት ቆንጆ::

ለሕፃናቲሆሙ ምስለ አዕሩጊሆሙ:: ከሽማግሎች ጋራ ሕፃናቱን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል:: የሚዘምት ሕፃን የሚዘምት ሽማግሌ:: አንድም አንድ አንድ ወገንም ይለጣል::

፳፮. ወእቤ ከመ እዝርዎሙ:: አጠፋቸው ዘንድ አጠፋቸዋለሁ:: ወእስዐር እምድር ዝክሮሙ:: ስም አጠራራቸውን ከዚህ ዓለም ላጥፋ አልሁ::

ወእምዕጓለእመሕያው። ከሰው ልይቼ ሳጥፋ እልሁ።
፳፮. በመዓት ፀረ ኮኑኒ። ጣዖቱን በማምለክ ጠላት ሆነውኛልና።
መዓተ አረሚ እንዲል።
ከመ ኢይትዐበዩ ሀር። ሀር እስራኤል እንዳይታበዩ።
ወኢይበሉ እዴነ ፀንዓት። ሥልጣናችን በአሕዛብ በረታች እንዳይሉ።
፳፯. እስመ ሕዝብ ኀጉላነ ምክር እሙንቱ። እስራኤልም ምክር ያጡ ወገኖች ናቸውና።
አልቦሙ ምልሕ ወኢ ሃይማኖት። የበጀ ምግባር የበጀ ሃይማኖት የላቸውምና በከንቱ ይታበያሉ እንጂ እንዳይታበዩ።
አኮኑ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለዝ ኵሉ። የአሕዛብን ጥፋት የእስራኤልን ድኅነት ያደረገ እግዚአብሔር አይደለምን ለምን ይታበያሉ።
እንደም ከመ ኢይትዐበዩ ፀር። ፀር አሕዛብ እንዳይታበዩ።
ወኢይበሉ እዴነ ፀንዐት። ሥልጣናችን በእስራኤል በረታች እንዳይሉ። ወእምዕጓለእመሕያው። በመዓት ተቆጥቼ ከሰው ለይቼ ጠላታቸውን ባጠፋላቸው ፀረ ኮኑኒ። እስራኤል ጠላት ሆኑኝ።
አኮኑ እግዚአብሔር <u>ዘገብሮ ለዝ ኵሉ። እስመ ሕዝብ ሕጉላነ ምክር እሙንቱ።</u> አሕዛብ ምክር ያጡ ወገኖች ናቸውና።
አልቦሙ ምልሕ ወኢ ሃይማኖት። ምግባር ሃይማኖት የላቸውና የአሕዛብን ጥፋት የእስራኤልን ድኅነት ያደረገ እግዚአብሔር አይደለም? ተቆጥቶ ከሰው ለይቶ ጠላታቸውን ቢያጠፋላቸው ለምን ጠላት ሆኑት።
፳፱. ወኢሐለይዎ ከመ ያእምርዎ ለዝንቱ። አሕዛብ ይህን ያውቁት ዘንድ አላሰቡትም።
<u>ወኢያአምርዎ /ወኢያአምሩ/</u> በመዋዕል ዘይመጽእ። በሚመጣው ዘመን የሚሆነውን አያውቁትም /አያውቁም/።
፴. እፎ ያነትዮሙ ፩ዱ ለ፲ቱ ፻። ከእስራኤል አንዱ ከአሕዛብ ሺሁን ድል እንዲነሳ አላወቁም /አያውቁም/። ሶምሶን በተናቀች መንሰከ አድግ ሺሁን ሰው እንዳጠፋ።



ታሪክ ከነገደ ዳን የተወለደ ማኑሄ የሚባል ሰው ነበረ። ሚስቱ እንትኩ ትባላለች ልጅ ባለመውለዳቸው /ስላሌላቸው/ ዘወትር ያዝኑ ነበር። ከእለታት በአንድ ቀን ይች እንትኩ /እንትኩይ/ ውሃ ለመቅዳት እንጨት ለመስበርም ቢሉ ከውጣች ዘንድ መልአክ አገኛት /አገኘች/። ልጅ ትወልጃለሽና መሥዋዕት የማይሆነውን አትብዪ ራሱን አይላጭ አላት። ሄዳ ለባሏ ነገረችው ለሚስቱ የገለጽክላትን ለእኔም ግለጽልኝ ብሎ ጸለየ። በነጋው ብትሄድ አገኘችው ሄዳ ያን ሰው እንጂ አገኘሁት አለችው። ሄዶ ትናትና ሚስቱን እንዲህ ያልሃት አንተ ነህ? አለው ያንገራገረው ይመስላል አዎን የነገርኋትን ሁሉ አታስፈርሳት አለው። ምን ምልክት ታሳየኛለህ አለው በግ ሠውተህ ሥጋውን ባገልግል ደሙን በመንቀል አድርገህ አምጣ አለው። አመጣ ካጠገቡ ጎጥፍ ድንጊያ አለ ሥጋውን ከዚያ ላይ አድርገው ደሙን በላዩ አፍስሰበት አለው እንዳለው አደረገ። ከሰማይ እሳት አውርዶ አብልቶለታል እንዲረዳው። መልአኩ እሳቱን ተረግጦ አረገ።
ሀእእመራ ለእንትኩ ይላል። በግብር አወቃት ተጸነሰ ተወለደ ሶምሶን አሉት ፀሐይ ማለት ነው። ሽምሽ እንዲል ዓረብ አደገ። በዚያ ወራት እስራኤል ለኢሎፍሊ ግብር ይገብሩ ነበር። ይህ ማኑሄ ግብር ይዞ ሲሄድ አብሮ አባቱን ተከትሎ ሄደ። መልክ መልካም ሕፃን አይቶ ተመለሰ አግባ አሉት። አግባ ካላችሁኝማ እንዲህ ያለች ብላቴና አይቻለሁና እሷን አጋቡኝ አለ። እንዴት ግዙራን ስንሆን ሥርዓት አፍርሰን ከቆላፋን /ካልተገረዙት/ ጋር እንጋባ አይሆንም አሉት። እንግዲያስ እኔም አይሆንም አለ። ምን እናደርጋለን ብለው ሶምሶን ያለውን ነገር ሊያቆሙ /ቃል ሊገቡ/ ሲሄዱ አንበሳ መደብ /ዓይነ ምድር ለመቀመጥ/ ወጣ። አንበሳ አፉን ከፍቶ መጣበት። አንድ ጊዜ በጡጫ ቢለው አርፏል። እንድም መንጋጋውን ይዞ ሰነጠቀው ነገር አቁመው /ቃል ተገባብተው/ ተመለሱ። ሊሞሽር ሁለተኛ ሲሄድ ከዚያ ቦታ ንብ ገብቶ ማር ሠርቶ አገኘው። ቀርጦ

በልቶ የተረፈውን ለዘመዶቹ ይዞላቸው ሄደ። እልነገራቸውም ምንም ቢሆን ኃይሉ ተሰምቷልና ሰላሳ እላማጅ /ሚዜዎች/ ሰጡት። ከጨዋታ የተነሣ ምሳሌ መስዬ ነግሬያችሁ በ፯ዱቱ ቀን ፀሐይ ሳትገባ ብትነግሩኝ ፴ መጎናጸፊያ ከነቀሚሱ እሰጥ እናንተ ምን ትሰጡ አላቸው። እኛም እንሰጣለን ብለው ተወራረዱ። መስል ምሳሌክ እሉ። እምአፈ በላዒ ተረክበ መብልዕ ወእምአፈ ጽኑዕ /ግሩም/ ወጽአ ጥዑም አላቸው። የማይሆንላቸው ሆነ ይህን ሰው እኛን ልታደኸዩ አምጥታችሁታል ጠይቀሽ ንገሪን አሏት። ብትጠይቀው አይሆንም አላት። እንደ ማኩረፍ አለች ምንም ቢሆን ሴት ታሸንፋለችና ከአፈአንበሳ ማር አግኝቼ በልቼአለሁ አላት። ሄዳ ነገረቻቸው በሰባተኛዪቱ ቀን ፀሐይ ሳትገባ መጥተው ሶምሶን ምሳሌህን እንንገርህ አሉት። በሉ ንገሩኝ አላቸው። እምአፈ በላዒ ተረክበ መብልዕ ወእምአፈ ፅኑዕ ወጽአ ጥዑም። ከአንበሳ የበረታ አለን? ከማርስ የጣፈጠ አለን? ከአፈ አንበሳ ማር አግኝተህ በልተሃል አሉት። ወሶበሰ እምኢያሥራኀክምዋ ለዕጉልትየ እምኢረከብክምዋ ለምሳሌየ። ሚስቴን ባትዘበዝቧት ምሳሌዬን ባላገኛችኋትም ነበር ብሎ ተቆጥቶ በረሀ ወረደ። ከነሱ ወገን ፴ ሰው ገድሎ ልብሳቸውን ገፎ አምጥቶ ጥሎላቸው ሄደ። እሷንም ካላማጆቹ ሳንዱ ድረዋታል። በሦስት ወሩ የበግ ጠቦት እያሳበ መጣ /ሄደ/ ሚስቴን ስጡኝ አላቸው። እሷንስ ለሌላ ሰጥተናታል ትወድ እንደሆነ ከሷ የምታምር ትንሽ እኅቷ አለች እሷን አግባ አሉት። ሚስቴን እንጅ ሌላ አልሻም /አይሆንም/ አለ። እሷንስ አንድ ጊዜ ሰጥተናታል አይሆንም አሉት። በሩጫ ፫፻ ቀበሮ እያባረረ ይዞ ፻፶ ዳቦት እንደመስቀል እያደረገ ሠራ። ያን እያቃጠለ እንዱን ከሁለቱ ጅራት እየቋጠረ ሰደዳቸው። ምን ተከተለን እያሉ አዝመራቸውን ቁመናውን ክምሩንም አቃጠሉት። ይህን ያደረገ ማነው አሉ። ሶምሶን አላቸው ምን ቢሆን አሉ። አማቾቹ በድለውት አሏቸው። ሄደው ዘረፏቸው ሶምሶን እንተን ደስ ይበልህ ብለን እንዲህ



አደረግን አሉት መልካም አደረጋችሁ ይህን ባታደርጉ ጠቤ ከእናንተ ጋራ ነበር አላቸው። ማን መብት ሰጠውና እንዲህ ይለናል ብለው ሲያንጎራጉሩ ሰምቶ ምን ያንጎራጉራሉ ብሎ ጎመዱን አንስቶ ጭን ጭናቸውን ሰብሮ ሄደ። በዓተ ኤጣም /ኤላም/ ተሠወረ። ተሰብስበው ሄደው ዘመዶቹን ያዟቸው ስታመጡ ሶምሶንን አምጡ በቀረው እናንተን እናጠፋችኋለን አሏቸው። ፫ኤል ከሦስት መቶ የሚበዙ ሆነው ሄደው ሶምሶን እባክህን ባንተ ምክንያት እንጥፋ አለፍልን አሉት። በሉ እናንተ ሳታጠፉኝ ማሱልኝ አላቸው። እንዲህ ማሰቱ ኃይሉ በአሕዛብ እንጂ በ፫ኤል አልታዘዘምና ማሉለት። በ፪ት ሳመ ገመድ /ባልደረቀ እርጥብ ጠፍር/ አሥረው ይዘውት ሄዱ ከእስራኤል እጅ ሲወጣ /ወጥቶ/ በአሕዛብ እጅ ሲገባ ያችን እንደፈትል ክር ቆርጦ ግራ ቀኝ ቢያይ መንሰክ አድግ አገኘ። ያን ቢያግዘገዝግ ሺህ ሰው እርስ በርሱ ተሰጋግቶ አልቋል። ከዚያው ውሃ ፈልቆለት ጠጥቷል።

ወ፳ቱ ይሰድድምሙ ለ፻፻። ከእስራኤል ሁለቱ ከአሕዛብ አልፉን /አሥር ሺሁን/ ድል እንደነሷቸው አላወቁም። በባእል ጊዜ ተማምለው ተሰፋፈሩ /ተሰለፉ/።

ታሪክ እስራኤል አሕዛብን ሳንወጋ እህል ውሃ እንቀምስም ብለው አሕዛብም እስራኤልን ሳንወጋ እህል ውሃ አንቀምስም ብለው፡ የሳኦል ልጅ ዮናታን ብላቴናውን አስከትሎ ወጣ። እስራኤል ድሮ ወባት ሲገቡ /አምነው እጅ ሲሰጡ/ አንድ አንድ እያሉ መጡ ያሉን እንደሆነ በእጃችን ጥሏቸዋል ዝም ያሉን እንደሆነ በእጃቸው ጥሎናል አለው። ይህን ለብላቴናው ሲነግረው እስራኤል ድሮ ወባት ሲገቡ አንድ አንድ እያሉ መጡ አይዞአችሁ ኑ እንነካችሁም አሏቸው። ያሉበትን ተራራ በእጁም በእግሩም ብሎ ወጥቶ ሃያ ሰው ገደለ። ሳኦል አሻግሮ በመነጥር ቢያይ እንደወፍ ሲነጣጠቁት አይቶ ከኛ ወደ አሕዛብ ለፈር የሄደ ሰው አለን? አስኪ ሰው ቍጠሩ /ፍቀዱ/ አለ ልጅህ ዮናታን የለም አሉት። ሄደው ገጠሙ ከአሕዛብ ሰባት ሺህ ፈረሰኛ

ሦስት ሺህ ባለ ሠረገላ አልቋል:: ምክንያት መሆናቸውን መናገር ነው::
እስመ እግዚአብሔር ፈደዮሙ:: እግዚአብሔር ፍዳውን እምጥቶባቸዋልና::
ወአምላክነሂ እግብኦሙ:: ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ጥሏቸዋልና::

፴፩. እስመ ኢኮነ አምላክነ ከመ አማልክቲሆሙ:: ሆኖም ያ ግን እንደነሳቸው እንደ ጣዖቱ አይደለምና::
ዐርነስ ዐብዳን:: ጠላቶቻችን አሕዛብ ሰነፎች ናቸው ይላሉ እስራኤል:: አንድም ወኢሐለዩ:: እስራኤል ይህን ያውቁት ዘንድ አላሰቡትም::
ወኢየአምሩ በመዋዕል ዘይመጽእ:: በሚመጣ ዘመን የሚሆነውን አያውቁትም /አያውቁም/::
እፎ ያነትዮሙ አሐዱ... ከአሕዛብ አንዱ ከእስራኤል ሺሁን ድል እንዲነሣቸው አላወቁም::
ወክልኤቱ ይሰድድዎሙ ለእልፍ ከአሕዛብ ሁለቱ ከእስራኤል እልፉን ድል እንዲነሷቸው አላወቁም:: ወያሜምዑ እምድያም ቆጽል ይላል:: ቅጠል ኮሸሽ ባለ ቁጥር ኢሎፍሊ መጡ እያሉ ነደል ወድቀው ባሕር ጠልቀው ይቀሩ ነበር አይለውጥም::
ዐርነስ ዐብዳን:: ጠላቶቻችን እስራኤል ሰነፎች ናቸው ይላሉ ነቢያት ካህናት::

፴፪. እስመ ከመ ዐፀደ ወይነ ሰዶም ዐፀደ ወይኖሙ:: የሕግ ማደሪያ ልቡናቸው የሰዶም ሕግ ማደሪያ እንደሆነ እንደ አሕዛብ ልቡና ሆኗልና::
ወሐረጎሙኒ እምነ ገሞራ:: ግብራቸው የገሞራ ነው::
አንድም ትውልዳቸው ከገሞራ ነው:: ወሐረገ ሰዶምኒ ትእኅዝ በሊዓ እንዲል::
ወእስከሎሙኒ እስካለ ሐሞት:: እስካለቸው /ፍሬያቸው/ የሐሞት እስካል ነው:: አንድም ግብራቸው መራራ ነው::
ወቀምሐሙኒ መሪር:: ግብራቸው መራራ ነው::



፴፫. ኀምዘ አርዌ ምድር ወይኖሙ:: ወይናቸው የእባብ መርዝ ነው:: ያ እንዲያጠፋ የሚያጠፋ ነው::
ኀምዘ አፍዖት ዘይቀትል:: ከዚያም ዘንድ የሚገድል የእፉኝት መርዝ ነው:: ያ መድኃኒት የሌለው ነው::

፴፬. አኮኑ ዝንቱ ትእዛዝ ዘእምኀቤየ ውእቱ:: ይህ ትእዛዝ ከእኔ የተገኘ አይደለም:: የአሕዛብ ጥፋት የእስራኤል ድኅነት ዘውትትሙ ውስተ መዛግብትየ:: በሣጥን ልቡናዬ ለጥፋት ተቆጠሩ::

፴፭. በዕለተ ኵነኔ እትቤቀሎሙ:: በፈረድኩበት ቀን አጠፋቸዋለሁ::
ወበጊዜ ይድሕፅ እግሮሙ:: ልቡናቸው በዝቢረ ኃጢአት በአምልኮ ጣዖት በተሰነካከለ ጊዜ::
አንድም ወበጊዜ፡ ይድሕፅ እግሮሙ ይላል ሳይናበብ:: በዚዜው ጊዜ ሰውነታቸው በመቅሠፍት ይሰነካከላል::
እስመ ቀርበ ዕለተ ኀልቆሙ:: ለጥፋት የተቆጠሩበት ቀን ደርሷልና::ኅልቆሙ ባለው ኀልቀቶሙ ይላል:: የሚያልቁበት ቀን ደርሷልና::
እስመ በጽሐ ድልው ውእቱ ለከሙ:: በእናንተ የተዘጋጀ መቅሠፍት ደርሷልና::
አንድም እስመ በጽሐ:: መቅሠፍቱ ደርሷልና::
ወድልው ለክሙ:: በእናንተም የተዘጋጀ ነውና::

፴፮. እስመ ይኴንን እግዚአብሔር ሕዝቦ:: እግዚአብሔር ለእስራኤል በአሕዛብ ይፈርዳልና::
ወይትናበብ በእንተ አግብርቲሁ:: ስለባሮቹ ስለነቢያት ስለካህናት ብሎ ለእስራኤል ይፈርዳልና::
እስመ ርእዮሙ ከመ ተመስዉ ወኀልቁ:: በመከራው እንደተፈጸሙ አይቷቸዋልና::
ወተዘንጕጉ በኀበ ሀለዉ ባሉበት አገር ማሽሟጠጫ /መሽሚጠጫ/ እንደሆኑ አይቷቸዋልና::

፴፯. ወሶበ ሠርሑ ይቤ እግዚአብሔር:: በመከራው በደከሙ ጊዜ እንዲህ አለ::

አይቴ እሙንቱ አማልክቲክሙ እለትትዌከሉ ቦሙ:: የምትታመኑባቸው አማልክቶቻችሁ ወዴት ደረሱ::

፴፰. ወእለ ትበልዑ መሣብሕተ መሥዋዕቶሙ:: ስቡን መሥዋዕት የምትበሉላቸው::
ወትሰትዩ ወይነ ሞጻሕቶሙ:: ከወይኑ ፍልቅ አድርጋችሁ አፍስላችሁ የምትጠጡላቸው::
ይትነሥኡኬ ወይርድኡክሙ:: ይነሷ ይርዷችሁ!
ወይኩኑክሙ መድኃኒክሙ:: ያድኗችሁ!

፴፱. አእምሩ አእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር:: እግዚአብሔር እኔ እደሆንኩ እወቁ እወቁ::
አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ:: ያለ እኔ ሌላ አምላክ እንደሌለ እወቁ እወቁ::
አነ እቀትል ወአሐዩ:: የምገድል የማድን እኔ እንደሆንኩ እወቁ እወቁ::
እቀሥፍሂ ወእሣሀል:: በመከራ የምገርፍ መልሼ ይቅር የምል እኔ እንደሆንኩ እወቁ እወቁ::
ወአልቦ ዘያመሥጥ እምእዴየ:: ከሥልጣኔ የሚያመልጥ እንደሌለ እወቁ እወቁ::

፵. አሰመ አሌዕል ውስተ ሰማይ እዴየ:: እጄን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጌ እምላለሁና::
እምሕል በየማንየ ወእብል ሕያው አነ ለዓለም:: አማንየ በርእሰየ ብዬ እምላለሁና::

፵፩. ወእበልሓ ከመ መብረቅ ለመጥባሕትየ:: ሾተሌን እንደመብረቅ አፎት አፋጥናታለሁና /አቀናጣታለሁና/
ወትቀውም እዴየ በኲነኔየ:: በፈረድኩበት ቀን እደ መዓቱ ትፀናለች:: ከፍርዴ ጋራ እደ መዓቱ ትፀናለች::
ወእትፌደዮሙ በቀለ ለፀርየ:: ከጠላቶቼ በቀልን እከፈላቸዋለሁ:: ወእትቤቀሎሙ ለጸላእትየ:: ጠላቶቼን ተበቅዬ አጠፋቸዋለሁ::

፵፪. ወእሰክሮን በደሞሙ ለአሕፃየ:: ፍላፃቼን በደማቸው አሰክራቸዋለሁ:: ወትበልዕ ሥጋሆሙ መጥባሕትየ:: ሾተሌ



ሥጋቸውን ትበላለች:: እምደመ ቅቱላን ወፂውዋን:: ከሞቱት ከተማረኩት ደም::
አሰክሮን ከሞቱትስ ይሁን ከተማረኩት እንዴት ነው ቢሉ የፈለማ /መለያ ምልክት/ እያሉ ይወጓቸዋልና::
እርእሰተ መላእክተ ፀር::
የጠላቶችን የአለቆችን ቸብቸቦ ትበልዕ:: አንድም የአለቆችን አለቆች ትበልዕ::

፵፫. ይትፌሥሓ ኲሉን ሰማያት ኅቡረ:: ሰማያት ተባብረው ደስ ይላቸዋል:: አንድም ልዑላኑ ተባብረው ደስ ይላቸዋል::
ወይሰግዱ ሎቱ ኲሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር:: መላእክት ይሰግዱለታል::
ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስለ ሕዘቢሆሙ:: ሁለቱ ነገድ ከአሥሩ ነገድ ጋራ ደስ ይላቸዋል:: ወይብሉ ኲሎሙ ውሉደ እግዚአብሔር ፅኑዕ ውእቱ:: ኽኤል ከሃሊ ነው ይላሉ::
እስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ:: የእስራኤልን ደም አስቦ አሕዛብን ይበቀላልና::
ያትቤቀል ወይትፈደይ በቀለ ለፀሩ:: ከጠላቶቹ ከአሕዛብ በቀልን ይከፈላል::
ወይትቤቀሎሙ ለጸላእቱ:: ጠላቶቹን ተበቅሎ ያጠፋቸዋል
ወያነጽሕ እግዚአብሔር ምድረ ለሕዝቡ:: ለወገኖቹ ለእስራኤል ምድረ ርስትን የምትገባ አድርጎ ያወርሳቸዋል:: ጥንቱንም የሴም ዕፃ ናትና::
አንድም ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስለ ሕዘቢሆሙ:: ሊቃነ መላእክት ተባብረው ደስ ይላቸዋል::
ወይሰግዱ ሎቱ ኲሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር:: ሠራዊተ መላእክት ይሰግዱለታል::
ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስለሕዝቢሆሙ:: ኖሎት ከኖሎት ጋራ /እረኞች ከእረኞች ጋራ/ ደስ ይላቸዋል::
ወይብሉ ኲሎሙ ውሉደ እግዚአብሔር ፅኑዕ ውእቱ:: እኑም /ሥሩዕ/ እኑም በሥጋ ሰው የሆነ ሥሩዕ ከሀሊ

እንደማለት ነው:: ከእግዚአብሔር አብ የተወለደ ወልድ ከሃሊ ነው ይላሉ::

፴፬. አስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ:: የምእመናንን ደም አስቦ አጋንንትን ይበቀላልና:: ይትቤቀል:: ከጠላቶቹ ከአጋንንት በቀልን ይከፈላል:: ወይትቤቀሎሙ ለጸላዕቱ:: ጠላቶቹ አጋንንትን ተበቅሎ ያጠፋቸዋል:: ወያነጽሕ እግዚአብሔር ምድረ ለሕዝቡ:: ለወገኖቹ ለምእመናን መንግሥተ ሰማይን የምትገባ አድርጎ ያወርሳቸዋል::



## ፬. ጸሎተ ሐና እመ ሳሙኤል ነቢይ

ሐና ማለት ፍሥሐ ወሐሤት ማለት ነው::

ወሀሎ ፩ዱ ካህን እምአርማቴም ዘመሴፋ ዘደብረ ኤፍሬም ዘስሙ ሕልቃና ይባል::

ታሪክ የኤፍሬም ዕፃ የምትሆን መሴፋ የመሴፋ ክፍል የምትሆን አርማቴም ከአርማቴም ስሙን ሕልቃና የሚሉት አንድ ካህን ነበር::

ወሀሰዋሁ ክልዔቱ አንስት ይላል:: ሁለት ሚስቶች ነበሩት::

ስእሐቲ ስማ ሐና ወስካልዕታ ፍናና:: አንዲቱ ሐና አንዲቱ ፍናና ትባል ነበር:: አሁን ካህን ነበር እስ ሁለት ሚስቶች ነበሩት እለሳ:: እንደምን ቢሉ ጌታ በዚያ ወራት /ጊዜ/ ብዛታቸውን እንጅ ሥርዓት አሳፀናባቸውም ነበርና:: እንደ ዛሬም እእምሮ አልለፋም ነበር::

ወሰሰዓመት የዐርግ ፫ተ ጊዜ:: ከዓመት ሦስት ጊዜ ኢየሩሳሌም ወጥቶ በዓል ያደርግ ነበር::

ለያስተርእ ተባዕትከ ፫ተ ጊዜያተ ለለዓመት ትላለችና እሪት:: ከተረፈ መሥዋዕቱ አንድ ዕፃ ለሐና ሁለት ዕፃ ለፍናና ይሰጥ ነበር:: ምነው ሐናን ጠልቶ ፍናናን ወዶ ነው ቢሉ መውደድስ ሐናን ይወዳል:: ያቺ ፍናና ልጆች አሏት ከልጆቿ ጋር ትበላዋለች:: ይህቺ (ሐና) ልጅ የላትም:: እርሷም ወጥታ እስከትመለስ ድረስ አትበላም ነበር:: ይህስ አይቻልም ብሎ ደስ ብሏት አትበላም ነበር:: ይህስ ስለምን ልጅ ያልሰጣት ቢሉ የብስጭት ኀዘን ታዝን ነበርና:: ይህስ ቢሆን በኋላም ባልሰጣትም ነበር ብሎ አዝና ታግኘው ብሎ:: አዝኖ ያገኙት ልጅ ይረባል ይጠቅማልና::

ኀሎ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ እንዲል:: ይቅርታውን ያለጊዜው አይሠራውምና ከዕለታት ባንዱ ቀን ስታዝን አይቶ::

ሐና ለምንት ትቀሥፊ ልበኪ በኀዘን:: ልብሽን በኀዘን ጨንገር ለምን ትገርፊያለሽ ኢይኄይሰኪኑ እም፲ቱ ትውልድ ከ፲ ልጅ እኔ አልበልጥም /አልሻልምን/? አላት:: ኋላ ከቤተ እግዚአብሔር ገብታ እግዚአብሔር ጸባዖት ኤሉሄ አለች:: ጸባዖት

መዋዒ፡ እግዚአ ኀይላት። አዶናይ፡ ኄሩይ። ኤሎሄ፡ ፈጣሪዩ ማለት ነው።

**ለእመ ነጽሮ ነጸርከ ኅዘነ ሕማማ ለዓመትከ። ኀዘኔን ዓይተህ**

**ወወሀብካ ዘርዓ ብእሴ። ልጅ ብትሠጠኝ፡**

እነሂ እሁቦ ሀብተ በቅድሜከ። እኔም ስጦታ አድርጌ ላንተ እሰጠዋለሁ አለች።

ኢይሰቲ ወይነ ወሜሰ። የማር ጠጅ ወይን ጠጅ አይጠጣም። የማር ጠጅስ በእገራቸው የሰም ብሉ ጉሽ የወይን ጠጅ ወይም ደረቅ የወይን ጠጅ አይጠጣም።

ወኢየዐርግ ሐፂን ዲበ ርእሱ። ምላጭ ከራሱ አይወጣም ይኸውም ልማድ ነው። የስእለት ልጅ አይላጭም። ያን ጊዜ ዔሊ በጥንተ ደብተራ ወንበር አዘርግቶ ተቀምጦ ነበር። ሰሰምን ቢሉ መሥዋዕተ ነግህ እሰፈ መሥዋዕተ ሠርክ አቅርቡ ለማለት። እንድም ኢይባዕ ሞዓባዊ ወዓሞናዊ ያለውን ሰመጠበቅ።

እንድም እሥራቱን በኵራቱን ቀዳምያቱን ለመቀበል በኵራት የሰው የእንስሳ መጀመሪያ የተወሰደው ቀዳምያት የእህል አስቀድሞ የደረሰው በማናቸውም ምክንያት ከተቀመጠ ዘንድ ገብታ ስትጸልይ አይቶ።

ወእምስላ ዔሊ ከመ ሰክርት ይላል። ሰካር ሴት አስመሰላት ሥርዓት ብትሰወጥበት። ሰልማዱ ነገር ሲያገኛቸው ሰሊቀ ካህናቱ ይነግሩታል ሊቀካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ዕጣን እጥኖ ቃሰ እግዚአብሔር ጠይቆ ይነግራቸዋል። እሷ ግን ሰእሩቅ ብእሲ ቢነግሩት ምን ግዳጅ ይፈጽማል ብላ እንደ ሰብአ ሐዲስ ገብታ ስትጸልይ አይቶ።

ወይቤላ ንዒ ጻኢ እምቤተእግዚአብሔር ወእስሰሊ ወይነኪ በንዋም። ስካርሽን በእንቅልፍ አሳልፊው አላት፡ ወይን አሰው በግብሩ። እልቦ አለችው ኢትረስያ ለዓመትከ ከመእዋልድ ርኵሳት። እኔን ባርያህን እንደቅሬ እንደ ደንገጥር አታድርገኝ ቅሬ ደንገጥር ሥርዓት አፍራሽ ናት በልታ ጠጥታ ትገባለች። እንድም እንደ እሕዛብ ልጆች አታድርገኝ። እነዚያ ሥርዓት አልተሠራላቸውም።



**እላ አኪተ መዋዕል እነ።** ቀን የባሰኝ ወራት ያዋረደኝ ነኝ እንጂ አለችው። **ደኀና ከሆንሽ**

**ሑሪ በሰላም አምላከ እስራኤል የሃሉ ምስሌኪ** ብሎ ሰደዳት።

ናሁ ረከበት ዓመትከ ሞገሰ በቅድሜከ ብላለች። ደግ ሰው ሲመርቅ ደስ ያሰኛልና ደግ ሰው የተናገረው አይቀርም ብላ ሄዳ አትበላም ቢሉ በላች ደስ ብሏት እብዛታ አትበላም ቢሉ ደስ ብሏት በላች በበነጋታው ቤተእግዚአብሔር እጅ ነስተው ሄዱ።

ወእእመራ ለሐና ይላል፡ በግብር አወቃት ተፀነሰ ተወለደ ስሙን ሳሙኤል አለችው።

እስመ እምኀበ እግዚአብሔር ሰአልክዎ ትቤ። ከእግዚአብሔር ለምኜ አገኘሁት ስትል። ባሏ እንሂድ አላት መልሼ እንዳላመጣው ተስዬ ወልጄዋለሁ ትቼውም እንዳልመጣ መዋዕለ ጥብ አልተፈጸመምና (መዋዕለ ጥብን አልፈጸመምና) ጡት አልጣለም አለችው።

ንበሪ ዘይኤድመኪ ለእዕይንትኪ ባሏ፡ አቅሚ ዘወጽአ እምአፉኪ አላት። ከሴቶች ጽንት አይታጣምና በ፫ ዓመቱ ፪፻ ዳቦ ፪፻ የበሰስ ፍንጣ ሙዳዩ ሙሉ ዘቢብ ማድጋ ሙሉ ስልቅ አድርጋ ሄደች። ፊት ጥንተ መሥዋዕቱን ሠዋ ኋላ ሳሙኤል በተወሰደ ጊዜ የተወሰደ ወይፈን ነበር ያን ሠዋ ልጁን ከመሥዋዕት ይቆጠርልኝ ሲል ሄዳ ከፊቱ ቆመች።

ሰምዓኒ እግዚኦ ሕይወተ ነፍስከ። በረከትህን ስማኝ፡ የሰውነትህ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ቢመርቀኝ ልጅ ያገኘሁ እኔ እንደሆንኩ ስማኝ። እንድም ሕያውት ነፍስከ፡ በመንፈስቅዱስ ሕያውት የሆነች ሰውነትህ ብትመርቀኝ ልጅ ያገኘሁ እኔ እንደሆንኩ ስማኝ።

**ከመ እንታክቲ ብእሲት ዘቆምኩ ቅድሜከ ወበዓዕኩ ወጸሰይኩ፡**

**ወወሀበኒ እግዚአብሔር ስእለትየ እነሂ ወሀብክዎ ሁብተ በቅድሜከ። ከመ ይትቀነይ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ፡** እስከ እመ ይመውት ብላ ከዚያ ይህን ተናግራለች። በዚህም ሦስት ነገር አሳበት።

፩ኛ. ትንቢት፡ እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጐድጐደ፡
፪ኛ. ምዕዳን ኢትትመክሁ ወኢትንብቡ ዐቢያተ።
፫ኛ. አኰቴት፡ እስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር፡ ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ ወአልቦ ቅዱስ ዘእንበሌከ እግዚእ፡
፬ኛ. ፀንዐ ልብየ በእግዚአብሔር። በጎንጅ አብነት ሃይማኖት። የነቢዩ የሳሙኤል እናት ሐና የተናገረችው ነገር ይህ ነው። ጸሎትን ነገር ይላል ወጸለየ ጠቢት። ጸሎተ ትፍሥሕት ጸሎትስ ተናግሮተ ስብአ ምስለ እግዚአብሔር እንዲል። ነቢይ ቢል ለሳሙኤል ነቢይት ቢል ለሐና ይቀጸላል /ይቀጸላል/።
፩. ፀንዐ ልብየ በእግዚአብሔር። ሐሩ በሰላም አምላከ እስራኤል የሃሉ ምስሌኪ ብሰህ በሰደድከኝ ጊዜ ልቡናዩ በእግዚአብሔር አምኖ ፀና።
ወተለዐለ ቀርንየ በአምላኪየ ወመድኀንየ። በፈጣሪዩ በመድኃኒቴ አምኜ ሥልጣኔ ከፍ ከፍ አለ።
ወርኀበ አፉየ ዲበ ጸላእትየ። በጠላቶቼ ላይ አፌ ሰፋ አለ በእፍ ላይ እፍ ጨመርክልኝ ማለት አይደለም። ለሁተ ማሕፀን ይብስተ እጥባት ኀጥአተበረከት እያሉ ሰሚሰድቡኝ ሰዎች ርጉተ ማሕፀን ልምልምተ አጥባት ምልዕተ በረከት ነኝ ብዬ እንድመልስላቸው አደረግኸኝ ስትል ነው።
ወተፈሣሕኩ በአድኀኖትከ። በትድግናህ ደስ አለኝ በማርቃንከ ይላል። አድኀኖት ማለት ነው።
እስመ አልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ። እንደ እግዚአብሔር ክቡር የለምና።
ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ። እንደ ፈጣሪያችን እውነተኛ የለምና።
እስመ አልቦ ቅዱስ ዘእንበሌከ እግዚእ። አቤቱ ያላንተ ክቡር የለምና ሦስት ጊዜ መላልሳ ተናገረች ለአፅንዖተ ነገር። አንድም ለአጠይቆተ ፫ቱ አካላት።
፪. እስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር። አብ፡ ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ ወልድ፡ ወአልቦ ቅዱስ ዘእንበሌከ እግዚእ መንፈስ ቅዱስ።
፫. ኢትትመክሁ ወኢትንብቡ ዓቢያተ።



እናንተ የፍናና ዘመዶች አትመኩ ፅኑ ፅኑ ነገር አትናገሩ ዕፁተ ማሕፀን ይብስተ እጥባት ኀጥአተ በረከት እያላችሁ።
ወኢይጻእ ዐቢይ ነገር እምአፉክሙ። ይብስተ አጥባት ኀጥአተ በረከት እያላችሁ ካፋችሁ ፅኑ ፅኑ ነገር አይውጣ።
እስመ እግዚአብሔር አምላክ ማእምር ውእቱ። እግዚአብሔር አዋቂ ነውና አውቆ ያጠፋችኋልና /ይፈርዳልና/።
እግዚአብሔር አስተደለወ መንበሮ። እግዚአብሔር መንበረ መንግሥቱን አበጃጀ በፍናና ዘመዶች ሊፈርድባቸው ለሐና ዘመዶች ሊፈርድላቸው።
፬. አድከመ ቀስተ ኃያላን። የፍናና ዘመዶች ስልጣንን አደከመ። ወአቅነቶሙ ኃይለ ለድኩማን። ለሐና ዘመዶች ኃይልን እንደ ዝናር አስታጠቃቸው።
ስጉባን አክል ርኅቡ። ፪ ዕጣ ተቀብለው ጠግበው ይኖሩ የነበሩ የፍናና ዘመዶች ተራቡ።
ወርኁባን ፀግቡ። አንድ ዕጣ ተቀብለው ተርበው ይኖሩ የነበሩ የሐና ዘመዶች ጠገቡ።
እስመ መካን ወለደት ፯ተ። መካን ሐና ፍጹም ሳሙኤልን ወልዳለችና።
እስመ ጉልቄ ሳብዕ ፍጹም ውእቱ በኀበ ዕብራውያን እንዲል። አንድም ወሐወጸ እግዚአብሔር ለሐና ወወለደት ዓዲ ፫ተ ደቂቀ ወ፪ተ አዋልደ ይላል። ሳሙኤልን ስለሁለት ቆጥሮ። ምስፍና የሙሴን ክህነት የአሮንን ይዟል።
ወወላድስ ለእነት ወሊደ። ወላድ ፍናና ግን መውለድ ተሳናት በቅናት ማሕፀኗ ደርቋል። አንድም እንደ ሳሙኤል ያለ፡ አንድም ልጅ መውለድ ተሳናት፡ አንድም የወላድ መሐን ሆነች። ልጆቿ አልቀውባታል።
እግዚአብሔር አስተዳለወ መንበሮ። እግዚአብሔር መንበረ መንግሥቱን አዘጋጀ። በግብፃውያን በባቢሎናውያን ሊፈርድባቸው ለእስራኤል ለትሩፋን ሊፈርድላቸው።
አድከመ ቀስተ ኃያላን። የግብጻውያንን የባቢሎናውያንን ሥልጣን አደከመ። ወአቅነቶሙ ኃይለ ለድኩማን። ለእስራኤል ለትሩፋን ኃይልን እንደ ዝናር አስታጠቃቸው።

፭. ፅጉባነ እክል ርኅቡ:: ግብጻውያን ተራቡ አንበጣ በልቶባቸው በረድ መትቶባቸው:: እንድም ባቢሎናውያን ተራቡ የቂሮስ የዳርዮስ ጦር ዘርፏቸው::

ወርጉባን ፀግቡ:: በግብጽ ተርበው ይኖሩ የነበሩ እስራኤል ጠገቡ:: መና ከደመና ወርዶላቸው ውሃ ከድንጊያ ፈልቆላቸው:: በባቢሎን ተርበው ይኖሩ የነበሩ ትሩፋን ጠገቡ::

፯ እህጉር ወግተው ብዕለ እሕዛብን ዘርፈው ወጥተዋል::

እስመ መካን ወለደት ፯ተ:: መካን ቤተ እስራኤል ፍጹም ሙሴ አሮንን ዮሴዕ ዘሩባቤልን አስገኝታለችና::

ወወላድስ ስእነት ወሊደ:: ወላድ ግብጽ ግን እንደ ሙሴ እንደ አሮን ያለ ልጅ ማስገኘት ተሳናት:: እንድም የወላድ መሐን ሆነች ባሕር እስጥምባት ቸነፈር ፈጅቶባት ወላድ ባቢሎን እንደ ዮሴዕ ዘሩባቤል ያለ ልጅ ማስገኘት ተሳናት:: እንድም የወላድ መሐን ሆነች የቂሮስ የዳርዮስ ጦር ፈጅቶባት::

እንድም እግዚአብሔር አስተዳለው:: እግዚአብሔር መንበረ መንግሥቱን /መንግሥተ ሰማይን/ አዘጋጀ:: በአይሁድ በአጋንንት ሊፈርድባቸው ለነፍሳት ለሐዋርያት ሊፈርድላቸው::

አድከመ ቀስተ ኃያላን:: የአይሁድን የአጋንንትን ሥልጣን አደከመ:: ወእቅነቶሙ ኃይለ ለድኩማን:: ለነፍሳት ለሐዋርያት መንፈሳዊ ኃይልን እንደ ዝናር አስታጠቃቸው::.

ፅጉባነ እክል ርኅቡ:: አሥራቱን በኩራቱን ቀዳምያቱን ተቀብለው ጠግበው ይኖሩ የነበሩ ሐና ቀያፋ ተራቡ:: እንድም እከለ ሥልጣንን ጠግበው ይኖሩ የነበሩ አጋንንት ከእክለ ሥልጣን ተራቡ::

ወርጉባን ፀግቡ:: ከትምህርት ተርበው ይኖሩ የነበሩ ሐዋርያት ልጅነቱን ትምህርቱን እንድም ከልጅነት ከክብር ተርበው ይኖሩ የነበሩ ነፍሳት ልጅነቱን ክብሩን አግኝተው ጠገቡ::

እስመ መካን ወለደት ፯ተ:: መካን ወንጌል ፍጹም ክርስቶስን አስገኝታለችና:: መካን እላት ሥርዓቷ በመልክጼዴቅ ጊዜ ታይቶ ኖራ ኖራ ተሠርታለችና::



ወወላድስ በእነት ወሊደ:: ወላድ ኦሪት ግን እንደ ክርስቶስ ያለ ልጅ ማስገኘት ተሳናት::

እንድም የወላድ መካን ሆነች:: የጥጦስ የአስባስያኖስ ጦር ፈጅቶባት::

፮. እግዚአብሔር ይቀትል ወየሐዩ:: እግዚአብሔር ይገድላል ያድናል::

ይቀትል: በሥጋ: የሐዩ: በነፍስ:: እንድም ይቀትል ጠላቶቹን: የሐዩ ወዳጆቹን:: እንድም እንድ አንዱን ሰው ገድሎ ያድናል:: እንደ ወልደ መበለት እንደ ወለተ ኢያኢሮስ ያሰውን::

ያወርድሂ ውስተሲኦል ወየዐርግ:: ወደ መቃብር ያወርዳል ከመቃብር ያወጣል እንደ አልዓዛር ያሰውን::

፯. እግዚአብሔር ያነዲ ወያብዕል:: ያደኸያል ያከብራል እንደ ኢዮብ::

የኀሥርሂ ወያከብር:: ያዜጋል /ያዋርዳል/ ያከብራል::

፰. ዘያነሥእ እምድር ሰነዳይ:: ደሀውን ከንዴቱ የሚያነሣው እሱ ነው:: ማናቸውንም ደሃ::እንድም ሳሙኤልን ሳዖልን ዳዊትን::

ወያሌዕሎ እመሬት ለምስኪን:: ምስኪኑን ከንዴት እንሥቶ ከፍ ከፍ የሚያደርገው እሱ ነው::

ከመ ያንብሮ ምስለ ዐበያተ ሕዝቡ:: በወገኖቹ ከተሾሙ ከአለቆች ጋር ያኖረው ዘንድ:

ወያወርሶ መንበረ ከብር:: መንበረ ክብርን ያወርሰዋል:: ለሳሙኤል መንበሩን ለሳኦል ለዳዊት ዙፋኑን::

እንድም ዘያነሥእ:: ነዳየ እእምሮ አዳምን ከንዴተ ነፍስ የሚያነሳው እሱ ነው::

ወያሌዕሎ እመሬት ለምስኪን:: ምስኪነ እእምሮ አዳምን ከንዴተ ነፍስ አንስቶ ከፍ ከፍ የሚያደርገው እሱ ነው::

ከመ ያንብሮ ምስለ ዐበይተ ሕዝቡ:: ከአለቆች ጋር ያኖረው ዘንድ::

ወያወርሶ መንበረ ክብር:: መንበረ ብርሃንን ያወርሰዋል::

ወይሁብ ጸሎቶ ለዘጸለየ::

ለጸለየ ጸሎቱን ይሰጠዋል አለ:: እንዲጸልይ ያደርገዋል:: አንድም የጸሎቱን ዋጋ ይሰጠዋል ሀበ:: ዘወትር ጸሎተን እንዲል::

፱. ወባረከ ዓመተ ጻድቃን:: የወዳጆቹን ዘመን አበዛ አከበረ አሰጀ:: እስመ ኢኮነ ፅኑዓ ኃይለ ሰብእ:: የሰው ኃይሉ ፅኑ አይደለምና አለ:: ሰው የገዛ ዘመኑን ማብዛት ማክበር ማበጀት አይቻለውምና:: አንድም የሰው ኃይሉ ፅኑ አይደለምና::

፲. እግዚአብሔር ያደክሞሙ ለፀሩ:: እግዚአብሔር ጠላቶቹን ያደክማቸዋል::

እግዚአብሔር ባሕቲቱ ቅዱስ:: ብቻውን ክቡር ምስጉን የሚሆን እግዚአብሔር ጠላቶቹን ያደክማቸዋል::

ኢይትመካህ ጠቢብ በጥበቡ:: ብልህ በብልሀቱ አይመካ ዓየረ ዓየራትን ሙጸአ ነፋሳትን ምሕዋረ ከዋክብትን አውቃለሁ ብሎ አይበል::

ኢይትመካሕ ኃያል በኃይሉ:: ኃይለኛ በኃይሉ አይመካ:: ብሮጥ እቀድማለሁ ባስር አጠብቃለሁ ብመታ አደቃለሁ ብሎ:: ኢይትመካሕ ባዕል በብዕሉ:: ባለጸጋ በብዕሉ አይመካ ወርቁ ብሩ በሣጥኔ እህሉ በጎተራዬ ላሙ በሬው በበረቴ አለ ምን አግኝቶኝ ብሎ:: ፫ አርእስት ተናግሯል:: ለሣ'ለቱም ያመጣል:: ዘሰ ይትሜካሕ በዝ ለይትመካሕ:: የሚመካ ሰውስ በዚህ ይመካ በዝ ያለውን ያምጣው::

፲፩.በአእምሮ ወበለብዎ እግዚአብሔር:: እግዚአብሔርን በማወቅ ይመካ ጠቢብ ላለው::

በገቢረ ፍትሕ ወርትዕ በማዕከለ ምድር:: የተበደለውን በማስካስ የተቀማውን በማስመለስ ይመካ: ኃያል ላለው:: ወጽድቅ:: በመመጽወት ይመካ: ባዕል ላለው:: ይህ ቅሉ ይመካበት ማለት አይደለም ደስ ይበለው ሲል ነው::

፲፪.እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጐደጐደ: እግዚአብሔር አንጐደጐደ ውስተ ሰማይ <u>ወዐርገ ይላል</u>:: እግዚአብሔር በሳሙኤል ጊዜ በሰማይ ድምፅ አሰማ ልዕልናውን ገለጠ:: ሳሙኤል በመሲፋ ጉባዔ ሠርቶ ሲያስተምር ኢሎፍላውያን በጠላትነት ተነሱባቸው:: ጸሊ ወኢታርምም በእንቲአነ አሉት::



መሐሰዐ እጓሊ ሠውቶ ቃለ እግዚአብሔር ጠየቀ መብረቅ ነጐድጓድ አሰምቶታል:: ወአኀዙ ይትቃተልዎሙ:: ወዲያው እስራኤል ድል አድርገዋል:: ጻድቅ ሳሙኤል ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ይገዛል::

ወይሁቦሙ ኃይለ ለነገሥትነ:: ለነገሥት ለሳኦል ለዳዊት ኃይልን ይሰጣቸዋል::

ወያሌዕል ቀርነ መሲሑ:: ይልቁንም የዳዊትን ሥልጣን ከፍ ከፍ ያደርጋል:: ይልቁንም አለ:: እንግሥ ለነ እንግሥ ለነ እያሉ ቢዘበዝቡት ዘመነ መሳፍንት ሳይፈጸም ዘመነ ነገሥት ሳይደርስ ንጉሠ መዐት ሳኦልን አንግሦባቸዋል:: ኢያጠፍእ ምስፍና ወምልክና እምአባሉ ለይሁዳ ተብሎ ትንቢት ከተነገረለት ሱባዔ ከተቆጠረለት ነውና::

አንድም እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጐድጐደ:: እግዚአብሔር በዳዊት ጊዜ በሰማይ ድምፅ አሰማ ልዕልናውን ገለጠ::

ታሪክ ዳዊት በነገሠ ጊዜ ኢሎፍላውያን በጠላትነት ተነሱበት ልሸሽ ልዋጋ? አለው እስከ ቀላውትሞን ሽሽ ከዚያ በኋላ መብረቅ ነጐድጓድ አሰማሃለሁ ዙረህ ግጠም ድል ታደርጋለህ ብሎታል::

ወውእቱ ጻድቅ ይኴንን እስከ አጽናፈ ምድር:: ዳዊት ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ይገዛል::

አንድም እግዚአብሔር ዐርገ ውስተ ሰማያት አንጐድጐደ::

በ፵ ቀን ሰማየ ሰማያት ዓረገ::

ወውእቱ ጻድቅ ይኴንን እስከ አጽናፈ ምድር:: ጻድቅ ክርስቶስ ጽንፍ እስክ ጽንፍ /ከአድማስ እስከ አድማስ/ ይገዛል:: እኛ ባወቅን እስከ አድማስ ከዚያ ወዲያ እሱ ባወቀ::

ወይሁቦሙ ኃይለ ለነገሥትነ:: ለሐዋርያት ኃይልን ልጅነትን ይሰጣቸዋል:: ነገሥት ይላቸዋል ሐዋርያትን:: ነገሥታት ዓይን በፍላት እጅ እግር በስለት እንዲሰሩ እንዲቆጡ ዐይነ ነፍስ እደ ነፍስ ይነሳሉ::

ነገሥታት ርስት ጉልት እንዲተክሉ ሰማያዊ ርስት ይተክላሉ::

ወያሌዕል ቀርነ መሢሒሁ፡ ቀርነ መሢሒናሁ ቢል የክቡርነቱን ሥልጣን ከፍ ከፍ ያደርጋል።
ቀርነ መሢሐ ቢል፡ የጴጥሮስን ሥልጣን ከፍ ከፍ ያደርጋል።



## ፩. ጸሎተ ሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ

ሕዝቅያስ ማለት አዚዝ ፅኑዕ ኃያል ማለት ነው። አንድም አንበሳ ማለት ነው። ኃያል ካለው ይገባል።

ወእመ ፲ቱ ወ፬ቱ ዓመተ መንግሥቱ ለሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ ዐርገ ሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ በአህጉረ ይሁዳ እለ ቦነ ቅዕር፡ ጥቅምም ይላል። ሕዝቅያስ በነገሠ በ፳፱ ዓመት ሰናክሬም ዘምቷል፡ ሕዝቅያስ በነገሠ በ፳ ዓመቱ ፲ሩ ነገድ ተማርከዋል። ፲ሩ ነገድ በተማረኩ በ፲ ዓመት ሰናክሬም ዘምቷል። ስለምን ዘመተ ቢሉ ባለጌ ገንዘቡን ለከፈለ አያዝንም ባልንጀራው ለቀረ ነው እንጂ እንዲሉ። የ፲ሩ ነገድ ንጉሥ ሆሴዕ ወልደ ኢላ አባትህ እኛን ማርኮ ንጉሠ ነገሥት ተባለ። አንተስ እነዚህን ማርከህ ንጉሠ ነገሥት አትባልም? አለው። አንድም እራሱ በአባቱ ተነተ፡ አንድም ጌታ በ፪ቱ ነገድ ቢያዝን እንዲዘምት አደረገው። ይኸውም ሲታወቅ ሚካኤል በነጭ በግ ተመስሎ እየመራ ለኪሶን አደረሰው። ለኪሶን ሲደርስ ተሠወረው።

ቦኑ ግልፎ ዘያድኅና ለኢየሩሳሌም በከመ ረሰይክዋ ለሰማርያ ከማሁ እሬስያ ለኢየሩሳሌም ወለከሉ ኅብረ ጣዖታ ብሎ እግዚአብሔርን ጣዖት ብሎ ሰደበ። መልአኩ ለይፋን መተ ቢታየው በ፩ ቀን ሌሊት ፻፹ አልፍ ከአምስት ሺ /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ/ ሠራዊት አልቆበት አድሯል። ይህ ቅስ አበጋዙ ነው። እርሱ /ሰናክሬም/ ግን ወዘይኄልቅዎ ሕፃናት ይላል። ሕፃናት የሚቆጥሩት ፭ም ፯ም ሆኖ አጋንንት የፈረስ የሠረገላ ድምፅ እያሰሙት ነነዌ ወርዶ ወእንዘ ይሰግድ ውስተ ቤተ ሲድራክ አምላኩ፡ ቀተልዎ አድራማሌክ ወሶርሶር ደቂቁ። ያን ሁሉ ሠራዊት አስጠፍቶ በማን ፊንታ ሊነግሥ መጥቶአል ብለው ተቀብለው ገድለውታል። በስምን ነነዌ ወርዶ እንዲሞት አደረገ ቢሉ በኢየሩሳሌም የመምለኬ ጣዖት ደም አይፍሰስበት /አይፈሰባትም/ ብሎ። ምነው ሠራዊቱስ መምላክያነ ጣዖት አይደሉም? ቢሉ በሱ ይፀናበታል /ይፀናል/ አጋንንት መከራ

ያፅኑበት ብሎ የፈረስ የሠረገላ ድምፅ እያሰሙት የጣያቱን ደካማነት ለማጠየቅ:: ነቢዩ ተናግሮበት ነበርና::
እሬስዮ ለሰብኮከ መቃብሪከ ብሎ::

ወውእቱ እሚረ ደወየ ሕዝቅያስ መበጽሐ እስከ ለሞት ይላል:: በዚያ ወራት ታመመ ለሞት ደረሰ አሁን ጠላት ጠፋለት አሁን ታመመ እስ እንደምን ነው ቢሉ:: ነቢያተ ሐሰት ተነሥተው ድንግል የተባለች ኢየሩሳሌም ናት የአሕዛብ የፈረሳቸው ኮቴ ያልረገጣት አለንጋቸው ያልጮኸባት: ወልድ የተባልህ አንተ ነህ አሉት:: አሆን ይሆናል አለ:: ከዚህ የተነሳ ታመመ ደህሰ ዳኛው ሳይለወጥ ሸንጎው ሳይመለጥ እንዲሉ ይህን የተናገረ ኢሳይያስ በዘመኑ እለ አይደለም ይሰዋል ብሎ ሕገ ሰብሳብን ቢንቅ ታመመ:: ከሕገ ሰብሳብ ሳልለይ እንዲህ ያለ ሥራ የተሠራልኝ ከሕገ ሰብሳብ ብለይ እንደት ያለ ሥራ ይሠራልኝ ብሎ ከስ ምናሴ ከምናሴ አመቤታችን ከእመቤታችን ጌታ የሚወለድ ነውና:: በዚህም አይታመምም የሕጋውያን ፴ ሲሆን የመነከሳት ፳ ነው ኩበራቸው ብሎ ቢመካ ታመመ:: እንደኔ ያለ ንጉሥ የሌሊት ግሥንግሣ የቀን ዘለሳ /አጥር/ ሳይመታው ጠላቱን የሚያጠፋ ወዴት ይገኛል ብሎ ቢመካ ታመመ::

ኢሳይያስን ከመዝ በሎ ለሕዝቅያስ ንጉሥመ ለሕዝብየ ሥራዕ ቤተከ እስመ አንተ ትመውት ወኢተሐዩ በለው አለው:: ሄዶ ነገረው:: መቦር ቢሳነው ከነእልጋው አዙሩኝ ብሎ ፊቱን ወደ ቤተ እግዚአብሔር መልሶ አለቀሰ::

ተዘከር እግዚኦ ዘከመ ሖርኩ ቅድሜከ በጽድቅ ወበርትዕ ወበፍጹም ልብ ገበርክዋ ለሠናይት አለ:: ጌታ የልብን መመለስ እንጂ ብዝኀ ጸሎት አይሻም /አያሻውምና/:: ወበጽሐ ኢሳይያስ ማዕከለ ዐፀድ ይላል:: ንጉሡና ሊቀ ካህናቱ በአንድ ወጥተው ከሯቱ ከ፮ቱ ቆመ ብእሲ ሲደርሱ የሚለያዩበት እለ:: ከዚያ ሲደርስ ተመየጥ አለው:: ከመዝ በሎ ለሕዝቅያስ ንጉሦመ ለሕዝብየ ሰማዕኩ ጸሎተከ ርኢኩ እንብዐከ ወተሐዩ እምደዌከ ወእስከ ሠሉስ ዕለት ተዐርግ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አለው ሄዶ ነገረው በምንት አእምር አለ::



ናሁ ይወርድ ጽላሎት ዲበ ፲ቱ መዓርጋት:: ፲ኛውን እርከን ጥላ አልብሶታል:: ለእመ ይገብእ ፀሐይ ድኀሬሁ ፲ተ ማዓርጋተ:: ተመልሶ ፀሐይ ቢሆን እወቅ አለው:: አባቱ አካዝ የሠራው ፩ ግንብ ነበር:: የቤተ መቅደስም ነው ይላሉ ኢይፈቅድ ዘንተ ትእምርተ:: ይህንስ እኔና አንተ ብቻ እውቀነው እንቀራለን ያሰኛል::

እመሰ ይትከሀል: የሚደረግልኝስ (የሚቻልስ) ከሆነ:

ለይባእ ፀሐይ ድኀሬሁ ዲበ ፲ቱ መዓርጋት:: ሠርክ ሁኗል ፲ሩን ኬክሮስ ተመልሶ ዘጠኝ ይሁንልኝ አለ::

ይኩን ከመ ትቤ አለው:: ተሰዓት ሆኗል:: እንድም ጽላሎት ያለው ፀሐይ ነው:: በግብሩ ሠርክ ሆኗል ተሰዓት ቢሆን እወቅ አለው::

ኢይፈቅድ ዘንተ ትእምርተ:: ይህስ ያንሰኛል::

እመሰ ይትከሀል: የሚደረግልኝ (የሚቻልስ) ከሆነ::

ለይግባእ ፀሐይ ድኀሬሁ ፲ተ መዓርጋተ:: ፲ሩን ወደ ኋላው ትቶ ፴ ኬክሮስ ተመልሶ ፲ ሰዓት ይሁንልኝ አለ::

ይኩን በከመ ትቤ አለው:: ፲ ሆኗል:: ያን ጊዜ መሮዳህ የሚባል የባቢሎን ንጉሥ ነበር:: ዛሬ እንዲህ የሆነበት ምን ቢሆን ነው ብሎ ጠየቀ /እንዲህ ያለ ሥራ የተሠራበት ምንድን ነው/ አለ:: እንዲህ ያለ ደግ የእስራኤል ንጉሥ ከደዌው የተፈወሰበት ቀን ነው አሉት:: ለዚህስ ሊገብሩለት ሊቀቅሉለት ይገባል ብሎ ወፈነወ መሮዳህ በልዳንሃ ወልደ በልዳዳን መጻሕፍተ ወተናብልተ ዘምስለ እምኃ ብዙኀ እንዲል ገብሮለታል:: እምጽኡ ፍሬ በሰሰ ቆጽለ በሰስ ደመ በሰስ እፀቀ በሰስ:: ሁሉም እፅቅ ባለው ይከታል /ይካታተል/ ይህን እምጥታችሁ ቅብዑ ሀበጦ ሰእግዚእከሙ ብሏቸዋል::

ወናሁ ወሰኩከ ፲ተ ወ፭ተ ክራማተ በዲበ ክራማቲከ አለው:: የሱስ ቢመካ ነው ተነስቶ የነበረ ቢሉ የሱን ጨርሶለታል:: የሱስ አልቆ ነበር ቢሉ የሰናክሬምን ደርቦለታል::

እመ ደወየ ሕዝቅያስ ወሐይወ እምደዌሁ:: ሕዝቅያስ በታመመ ጊዜ ከደዌውም በተፈወሰ ጊዜ የተናገረው ነገር ይህ ነው::

፩. አንሰ እቤ በኑኀ መዋዕልየ። ባለ በዘመኔ የማይገባ ነገር ተናገሬ ማለት ዕድሜዩ ይጠር ብዬ
ውስተ እናቅጸ ሲኦል ኀደጉ ዘተርፈ ዐመትየ። የቀረው ዘመኔን በመቃብር አጣሁት ብዬ ነበር፡
ወእቤ ኢይሬኢ ሰብአ እምእዝማድየ። ከዘመዶቼ ሰው አያለሁ አላልሁም ነበር፡
ወኀጕልኩ ዘተርፈ ሕይወትየ። የዘመኔን ቅሬታ በመቃብር አጣሁት ብዬ ነበር።

፪. ወጽአት ወኀለፈት እምኔየ። ነፍሴ ከሥጋዬ ተለይታ ሔደች ብዬ ነበር።
ከመ ዘየኀድር ወይተክል ደብተራሁ፡ ከመ ዘያተክል ደብተራሁ ይፈረር ወየኀድር ሲል ነው። ድንኳን ተክሎ ራቱን ተመግቦ አድሮ ያ ድንኳኑን ነቅሎ እንዲሄድ።
ከማሁ ኮነት ነፍስየ በሳዕሊየ። ነፍሴ ከሥጋዬ ተለይታ ሄደች ብዬ ነበር።
ወከመ ዕጡፈ ፀምር ዘእልጸቀ ይግምድም፡ ዕጡፍ ፀምር ሲል ነው። ሊቆርጡት የቀረበ ሸማ ዘለስ /ዘነፍ/ ብሎ ወደጉድጓድ እንዲወድቅ ሥጋዬ በመቃብር ወደቀች ብዬ ነበር። እንድም ቁጢቱ /ዘሀው/ ከሳይ እንዲቀር ነፍሴ ከሥጋዬ ተለይታ ሄደች ብዬ ነበር።

፫. ወውእተ እሚሬ ተሀወኩ ከመ አንበሳ እስከ ይጸብሕ። አንበሳ እስኪጠባ /እስኪነጋ/ ድረስ ምግብ በመሻት እንዲታወክ በዚያ ወራት ታወክሁ እንዘሳ ርሁብ ወተኩላ ጽሙዕ ይለዋል።
ከማሁ ተቀጥቀጣኒ አሰፅምትየ። ሰውነቴ በመከራው ቆሰለች /ኀሰቆለች/።
እኀዘኒ እምነግህ እስከ ሠርክ። ከጧት እስከ ማታ ያዘኝ ቀን ቀን ይጸናበት ነበር። እንድም ከፎቱ ቀን አንዱ ቀን ጸንቶበት ነበር።

፬. ወከመ እድገ መረብ ከማሁ እነቁ። እንደ ምድረ በዳ አህያ እጮሃለሁ ይህ የበዳ /የምድረበዳ/ አህያ ሲርበው ከተራራ ወጥቶ ይጮሃል። ነፋስ መዓዛ ሳዕር መዓዛ ማይ ያሸተዋል። ሄዶ በልቶ ጠጥቶ ሰፍራውን አይለቅም።



ወከመ ርግብ እነብብ። እንደ ርግብ እናገራለሁ ይህች ርግብ የምትናገረው በጉሮሮዋ ነው አሉም ውጋቱ አሳናግረው አያለ።

፭. ደከማ አዕይንትየ ወስዕንኩ ነጽሮ ኀበ እግዚአብሔር ለማየ። ዓይኖቼ ፈዘዙ ወደ ሰማይ ወይም ወደ እግዚአብሔር አትኩሮ ማየት ተሳነኝ።

፮. ተሣሃለኒ ወአእትት ሕማማ ለነፍስየ። ይቅር በለኝ ለሰውነቱ ደዌዋን አርቅላት።

፯. እግዚኦ በእንቲአሃ እቤለከ። ስለእሷ እንዲህ እልሃለሁ።
ወአንሣእካ ለነፍስየ። ሰውነቴን ከደዌዋ ፈወስካት እልሃለሁ።

፰. ተፈሣሕኩ ወሐዮኩ። ሐዮኩ ወተፈሣሕኩ ይላል። ከደዌዬ ተፈወስኩ ወተፈሣሕኩ በዚያው ደስ አለኝ። እንድም ወተፈሣሕኩ በሞቱ ለናክሬም ደስ አለኝ ወሐዮኩ። ከደዌዬ ተፈወስኩ። ወተሣሀልካ ለነፍስየ ከመኢትትኀጐል። ነፍሴ በመቃብር ፈርሳ በስብሳ እንዳትቀር ሰውነቴን ይቅር አልካት።
ወገደፍከ ድኅሬየ ኵሎ ኀጢአትየ። ኀጢአቴን ሁሉ በኋላዬ ጣልክ በኋላ የጣሉት እንዳይታይ እንዳይታሰብ አላሰብክብኝም።

፱. እስመ አኮ እለ ውስተ ሲኦል ዘይሴብሑከ። በመቃብር ያሉ የሚያመሰግኑህ አይደለምና።
ወአኮ እለ ይመውቱ ዘይባርኩከ። የሞቱት ሰዎች የሚያመሰግኑህ አይደለምና።

፲. ወኢይሴፈዉ ሣህለከ እለ ውስተ ሲኦል። በመቃብር ያሉ ሰዎች ይቅርታህን ተስፋ አያደርጉምና። ዘናም ለዘር ጠል ለመከር ይስጠናል ብለው።
ሕያዋን ከመ ይባርኩከ ከመ አነ ይእዜ። እኔ እንዳመሰግንህ ሕያዋን ያመሰግኑሃል እንጂ።
ዛቲ ተግሣጽ ትኩነኒ እምዮም እግዚኦ። ይቺ ተግሣጽ እቤቱ ትሥራኝ ትቅጣኝ ትዝ ትዝ ትበለኝ አልደግምም። እንድም ሕዝቅያስ ቢጨንቅህ ትቀባጥራለህ እንጂ የቀደመ ግብርህን መች ትተዋለህ ትለኝ እንደሆነ እቤቱ ይቺ ተግሣጽ ትሥራኝ ትቅጣኝ ትዝ ትዝ ትበለኝ አልደግምም።

እነግር ጽድቀከ በዳግናየ:: ባለ በዘመኔ ሁሉ ቸርነትህን እናገራለሁ::
እገብር ደቂቀ ይላል አብነት::
፲፩.ወትረ እሴብሐከ ወእዜምር ለከ:: ዘወትር አንተን አመሰግንሃለሁ ለአንተ ምስጋና አቀርባለሁ::
በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ:: ባለ በዘመኔ ሁሉ::
በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር:: በቤተ እግዚአብሔር ሆኜ::

## ፮. ጸሎተ ምናሴ ነቢይ

ምናሴ ማለት መርስኤ ኀዘን ማለት ነው፡ የሕዝቅያስ ልጅ ነው:: አባቱ የሠራውን አፍርሷል:: አባት ቀፎ ቢያበጅ ልጅ ጦገዛ መንጎዛ /የቀፎ ማር የሚበላ አውሬ/:: ይዋጅ እንዲሉ ሥዕለ ንስር አቁሟል መንቅሖ /መንሥኤ/ ምውት ካህን አሥነሥቷል:: ልጁን ለጣዖት ሠውቷል:: ኢሳይያስ ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ብሎ ቢናገር በኵላብ አስቀሎ በመጋዝ አስተርትሮ ገድሎታል /አስገድሎታል/ ከዕለታት አንድ ቀን ለአደን ከወጣ ዘንድ አስበቀፊት፡ ሆኒሐርድን፡ አስራዶን፡ ንዑስ ሰናክሬም ይለዋል:: አስልሎ ይዞ ወስዶ ቡበረት ቀፎ አግብቶ ቀን ዋዕየ ፀሐይ ከሚጸናበት ይጥለዋል ሌሊት ውርጭ /ብርድ/ ከሚጸናበት ይጥለዋል፡ ከዚያው ሆኖ ንስሓ ገባ:: መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ከነቀፎው ተሸክሞ ወስዶ በአንቀጸ ኢየሩሳሌም ጣለው ለነቢያት ለካህናት ንጉሣችሁ ከዚያ አለላችሁ ሄዳችሁ ልብሱን አልብሳችሁ አምጡት አላቸው:: ሄደው ልብሱን አልብሰው አመጡት:: ዘመነ መንግሥቱ ፶፭ ዘመን ነው:: ፶ውን ጣዖት እያመለከ ፭ቱን ዘመን ያንን የብረት ቀፎ ከፊቱ አድርጎ እያለቀሰ ገዝቷል:: በሚሞትበት ጊዜ ዳዊት ሰሎሞን በተቀበሩበት አትቅበሩኝ በገነተ ዖዛ ቅበሩኝ ብሏቸዋል:: እንተ ይእቲ ምቅዋመ አእዱግ ይላታል::
ነቢይ ንጉሥ ይላል:: ምናሴ የተናገረው ነገር ይህ ነው::
፩. እግዚኦ አኃዜ ኵሉ ዓለም::
ይህን ዓለም የምትገዛ አቤቱ፡ እንድም ይህን ዓለም እንደ ጽና እንደ ጥላ እንጠልጥለህ እንደ እንቁላል ጨብጠህ የያዝከ አቤቱ
አምላኮሙ ለአበዊነ:: የአባቶቻችን ፈጣሪ:



ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ:: የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ፈጣሪ አቤቱ:
፪. ወለኵሉ ፍሬሆሙ ለጻድቃን::
የልጆቻቸው ፈጣሪ አቤቱ:
፫. ዘገበርከ ሰማየ ወምድረ ምስለ ኵሉ ዓለሞሙ:: ሰማይና ምድርን ከዓለሞቻቸው /ከዓለማቸው/ ጋራ የፈጠርከ አቤቱ ሰማይ ከነግሡ ምድር ከነልብሱ እንዲሉ ሰማይን ከፀሐይ ከጨረቃ ከከዋክብት ምድርን ከአዝርዕት ከአትክልት ጋራ::
፬. ዘገሠጽካ ለባሕር በቃለ ትእዛዝከ:: ውቅያኖስን በቃልህ የገሠጽከው:
እስከ ዝየ ብጽሒ ወኢትትዐደዊ እምወሰንኪ ዳዕሙ ይትከወስ ማዕበልኪ ብለህ:
ዘአጸከ ቀላያተ ወኀተምኮ ግሩመ:: ቀላያተ ውቅያኖስን በብሔሞት የዚጋህ ግሩም ብሔሞትን በዚያ የወሰንከ አቤቱ::
፭. ውእቱኒ በስቡሕ ስምከ:: ይኸውም ክቡር በሆነ በስምህ ነው እንዲህ ያደረግከ አቤቱ::
እንድም ዘገሠጽካ:: ባሕረ ኤርትራን ከሦስት ከአራት ከፍለህ በቃልህ የገሠጽከው አቤቱ
ዘዐጸከ ቀላያተ:: ኤርትራን በፈርዖን የዚጋህ ግሩም ፈርዖንን በዚያ የወሰንከ አቤቱ
ውእቱኒ በስቡሕ ስምከ:: ይኸውም ክቡር በሆነ በስምህ ነው:: እንዲህ ያደረግህ አቤቱ
እንድም ዘገሠጽካ:: ባሕረ ገሃነምን በቃልህ የገሠጽከው አቤቱ
እንድም ዘአጸከ:: ቀላያተ ገሃነምን በዲያብሎስ የዚጋህ ግሩም ዲያብሎስን በገሃነም የወሰንከ አቤቱ ውእቱኒ እያሰውሃም::
፮. ዘኵሉ ይርዕድ ወያድለቀልቅ እም ቅድመ ገጸ ኃይልከ:: ከገጸ መሀትህ የተነሳ ሁሉ የሚርድ የሚንቀጠቀጥ አቤቱ::
፯. እስመ አልቦ ጽንፍ ለዕበየ ስብሐቲከ:: ለጌትነትህ ጽንፍ፡ ዳርቻ የለውም::
፰. ግሩም መቅሠፍተ መዐትከ ላዕለ ኀጥአን:: ፈርደህ የምታመጣው መቅሠፍት ግሩም ነው::

አልቦ ኍልቍ ወአልቦ መስፈርት ለሣህለ ትእዛዝከ። እዝዘህ ለምታደርገው ይቅርታህ ሥፍር ቍጥር የለውም።
እስመ አንተ እግዚአብሔር ባሕቲትከ ልዑል። ገናና ጌታ አንተ ብቻ ነህና መሐሪ ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ሣህል። መዓትህ የራቀ ቸርነትህ የቀረበ እንደም መዓትህ ያነሠ ቸርነትህ የበዛ ቸር ነህ።

፱. ወመስተመይጥ ላዕለ ኄጋዮሙ ለዕጓለ እመሕያው። የሰውን ኃጢአት አይተህ እንዳላየህ ከመዓት ወደ ምሕረት የምትመለስ አንተ ነህ።

፲. ይእዜኒ እግዚኦ አምላኮሙ ለጻድቃን። ይእዜኒን ያስጠብቃል። የጻድቃን ፈጣሪ አቤቱ
እስመ አኮ ለጻድቅ ዘገበርከ ለንስሓ። ንስሓን የሠራኸው ለጻድቅ አይደለምና። አኮ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እለኢአበሱ ለከ፡ ኢያከ ሲል ነው። አንተን ላልበደሉ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ አይደለምና

፲፩. እላ ተመየጥ ንስሓ ዚአየ ለኃጥእ። ለኃጥእ ነው እንጂ ለጻድቅ አይደለምና ይእዜኒ ተመየጥ። ዛሬም ንስሐዬን አይተህ ከመዓት ወደ ምሕረት ተመለስ።

፲፪. እስመ አበስኩ እምኍልቈ ኆጻ ባሕር። ከባሕር አሸዋ ይልቅ በድያለሁና ወብዙኀ ኃጢአትየ። ኃጢአቴም ብዙ ነውና።
አኮ ድልወት ሊተ እንቃዕዶ ወእርአይ ኑኆ ለሰማይ። ወደ ሰማይ አቅንቼ የሰማይን ምጥቀቱን ላይ አይገባኝም። ከተበደለ የበደለ ያፍራልና።
እምብዝኀ ጌጋይየ። ከኃጢአቴ ብዛት የተነሣ
ሠራሕኩ በመዋቅሕተ ሐፂን። በግር ብረት ደከምኩ።
ከመ እስሐታ ለነፍስየ እምኀጢአትየ። ለውነቴን ኃጢአት ከመሥራት አሳርፋት ዘንድ።
ወበዝየኒ ኢተስሕትኩ። በዚህም ሆኜ ኃጢአት ከመሥራት አላረፍኩም ወየው ከዚህ ወጥቼ ጠላቴን እንዳደረገኝ አድርጌው እያልኩ።
እስመ ወሀኩ መዓተከ። መዓትህን አነሳስቼአለሁ።
ወእኩየኒ በቅድሜከ ገበርኩ። በፊትህ ክፉ ሥራ ሠራሁ።



፲፫. እንዘ አዐቅብ ከንቶ ወእስዝኀ ዘኢይበቍዐኒ። ከንቱ ጣዖትን ስጠብቅ የማይረባኝ የማይጠቅመኝን ነገር አበዛሁ።

፲፬. ወይእዜኒ እሰግድ በብረከ ልብየ። ዛሬም ታሥራአለሁና በአብራክ ሥጋ መስገድ ቢሣነኝ በአብራከ ልብ እሰግዳለሁ።
እንዘ እስእል ምሕረተ ዚአከ። ቸርነትህን እየለመንኩ።

፲፭. አበስኩ እግዚኦ አበስኩ። አቤቱ በደልሁ በደልኩ።
ወኀጢአትየኒ አትአመን። አምናለሁ ሠርቼ አልሠራሁም አልልም።

፲፮. እትመሐለል ወእስእለከ እለምንሃለሁ
ተሠሃለኒ እግዚኦ ተሠሃለኒ። አቤቱ ይቅር በለኝ ይቅር በለኝ።
ወኢትመጥወኒ ለኀጢአትየ። በኃጢአቴ ለመጣ መከራ /ፍዳ/ አትስጠኝ እንደ ሰጠኸኝ አትቅር።

፲፯. ወለዓለምስ ኢትዕቀብ ሊተ እከይየ። ኃጢአቴን አንድ ጊዜ ብትጠብቅ ለዘላለሙ አትጠባበቅብኝ /አትጠብቅብኝ/።
ወኢትትበቀለኒ በማዕምቅቲሃ ለምድር። በምድር በሆልቋ አትበቀለኝ በፋርስ በመቃብር በሲኦል።
አንተ እግዚኦ አምላኮሙ ለእለ ይኔስሑ። ንስሓ ለገቡ ሰዎች ፈጣሪያቸው የምትሆን አቤቱ፡
ያስተርኢ ኂሩትከ በላዕሌየ። ቸርነትህ በኔ ለሌላው ይገለጥ።
ሊተ ለኔ ይገለጥ።
ከመ እንዘ አኮ ድልውት ሊተ አድኀንከኒ በብዝኀ ሣህልከ።
መዳን የማይገባኝ ስሆን በይቅርታህ ብዛት እንዳዳንከኝ
ያስተርኢ። እንድም እንዳዳንከኝ መጠን

፲፰. እሴብሐከ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ። በሚመጣው ዘመን ሁሉ አመሰግንሃለሁ።
አንድም በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ። ባለ ዘመኔ ሁሉ በ፯ቱ በ፲፪ቱ በ፳፬ቱ ጊዜያት አመሰግንሃለሁ።
እስመ ኪያከ ይሴብሑ ኵሉ ኃይለ ሰማያት። ሊቃነ መላእክት አንተን ያመሰግናሉ /ያመሰግናሉና/።
ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም። ለዘላለሙ ለአንተ ምስጋና ይገባል።

# ፳. ጸሎተ ዮናስ ነቢይ

ዮናስ ማለት ርግብ ማለት ነው። ወሀሎ አሐዱ ወልደ ብእሲት በስራጵታ ያላል። በሕፃንነቱ ሞቶ ኤልያስ አስነሥቶ የኤልያስ ደቀ መዝሙር ሆኖ አደገ ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶት ነበረ ወርደህ እስከ ሠሉስ ዕለት ትትገፈታዕ ነነዌ ሀገር በነድ ብለህ አስተምር አለው። አንተ መሐሪ ነህ ብትምራቸው ነቢየ ሐሰት እባል የለም? አለው መሐሪ ብሆን ምን ይከፋል ግድ የለም ግድ የለህም/ አለው ይህ ሁሉ እንጂ ከፋት ቢያገኘኝ ነው የሚዘገዘገኝ ብሎ ወተንሥአ ዮናስ እምገጸ እግዚአ ያላል። ጌታ ከማያገኘው ቦታ ከብልሎ ሄደ። ርግብ ያሰኘው ይህ ነው።

ወተሐስበ ሐመርሙ ያላል። መርከብ ጭኖች /ለመርከባቸው ዋጋ ሰጥቶ/ ተሣፈ ማዕበል ሞገድ ተነሣባቸው በክብደው እንጂ ነው ብለው ጓዛቸውን እያነሱ ይጥሉ ጀመር። ፀጥ የማይልላቸው ሆነ። ከኛ የበደለ ሰው አለን? ዕጣ እንጣጣል ብለው ዕጣ ቢጣጣሉ በዮናስ ወጣበት።

ወንኀረ ዮናስ ውስተ ከርሠ ሐመር ያላል። ተኝቶ ሲያንኮራፋ ነበር። ሊቀ ሞትያው /የመርከቡ ካፒቴኑ/ ቀሰቅሶ ሁሉ ወደ ፈጣሪው ሲያለቅስ ሲጨነቅ/ አንተ የማታለቅስ የማታዝን ፈጣሪህ ማነው? ነገድህስ ከማነው? አለው። ነገዴም ዕብራዊ ነኝ ፈጣሪዬም ሰማዩን ምድሩን የብሱን ባሕሩን የፈጠረ ፈጣሪ ነው። ይህ መከራ የመጣባችሁ በኔ ነው እኔን ካልጣላችሁ ጸጥ አይልላችሁም አላቸው መጣሉን ተስቅቀው ወደ ኋላ ተመለሱ ፀጥ የማይልላቸው ሆነ።

ኢትረሲ ደሞ ለዝ ብእሲ ደመ ጻድቅ ብለው ጣሉት። ዓሣ ዐንበሪ ቀለመው/ ተቀብሎ ዋጠው/ ባሕርም ድርጎዋን ተቀብላ ጸጥ አለች። ሶስት ቀን ወስዶ በአንቀጸ ነነዌ ተፋው እንደ ጸዳ ካለች ቦታ ደርሶ ይህች ሀገር ማን ትባላለች ብሎ ጠየቀ ነነዌ ትባላለች አሉት። በፈቃደ እግዚአብሔር መጥቻለሁ ብሎ ከዚያ ገብቶ እስከ ሠሉስ ዕለት ትትገፈታዕ ነነዌ በነድ ብሎ አስተማረ። ሰልምናሶር ነበር ንጉሡ አዋጅ ነገረ ጥጃ ከእናቱ ልጅ ከጡቱ ሳይገናኙ አዘኑ። እሱም ኃዘናቸውን አይቶ አዘነ እሳቱ ይቀራል ብሎ።



እሱም ኀዘንከኑ ዮናስ፡ እሳት ባለማዝነሜ አዘንክ? አለው እምን አለ። ይህን ብሎት ተሰወረ። የሽማግሌ ልጅ መታየቱ መቀሳወጡ እንዲሉ እንዲህ ማለቱ ሊያዘንም ነው ብሎ፡ እንደ ካይላ ሜዳ ካለ ወጥቶ ጎጆ ሠርቶ ተኛ። ቢነቃ /ቢነሳ/ ቅል በቅላ ጎጆውን አልብሳለት ሰውነቱን ደስ ብሎት አገኘ። መልካም ብሎ ሁለተኛ ብንን ቢል ያችን ቅል ትል/ ቆማምጦ/ ቆራርጦ/ በልቷት። ሀሰይ ራሱን መትቶት አዳኒት የምትባል ራስ ፍልጠት ቀጭን ሰጥር ውጋት ተነስቶበት አገኘ እንዲያውም ነቢየ ሐሰት እየተባሉ ከመኖር መሞት ይሻላል አለ።

ኀዘንከኑ ዮናስ በእንተ ዛቲ ሐፃሐፃ ዘኢተከልካ ወዘኢሰቀይካ ዘሌሊተ በቈለት ወሌሊተ ማስነት። ሌሊት ያለው መዓልቱን ነው። የሌሊት ሥራ ስለተሠራበት። እንድያም ሰኞ ለማክሰኞ በቅላ እድራ ማክሰኞ ለረቡዕ ደርቃለች እያን አለው። እንስኑ ኢያምሕካ ለነነዌ ሀገር ዐባይ ዘሀሰዉ ውስቴቱ አለ፡ ይበዝኑ እም ፲ቱ ወ፪ቱ፼ እለ ኢፈለጡ የማናሞ ወጸጋሞሙ። ከመቶ ሃያ ሺሕ የሚበዙ ከመቶ ሃያ ሦስት ሺህ የሚያንሱ ቀኝ ግራቸውን የማይለዩ ሕፃናት ላሉባት ለነነዌ ማዘን አይገባኝምን አለው።

እንድያም ቀኝ ግራ ብለው የሚወረወሩ አርበኞች ላሉባት ለነነዌ ማዘን አይገባኝም? አለው። እውነት ነው ጌታዬ ይገባል አለው። ይህችም ነነዌ ወምዕዋደ ቅጽራ እምአንቀጽ እስከ አንቀጽ ምሕዋረ ፫ቱ ዕለታት ይላታል፡ የሶስት ቀን ጎዳና ናት። ነቢየ ሐሰትም እንዳይባል ረቡዕ በሠርክ እንደ ደመና እንደ ደመና ሆኖ ታይቶ ተመልሷል ይህም ምሳሌ ነው። ዮናስ የወልደ እግዚአብሔር፡ ከርሠ ዓንበሪ የመቃብር፡ ከዚያ ሶስት መዓልት ሶስት ሌሊት አድሯል። ጌታም በከርሠ መቃብር ሶስት መዓልት ሶስት ሌሊት አድሮ ተነሥቷል። ይህንንም እስከ ሠሉስ ዕለት ያለውን ጦቢት በሶስተኛው ትውልድ ትጠፋለች ማለት ነው ብሎ ተርጕሞታል። በእስራኤል የቆጠሩ እንደሆነ በኢኮንያን ተማርከው በሰላትያል ተሰፋ ሰምተው በዘሩባቤል ወጥተዋል። በአሕዛብ የቆጠሩ እንደሆነ በናቡከደነፆር ተማርከው በኢዮርማሮዴቅ ተሰፋ

ሰምተው በብልጣሶር ወጥተዋል። ነቢዩ ዮናስ የተናገረው ነገር ይህ ነው።

፩. <u>ጸራሕኩ በምንዳቤየ ኀበ</u> እግዚአብሔር አምላኪየ። በመከራዬ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኼ ለመንሁ
፪. ወሰምዐኒ በውስተ ከርሠ ሲኦል። በባሕር ውስጥ ሆኜ የለመንኩት ልመናዬን ሰማኝ። አንድም በባሕር ውስጥ ባለ በከርሠ ዓንበሪ ሆኜ የለመንኩት ልመናዬን ሰማኝ።
ወሰምዐኒ ቃልየ። ልመናዬን ሰማኝ።
ወገደፈኒ ውስተ ማዕምቀ ልበ ባሕር። ማዕምቅ ልዑ የተደራረበ ነው። በጥልቁ ጣለኝ
ወአፍላግኒ ዐገቱኒ።
ፈሳሾች ከበቡኝ ነቢይ ነውና በላይ የሚሄደውን ያያል።

ከዚያው ውስጥ የሚገባውን።
ኵሉ ማዕበልከ ወሞገድከ እንተ ላዕሌየ ኀለፈ። ማዕበል ሞገዱ ተመላለሰብኝ።

፫. ወእቤ ተገኀልኩኑ እንጋ እምቅድመአዕይንቲከ። ከባለሟልነትህ እንደተለየሁ ቀረሁ ይሆን አልኩ።
ሀሉኩኑ እርአይ ጽርሐ መቅደስከ።
ከዚህ ወጥቼ ቤተ መቅደስን አይ ዘንድ አለኝ? ይሆን አልኩ።
፬. አሕዘዘኒ ማይ፡ እስከ ነፍስየ። ሰውነቴን እስከ ማጥፋት ደርሶ ውሃው አነዘዘኝ ሲጥሉት እንዝዞታልና
ወቀላይኒ መልዐኒ። ውሃው መላብኝ።
ናሁ ርእስየ ውስተጥንቃቃተደብር። ራሴ በምሽጉ/በባሕር አዝዋሪ /አለ። እንደ ንዋየ ውስጥ ነው። ንቅዓታተ ደብር ቢል በክፍልፍሉ አለ። ነቢይ ነውና በተራራና በተራራ መካከል ሲወስደው ያያል።
ወወረድኩ ውስተምድር ከመመልሕቅ ታሕተ። መልሕቅ ሲጥሉት ወደ ታች እንዲወርድ እንደዚያ ወረድኩ።



፭. ትዕርግ ሕይወትየ ዘእንበለ ሙስና ኀቤከ እግዚእ አምላኪየ። ሰውነቴ ጥፋት /ጉዳት/ ሳያገኛት ወደአንተ ትምጣ።

፮. ሶበ ኀልቀት ነፍስየ ተዘከርክዎ ለእግዚአብሔር። ነፍሴ ከሥጋዬ እለይ እለይ /ልለይ ልለይ/ ባለች ጊዜ እግዚአብሔርን በጸሎት አሰብኩት።
ትብጻሕ ጸሎትየ ቅድሜከ ጽርሐ መቅደስከ።
በፊትህ ሆኜ የጸለይኋት ጸሎት ወዳንተ ትድረስ?
፯. እለሰ ዐቀቡ ከንቶ ወሐሰተ ገዳፉ ሣህሎሙ። ከንቱ ጣዖትን የተጠባበቁ ሰዎች ይቅርታቸውን አጡ። አንድም ይቅርታቸው እግዚአብሔርን አጡ። አንድም ገንዘባቸውን አጡ። ሐሰትም ያለው ጣዖቱን ነው። አንድም ሐሰተ ይላል። በሐሰት ይቅርታቸውን አጡ።

፰. አንሰ ምስለ ቃለ ስብሐት በተጋንዮ እሠውዕ ለከ። በመገዛት ከምስጋና ጋራ ላንተ መሥዋዕትን አቀርባለሁ።
መጠነ ጸለይኩ በሕይወትየ እዐስዮ ለእግዚአብሔር። በሕይወቴ የጸለይኩትን ያህል በከርሠ ዓንበሪ ሆኜ አቀርባለሁ። አንድም በከርሠ ዓንበሪ ሆኜ የጸለይኩትን ያህል ከከርሠ ዓንበሪ በወጣሁ ጊዜ እቀርባለሁ። አንድም መጠነ በፃዕኩ። የተሳልሁትን ያህል እሰጣለሁ። ከዚህ ብታወጣኝ ይህን እደርጋለሁ ብዬ።

## ፷. ጸሎተ ዳንኤል ነቢይ ስብሐት ዘእምአዛርያ

ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነው:: የዳንኤል እናትና ፫ቱ ደቂቅ ካንድ ሆድ ይወጣሉ::: ጻድቃንን ከኀጥአን ጋራ ያስማርካቸዋል:: ስለ ምን ቢሉ መከራ ቢበዛ ጸጋ ክብር ይበዛላቸዋል ብሎ:: ተሹመው ተሽልመው እስራኤልን ሊጠብቋቸው መከረው አስተምረው ከገቢረኀጢአት ከአምልኮተ ጣዖት ሊያድኗቸው:: ከምርኮ በኋላ ናቡከደነፆር ኀረዩ ሲተ እምደቂቀ፪ዋ አለ:: ቢቆም የማይታከተውን ጥበብ የሚለማማውን እያያችሁ ምረጡ:: መርጣችሁ ፈላስፋ ሕሙግ መብልዕ የሐምግ ልበ ይላልና:: ጽሩይ ጽሩይ ምግብ እየመገባችሁ መሐርዎሙ መጽሐፈ: ወነገረ ፋርስ:: መጽሐፈ: ወግ ታሪክን:: ወነገረ ፋርስ: ቋንቋን:: አንድም መጽሐፈ: ፍልስፍናን:: ወነገረ ፋርስ: ጥንቆላን:: አስተምሯቸው አለ:: አስፋኒዝ ይለዋል:: ቢትወዳዱ እነዚህን መርጦ አምጥቶ ከፊቱ አቆማቸው:: ወወለጠ ስሞሙ ያላል:: ስማቸውን ለውጦታል ሲለውጥም በእንጻር በእንጻር ይለውጣል:: ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነበር:: ብልጣሶር ብሎታል /አለው/ አምላክ ቤል ሲል:: አናንያ ማለት በግዕ ደመና ማለት ነበር:: ሲድራቅ ብሎታል /አለው/ ጸሐፊ ጸሐቂ ፍንው ትጉሕ ለግብረ ንጉሥ ሲል ነው:: አዛርያ ማለት ረዳኢ ረድኤተ እግዚአብሔር ማለት ነበር:: ሚሳቅ ብሎታል /አለው/ ሠቃዪ አትክልት አሠናዪ አትክልት ሲል:: ሚሳኤል ማለት ሰምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነበር::

አብደናጎ ብሎታል: ገብረ ዳጎን ሲል:: አሚሳድ ይለዋል መምህሩ ለሱ ስጣቸው ሀበነ ዘርዓ ምድር አሉት ስለምን ቢሉ ተጸይፈው ዛሬ እኛ የእስላምን እንጀራውን እንድንጸየፈው ጥሬውን እንዳንጸየፈው:: ደግሞም በተድላ በደስታ ከተማሩት በመከራ የተማሩት ትምርት ይበልጣልና:: ይህስ ዘርዐ ምድር ያለው ምንድን ነው ቢሉ ሽምብራ ይህስ ተድላ ደስታ ይሆናል:: ባቄላ ነው::



ለእመ ርእየክሙ ንጉሥ ድግዱጋኒክሙ እምእለ ይሴሰዩ እማእደ ንጉሥ ኢይኳንነኒኑ ርእስየ አለ:: ከንጉሥ ማዕድ ከሚመገቡ ይልቅ እናንተ ጠቁራችሁ ከስታችሁ ቢያያችሁ ከታች ባቴን ከላይ አንገቴን አይሠራኝም አይቀጣኝም? አላቸው:: ፍትነነ አሡረ መዋዕለ ለአግብርቲከ:: አሥር ቀን ፈትነኸን የከሳን የጠቆርን እንደሆን እንዳልከን እንሆናለን አሉት:: አሰር ቀን ሙሉ ባቄላ ሲሰጣቸው ሰነበተ::

ኀየሰት ነፍሶሙ ወሠነየት ራእዮሙ እምእለ ይሴሰዩ እማዕደ ንጉሥ ይላል:: እንደ ብርሌ ጠርተው እንደብርጭቆ አንጸባርቀው አገኛቸው:: እኔ ትከሳላችሁ ትጠቁራላችሁ ብዬ ነው እንጂ ብሎ ለነሱ የመጣውን እሱ እየተመገበ ሶስት ዓመት ሙሉ ባቄላ ሲሰጣቸው ኖረ::

በሶስተኛው ዓመት ንጉሥ እስኪ አምጣቸው ጥበብ እመረምራቸዋለሁና አለው:: ቢመረምር ወሶበኀሠሠ ንጉሥ በኀቤሆሙ ረከበ ትዕሥርተ እድ እምኵሎሙ ጠቢባነ ባቢሎን ይላል:: አስር እጽፍ ጥበብ አገኘባቸው መልካም ነው ተቀመጡ አላቸው:: ይህ በሆነ በሁለት ዓመት ንጉሡ ከሰገነት ላይ ተቀምጦ ሁሉ ሲፈታ ሲታጠቅ አይቶ እኔ ሁሉን እንደ ሰም አቅልጬ እንደገል ቀጥቅጬ ገዛሁት ከኔ በኋላ የሚነሳው ከኔ የበለጠ ይሆን ከኔ ያነሰ? ብሎ አሰበ:: ቀን ያሰበውን ሌሊት ያሳየዋል ቀን የለቀሙ ሌሊት ይቅሙ እንዲሉ:: ርእሱ ዘወርቅ እንግድዓሁ ዘብሩር ሐቌሁ ዘብርት ቍየጺሁ ዘሐጺን መንፈቀ እግሩ ዘልሕኵት ወዘሐፂን:: ሽቅብ ነው ያሉ እንደሆነ እንደ አፍራኔቆ /አፍራኒቆን/ ድንኳን/ ክብ ድንኳን/:: ግድም ነው ያሉ እንደሆነ እንደነፍጥ መሸቢያ /እንደ ጥይት ካርታ/ እንደ አልጋ ሸንኮር: እሱ ጣዖቱን ጣዖቱ እሱን ሲመለከት ከረጅም ተራራ የሰው እጅ ሳይነካው ደንጊያ ተፈንቅሎ ወርዶ ያን ቀጥቅጦ ደንጊያው ተራራ ሲያህል ተራራው በዓለም ሲመላ አይቷል:: ብንን ቢል ጠፋው ስለምን ቢሉ የንጋት እንቅልፍ ነበረበትና:: አንድም ራእዩ ግሩም ነውና:: የዳንኤልን ክብር ለመግለጽ ሲነጋ ከበላው አብልቶ ከጠጣው አጠጥቶ የሚያኖራቸው ብዙ ማእምራን ጠቢባን

ነበሩት:: እነዚያን አስጠርቶ ሕልም አይቼ ጠፍቶኝ ሕልሜን ከነትርጓሜው ትነግሩኝ ብዬ አላቸው:: ንጉሥ ሥርዓት ለወጥከብን ዮሴፍ ለፈርዖን ቢተረጉምለት ሕልሙን ነግሮት ነው:: ሕልሙን ንገረን እንተርጉምልህ አሉት ቢጠፋኝ ነው እንጂ አላቸው:: ባይሆንም ቀን ስጠን አሉት አይድዑኒ እንበለ ይሕልፍ ጊዜሁ:: ይህን ጊዜ ትዝ ትዝ ብሎኝ ሳለ ንገሩኝ ድኅረሰ ትፈጥሩ ካልዐ ነገረ ኋላማ ልብ ወለድ አምጥታችሁ ይህ ነው ልትሉኝ አያደለምን? አላቸው:: የማይሆንላቸው ሆነ እንኪያ ፈረስ አይደላችሁ አልጋልባችሁ በቅሎ አይደላችሁ አላስግራችሁ በሰይፍ በላቸው አለ::

ወወጽአ አርዮክ /ያሮክ/ ሰያፊ ወአኀዘ ይቅትሎሙ ለጠቢባነ ባቢሎን ይላል:: ሁለቱን ሰስቱን እንደነሳላቸው /እንደነሣሣላቸው/ ዳንኤል ፫ቱ ደቂቅ ከከተማ በአፍኣ ነበሩ:: ዳንኤል ቀረብ ብሎ ይጠይቃል:: በይነ ምንት ወጽአ ዝንቱ ፅኑዕ ትእዛዝ እምቅድመ አዕይንቲሁ ለንጉሥ አለው:: ኧረ ይህስ ለእናንተም አይቀርላችሁም ንጉሥ ሕልም አልሞ ሕልሙን ከነትርጓሜው የሚነግረው እጥቶ አለው:: እነሱንም አትጨርሻቸው ተዋቸው ሕልሙን እኔ እነግረዋለሁ አለው::

ነገር ግን ቀን አስጠኝ አለው ገብቶ ከምርኮ ልጆች እንዲህ የሚል አለ አለው:: ሦስት ቀን ሰጥቼሀለሁ በለው አለው ሱባዔ ገቡ በሶስተኛው ቀን ተገለጸላቸው:: ለዳንኤል ግን ዕለቱን ተገልጾለታል:: ስለምን ቢሉ ጥሬ እንብላ ውሀ እንጠጣ በማለት ጾንቶ ይኖር ነበርና:: ስለተገለጸለት ዕለቱን ልውጣ አላለም ዛሬ ሱባዔ የገባ ሰው ነገሬ ከቀናልኝ ብሎ ሱባዔውን ሳይፈጽም መውጣት እንዳይገባው ሲያጠይቅ:: በሶስተኛው ቀን ለሁሉም ተገለጸላቸው ሂዱ ንገሩልኝ አለ:: ነገሩለት ግባ በሉት አለ ገባ::

ትክልኑ ትንግረኒ ሕልምየ ወፍካሬሁ አለው:: ይህ ዳንኤል እጥር ምጥን ያለ መልከ መልካም ነበረ:: እኔ በጥበብ ከሁሉ እበልጣለሁ ብዬ አይደለም ነገር ግን ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሔር እንጂ የገለጸለት ነው ብሎ አምልኮተ



እግዚአብሔርን ለበከለት:: አለኪ በል ንገረኝ አለው:: እንዲህ እንዲህ ያለ አላየህምን አለው::

ሕልምየ ውእቱ ንግረኒ ፍካሬሁ: አለው:: እንኪያስ ቀን ያሰብከውን ሌሊት አሳይቶሃል ባንተ ጊዜ የሚሆነውን ካንተ በኋላ የሚደረገውን:: ርእሱ ዘወርቅ: የተባልህ አንተ ነህ:: ወርቅ መክብበ ንዋያት ነው:: አንተም ንጉሠ ነገሥት ነህ:: እንግድዓሁ ዘብሩር የተባለ ዳርዮስ ነው:: ብር ከወርቅ በታች ከሌሎች ንዋያት በላይ ነው:: ዳርዮስም ካንተ በታች ከሌሎች ነገሥታት በላይ ነውና:: ሐቌሁ ዘብርት የተባለ ቂሮስ ነው:: ብርት ቢመቱት ከሩቅ ይሰማል ቂሮስም ዜና መንግሥቱ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይሰማልና:: ቍየጺሁ ዘሐፂን የተባለ እስክንድር ነው:: ብርት ጽኑዕ ነው እስክንድርም ኃያል ንጉሥ ነው:: መንፈቀ እግሩ ዘልሕኵት ወዘሐፂን የተባሉ እስክንድር በጊዜ ሞቱ የሚያነግሣቸው ድኩማኑ ኃያላኑ ነገሥታት ናቸው:: ድኩማኑ ሰልፎስ ድማጥርያኖስ: ኃያላኑ አንጥያኮስ በጥሊሞስ:: አንድም ወዘመዋዕሊሆሙ ለእሉ ይመጽእ እምላክ ሰማይ ይላል ብሎ: በመንግሥት ያወርዱታል:: ርእሱ ዘወርቅ: መንግሥተ ባቢሎን:: እንግድዓሁ ዘብሩር: መንግሥተ ሜዶን:: ሐቌሁ ዘብርት: መንግሥተ ፋርስ:: ቍየጺሁ ዘሐጺን: መንግሥተ ጽርዕ:: መንፈቀ እግሩ ዘልሕኵት ወዘሐፂን: መንግሥተ ሮም:: አንድም ጽርዕን ከፋርስ ደርቦ ቍየጺሁ ዘሐፂን መንግሥተ ሮም:: መንፈቀ እግሩ ዘልሕኵት ወዘሐፂን: በሮም ያሉ ድኩማኑ ኃያላኑ ነገሥታት ናቸው:: ይህ ምሳሌ ነው:: ደብር የሰማየ ሰማያት: እብን የጌታ:: ከረጅም ተራራ የሰው እጅ ሳይነካው ተፈንቅሎ መውረዱ ያለ አንገብሮ /ያለ መገደድ/ ከሰማየ ሰማያት የመውረዱ: አንድም ደብር የእመቤታችን: እብን እይለወጥም የጌታ:: የሰው እጅ ሳይነካው ከረጅም ተራራ ተፈንቅሎ መውረዱ ያለ ዘር ከእመቤታችን የመወለዱ:: ያን ቀጥቅጦ ደንጊያው ተራራ ሲያህል ማየትህ ይህን ሁሉ አጥፍቶ ልዕልናውን የመግለጹ: ተራራው በዓለም ሲመላ ማየትህ ሕማሙ ሞቱ ጽንፍ እስከ ጽንፍ የመስበኩ አምሳል ነው ብሎ ተርጉሞለታል:: አሙን ሕልሙ ወርቱዕ ፍካሬሁ ብሎ አድንቆ ራስ ቢትወደድ ሾሞታል ይህንንስ

ሌላ ያቦታል ብሎ ሲቀ ጠቢባንነት ሾሞታል:: ፫ቱ ደቂቅም ወግዴ በዘመኑ እንዲሉ ቀኝአዝማች ግራአዝማች ከንቲባ እየሆኑ ተሾመዋል:: ሹመታቸውም የዳንኤል በከተማ: የ፫ቱ ደቂቅ በአፍኣ ነው:: ጥበበ እግዚአብሔር ነው:: ዳንኤል በከተማ ያሉ እስራኤልን ሊጠብቃቸው: ፫ቱ ደቂቅ በአፍኣ ያሉ እስራኤልን ሊጠብቋቸው:: ይህ በሆነ በሁለት ዓመት ፫ቱ ደቂቅ ከሹመቱ ያስለቀቁት ነው ይላሉ ሌላም ነው ይላሉ ዳንኤል በንኳን ርእሱ ዘወርቅን የተረጐመልህ ላንተ ነው የወርቅ ጣዖት አቁመህ ኢታስግደውም? አለው:: እውነት አንጂ ነው ብሎ ፰ ክንድ ቁመቱ: ፮ ክንድ ደረቱ: ጣዖት በሐቅለ አዱራን ይቁም ብሎ አዘዘ ቆመ:: ዘኢሰገደ ለምስል ዘወርቅ ዘገበርኩ በእዴየ ይትበርበር ቤቱ ወይትሐየድ ንዋዩ ወይትኰነን ነፍሱ ብሎ አዋጅ ነገረ:: ጽርዕ ሚዶን ፋርስ ባቢሎን ሰገዱ:: ፫ቱ ደቂቅ ሳይሰግዱ ቀሩ ያው ሰው ሄዶ ኸረ ቀኝአዝማች ግራአዝማች ከንቲባ አድርገህ የሾምካቸው ሲድራቅ ሚሳቅ አብደናጎ ሳይሰግዱ ቀሩ አለው /ብለው ነገሩት/:: ወአዘዘ በመዓት ያምጽእዎሙ:: ተቆጥቶ ያመጧቸው ዘንድ አዘዘ:: አንድም እያጣደፋችሁ አምጧቸው አለ መጡ /አመጧቸው/:: አማንከሙኑ ሲድራቅ ወሚሳቅ ወአብዳናጎ ዘኢትሰግዱ ለምስል ዘገበርኩ በእዴየ ወኢታመልኩ አምላኪየ አላቸው::

እ ንጉሥ ኢንፈቅድ ንሰጠውክ በዝንቱ ግብር ሀሎ አምላክነ ዘናመልክ ኪያሁ በሰማይ አሉት::

መኑ ያድኅነክሙ እምእዴየ ወእምእቶነ እሳት አላቸው:: ሀሎ አምላክነ ዘፈጠረ ኪያከ ወኪያነ ውእቱ ያድኅነነ እምእዴከ ወእምእቶነ እሳት አሉት:: ያን ጊዜ ሰይፍ ጦር ቃጣባቸው:: ኋላ ያን ትቶ ጉድጓድ አስቆፍሮ እሳት አስነድዶ ከነቁንጽል/ ከእጭር / ቀሚሳቸው በተራዳ እየገፋ ጣላቸው /እየገፉ ጣሏቸው/ ስለምን ቢሉ አላልቦ ይግደላቸው ብሎ:: ለዚህስ እሳቱ ይበቃል ብሎ ውሉደ መንግሥት ናቸውና እንዳይዋረዱ ብሎ:: ፫ቱ ደቂቅ በውስጥ ዳንኤል በአፍኣ ሆነው ተናግረውታል: ከአዛርያ የተገኘ ዳንኤል የተናገረው ነገር ይህ ነው:: ምነው እነዚያስ ተናግረው የለም? ቢሉ እነዚያ መከራውን እንደመሰቀቅ ብለዋል: ይህ አዛርያ



አጸንቷቸዋል አንድ ሰዓት አይደለም ምን ቁም ነገር አለው ብሎ:: ዳንኤል ጥሬ እንብላ በማለት እንደጸና::

፩. ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ:: ያባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን:: የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ:: አንድም ለሙሴ ባሕር የከፈለለት ለኢያሱ ፀሐይ ያቆመለት ዛሬም ለኛ እቶነ እሳትን ያበረደ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን::

እኩት ወስቡሕ ስምከ ለዓለም

ስምህ ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው:: እኛ ብናመሰግነው ክብር የሚጨመርለት እኛ ባናመሰግነው ክብር የሚጎድልበት ሆኖ አይደለም::

፪. እስመ ጻድቅ አንተ በኲሉ ዘአምጻእከ ላዕሌነ: ብነ ሲል::ነው ባመጣህብን ሁሉ እውነተኛ ነህና እውነት ፈርደህ አምጥተህብናልና::

እሙን ኲሉ ግብርከ:: ሥራህ ሁሉ የታመነ ነው::

ወርቱዕ ኲሉ ፍናዊከ:: ሥራህ ሁሉ የቀና ነው::

ወጽድቅ ኲሉ ኲነኔከ::

ፍርድህ ሁሉ እውነት ነው::

አንድም እሙን ኲሉ:: ኢታምልክ የታመነ ነው:: ኲሉ አለ ፍጹም ሲል ነው::

ኢ በሰማይ ወኢ በምድር ብሎ ከፍሎታል::

ወርቱዕ:: ፀኙ ቃላት::

ወጽድቅ ኲሉ ኲነኔከ:: ፭፻፷ ወነበበ አለ:: ያ እውነት ነው አንድም እሙን ሚጠት:: ወርቱዕ:: ዓዋዊ::

ወጽድቅ ኲነኔከ:: በሀገራችን ሳለን ያመጣኸው አባር ቸነፈር እውነት ነው አለ የሚገባ ነው::

፫. ወገበርከ ፍትሐ ወርትዐ በኲሉ ዘገበርከ ለነ ብነ ሲል ነው:: /ይላል/ በኛ ባደረግኸው ሁሉ ፍትሕ ርትዕን አደረግህ አለ:: እውነት ፈርደህ አመጣህብን::

ወዳበ ሀገረ አበዊነ ኢየሩሳሌም ቅድስት::

ብነ ወበሀገረ አበዊነ:: በአባቶቻችን አገር በኢየሩሳሌም ሳለን ያመጣኸው አባር ቸነፈር እውነት ነው አለ: እውነት ፈርደህ አመጣህብን::

እስመ በኩነኔ ጽድቅከ አምጻእከ ዘ ኵሎ በእንተ ኃጢአትነ:: ስለኃጢአታችን ይህን ሁሉ በእውነተኛ ፍርድህ አምጥተህብናልና አለ: እውነት ፈርደህ አምጥተህብናልና::

፱. እስመ አበስነ ወጌገይነ ዘንደግናከ ያ ግን የጣልንህ እኛ በድለናል ስሑታን ሆነናልና:: ዐመፅነ በኲሉ ወኢሰማዕነ ትእዛዘከ:: ፲ቱ ቃላትን አፈረስን::

ኢሰማዕነ:: ፫፻፰ ወነበቦ አለ: ያን አልሰማንም::

አንድም ዐመፅነ በኲሉ:: ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ዕፀው እእባንን በማመን (በማምለክ) በደልንህ::

ወኢሰማእነ:: ኢታምልክ ያልከውን አልሰማንም::

፲. ኢዐቀብነ ወኢገበርነ በከመ አዘዝከነ:: ያዘዝከንን አልጠበቅንም እንዳዘዝከን አላደረግንም::

ከመይኩን ሠናየ ላለሉነ:: መጠበቁ በጎ ይሆንልን ዘንድ: ሠናይ ይላል በመጠበቁ ክብር ረድኤት ይሰጠን ዘንድ::

፲፩. ኵሎ ዘአምጻእከ ላዕሌነ ወኵሎ ዘገበርከ ዲቤነ በኵነኔ ጽድቅ ገበርከ:: በኛ ላመጣኸው በኛ ባደረግኸው ሁሉ በእውነተኛ ፍርድህ አደረግህ አለ: እውነት ፈርደህ አመጣህብን::

፲፪. ወመጠውከነ ውስተ እደ ፀርነ ኀጥአን ወዓላውያን:: ኀጥአን ዓላውያን በሚሆኑ በጠላቶቻችን እጅ የጣልከንን መጣል ኃጥአን የሚላቸው ምግባር የሌላቸው: ዓላውያን የሚላቸው ሃይማኖት የሌላቸው ናቸው:: እሊህ ግን ሁሉም የላቸውምና ኃጥአን ዓላውያን አላቸው::

እለ ርጉቃን ወግሑሣን እምኔከ:: ኃጥአን ያለውን ርጉቃን ዓላውያን ያለውን ግሑሣን ብሎ ደገመው::

ወንጉሥ ዐማፂ ወእኩይ እምኵሉ ምድር: ወውስተ እደ ንጉሥ ይላል:: ከሰው ሁሉ በሚከፋ በናቡከደነፆር እጅ የጣልከንን መጣል:: ቢከፋ ቢከፋ ከፈርዖን ይከፋል? ቢሉ ለጊዜው አዎን ይከፋል:: ፈርዖን ለእግዚአብሔርኒ ኢየአምሮ



አለ እንጂ አነ ውእቱ አላለም:: እሱ ግን አነ ውእቱ ዘአሠርቅ ፀሐየ ብሏል::

፲፫. ወይእዜኒ አኮ: ድልወት ለነ ንክሥት አፉነ:: አሁንም አድነን ብለን እንለምንህ ዘንድ አይገባንም ኃጥአን ነን::

ሐፍረት ወዝንጓኤ ኮነሙ ለአግብርቲከ ለእለ ይፈርሁከ:: በሚያመልኩህ በሚፈሩህ በባሮችህ በነቢያት በካህናት የመጣውን ሽሙጡን ተግዳሮቱን አይተህ ለምተህ ይቅር በለን እንጂ::

፲፬. ኢትመጥወነ: ለግሙራ በእንተ ስምከ:: ስምየኒ መሐሪ ወመሥተሣህል ስላልከው ስለስምህ ብለህ ለመከራው አትስጠን እንደሰጠኸን አትቅር::

ኢትሚጥ ኪዳነከ ወኢታርሕቅ ምሕረተከ እምኔነ:: መሐላሕን ቸርነትህን ከእኛ አታርቅ ኪዳነ ምሕረተነም ይላል::

በእንተ አብርሃም ፍቁርከ:: ብየ ዓርከ አብርሃም በዲበ ምድር ስላልከው ስለ አብርሃም ብለህ::

ወበእንተ ይስሐቅ ቍልዔከ:: እምይስሐቅ ይሰመይ ለከ ዘርዕ ስላልከው ስለይስሐቅ ብለህ::

ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ:: እምይእዜሰ ኢይሰመይ ስምከ ያዕቆብ አላ ይሰመይ ስምከ እስራኤል ስላልኸው ስለ ያዕቆብ ብለህ ይቅር በለን::

፲፭. እለተናገርኮሙ ወትቤሎሙ ከመታብዝኅ ዘርዖሙ ከመ ኮከበ ሰማይ:: ልጅ የልጅ ልጃቸውን እንደ ሰማይ ኮከብ::

ወከመ ኖፃ ባሕር ዘድንጋገ ባሕር:: እንደ ባሕር አሸዋ ታበዛላቸው ዘንድ ስለተናገርካቸው ስለእነሱ ብለህ ይቅር በለን::

እስመ ውኅዳን እሙንቱ እምኵሉ አሕዛብ:: ከአሕዛብ ይልቅ ጥቂቶች ላሉ አብርሃም ከሣራ: ይስሐቅ ከርብቃ: ያቆዕብ ከራሔል ከልያ::

ወኮነ ኅሡራነ በኵሉ ምድር ዮም በእንተ ኀጢአትነ:: ስለኀጢአታችን በባቢሎን የኀሰቆልን ሆን::

፲፮. <u>አልቦ በዝ</u> መዋዕል መልእክ ኢ ነቢይ ወኢ ንጉሥ:: አለቃችሁ አያድናችሁም ትለኝ እንደሆን እንደ ኢያሱ ያለ

ክፉውን ተመራምሮ አጥፍቶ የሚያድን አለቃ የለንም (የለንምና)::

<u>ታሪክ</u> ይህ ኢያሱ ተሳለ ለብአ ኢያሪኮን በእጀ ብትጥልልኝ ከዚያ ያገኘሁትን ሁሉ ለቤተ እግዚአብሔር እሰጣለሁ ብሎ ሕዝቡም ተሳሉ:: ይህች ኢያሪኮ ፯ ቅፅር ያላት ናት ፯ ቀን እየዞረ ሲሰፍር ሰንበተ በ፯ኛው ቀን የነጋሪት ድምፅ አሰማባት ሻ / ናድ : ወለል/ ብላ ፈረሰች:: አክአን ወልደ ከርሚ ይለዋል:: ሀምሳ ወቄት የምትሆን ልሳነ ወርቅ ሁለት መቶ ምዝምዝ ብር አራት ጎሞር አምስተኛ ወርቀ ዘቦ ያላት ግምጃ አገኘ ያን ከድንኳኑ ወስዶ ጉድጓድ ቆፍሮ በታች ወርቁን በላይ ብሩን ከዚያ በላይ ግምጃውን አድርጎ ቀበረው ካጠገቡ ጋይ የምትባል አገር ነበረች ለላይ ሰደደ /ሰዶ/ ይህችስ አንተንም የምታስጭን አይደለችም ቢሆን ሁለት ሺ ባይሆን ሶስት ሺ ጦር ይበቃታል አሉት:: ሶስት ሺ ጦር ሰደደ እስራኤል ድል ሆኑ:: ከእስራኤል ፴፮ ሰው ሞተ:: ኢያሱ በግንባሩ ደብተራ ወደቀ::

በይነ ምንት አዕድዎ አዕደዎሙ ገብርከ ዮርዳኖስ ናሁ እስራኢል ሜጠ ዘባኖ ቅደመ ፀሩ:: እስራኤል ጀርባውን መልሶ ፊቱን ቀልሶ ሸሸ ብሎ ፸ ሊቃናትም ወደቁ ጌታ በሠርክ መጥቶ አንተስ ሰባ ሊቃናትስ ለምን ወደቃችሁ ለኔ ክተሳልከው ገንዘብ ያስቀረ አለ:: ያን ተመራምረህ ካለጠፋህ በረድኤት ካንተ ጋራ አልኖርም አለው:: ሊቀ ካህናቱ አልዓዛር ነበር አልዓዛርን /ካህናቱን/ ልብሰ ተክህኖ አልብሶ በየነገዳችሁ እለፉ ሂዱ አላቸው:: ነገደ ዛራ ሲያልፍ ምልክት ታየ:: ምልክቱም ልብሱ ይጠቁራል ይነፋል እነዚያን ደግሞ አንድ አንዳችሁ እለፉ አላቸው:: ይህ አክአን ሲያልፍ ጭራሽ ጠቆረ ቃልም ተሰማ ይላሉ::

እመኖ ወልድየ:: ልጄ አላዋቂ አታድርገው:: ምን ምን ወሥደሃል አለው:: እንዲህ እንዲህ ያለ ወስጃለሁ አለው:: ሚስቱን ልጆቹን ከብቶቹን እሱን አድርጎ በቆላተ ኤሜቃኮር በእሳት አንጠቅጥቆ ገድሎታል:: እንዲህ አድርጎ ክፉ ክፉውን ተመራምሮ አጥፍቶ የሚአድን አለቃ የለንም::



ኢ ነቢይ:: ነቢያችሁ እያድናችሁም ትለኝ እንደሆነ እንደ ሙሴ ያለ:: እምትጥስዮሙ ለእሉ ሕዝብከ ጠስየኒ ሊተ እመጽሐፈ ሕይወት ዘጸሐፍከኒ ብሎ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ የሚያድን ነቢይ የለንም::

ወኢ ንጉሥ:: ንጉሣችሁ እያድናችሁም ትለኝ እንደሆነ እንደ ዳዊት ያለ: ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ አነ ኖላዊ /እንዝ እነ/ ኖላዊ ብሎ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ የሚያድን ንጉሥ የለንም::

ታሪክ ዳዊት የእስራኤልን ብዛት ሊያይ ቢሻ አስቆጠራቸው:: ነገደ ይሁዳ አምስት መቶ ሺሕ ሆኑ:: ፲ሩ ነገድ ተኩል ስምንት መቶ ሺሕ ሆኑ:: ፪ቱ ነገድ ተኩል ክረምት ገባና ሳይቆጠሩ ቀሩ:: በዚህ ቢያዝን ጋድን በልማደ ነቢያት ላከበት:: ብዛታቸውንስ ልታይ ብትወድ ግባት አለኝተህ/ሰብስባ ጠርተህ/ ባየሃቸው ነበር እንጂ:: አሁንም ከረኃብ ከጦር ከቸነፈር ከሊህ ከሶስቱ ምረጥ ብሎሃል አለው::

እምእደቅ ውስተ እደ ሰብእ ይኄይሰኒ ወዲቅ ውስተ እደ እግዚአብሔር አለ:: ረሀብንስ አላነሳውም ከሁሉም ይጸናልና:: ከዚህ በኋላ መልአክ መደምስስ በዓውደ ኦርና ሲቀስፍ ታየው::

ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ እንዝ አነ ኖላዊ ዘአበስኩ:: በግ እረኛው ሲቆጥረው አልቆጠርም ይላል?

ዛቲ እዴከ ትኩን ላዕሌየ ወላዕለ ቤተ አቡየ ብሎ ወደቀ:: ቸነፈሩ ፀጥ አለ ያንጊዜ ያለቁት ሰባ ሺሕ ከሶስት ናቸው እስከ ቀትር::

ኢ ቍርባን ወኢ መሥዋዕት:: ቍርባናችሁ መሥዋዕታችሁ እያድናችሁም ትለኝ እንደሆነ ቍርባን መሥዋዕት የለም:: መሥዋዕት የላሙ የበጉ: ቍርባን የስንዴው የእህሉ አንድም መሥዋዕት ተረፉ ቍርባን የሚፈስሰው ደሙ የሚጤሰው ስቡ::

ወኢ ኀበ እለ ያጸነሕሑ ዕጣነ:: ሊቀ ካህናቱ እያድናችሁም ትለን /ትለኝ/ እንደሆነ እንደ አሮን ዕጣን አጥኖ የሚያድን ሊቀ ካህናት የለንም:: አንድም ዕጣን የሚያጥኑበት ማዕጠንት የለም:: ኤርምያስ ቀብሮት ሄዷል:: አንድም ዕጣን ይላል:: ዕጣን በባቢሎን የለም ማለት አይደለም መሥዋዕቱ ሲቀር ዕጣኑም ቀርቷል::

ወኢ ብሔር ኀበ እለ ይፈርዩ በቅድሜከ ይርከቡ ሣህለከ:: ይቅርታህን ሊያገኙ ምግባር ትሩፋት የሚሠሩበት አገር የለም:: ለሥራ ቦታ ያግዛልና::

፴፱. ዘእንበለ በነፍስ የዋሕ ወበመንፈስ ትሑት ተወከፍ ለነ:: በትሑት ሰብእና በየዋሕ /በቅን/ ልቡና ያቀረብንልሕን ተቀበልልን እንጂ:: እንደ መሥዋዕቱ ጸሎታቸውን: እንደ ምሥዋዐ ብርቱ ልቡናቸውን: እንደ ሊቀ ካህናቱ እንደበታቸውን: እንደ ቤተ መቅደስ ሰውነታቸውን: አድርገው ይናገራሉ::

፵. ከመ ዘመሥዋዕተ ሐራጊት ወእልሕምት:: ሐራጊት የዳዊት የሰሎሞንን:: እልህምት: የሙሴ የአሮንን መሥዋዕት እንደተቀበልክ ተቀበልልን::
ወከመ ዘእዕላፍ: አባግዕ ስቡሐን:: የኢዮስያስን መሥዋዕት እንደተቀበልክ ተቀበልልን:: እልቦ ዘገብረ በዓለ ዘከመ ገብረ ኢዮስያስ ይለዋልና::
ከማሁ ይኩን መሥዋዕቲነ በቅድሜከ ዮም:: ጸሎታችን በፊትህ እንዲህ ይሁን እለ ወደህ ተቀበልልን::
ወፍጹመ ይኩን በኀቤከ:: ባንተ ዘንድ ፍጹም ይሁን::
ከመ ኢይትኀፈሩ ኵሎሙ እለ ይትዌከሉከ:: ባንተ ያመኑ ሁሉ መከራ መጥቶባቸው እንዳያፍሩ::

፵፩. ወይእዜኒ ንተልወከ በኵሉ ልብነ ወንፈርሐከ:: አሁንም በፍጹም ልቡናችን እንፈራሃለን እናመልክሃለን::
ወነኀሥሥ ገጸከ ዳዕሙ ኢታስተሐፍረነ:: አታሳፍረን እንጂ ረድኤትህን እንሻለን::

፵፪. ወግበር ምስሌነ በከመ ተመይጦትከ:: ከመዓት ወደ ምሕረት እንደመመለስህ መጠን ቸርነትህን አድርግልን::
ወበከመ ብዝኀ ምሕረትከ አድኅነነ በተእምሪከ:: እንደ ቸርነትህ ብዛት መጠን በተእምራትህ አድነን::
ሀብ ስብሐተ ለስምከ እግዚኦ:: ለስምህ ምስጋናን ስጥ አለ:: አቤቱ እኛን አድነህ ስምህ እንደሚመሰገን አድርግ::



፵፬. ይትኀፈሩ ኵሎሙ እለ አርእይዎሙ ሥቃየ ለአግብርቲከ:: በባሮችህ በነቢያት በካህናት መከራ የሚያፀኑባቸው ይፈሩ ይጎስቁሉ::
ይትኀፈሩ በኵሉ ትዕግልቶሙ ወይትቀጥቀጥ ኀይሎሙ:: የሰው ገንዘብ በመቀማታቸው አምልኮትህን በመቀማታቸው ይጎስቁሉ ይትኀፈሩ ይድከም ኃይሎሙ ይሕልቅ ብዕሎሙ ይላል:: ኃይላቸው ይድከም:: ብዕላቸው ይለቅ::

፵፭. ወያእምሩ ከመ አንተ እግዚአብሔር አምላክ ባሕቲትከ:: አንተ ብቻ አምላክ እንደሆንክ ይወቁ::
ስቡሕ በኵሉ ምድር ወበኵሉ ዓለም: በኵሉ ምድር: በዚህ ዓለም::
ወበኵሉ ዓለም: በሰማይ::
እንድም በኵሉ ምድር: በኢየሩሳሌም::
ወበኵሉ ዓለም: በባቢሎን::
እንድም በኵሉ ምድር: በባቢሎን::
ወበኵሉ ዓለም: በከሳውዴዎን:: ክቡር ምስጉን አንተ ብቻ እንደሆንክ ይወቁ::

## ፱ ጸሎተ ፫ቱ ደቂቅ

ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጦ ለነበልባል ወኮነ ከመ ነፋስ ቈሪር ይላል:: ቅዱስ ገብርኤል ወርዶ ቢባርከው ቀዘቀዘ በምንጣሐት ያጠፋት መስኳቸው ወወደዩ ውስተ እሳቱ ተየ ወፒሳ ወሰጠጽዮን ወቀለምጺዳ ይላል::

ተየ ድኝ ፒሳ ሰም አደሮማር ሰጠጽዮን የወይን ሐረግ ዶግ ቀለምጺዳ ቅንጭብ ቁልቋል የሚያናድደውን ሁሉ ጨምረዋል /ጨምረውበታል/::

ወተለዐለ ነበልባሉ መጠነ ፵ ወ፱ቱ በእመት ይላል:: በምን ታውቋል ቢሉ ካጠገቡ ዛፍ ነበረ ያንን ወጥቶ በልቶታል:: ቢሰፍሩት ፵፱ ክንድ ሆኗል:: እንድም ነበልባሉ አልፎ የወደቀበት

መሰከ:: እንድም ዳንኤል በእመተ ጸጋ ሰፍሮታል /በጸጋ አውቆ ቆጥሮታል/ በመከራ ላይ መከራ ቢያጸኑባቸው በምስጋና ላይ ምስጋና ያጨምራሉ ፫ቱ ደቂቅ የተናገሩት ነገር ይህ ነው::

፩. ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ:: ያባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን:: የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ:: እንድም ለሙሴ ባሕርን የከፈለለት ለኢያሱ ፀሐይን ያቆመለት ዛሬም ለኛ እቶነ እሳትን ያበረደልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን::
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም:: ስምህ ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው:: እኛ ብናመሰግነው ክብር የሚጨመርለት እኛ ባናመሰግነው ክብር የሚጎድልበት አይደለም::
ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ:: ክቡር ልዩ የሆነ የጌትነቱ ስም ይክበር ይመስገን::
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ በኵሉ ዓለም:: ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው::

፪. ቡሩክ አንተ በጽርሐ ቅድሳተ ስብሐቲከ:: በጽርሐ አርያም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለህ የምትመሰገን ክቡር ምስጉን አንተ ነህ::
ስቡሕኒ አንተ ወእኩት አንተ ለዓለም:: ለዘላለም ክቡር ምስጉን ነህ::

፫. ቡሩክ አንተ ዘትሬኢ ቀላያተ ነቢረከ ላዕለ ኪሩቤል:: በኪሩቤል ላይ ሆነህ ቀላያተ ውቅያኖስን ቀላያተ እቶነ እሳትን ቀላያተ ገሀነምን የምታይ አንተ ክቡር ምስጉን ነህ::
ስቡሕኒ አንተ ወልዑል አንተ ለዓለም:: ለዘላለም ክቡር ምስጉን አንተ ነህ::

፬. ቡሩክ አንተ በዲበ መንበረ መንግሥትከ:: በጌትነትህ ዙፋን ክቡር ምስጉን አንተ ነህ:: ስቡሕኒ አንተ ወቡሩክ አንተ ለዓለም:: ለዘላለም ክቡር ምስጉን አንተ ነህ::

፭. ቡሩክ አንተ በመልዕልተ ሰማያት:: በሊቃነ መላእክት ክቡር ምስጉን አንተ ነህ::
ስቡሕኒ አንተ ወክቡር አንተ ለዓለም:: ለዘላለም ክቡር ምስጉን አንተ ነህ::



ስለምን ከፍ ብለው ፲: ፰: ዝቅ ብለው ፬: ፭: ያልተናገሩ ፯ የተናገሩ ስለምን ነው ቢሉ ሰውስ ከፍ ብለው ፲: ፰: ዝቅ ብለው ፬: ፭: ቢናገሩም ስለምን ነው ማለቱን አይተውም ብሉ መንፈስ ቅዱስ እንደመገባቸው ተናግረዋል:: እኛ ከእቶነ እሳት በወደቅን በ፲፪ ዘመን ሰው ይሆናል ሥጋ ይለብሳል ቢሉ:: በዘመናቸው የነበረ ዳንኤል ፩፻፺ አለ: እነሱ ፲፪ አሉ: እንደምን ነው ቢሉ እሱ ከሚጠት እስከ ጽንስ ቆጥሮ እነሱ ከእቶነ እሳት እስከ ዕርገት ቆጥረው ነው:: የሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥቱ ፲፩ ዓመት ነው:: በ፭ኛው ወድቀዋል:: ከሴዴቅያስ ፯ የናቡከደነፆር ፳፭:: የዮርማሮዴቅ ፳፪ የብልጣሶር ፳፫ ይህን ቢያገናኙት /ቢገጥሙት/ ፸፯:: የጌታ ፴፫:: በጠቅላላ ፻፲:: ፩፻፺ን እና ፻፲ን ቢያገናኙ /ቢገጥሙት/ ፲፪ ይሆናል:: ወተሰዐለ ነበልባሉ መጠነ ፵ወ፱ቱ በእመት ያለው ግን የዘሩባቤል ዘመነ መንግሥቱ አምሳል:: ፵፱ ዘመን ገዝቷል:: ፯ን እና ፵፱ን ቢያገናኙ (ቢቆጥሩ) ፶፮ ይሆናል:: በ፭ ሺህ ከ፭፻ ዘመን ሰው ይሆናል ሥጋ ይለብሳል ቢሉ::

፲ ኀበ ባረኩ አናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል::

አናንያ አዛርያ ሚሳኤል ምስጋና ካቀረቡ ዘንድ:

፩. ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር:: ፍጥረቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል አሉ:: ፫ቱ ደቂቅ አሉ:: ፫ቱ፻:: ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም:: ለዘላለሙ ክቡር ምስጉን ነው::

፪. ይባርክዎ ሰማያት ለእግዚአብሔር:: ኵሉ ያለውን ይተረትራል:: ፯ቱ ሰማያት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል:: ስቡሕኒ: አይለውጥም::

፫. ይባርክዎ መላእክተ እግዚእ ለእግዚአብሔር:: ሰራዊተ መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል:: ስቡሕኒ: አይ::

፱. ይባርክዎ ኵሉ ማያት ዘመልዕልተ ሰማያት ለእግዚአብሔር። ከጠፈር በላይ ያሉ ሐኖስ እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል። ማያት ሰማያት ብሎ አበዛ በ፬ቱ ማዕዘን ጸንቶ የሚኖር ስለሆነ ሰቡሕኒ፡ እይ።

፲. ይባርክዎ ኵሉ ኃይለ እግዚእ ለእግዚአብሔር። ሊቃነ መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ሰቡ እይ።

፲፩. ይባርክዎ ፀሐይ ወወርኅ ለእግዚአብሔር። ፀሐይ ጨረቃ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ሰቡ እይ።

፲፪. ይባርክዎ ከዋክብተ ሰማይ ለእግዚአብሔር። በሰማይ ያሉ ከዋክብት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፫. ይባርክዎ ጠል ወዝናም ለእግዚአብሔር። ጠል ዝናም እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፬. ይባርክዎ ኵሉ መንፈስ ለእግዚአብሔር ፫ቱ ነፋሳተ መዓት ፬ቱ ነፋሳት ምሕረት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፭. ይባርክዎ እሳት ወላህብ ለእግዚአብሔር። እሳት አካሉ ላህብ ዋዕዩ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፲፮. ይባርክዎ ሌሊት ወመዓልት ለእግዚአብሔር። ፲፪ቱ ሰዓተ መዓልት ፲፪ቱ ሰዓተ ሌሊት እግዚአብሔር ያመሰግኑታል።

፲፯. ይባርክዎ ጠል ወዐውል ለእግዚአብሔር። ጠል ዓውል እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ምነው ጠልንማ ተናግሮት አልነበረም? ቢሉ ጠሉ ሐጋይ ጠሉ ክረምት ጠሉ መዓት ጠሉ ምሕረት አሉና። አውልዕ ዋግ ነው።

፲፰. ይባርክዎ ቍር ወአስሐትያ ለእግዚአብሔር። ቍር አስሐትያ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ቍር ብትኑ አስሐትያ ግግሩ። ወይትፈለጥ ከመ ሰባረ ማሕረጽ /ማጎው/ የሚለው።

፲፱. ይባርክዎ በርህ ወጽልመት ለእግዚአብሔር። ጨለማ ብርሃን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳. ይባርክዎ ደደክ ወመርቄ ለእግዚአብሔር። ደደክ ደጋ መርቄ ቆላ። እንድም ደደክ ቀቅ፡/ብርድ/ መርቄ ዋዕዩ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።



፳፩. ይባርክዎ በረድ ወጊሜ ለእግዚአብሔር። በረድ ጊሜ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። በረድ የሚለው መዝገብተ ደመናት ወስደው ደመናውን ይዘረጋሉ። ማያት ይቋጥራሉ። መዛግብተ ነፋሳት ጭነው ይወጣሉ። ከዚያ ሲያማታው ይወርዳል። እንድም ሄኖክ ወርኢኩ መዝገበ በረድ ይላልና፡ ቤቱ አለው። ጊሜ ላህበ ምድር ነው።

፳፪. ይባርክዎ መብረቅ ወደመና ለእግዚአብሔር። መብረቅ ለሚሉው መላእክት ድኝ አሸዋ ጨምረው ጭነው ይወጣሉ። ከዚያ ሲያጋጩት ይወጣል ቡላድ/ደንጊያና ደንጊያ/ ሲያጋጩት እሳት እንዲወጣ። ደመና፡ ርጡብ ጢሰና ይቡስ ጢስ በፀሐይ ሞቀው አንድ ደመና ይሆናሉ። ወይመውቅ ፀሮሙ በፀሐይ ወያከውሉ አሐደ ደመና እንዲል።

፳፫. ትባርኮ ምድር ለእግዚአብሔር። ምድር እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች። አስከ አሁን በወንድ አንቀጽ ሲናገር መጥቶ አሁን በሴት አንቀጽ ተናገረ። ሴት ከባሏ ዘር ተቀብላ ልጅ እንድታስገኝ ምድርም ከሰማይ ዝናምን ተቀብላ አትክልትን አዝርዕትን ታስገኛለችና።

፳፬. ይባርክዎ አድባር ወአውግር ለእግዚአብሔር። አድባር ተራሮች /ተራራዎች/ አውግር ኮረብቶች /ኮረብታዎች/ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳፭. ይባርክዎ ኵሉ ዘይበቍል ውስተ ምድር ለእግዚአብሔር። በምድር የሚበቅለው ሁሉ አዝርዕት አትክልት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳፮. ይባርክዎ ቀላያት ለእግዚአብሔር። ቀላያት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ። በሀገራችን ጣና በሀገራቸው ምጥዋ።

፳፯. ይባርክዎ ባሕር ወአፍላግ ለእግዚአብሔር። ባሕር በፈሳሽ መካከል ያለው፡ አፍላግ ፈሳሹ እንደ ዓባይ እንደ በሽሎ ያሉት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፳፰. ይባርክዎ ዐንበር ወኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ማይ ለእግዚአብሔር። ዓሣ ዐንበሪ በውስጡ ያሉት አዞ ጉማሬ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

፸፱. ይባርክዎ ኩሉ አዕዋፈ ሰማይ ለእግዚአብሔር:: አእዋፍ እግዚአብሔርን ያመሰግናትታል::

፹. ይባርክዎ ኩሉ አራዊት ወእንስሳ ለእግዚአብሔር:: አራዊት እንስሳት እግዚ. ያመሰግኑታል::

፹፩. ይባርክዎ ደቂቀ ዕጓለእመሕያው ለእግዚአብሔር:: ሰዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል:: ቤት ሠርቶ ጉልላት እንደ መሥራት ጥቁር ጥሎ ነጭ እንደመጣል ሰውን በላይ አደረገው /አመጣ/::

፹፪. ይባርክዎ እስራኤል ለእግዚአብሔር:: ከዚያውም ዘንድ ምእመናን ይበልጣሉና: እስራኤል እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል::

፹፫. ይባርክዎ ካህናተ እግዚእ ለእግዚአብሔር:: እንደ ዲያቆናት ያሉት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል::

፹፬. ይባርክዎ አግብርተ እግዚእ ለእግዚአብሔር:: እንደ ቀሳውስት ያሉት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል::

፹፭. ይባርክዎ መንፈስ ወነፍስ ጻድቃን ለእግዚአብሔር:: የጻድቃን ሰውነታቸው ልቡናቸው እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል::

፹፮. ይባርክዎ ጻድቃን ወትሑታን ልብ ለእግዚአብሔር:: ጻድቃን ወጣንያን: ትሑታን ፍጹማን: ወይሬስዩ /ወይሬእዩ/ ርእሶሙ ከመ ነፍስ/መንፈስ/ እንተ ትማልም ኀለፈትእንዲል/ የሚሉቸው/ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል::

፹፯. ይባርክዎ አናንያ: ወአዛርያ: ወሚሳኤል ለእግዚአብሔር:: ከዚያውም ዘንድ ሰማዕታት ይበልጣሉና አናንያ አዛርያ ሚሳኤል እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል::

ንባርክ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን እናመሰግነዋለን:: አንድነታቸውን ሲያዩ ንባርክ: ሦስትነታቸውን ሲያዩ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሉ:: አንድም የ፫ቱ ደቂቅን ቃል ፫ቱ፮ ይተረጕማሉ ይባርክዎ ማለታቸው:: ንባርክ ለእግዚአብሔር ማለታቸው: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሲሉ ነው ብለው::



አንስ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል::

ታሪክ:-

ይህ ናቡከደነፆር ከሰገነት ላይ ሆኖ አይቶ

ስለነ አናንያ ፫ቱ አደው ወደዶን ውስተ እሳት ናቸው አራእ. ፬ቱ አደው እንዘ ያንሶሰዉ ማእከለ ነደ ውስተ እቶን እሳት:: ወራብዑሰ ይመስል ገጹ ከመ ገጸ ወልደ እግዚአብሔር አለ:: ዛሬ ሰው መልክ መልካም ሕፃን ያየ እንደሆን የንጉሥ ልጅ መልክ ይመስላል እንዲል ፀሐይ ይመስላል አለ:: አንድም ሙሴን ይመስላል አለ:: በሬተ ብርሃን ተሥሎበት ተወለደ ሲሉ ይሰማልና:: አንድም መልአክ ፊቱን ጸፍቶ አፉን ከፍቶ አናግሮታል:: ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ ወልደ እግዚአብሔር ማለት ነውና:: ከዚያ ወርዶ አንትሙ ሲድራቅ ወሚሳቅ ወአብደናጎ አግብርቲሁ ለልዑል: ንዑ ጻእ ዝየ አላቸው:: ተራዳ ትከሉልን ገመድ ማሰሉን ሳይሉ እንደሳቢሳ ብር ብር እያሉ ወጥተዋል:: አዋጁን ዘአዋጅ መልሶታል::

ዘኢሰገደ ለአምላክ ሲድራቅ ወሚሳቅ ወአብደናጎ ይትበርበር ቤቱ ወይትሐየድ ንዋዩ ወይትከሉን ነፍሱ ብሏል:: ይህ ምሳሌ ነው:: በውስጡ ያሉት የጻድቃን ብሔት: ከዚያ የገባ እሳቱ እንዳላገኛቸው ጻድቃን በሲኦልም ሥቃየ ገሃነም አላገኛቸውም::

ነፍሶሙስ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለክርሞ ሥቃየ /እሳት/ ገሃነም እንዲል::

እደ እግዚአብሔር እንደ ድንኳን እንደ አጥር ሆና ትጠብቃቸው ነበር::

በአፍኣ /በውጭ/ ያሉት የኃጥአን ብሔት: ናቡከደነፆር የወልደ እግዚአብሔር: ከዚያ ወርዶ ጻእ ዝየ እንዳላቸው በአካለ ነፍስ ወርዶ እለ ውስተ ሲኦል ጻእ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ ብሏቸዋልና:: ይህንም መሥመሩን ቢቆጥሩት ፴፪: አንድ ሰቡሕኒ ጨምሮ ፴፫ ይሆናል:: በዚህ ዓለም ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ፴፫ ዘመን የመኖሩ ምሳሌ::

## ፲፮. ጸሎተ ዕንባቆም ነቢይ

ዕንባቆም ማለት ማእምር ጠቢብ ለባዊ ማለት ነው:: ዔዋዌ እንደደረሰ ተገልጸለት ፍልሰጥኤም ወጥቷል:: ከዚያ ሲኖር ለሰንደ. ሰባሪዎች /አጫጆች/ ምሳ ይዞ ሲሄድ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ ይህን ባቢሎን ወስደህ ለዳንኤል ስጠው አለው:: በገበ አንበሳ /አናብስት/ ወድቆ ነበርና አይቴት ባቢሎን ወአይቴት ዳንኤል አለው:: ወጾሮ በሥእርተ ርእሱ ይላል:: በራስ ጠጉሩ አንጠልጥሎ ወስዶ እንደተገጠመች ዛብዩ መግቦት እንደተገጠመች ወጥቷል: ይህ ምሳሌ ነው:: ዕንባቆም የወልደ እግዚአብሔር: ዳንኤል የአዳም: ጉብ የእመቤታችን: ምግቡ የምግበ ነፍስ: እንደተገጠመች ገብቶ እንደተገጠመች መውጣቱ በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና የመወለዱ ምሳሌ:: ዕንባቆም የተናገረው ነገር ይህ ነው::

፩. እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራሕኩ:: አቤቱ ቀድሞ ይህን ነሰም እምነበ አልቦ ነበ ቦ አምጥተህ ፈጠርከ ሲሉ ሰማሁ ሰምቼ ፈራሁ

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ:: ዛሬም እምነበ ቦ ነበ አልቦ ስታሳልፈው አይቼ ሥራህን አደነቅሁ::

፪. በማዕከለ ክልዔ እንስሳ ርኢኩከ:: በጻድቃንና በኃጥአን መካከል ንዑና ሑሩ ብለህ ስትፈርድ አየሁህ

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አእምረከ:: ዘመነ ምጽአት ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ

ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እሌብወከ:: ጊዜ ምጽአት ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ሶበ ትትሐወክ ነፍስየ እመንሱት በምሕረትከ ተዘከረኒ:: ከኃጥአን ጥፋት የተነሣ ሰውነቴ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ አለ:: ከጻድቃን ተዳርጎ /ጻድቃንን መስሎ/ ይናገራልና::

እንድም እግዚኦ ሰማዕኩ አቤቱ ቀድሞውን ጅውን ፱ /ስድስት መቶ ሺ/ እጋርን በምድረ በዳ እንደሻሽ አንጥፈህ እንደቅጠል አርግፈህ አስቀረሃቸው ሲሉ ሰማሁ ሰምቼ ፈራሁ::

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ:: ዛሬም ፲ሩን ነገድ ፪ቱን ነገድ ስታሰማርከ አይቼ ሥራህን አደነቅሁ::



በማዕከለ ክልኤ እንስሳ ርኢኩከ:: በስልምናሶርና በናቡከደነፆር መካከል አየሁህ::

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አእምረከ:: ዘመነ ዔዋዌ ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ወከመ ከመ ይበጽሕ ጊዜሁ እሌብወከ:: ጊዜ ዔዋዌ ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ሶበ ትትሐወክ ነፍስየ እመንሱት በምሕረትከ ተዘከረኒ:: ካሥሩ ነገድ ከሁለቱ ነገድ ጥፋት የተነሣ ሰውነቴ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ ከነቢያት ተዳርጎ ይናገራል::

እንድም እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራህኩ:: አቤቱ ቀድሞ ሰብአ ትካትን ሰብአ ሰዶምን አጠፋሃቸው ሲሉኝ ሰማሁ ሰምቼም ፈራሁ::

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ:: ዛሬም የባቢሎንን ሰዎች ስታጠፋ አይቼ ሥራህን አደነቅሁ::

በማዕከለ ክልኤ እንስሳ ርኢኩከ:: በዳርዮስና በቂሮስ መካከል አየሁህ::

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አእምረከ:: ዘመነ ሚጠት ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ወከመ ከመ ይበጽሕ:: ጊዜ ሚጠት ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ሶበ ትትሀወክ ነፍስየ እመንሱት:: ከባቢሎናውያን ጥፋት የተነሳ ሰውነቴ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ: በትሩፋን ተጎብቶ ይናገራል::

እንድም እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራሕኩ:: አቤቱ ቀድሞ ከአብ ያለ እናት ተወለድክ ሲሉ ሰማሁ ሰምቼም ፈራሁ::

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ:: ዛሬም ከቅድስት ድንግል ያለ አባት ስትወለድ አይቼ ሥራህን አደነቅሁ::

በማዕከለ ክልዔ እንስሳ ርኢኩከ:: በአድግና በላህም መካከል በጎል ተጥለህ አየሁህ:: አስተማወቅዎ እስትንፋሰ አድግ ወላህም በመዋዕለ ቊር ወአስሐትያ እንዲል::

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አእምረከ:: ዘመነ ሥጋዌ ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ወዘመ ከመ ያበጽሕ:: ጊዜ ሥጋዌ ሳያደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ሰበ ትትሀወክ ነፍስየ እመንሱት:: ከአይሁድ ጥፋት የተነሳ ሰውነቱ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ:: በምእመናን ተገብቶ ያናገራል:: እንድም እግዚአ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራሕኩ:: አቡቱ ቀድሞ ዲዮብሱስ በክድ ጨለማ አጎናጽፈህ ዕመቀ ዕመቃት አወረድከው ሲሉ ሰማሁ:: ሰምቼም ፈራሁ::

ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ:: ዛሬ በመስቀል ድል ስትነሳው አይቼ ሥራህን አደነቅሁ::

በማዕከለ ክልኤ እንስሳ ርኢኩከ:: በፈያታዊ ዘየማንና በፈያታዊ ዘጸጋም መካከል ተሰቅለህ አየሁህ:: እንድም በዮሴፍና በኒቆዲሞስ መካከል ገንዘው መቃብር ሲያወርዱህ አየሁህ::

ከመ ከመ ይቀርብ ዓመቲሁ አእምረከ:: ጊዜ /ዘመነ/ ስቅለት ሳይቀርብ እንደቀረበ እንደቀረበ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ወዘመ ከመ ያበጽሕ:: ጊዜ ስቅለት ሳይደርስ እንደደረሰ እንደደረሰ አድርጌ አውቅሃለሁ::

ሰበ ትትሀወክ ነፍስየ እመንሱት:: ከአጋንንት ጥፋት የተነሳ ሰውነቱ በታወከች ጊዜ በቸርነትህ አሰበኝ: ከነፍሳት ተዳርጎ ያናገራል::

፫. እግዚአብሔርስ እምቴማን ይመጽእ:: እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል:: ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወእምአህጉረ ይሁዳ:: ከደብረፋራን ከአህጉረ ይሁዳ ይመጣል:: እነዚህ ሁሉ ቀድሞ ከግብጽ ሲወጡ ታምራት አድርጎባቸዋል:: ያን ጊዜ ታምራት ሲያደርግ እንደመጣ ዛሬም ታምራት ሲያደርግ ይመጣል:: እንድም እግዚአብሔርስ እንተ የማን ይላል:: በየማናዊ ኃይል ይመጣል:: እንድም ታምራት በሚያደርግበት በሥጋ ማርያም ይመጣል::

ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን ወእምአህጉረ ይሁዳ:: ከድንግል ይወለዳል ወደብረ ፋራን ዘዕንባቆም እንዲል:: ወእም አህጉረ ይሁዳ: ከነገደ ይሁዳ ይወለዳል: ይሁዳ ዕጓለ አንበሳ ተብሎ ከተነገረለት::

ከደነ ሰማያተ ሥኑ:: ሥኑ /ሥልጣኑ/ ሰማያትን ከደነ::



ወመልዐ ምድረ ስብሐቲሁ:: ጌትነቱ ምድርን መላ:: እንድም ሥልጣኑ ሰማይን ምድርን ፈጠረ:: የእስራኤል ልዑላኑን ትሑታኑን አስማረከ:: እንድም የባቢሎናውያንን ልዑላኑን ትሑታኑን አጠፋ:: እንድም የእስራኤል ልዑላኑ ትሑታኑን መለሰ::

<u>እንድም</u> ከደነ ሰማያተ ሥኑ:: በዕለተ ልደት መላእክት አመሰገኑት::

ወመልዐ ምድረ ስብሐቲሁ:: ኖሎት አመሰገኑ::

እንድም ከደኑ ሰማያተ ሥኑ:: በዕለተ ስቅለት ፀሐይ ጨለመ ጨረቃ ደም ሆነ ከዋክብት ረገፉ::

ወመልዐ ምድረ ስብሐቲሁ:: አዕባን ተፈተቱ: መቃብራት ተከፈቱ: ሙታን ተነሡ: መንጦላዕተ ቤተ መቅደስ ከሁለት ተከፈለ ኋላም ያሳልፋቸዋል::

፬. ወፀዳሉኒ ከመ ብርሃን ውእቱ:: ጸዳለ ረድኤቱ እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛል ኃጥእንን አጥፍቶ ለጻድቃን: አሰሩን ነገድ አስማርኮ ለሁለቱ ነገድ: ሁለቱን ነገድ አስማርኮ ለነቢያት ለካህናት: የባቢሎንን ሰዎች አጥፍቶ ለትሩፋን: አይሁድን አጥፍቶ ለምእመናን: አጋንንትን አጥፍቶ ለነፍሳት: ያደረገው ፀዳለ ረድኤቱ እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛል:: ፀዳልናሁ ቢል ብርሃንነቱ እንደ አብ ብርሃን ነው:: ብርሃን ዘእምብርሃን እንዲል::

አቅርንት ውስተ እደዊሁ:: አቅርንት በእጆቹ ተይዘዋል ማለት ሥልጣን የባሕርዩ ነው:: እንድም ስልምናሶር ናቡከደነፆር በሥልጣኑ ተጠብቀዋል:: አቅርንት አላቸው:: እስራኤልን ይቀጣባቸዋልና: እንድም ቂሮስ ዳርዮስ በሥልጣኑ ተጠብቀዋል አቅርንት አላቸው:: አሕዛብን ይቀጣባቸዋልና እንድም በሰውነቱ ሥልጣን የባሕርዩ ነው:: ቅንዋት በእጆቹ ተቸንክረዋል:: እንድም ሄኖክ ኤልያስ በሥልጣኑ ተጠብቀዋል::

ወረሰየ ፍቁረ በፅንዐ ኃይሉ: በፅኑዕ ኃይሉ ይላል:: በፅኑ ኃይሉ ወዳጅ አደረገ:: ኃጥእንን አጥፍቶ ጻድቃንን: አሥሩን ነገድ አስማርኮ ሁለቱን ነገድ: ሁለቱን ነገድ አስማርኮ ነቢያት

ካህናትን፡ የባቢሎንን ሰዎች አጥፍቶ ትሩፋንን፡ አይሁድን አጥፍቶ ምእመናንን፡ አጋንትን አጥፍቶ ነፍሳትን።

፰. ወየሐውር ቃል ቅድመ ገጹ። በፊቱ ቃል ይሄዳል ማለት ይማረኩ ብሎ ያዝዛል ይማረካሉ። ይውጡ ብሎ ያዝዛል ይወጣሉ። አንድም ዘሩባቤል ከባቢሎን በወጣ ጊዜ ሳንቲ ዛጉፍ ዲቦ አንበሳ /እምቢልታ ቀንደ መለከት ነጋሪት/ እያስመታ ወጥቷል። አንድም ቃለ ዓዋዲ ዮሐንስ በፊቱ ይሄዳል አለ። መንፈቅ ጸንስ መንፈቅ ማስተማር ይቀድመዋል። አንድም ቃለ ወንጌል ፀኤት ፊት ትንገራለች።
ወይወጽእ ውስተ ገዳም እምድኅረ እገሪሁ። በእገሪሁ በስልምናሶር በናቡከደነፆር አድሮ፡ ወደ እስራኤል ከተማ ይሄዳል።
ድኅረ እገሪሁ፡ እስራኤል ስልምናሶርን ናቡከደነፆርን ይከተላሉ ይማረካሉ። አንድም በእገሪሁ፡ በቂሮስ በዳርዮስ አድሮ ወደ አሕዛብ ከተማ ይሄዳል። ድኅረ እገሪሁ እስራኤል ቂሮስ ዳርዮስን ይከተላሉ አለ ይወጣሉ። አንድም በእገሪሁ፡ በእግሩ ከሲቶስጦራ ወደ ቀራንዮ ይሄዳል። እንደጌትነቱ ፈረስ ሳቡልኝ ሠረገላ ጥረቡልኝ አይልም። ድኅረ እገሪሁ ጻድቃን እሱን አብነት አድርገው ይመንናሉ። ተስቅለ አፍኣ እምትዕይንት እንዲል። ጥንቱን ከከተማ አፍኣ መስቀሉ እኔን አብነት /ምሳሌ/ አድርጋችሁ መንኑ ሲል ነውና። አንድም በእገሪሁ፡ በሐዋርያት አድሮ ወደ አሕዛብ ከተማ ይሄዳል። ድኅረ እገሪሁ፡ አሕዛብ ሐዋርያትን ይከተላሉ አለ ያምናሉ። አንድም በእገሪሁ በሄኖክ በኤልያስ አድሮ ወደ ሐሳዊ መሢሕ ከተማ ይሄዳል።

፱. ወሰበሂ ይቀውም ታድለቀልቅ ምድር። በመዓት በተነሳ ጊዜ ምድር ትናወጣለች። በዓዋዊ ኢየሩሳሌም፡ በሚጠት ባቢሎን፡ በዕለተ ዓርብ በቁሙ ኋላም ታልፋለች።
ወእመሂ ነጸረ ይትመሰዉ አሕዛብ። በዓይነ መዓት በተመለከተ ጊዜ አሕዛብ እንደሰም ይቀልጣሉ። በዓዋዊ ኢየሩሳሌም፡ /እስራኤል/ በሚጠት ባቢሎን /አሕዛብ/፡ በዕለተ ዓርብ አይሁድ፡ በምጽአት ኃጥአን።



ወይትቀጠቀጡ አድባር እምኃይሉ። ከኃይሉ የተነሣ ተራራዎች ይቀጠቀጣሉ አለ፡ የእስራኤል ነገሥታቱ ይማረካሉ።
ወይትመሰዉ መኳንንቱ ይማረካሉ።
አንድም ወይትቀጠቀጡ። የባቢሎናውያን ነገሥታቱ ይጠፋሉ ወይትመሰዉ መኳንንቱ ይጠፋሉ።
አንድም ወይትቀጠቀጡ። በዕለተ ዓርብ ሐና ቀያፋ በጿቱ ታምራት ይቀጠቀጣሉ።
ወይትመሰዉ፡ አውግር ዘእምዓለም። ሄሮድስ ጲላጦስ ድል ይነሣሉ ኋላም ያልፋሉ።
ወፍኖቶሂ ዘእምዓለም ርኢኩ። ዛሬም ይህን ዓለም እምኀበ ቦ ኀበ አልቦ ስታሳልፈው እንዳየሁ ቀድሞ እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ ፈጠርከው ሲሉ ሰማሁ። ዛሬ አሥሩን ነገድ ሁለቱን ነገድ ስታስማርክ እንዳየሁ ቀድሞም ፰፻ /ስድስት መቶ ሺሁን/ አጋር በምድረ በዳ እንደሻሽ እንጥፈህ እንደቅጠል አርግፈህ እስቀረሃቸው ሲሉኝ ሰማሁ፡ ዛሬ የባቢሎንን ሰዎች ስታጠፋ እንዳየሁ ቀድሞም ሰብአ ትካትን ሰብአ ሰዶምን አጠፋሃቸው ሲሉኝ ሰማሁ። ዛሬ ከድንግል ያለ አባት ስትወለድ እንዳየሁህ ቀድሞም ከአብ ያለ እናት ተወለድከ ሲሉኝ ሰማሁ። ዛሬ በመስቀል ድል ስትነሳ እንዳየሁህ ቀድሞም ዲያብሎስን ቢከድ ጨለማ አጎናጽፈህ ዕመቀ ዕመቃት አወረድከው ሲሉኝ ሰማሁ።

፲. <u>አዕፃዳተ</u> ኢትዮጵያ ይደነግጹ። የምድያም ነገሥታት ይደነግጣሉ።
እዕፃዳቲሆሙ ለብሔረ ምድያም። ምድያም ለማለት ደገመው። በላዕለ አፍላግስ ኢትትመዐዕ እግዚኦ። አቤቱ በአፍላግ በእስራኤል አንድ ጊዜ ብትፈርድባቸው ዘወትር አትፍረድባቸው አፍላግ ይላቸዋል፡ ፈሳሽ ውኃን እየተካፈሉ እንዲወስዱት እየማረኩ እየተካፈሉ ይወስዷቸዋልና።

፲፩. <u>ወኢይከን</u> መዓትከ በላዕለ አፍላግ። በአፍላግ በእስራኤል መዓትህ አይፅና

ወኢ መቅሠፍትከ ዲበ ባሕር። በእስራኤል ከተማ መቅሥፍትህ አይፅና።
እስመ ተፅዕንከ ዲበ አፍራሲከ። በሰልምናሶር በናቡከደነፆር አድረህ መጥተሃልና።
አፍራሲከኒ ሕይወት ውእቱ። ሰልምናሶር ናቡከደነፆር ሕይወት ናቸው። ለነቢያት ለካህናት። ሕያዋን ቢል እስከ ጊዜ ሞታቸው።
አንድም እስመ ተፅዕንከ ዲበአፍራሲከ። በቂሮስ በዳርዮስ አድረህ መጥተሃልና።
አፍራሲከኒ ሕይወት ውእቱ። ቂሮስ ዳርዮስ ሕይወት ናቸው። ለእስራኤል። ሕያዋን ቢል እስከ ጊዜ ሞታቸው።
አንድም እስመ ተጽዕንከ ዲበ አፍራሲከ። በሐዋርያት አድረህ መጥተሀልና አፍራሲከኒ ሕይወት ውእቱ። ሐዋርያት ሕይወት ናቸው ለምእመናን። ሕያዋን ቢል በነፍስ። አንድም እስመ ተጽዕንከ ዲበ አፍራሲከ። በኪሩቤል ላይ ተቀምጠሀልና።
አፍራሲከኒ። ኪሩቤል ሕይወት ናቸው አለ፡ ለፍጡራን። ሕያዋን ቢል የባሕርይ።

፱. ወተርክ ወወሰቀ ቀስተከ ዲበ አብትር ይቤ እግዚአብሔር። እስራኤል ይሆንልኛል መስሎህ? /መስሎሃል/? በአሕዛብ ቀስትህን ሳብክ ቀፈርክ።
ፈለግስ ይሠጥቃ ለምድር። ነገር ግን አንተ እንዳልከው አይደለም ፈለግ አሕዛብ ከተማህን ከፍሏት ያልፋል።
አንድም ወተርከ ወወሰቀ ቀስተከ ዲበ አብትር አሕዛብ ይሆንልኛል መስሎህ? በእስራኤል ቀስትህን ሳብክ ቀፈርክ ፈለግስ። ነገር ግን አንተ እንዳልከው አይደለም።
ፈለግስ ይሠጥቃ ለምድር። ፈለግ እስራኤል ከተማህን ከፍሏት ያልፋል።
አንድም ወተርክ። አሕዛብ ይሆንልኛል መስሎህ? በሐዋርያት ቀስትህን ሳብክ ቀፈርክ ፈለግስ ነገር ግን አንተ እንዳልከው አይደለም ፈለግ ሐዋርያት ከተማህን ከፍሏት ያልፋል።



፲. ይሬእዩከ ወይዔዐሩ አሕዛብ። አሕዛብ አይተውህ ይጻጸራሉ /ይቸገራሉ/ በዔዋዌ እስራኤል፡ በሚጠት አሕዛብ በምጽአት ኃጥአን፡
ወይዜክሩ ማየ በውስተ ፍኖት። በጎዳና ውሃ ያስባሉ በዔዋዌ ደርቆባቸው ነበር።
ወእሦጡ ቀሳውቲሆሙ ዕራቆ እንዲል። በሚጠት ፈልቆላቸው ጠጥተዋል። አንድም ወይዘረዉ ከመ ማይ ይላል። ቀድሞ ደርቆብን ነበር ዛሬ ግን ፈልቆልን ጠጣን አያሉ።
ወወሀበት ቀላይ ቃላ። ቤተ እስራኤል ቃሏን ሰጠች አለ። አመሰገነች
ወእልዐለት ግርማሃ። መፈራቷን አበዛች።

፲፩.ተንሥአ ፀሐይ ወወርኅ ወቆሙ በሥርዐትከ። ፀሐይ ጨረቃ ተፈጠሩ በሥርዓትህ ጸንተው ኖሩ። አንድም የእስራኤል ፀሐይ ሊቀ ካህናቱ ወርኀ ንጉሡ ተማረኩ። በዔዋዌ ጸንተው ኖሩ። አንድም የባቢሎን ፀሐይ ንጉሡ ወርኀ ቢትወደዱ ጠፉ በጥፋቱ ጸንተው ኖሩ። አንድም የእስራኤል ፀሐይ ሊቀ ካህናቱ ወርኀ ንጉሡ ተመለሱ በሚጠት ጸንተው ኖሩ። አንድም በዕለተ ዐርብ ፀሐይ ጨለመ ጨረቃ ደም ሆነ ወቆሙ በሥርዓትከ እስከ ጊዜ ቀትር። ወፍናሠርከ ይበርህ ብርሃነ ፀሐይ እንዲል። ኋላም ያልፋሉ።
በብርሃነ ማዕበልከ የሐውሩ። ዓረብ ቅራ ጭሆ /እንደተሳለ ሰይፍ/ በሆነ ረድኤትህ ጸንተው ይኖራሉ።
ወበፀዳለ መብረቅ ወልታከ። እንደ ፀሐይ ደስ በሚያሰኝ ጋሻ ረድኤትህ ጸንተው ይኖራሉ።

፲፪.በመዓትከ ውኅደት ምድር። በፈረድክበት ቀን ምድር አነሰች በዔዋዌ ኢየሩሳሌም፡ በሚጠት ባቢሎን፡ ኋላም ታልፋለች።
ወታጸድፎሙ ለአሕዛብ በመዓትከ። አሕዛብን ፈርደህ ታጠፋቸዋለህ።

፲፫.ወወጻእከ ለአድኅኖ ሕዝብከ። ወገኖችህን ለማዳን ወጣህ።
ከመታድኅኖ ለመሢሕከ። ይልቁንም ቀብተህ ያነገሥከው ዘሩባቤልን ታድነው ዘንድ ወጣህ።

<u>እንድም</u> ወወጻእከ ከመታድኅኖ ይላል:: ልጅህን ታስነሳው ዘንድ ወጣህ::
ለአድኅኖ ሕዝብከ:: **ወገኖችህን ሊያስነሳቸው ወጣ ድኂና እሞት አድኅኖሙ እንዲል::**
ወወደይከ ውስተ እርእስቲሆሙ ለኃጥአን ሞተ:: በኃጥአን ቸብቸቦ ሞትን አመጣህ::
ወእንሣእከ ማእሰረ ውስተ ክሣውዲሆሙ ለዝሉቱ:: ከአንገታቸው ዛንጅርን አነሣህ አለ:: አገዛዝን አጠፋህላቸው::

፲፬.<u>ወመተርከ</u> እርእስተ ኃያላን እንዘ በድንጋጼ ይላል:: በድንጋጼ ሳሉ የኃያላኑን ቸብቸቦ ቆረጥክ:: ወይትሐወኩ ባቲ:: በዚችም ያዝኑባታል እ ንድም ይትሐወኩ ባቲ:: ይ ታወኩባት ዘ ንድ የኃያላኑን ቸብቸቦ ቆረጥክ:: ምነው አንድ ብልጣሶር እይደለም ቢሉ ንጉሣዊ አነጋገር ከመዝ ይብሉክሙ ንጉሥ እንዲል:: እንድም እሱ ከሞተ በኋላ ብዙ ሰዎች አልቀዋልና::

<u>ታሪክ:-</u>

እነዚህ ቂሮስ ዳርዮስ ተሰለው ገጠሙ:: ብልጣሶርን ድል ብናደርግ እስራኤልን ነፃ እናወጣለን ቤተእግዚአብሔር እንሠራለን ብለው:: ሁለት ጊዜ ድል አደረጋቸው ስለምን ቢሉ ኃይል የባሕርያችን ነው ባሉ ነበርና::
እንድም ኋላ ድል የሚያደርግ በፊት ድል መሆን ልማድ ነውና:: እነዚህን ድል አድርጎ አዳራሽ ተገኘ:: ከመኳንንቱ አንዱ ዛሬ እንጂ እስራኤል ሳይረዱን ዋሉ /ቀኑ/ ልበ እበር /ግብረ እበር/ ቢሆኑ ነው አለ:: እስራኤል ቢረዱስ ምን ሊጠቅሙ ባይረዱስ ምን ሊጎዱ ብሎ ናቡከደነፆር የአምላክ ዕቃ ለአምላክ ነው ብሎ አክብሮ ንዋየ ቅድሳቱን ከቤተ ጣዖት አኑሮት ነበር ጥንቱንም አባቴ አጥፍቷል ብሎ አስመጥቶ በጽዋው ቀድቶ ጠጣበት አጠጣበት በጻሕሉ ፈትፍቶ በላበት አበላበት:: በዚህ ምክንያት ማኔ ቴቄል ፋሬስ እያለች እጅ ክታበን ስትጽፍ አይቶ /ታየች/ ይህን አንብቦ ተርጉሞ የሚነግረኝ ሲሶ መንግሥት እሰጠዋለሁ አለ:: የሚተረጉምለት
ጦዳ አዝኖ ሳለ የናቡከደነፆር ሚስት እያቱ ነበረችና ዛሬ



የልጇ ምሳ ተመለገነለት ይሆን? ብላ ጠየቀች: ምሳውስ ተመስግኖለት ነበር ነገር ግን እንዲህ ያለ ጽሑፍ ተገኝቶ አንብቦ ተርጉሞ የሚነግረው አጥቶ አዝኗል አሏት:: ሴት ችኩል ናትና ልብሷን /ልብሴን/ ልልበስ አላለችም ሄዳ ዛሬ ምሳው ተመለገነልህ? አለችው ምሳውስ ተመለግኖልኝ ነበር ነገር ግን እንዲህ ያለ ጽሑፍ ተገኝቶ አንብቦ ተርጉሞ የሚነግረኝ አጥቼ አላት:: ለዚህማ ምን ይቸግርሃል ለአያትህ ለናቡከደነፆር ርእሱ ዘወርቅን የተረጐመለት ዳንኤል አለ እሱን አታስመጣውም አለችው ዳንኤል ተጠርቶ መጣ ይህን አንብበህ ተርጉመህ ብትነግረኝ ሲሶ መንግሥት እሰጥሀለሁ አለው:: ዳንኤልም መፍቀሬ ሢመት አይደለምና ሹመቱም ላንተ ይሁን አንብቤ ተርጉሜ እነግርሃለሁ:: ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ እንዲሉ ለአዳም ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያለውን እንዳስገዛለት ለአባትህ ፱ቱን መዓዝን ቢያስገዛለት አነ ውእቱ ዘአሠርቅ ፀሐየ አለ:: በዚህ እስከ የአምር ልዑል ክመይኳንን መንግሥተ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ወለዘፈቀደ ይሁብ /ወይሁብ ለዘፈቀደ/ ይላል:: በጠለ ሰማይ ተነክሮ ሰባት ዓመት ዕሪያ ሆኖ ኖረ:: እንተኒ ብልጣሶር ወልዱ እንተም የአራቢ /የፋቂ/ ልጅ አጥባቂ የአበያ ልጅ ወዳቂ የዘማ ልጅ ሳቂ የትዕቢተኛ ልጅ ናቂ እንዲሉ: አባትህ የአምላክ እቃ ለአምላክ ነው ብሎ አክብሮ ያኖረውን አምጥተህ በጽዋው ቀድተህ ጠጣህበት አጠጣህበት በጻሕሉ ፈትፍተህ በላህበት አበላህበት በዚህ ተጸፎብሀል ንባቡ በዕብራይስጥ ነው ማኔ ቴቄል ፋሬስ ትርጓሜው በሱርስት ነው ማኔ ማለት ለፈራ እግዚአብሔር ለመንግሥትከ ወሠለጣ ቴቄል ማለት ደለዋ ለመንግሥትከ ወተረክበት ሕጸጸተ ፋሬስ ማለት ተሥዕረት መንግሥትከ ወተውህበት ለፋርስ ወለሜዶን ማለት ነው:: አለው ምንም ቢተረጉምበት አሕዛብ የተናገሩትን አያስቀሩምና ቢትወደድነት ጌትነት ሰጥቶታል:: ይህን ሲተረጉም የሰማ ነው ይላሉ ጠጅ አሳላፊውም ነው ይላሉ ሲበጠብጠው ውሎ ነበርና ሌላ ከሚመስገንበት እኔ ልመስገንበት ብሎ ክተኛበት ቸብቸቦውን

ቆርጦ ወስዶ ግዳይ /ምርኮ/ ጣለላቸው። አንተ ለጌታህ ያሳዘንክ ብለው ተቀብለው ገድለውታል።

ወይከሥቱ አፉሆሙ ከመ ዘይበልዕ ነዳይ በጽሚት። ሁለት ሦስት ቀን ጦሙን ያደረ ደሀ ቀስ ብሎ እንዲያዋውጥ ቀስ ብለው ይናገራሉ የንጉሥ ሞት ደርሶ በአፍአ አይነገርምና።

፲፭. አኤድከ ውስተ ባሕር አፍራሲከ። ስልምናሶር ናቡከደነፆርን በእስራኤል ከተማ አመላለስከ፡

እንዘ የሆምሩ ማያተ ብዙኃ። ይኸውም ውሃውን እያደፈረሱ ነው አለ እስራኤልን እየማረኩ /እያጠፉ/ ነው።

እንድም አኤድከ ውስተ ባሕር አፍራሲከ። ቂሮስ ዳርዮስን በአሕዛብ ከተማ አመላለስከ።

እንዘ የሐነምጉ ማያተ ብዙኃ። ይኸውም አሕዛብን እያጠፉ ነው። እንድም አኤድከ ውስተ ባሕር አፍራሲከ። ሐዋርያትን በአሕዛብ ከተማ አመላለስከ

እንዘ የጎምጉ ማያተ ብዙኃ ይኸውም አሕዛብን እያሳመኑ ነው።

፲፮.አስተሐየጽኩ ወደንገፀኒ ልብየ። ያህን ሁሉ ተመልክቼ ልቡናዬ ደነገጠብኝ።

እምቃለ ጸሎተ ከናፍርየ። ገለጽልኝ ብዬ ከጸለይኩት ጸሎት የተነሣ ለዚህ ብሎ ገብቶ ኑሯል ቢሉ አዎን። አንድም ለሴላ ከነባ ዘንድ ተገልጾለታል።

ወቦአ ረዓድ ውስተ አዕፅምትየ። በሰውነቱ ረዓድ እንቅጥቅጥ አደረ።

ወተሆምገ ኩሉ ፈቃድየ በመትሕቴየ። በሰውነቴ ውስጥ ያለ ልቡናዬ በኃዘን ደፈረሰ

ወአዐርፍ በዕለተ ምንዳቤየ። በመከራዬ ቀን አርፋለሁ።

ለዐሪግ ውስተ ሕዝበ ፍልስጥኤም። ወደ ፍልስጥኤም ለመውጣት መከራሃለሁና። ዐሪግየ ቢል ወደ ፍልስጥኤም ወጥቼ አርፋለሁ።

፲፯.<u>እስመ በለስኒ</u> ኢትፈሪ። በለስ አታፈራምና

ወኢይከውን ፍሬ ውስተ ዐጸደ ወይን። በወይን ቦታ ፍሬ አይገኝምና ትሔሱ ግብረ ዘይት። ዘይት ቅብዕነቷን ታብላለች



ወምድርኒ ኢትገብር ሲሲተ። ምድርም አዝርዕትን አትክልትን አታስገኝምና።

<u>ተጎጉሉ</u> አባግዕ እመብልዕ። እምተበልዖ ሲል ነው። አባግዕ ከመበላት ርቀዋልና የድርቅ በግ አይበላምና

ወአልህምትኒ ኢይትረከቡ በውስተ ጎል። አልህምት ከበረት አይገኙምና እንዲህ ያለ ጽኑ መከራ ይመጣልና ወጥቼ አርፋለሁ።

እንድም እስመ በለስኒ ኢትፈሪ። በለስ ዘይቤ ቤተ እስራኤል አሙንቱ እንዲል። እስራኤል ምግባር ሃይማኖት አያስገኙምና

ወኢይከውን ፍሬ ውስተ ዓፀደ ወይን። ዓፀደ ወይኑስ ለእግዚአብሔር እስራኤል አሙንቱ እንዲል። በእስራኤል ልቡና ምግባር ሃይማኖት አይገኝምና ትሔሱ ግብረ ዘይት። መምህራን አያስተምሩምና

ወምድርኒ ኢትገብር ሲሲተ። አርድእት አይማሩምና ተጎጉሉ አባግዕ እመብልዕ። እስራኤል ከመሥዋዕትነት ርቀዋልና አለ ደስ ከማሰኘት።

ወአልህምትኒ ኢይትረከቡ በውስተጎል። መምህራን በጉባኤ አይገኙምና እንዲህ እንዲህ ያለ ጽኑ መከራ ይመጣልና ወጥቼ አርፋለሁ።

፲፰.አንስ እትፌሣሕ በእግዚአብሔር። ስለነዚያ /ስነዚያ/ ነው እኔ በእግዝአብሔር እምኚ ደስ ይለኛል።

ወእትሐሠይ በአምላኪየ ወመድኃንየ። በፈጣሪዬ በመድኃኒቴ እምኚ ደስ ይለኛል።

፲፱.እግዚአብሔር አምላኪየ ወኃይልየ። እግዚአብሔር ፈጣሪዬ ኃይሌ ዘይሠርዖን ለእገርየ ወለፍጻሜየ። እግሮቼን ፈጽሞ የሚያቅናናቸው /የሚያቀናቸው/ እሱ ነው።

ወዲበ ልዑላት ያጼዕነኒ። በኃያላኑ ላይ ያሠለጥነኛል። ፭ቱን ነገሥተ ፍልስጥኤም ይዞ፡ ፬ቱን ነገሥተ አሕዛብን ፬ቱን ነገሥተ ፍልስጥኤም ይዞ አምስቱን ነገሥተ አሕዛብ ድል አድርጓል።

ከመ እማዕ በመኃልይሁ። እሱን በማመስገን ድል እነሳ ዘንድ በፍኖቱ ቢል ሕጉን በመጠበቅ ድል እነሣ ዘንድ።

## ፲፪. ጸሎተ ኢሳይያስ ነቢይ

ኢሳይያስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው:: ኢያሱ ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት እንደሆነ:: ይኸውም መድኃኒት መባሉ እንደ ኢያሱ ባጭር ታጥቆ ዘገር ነጥቆ የእስራኤልን ጠላት አጥፍቶ እንደ ጌታ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ዓለምን አድኖ አይደለም:: መክሮ አስተምሮ ነው:: ይህን ስሙንም እናት አባቱ በ፫ ቀን ኢሳይያስ ብለውታል:: <u>አንድም</u> ነቢያት ካህናትን ማን እንበለው ብለዋቸው መክሮ አስተምሮ መድኃኒት እንዲሆን ተገልጾላቸው ኢሳይያስ በሉት ብለዋቸዋልና ኢሳይያስ ብለውታል:: <u>አንድም</u> ቅቡዕ እምቅብዓ ትንቢት ማለት ነው:: በዚህ በተሰጠው ትንቢቱ ሕዝቡ በሕገ ሲና አሕዛብ በሕገ ልቡና ረብህ ጥቅም እንዳላገኙ ሲያጠይቅ በእስራኤል ፫: በአሕዛብ ፬: ነገር ይናገራል:: በእስራኤል ሦስት ነገር:: አባር ቸነፈር: ዒዋዌ ሚጠት:: እሊህ ሦስቱ ሥጋውያን ለሦስቱ መንፈሳውያን አምሳል መርገፍ ናቸው:: እንደአባር ቸነፈር ርኃቅ እምእግዚአብሔር: እንደ ዒዋዌ ዒዋዌ ነፍስ: እንደሚጠት ሚጠተ ነፍስ: ዒዋዌ ሚጠት አንድ ወገን ነው ብሎ: ሦስተኛ ሥጋዌወልደእግዚአብሔርን ተናግሯል:: በአሕዛብ አራት: ትእምርት አፍርሆ:: ትእምርት አሕዛብን ሲያጠፉ አይተው እስራኤል ምልክት ያደርጋሉ አፍርሆ ሕግ ያልሠራላቸው አሕዛብን እንዲህ ሲያደርግ እኛን እንዴት ያደርገን ብለው ይፈራሉ: ሦስተኛ አምላካችን አይደለም ይላሉ የግድ አምላካቸው እንደሆነ:: አራተኛ በደባያት /በወንፈል በተራ/ እንዲጠፉ:: ትእምርትና አፍርሆ ይጎራበታሉ ብሎ:: ሁለተኛ አምላካችን አይደለም ይላሉ:: የግድ አምላካቸው እንደሆነ:: ሦስተኛ በደባያት እንዲጠፉ:: አራተኛ ሳያናግር /ሳይናገር/ እንዳያጠፋ ሠረይነ ሰብአ ወኢያሕየውነ /ወኢያሕዮነ/ ፈወስናሃ ለባቢሎን ወኢተፈወሰት እያሉ:: ይህ ሲነበብ ሲተረጐም ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ደረሰ ሐዋርያትም ፹፩ መጻሕፍትን ቆጥረው ለቀሌምንጦስ ሲሠጡ አንድ መጽሐፈ ኢሳይያስ ብለው ቆጥረዋል:: ይህም ለከንቱ የተጻፈ አይደለም:: እኛ ልንመከርበት ልንገሠጽበት ነው እንጂ:: ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጸ ዚአነ



ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ እንዲል:: ይህ ተራው ከሕዝቅያስ ነው:: የእመቤታችን ባለሟል እንደሆነ ለማጠየቅ ከዚህ አምጥተው ጠርዘውታል:: ኢሳይያስ የተናገረው ነገር ይህ ነው::

፩. <u>በሌሊት</u> ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ እግዚኦ አምላኪየ:: አቤቱ ፈጣሪዬ በሌሊት ልቡናዬ በጸሎት በአምልኮት ወደአንተ ትገሠግሣለች::

እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር:: በመንፈቀ ሌሊት ተነሥታችሁ አመስግኑ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና ጨለማ አይከለክለውምና::

<u>አንድም</u> በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ እግዚኦ አምላኪየ:: ሕዝቅያስ ነው በሌሊት መከራ ተይዤ ሳለሁ ልቡናዬ በጸሎት በእምልኮት ወደአንተ ትገሠግሣለች::

እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር:: ሕዝቅያስ ያዳን ሠናክሬም ይጥፋ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና እንደብርሃን ደስ ያሰኛልና::

<u>አንድም</u> በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ እግዚኦ እምላኪየ:: ትሩፍ ነው:: ፸ ዘመን ልቡናዬ በጸሎት በአምልኮት ወደአንተ ትገሠግሣለች:: እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር:: ትሩፋን ይዳኑ ባቢሎናውያን ይጥፉ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛልና::

አንድም በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ እግዚኦ አምላኪየ:: አዳም ነው አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን ልቡናዬ በአምልኮት ወዳንተ ትገሠግሣለች::

እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር:: ነፍሳት ይዳኑ አጋንንት ይጥፉ ያልከው ትእዛዝህ ብርሃን ነውና እንደ ብርሃን ደስ ያሰኛልና::

ተመሐሩ ጽድቀ ጽድቅ እለ ትነብሩ ውስተ ዓለም:: በዚህ ዓለም የምትኖሩ እስሩ ነገድ ሁሰቱ ነገድ ጽድቅን ተማሩ::

፪. <u>እስመ ኀልቀ</u> ኀጥእ ዘኢይትሜህር ጽድቀጽድቅ በዲበ ምድር:: በዚህ ዓለም በጎ መሥራትን የማይማር

ወኢይገብር ሠናየ:: በጎ ሥራ የማይሠራ ስድስት መቶ ሺህ አጋር በምድረበዳ እንደሻሸ ተነጥፎ እንደ ቅጠል ረግፎ ቀርቷልና::

<u>አንድም</u> ተመሐሩ ገቢረጽድቅ እስ ትነበሩ ውስተ ዓለም:: በዚህ ዓለም የምትኖሩ እስ ሕዝቅያስ ገቢረ ጽድቅን ተማሩ::

እስመ ኀልቀ ኀጥእ ዘኢይትሜሀር ገቢረ ጽድቅ በዲበ ምድር:: በዚህ ዓለም በጎ መሥራትን የማይማር

ወኢይገብር ሠናየ:: በጎ ሥራ የማይሠራ ሰናክሬም ጠፍቷልና::

<u>አንድም</u> ተመሀሩ ገቢረጽድቅ እለ ትነብሩ ውስተ ዓለም:: ትሩፋን ገቢረ ጽድቅን ተማሩ:: እስመ ኀልቀ ኀጥእ ዘኢይትሜሀር ገቢረ ጽድቅ በዲበ ምድር:: በዚህ ዓለም በጎ መሥራትን የማይማር

ወኢይገብር ሠናየ:: በጎ ሥራን የማይሠራ ብልጣሶር ጠፍቷልና::

<u>አንድም</u> ተመሀሩ ገቢረ ጽድቅ እስ ትነብሩ ውስተ ዓለም:: ምእመናን ገቢረ ጽድቅን ተማሩ::

እስመ ኀልቀ ኀጥእ ዘኢይትሜሀር ገቢረ ጽድቅ በዲበ ምድር:: በዚህ ዓሰም በጎ መሥራትን የማይማር

ወኢይገብር ሠናየ:: በጎ ሥራን የማይሠራ ዲያብሎስ በመስቀል ድል ተነስቷልና::

<u>የእትትዎ</u> ለኀጥእ:: አሥሩን ነገድ በዔዋዌ ያርቁታል::

ከመ ኢይርአይ: ስብሐተ እግዚእብሔር:: ስሁስቱ ነገድ የተደረገውን ታምራት እንዳያይ:: <u>አንድም</u> የእትትዎ ለኃጥእ:: ሠናክሬምን ከለኪሶን ያርቁታል::

ከመ ኢይርአይ ስብሐተ እግዚእብሔር:: እለ ተቀዋመ ወርቅን እለ ማዕጠንተ ወርቅን እንዳያይ <u>አንድም</u> እበውን በሞት ያርቁታል::

ከመ ኢይርአይ:: ስውሉድ የተደረገውን ታምራት እንዳያይ::

<u>አንድም</u> የእትትዎ ለኀጥእ:: ይሁዳን ከደብረ ታቦር ያርቁታል::



ከመ ኢይርአይ:: ብርሃን መለኮቱን እንዳያይ:: ምነው ቆቴስ ቀርተው የለም ቢሉ ስምንቱ ቅሉ የቀሩ በሉ ምክንያት ነውና:: <u>አንድም</u> ሥላሴ ኀጥእን <u>በሐሩታ</u> ያርቁታል:: ከመኢይርአይ ኢይረስ ይላል:: ክብሩን እንዳይወርስ ኢይሬእያ ያለውን ኢይወርሳ ብሉ እንደተረጎመው::

፫. <u>እግዚኦ ልዑል</u> መዝራዕተከ ኢያእመሩ:: አቤቱ አስሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ልዑል ሥልጣንህን አላወቁም

እምከመሰ አእመሩ ይትሐፈሩ:: ስልሳውን እልፍ አጋር በምድረ በዳ እደሻሽ አንጥፎ እንደቅጠል አርግፎ አስቀራቸው ቢሉ እየሰሙ ምነው አያውቁም ትሰኝ እንደሆነ ካወቁማ /ስ/ ያዋቂ አጥፊ ናቸውና ይጥፉ::

አንድም እግዚኦ ልዑስ መዝራዕተከ ኢያእመሩ:: አቤቱ የባቢሎን ሰዎች ልዑል ሥልጣንህን አላወቁም::

እመከመሰ አእመሩ ይትሐፈሩ:: ሰብአ ትካትን ሰብአ ሰዶምን አጠፋህ ሲሉ እየሰሙ ምነው አላወቁ ትለኝ እንደሆን ካወቁስ /ማ/ ያዋቂ በዳይ ናቸው: ይጥፉ

እግዚኦ ልዑስ መዝራዕተከ ኢያእመሩ:: አቤቱ አብ አይሁድ ልዑል ልጅህን የባሕርይ አምላክ እንደሆነ እላወቁም ::

ከልሙፅ ግንባር /ከደረቅ ግንባር/ ዓይን ሲፈጥር የአራት ቀን ሬሳ ሲያስነሳ እያዩ ምነው አያውቁ ትሰኝ እንደሆን ካወቁስ እዳለፈው::

አንድም እግዚኦ ልዑስ መዝራዕተከ ኢያእመሩ:: አቤቱ ወልድ አይሁድ ልዑል ሥልጣንህን አላወቁም::

እምከመሰ እአመሩ ይትሐፈሩ:: በልሙፅ ግንባር ዓይን ሲፈጥር የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን ሲያስነሳ እያዩ ምነው አያውቁ ትለኝ እንደሆን ካወቁስ እንዳለፈው::

ቅንዓት አኀዞሙ ለሕዝብ አብዳን:: ስነፎች ወገኖችን ቅናት ያዛቸው በዔዋዌ እስራኤልን: በሚጠት እሕዛብን: በዕለተ ዓርብ አይሁድን: በዕለተ ምጽአት ኃጥአንን::

ወይእዜኒ እሳት ትበልዖሙ ለፀር:: አሁንም ጠላቶችህን መቅሠፍት ታጠፋቸዋለች::

፲፪. እግዚኦ አምላክነ ሰላመ ሀበነ:: አቤቱ ፈጣሪያችን ፍቅር አንድነትን ስጠን::
እስመ ኵሉ ወሀብከነ መከራውን ሁሉ አምጥተህብናልና::

፲፫. እግዚኦ አምላክነ አጥርየነ:: አቤቱ ወገኖችህ አድርገን
እግዚኦ ዘእንበሌከ ባዕደ ኢነአምር:: አቤቱ ያለ አንተ ልዩ ጣዖትን አናውቅምና::
ወስመ ዚአከ ንጼውዕ:: ስምህንም በጸሎት በአምልኮት እንጠራሰን::

፲፬. ሙታንሰ ኢይሬእይዋ ለሕይወት:: ሙታን ልቡና እሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ሕይወትን አያይዋትም::
ወዓቅበተ ሥራይኒ ኢያንሥኦ:: ነቢያተ ሐሰት አንተ የገደልከውን ማዳን /ማንሳት/ አይቻላቸውምና::
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ:: ስለዚህ ነገር ስልምናሶርን ናቡከደነፆርን አምጥተህ አጠፋህቸው::
አንድም ሙታንሰ ኢይሬእይዋ ለሕይወት:: መታን ሕሊና /ልቡና/ እሰ ሠናክሬም ሕይወትን አያይዋትም::
ወዓቀብተ ሥራይኒ ኢያንሥኦ:: ካህናተ ጣዖት አንተ የገደልገውን ማዳን አይቻላቸውምና
በእንተዝ:: ስለዚህ ነገር ስልምናሶርን ናቡከደነፆርን አምጥተህ አጠፋሃቸው አንድም ሙታንሰ ኢይሬእይዋ ለሕይወት:: ሙታን ሕሊና እሰ ሠናክሬም ሕይወትን አያዩዋትም::
ወዓቀብተ ሥራይኒ ኢያንሥኦ:: ካህናተ ጣዖት አንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውምና
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ:: ስለዚህ ነገር ቅዱስ ሚካኤልን አምጥተህ አጠፋሃቸው አንድም ሙታንሰ ኢይሬእይዋ ለሕይወት:: የባቢሎን ሰዎች ሕይወትን አያይዋትም:: ወዓቀብተ ሥራይኒ ኢያንሥኦ:: ካህናተ ጣዖት አንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውም::
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ:: ስለዚህ ነገር ቂሮስ ዳርዮስን አምጥተህ አጠፋሀቸው:: አንድም ሙታንሰ ከሥጋቸው የተለዩ ነፍሳት አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን ሕይወተ ነፍስን አያይዋትም



ወዓቀብተ ሥራይኒ ኢያንሥኡ:: ነቢያተ ጽድቅ ስብ አጢሰው ደም አፍስሰው አንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውም::
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ: ሎሙ ይላል:: ስለዚህ ነገር አምላኪየ አምላኪየ ብሰህ ጸልየህ ዲያብሎስን አቅርበህ ድል ነሣሀቸው::
አንድም ሙታንሰ ኢይሬእይዋ ለሕይወት:: ሙታነ ልቡና አይሁድ ሕይወት ወልድን አያዩትም:: ወትፈትዉ አሐተ ዕለተ እመዋዕሊሁ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው እንዲል ወየው ከፃፎቱ ዘመን እንዲቱን ቀን አግኝተናት ብለዋል::
ወዓቀብተ ሥራይኒ ኢያንሥኡ:: ካህናተ ኦሪት አንተ የገደልከውን ማዳን አይቻላቸውም::
በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእኮሙ:: ስለዚህ ነገር ጥጦስ እስባስያኖስን አምጥተህ አጠፋሀቸው::
ወአእተትከ ኵሎ ትዕቢቶሙ:: ትቢታቸውን ሁሉ አራቅህ
ወስኮሙ እግዚኦ እኪተ:: አቤቱ በመከራ ላይ መከራ አምጣባቸው::

፲፭. ወስኮሙ እግዚኦ እኪተ ለክቡራን ምድር:: ክቡራን ምድር በሚሆኑ በነዚህ በመከራ ላይ መከራ አምጣባቸው:: ክቡራን ምድር ይሳቸዋል:: በወዲያው ዓለም ክብር የላቸውምና::

፲፮. እግዚኦ በምንዳቤየ ተዘከርኩከ:: አቤቱ በመከራዩ ጊዜ አሰብኩህ ወበኀዳጥ ሕማም ገሠጽከኒ:: በጥቂት መከራ ገሠጽከኝ::

፲፯. ከመእንተውስተማሕምም እንተእልጸቀት ለወሊድ:: ለመውሰድ የቀረበች ሴት እንድትጨነቅ
ወአውየወት በሕማማ:: በምጧ ጊዜ እንድትጮህ
ከማሁ ኮነ ለፍቁርከ::
ከማሃ ኮነ ለፍቁርከ:: ለወዳጅህ ለሕዝቅያስ ተጨነቅንለት አንድም ከማሃ ኮነ ፍቁርከ:: ወዳጅህ ሕዝቅያስ እንደሷ ተጨነቀ:: አንድም ከማሃ ኮነ ለፍቁርከ:: ለወዳጅህ ለትሩፍ እንደሷ ተጨነቅንለት::
ከማሃ ኮነ ፍቁርከ ወዳጅህ ትሩፍ እንደሷ ተጨነቀ አንድም ከመሃ ኮነ ለፍቁርከ:: ለወዳጅህ ለአዳም አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን እንደሷ ተጨነቅንለት:: አንድም ከማሃ ኮነ

ፍቁርከ፡ ወዳጅህ አዳም እምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን እንደሷ ተጨነቀ።

፲. <u>በእንተ ፈሪሆትከ</u> እግዚኦ ጸነስነ። እምልኮትህን ስለጣልን /ስላልጠበቅን/ ዒዋዌ አለ ሲሉ ሰማን።
ሐመምነዊ ወወለድነ። በአባር በቸነፈር ተያዝን ዒዋዌ አገኘን።
<u>አንድም</u> በእንተ ፈሪሖትከ እግዚኦ ጸነስነ። እምልኮትህን ስለጠበቅን ሚጠት አለ ሲሉ ሰማን።
ሐመምነዊ። ስባ ዘመን በመከራ ተያዝን
ወወልድነ። ሚጠትን አገኘን <u>አንድም</u> በእንተ ፈሪሖትከ እግዚኦ ጸነስነ እምልኮትህን ስለጣልን ዒዋዌ ነፍስ አለ ሲሉ ሰማን
ሐመምነዊ። ርኀቀ እም እግዚአብሔር አገኘን።
ወወለድነ። ዒዋዌ ነፍሰ አገኘን። አንድም በእንተ ፍሪሆትከ፡ አምልኮትህን ስለጠበቅን ሚጠተ ነፍስ አለ ሲሉ ሰማን።
ሐመምነዊ። እምስት ሺ ከአምሰት መቶ ዘመን በመከራ ነፍስ ተያዝን ወወለድነ። ሚጠተ ነፍስ አገኘን።
መንፈስ አድኅኖትከ በዲበ ምድር። ትድግናህን የምትፈጽምበት ረድኤትህ በዚህ ዓለም ለምእመናን ይደረግ።

፲፩. <u>ሙታን</u> ይትነሥኡ። ሙታን ይነሣሉ ሁሰቱ ነገድ
ወየሐይዉ እለ ውስተ መቃብር። እሰሩ ነገድ
ወይትፌሥሑ እለ ውስተ ምድር። ስልምናሶር ናቡከደነጾር መጣ መጣ ሲሏቸው ሰምተው ሸሽተው የሔዱት። ወይነግሩ ሠናይቶ ለእግዚአብሔር ለደስያት ወለግብጽ የሚላቸው።
እሰመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ። ካንተ የተገኘ ጠለ ረድኤት ሕይወታቸው ነውና።
<u>አንድም</u> ሙታን ይትነሥኡ። ሙታን አለ ሕዝቅያስ ይነሣሉ።
ወየሐይዉ እለ ውስተ መቃብር። በለኪሶን ያሉት
ወይትፌሥሑ እለ ውስተ ምድር። ሠናክሬም መጣ መጣ ሲሏቸው ሸሽተው የሄዱት
እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ። ካንተ የተገኘ ጠለ ረድኤት ሕይወታቸው ነውና።
<u>አንድም</u> ሙታን ይትነሥኡ፡ እንደ ወልደ መበለት እንደ ወለተ ኢያኢሮስ ያሉት ይነሣሉ።



ወየሐይዉ እለውስተ መቃብር። እንደ አልዓዛር ያሉት
ወይትፌሥሑ እለ ውስተ ምድር። ድውያን ደስ ይላቸዋል።
እንድም እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ። ካንተ የተገኘ ጠል ወልድ ሕይወታቸው ነውና።
አንድም ሙታን። በራሳቸው ፍዳ የተያዙት
ወየሐይዉ። በራሳቸው ፍዳ ላይ በእናት ባባታቸው ፍዳ የተያዙት
ወይትፌሥሑ እለ ውስተ ምድር። ምእመናን ደስ ያላቸዋል።
እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ። ካንተ የተገኘ ጠል ወልድ ሕይወታቸው ነውና።
እንድም ሙታን ይትነሥኡ። ያልተቀበሩት ይነሣሉ እንደ አርማጌዶን /የጥፋትና የጦርነት ቦታ/።
ወየሐይዉ እለ ውስተ መቃብር። የተቀበሩት ይነሳሉ።
ወይትፌሥሑ። ገብር እምግብር ተሰውጠው /ወዲያው አርፈው የሚገቡት/።
ንሕነሰ ንትዌለጥ በምዕር ከመ ቅጽበተ ዓይን ወኢንበጽሖሙ ለምዉታን የሚላቸው።
እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ። ካንተ የተገኘ ጠል ሕይወታቸው ነውና። በዕለተ ምጽአት ጠለ ምሕረት አለ። የሚያርከፈከፍ /የሚያከፈከፍ/።
ወታጠፍዕ ምድሮሙ ለኀጥአን። የኀጥእን ምድራቸውን ታጠፋለህ። በዒዋዌ ኢየሩሳሊም፡ በሚጠት ባቢሎን፡ ኋላም ሀገረ ነፍሳቸውን ታጠፋለህ።

፲፪. ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ። ወገኔ ሁለቱ ነገድ ወደ ቤትህ ግባ።
ወዕፁ ኆኅተከ። ደጅህን ዝጋ።
ወተኀባዕ ኀዳጠ ምዕረ። ጥቂት ሰዓት ተሠወር ለእስሩ ነገድ እረዳለሁ አትበል።
እስከ የኀልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር። የእግዚአብሔር መዓቱ በእስሩ ነገድ እስኪያልፍ ድረስ። እግዚአብሔር ለፈረደበት ሰው እረዳለሁ ማለት መከራው ይትረፈኝ ማለት ነውና።
<u>አንድም</u> ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ። ወገኔ ሕዝቅያስ ወደ

ቤትህ ግባ፡፡ ወዕፁ ኖኀተከ፡፡ ደጅህን ዝጋ፡፡ ወተኀባዕ ኀዳጠ ምእረ፡፡ ጥቂት ሰዓት ተሠወር ከሰናክሬም ጋር እዋጋለሁ አትበል

እስከ የኀልፍ፡፡ የእግዚአብሔር መዓት በሰናክሬም እስከሚያልፍ ድረስ

<u>አንድም</u> ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ፡፡ ወገኔ ምእመን ወደ ቤተ ልቡናህ ግባ

ወዕፁ፡፡ ህዋሳትህን ሰብስበህ ጸልይ

ወተኀባዕ ኅዳጠ ምእረ፡፡ ጥቂት ሰዓት ተሠወር

እስከ የኀልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር፡፡ የእግዚአብሔር መዓቱ ይህ ዓለም እስኪያልፍ ድረስ፡፡ መዓት አለው ያህን ዓለም፡፡ መዓቱም ምሕረቱም የሚደረግ /መደረጉ/ በዚህ ዓለም ነውና፡፡

## ፲፫. <u>ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም</u>

ማርያም ማለት ጸጋ ወሀብት ማለት ነው፡፡ ለጊዜው ለእናት ለአባቷ ጸጋ ሀብት ሆና ተሰጥታለች፡፡ ለኋላው ግን ላመነባት ሁሉ ጸጋ ክብር ታሰጣለችና፡፡ <u>አንድም</u> ፍጽምት ማለት ነው፡፡ ለጊዜው መልክ አቀናን ከደም ግባት ጋራ አስተባብራ ይዛ ተገኝታለች ለኋላው ግን ድንጋሌ ሥጋ ከድንጋሌ ነፍስ አስተባብራ ይዛ ተገኝታለችና፡፡ <u>አንድም</u> ልዕልት ማለት ነው፡፡ መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ናትና፡፡ ወአልቦ ዘይከብር እምኔሃ እምታሕተ እግዚአብሔር እንዲል፡፡ <u>አንድም</u> ተለአኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማለት ነው፡፡ ሰውንና እግዚአብሔርን የምታስታርቅ፡፡ ወእምጽኡ ማሬ ዘድዮስ እንዲል፡፡ ተፈሥሒ ቤተ ይሁዳ ወተሐሠዪ ቤተ እስራኤል፡ በሷ መወለድ እስሩን ነገድ ሁለቱን ነገድ ደስ ብሏቸዋልና፡፡ <u>አንድም</u> መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው፡፡ ያመነባትን ሁሉ አስከትላ ፊታውራሪ ሆና ይዛ ገነት መንግሥተ ሰማያት ታገባለችና /ታስገባለችና/ አንድም ማኀበረ ማሃይምናን ወመሃይምናት ማለት ነው፡፡ ሕዝቡን አሕዛቡን አንድ የምታደርግ <u>አንድም</u> ፀሐይ ማለት ነው፡፡ አስቴር ማለት ፀሐይ ማለት እንደሆነ ሠረገላ ፀሐይ ማለትም ነው፡፡ ማሪሃም የሚል አብነት ይገኛል፡፡ እመ ብዙኃን እግዝእተ ብዙኃን



ማለት ነው፡፡ አብርሃም ማለት አበ ብዙኃን ማለት እንደሆነ ይህስ እንደምን ነው ቢሉ፡፡

### <u>ታሪክ፡-</u>

ሐና ኢያቄም የሚባሉ ባልና ሚስት ነበሩ ልጅ አልነበራቸውም ልጅ ባለመውለዳቸው ያዝኑ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ቤተ እግዚአብሔር ደጅ ለመጽናት /እጅ ለመንሳት/ ከሄዱ ዘንድ ወርእዩ አርጋበ እንዘ ይትፌሥሑ በውስቴቶሙ ይላል፡፡ አርጋብ በልጆቻቸው ተድላ ደስታ ሲያደርጉ አይተው ሁሉ እንዲህ ይበዛል የኛን ተፈጥሮ ከደንጊያ አድርገኸዋል? ብለው አዘኑ ራእይ ያያሉ ለሷ የብርሃን መቀነት ሲሰጧት ለእሱ የብርሃን መቋሚያ ሲሰጡት፡፡ ተሰለው ይሄዳሉ ወንድ ቢሆን እኛን ይርዳን ያጥባን ያገልግለን እንልም ሴትም ብትሆን እኛን ትርዳን ታጥባን አንልም መሶበ ወርቅ ሰፍታ ግምጃ ፈትላ ለቤተእግዚአብሔር ታገለግላለች ብለው ተስለው ወጡ፡፡ ወአእመራ ለሐና ይላል፡፡ በግብር አወቃት አመቤታችን ተጸነሰች ተወለደች በተወለደችም ጊዜ ነዳያንን ምስኪናንን ጠርተው ምሳ አድርገዋል፡፡ በተወለደች በሦስት ዓመት ይህችን ሕፃን ተስለን ወልደናታል ዘመድ ሳትወድ እህል ሳትለምድ እንስጥ ብለው ሄዱ ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ነበር ተቀበለን አሉት የስእለት ልጅ እኔ ለብቻዬ እንዴት እቀበላለሁ መጥቅዕ ይመታ ሕዝቡ ይሰብሰቡ የምግቧ ነገር ይመከር እንጂ አላቸው፡፡ ከዚህ መሀል ያች ሕፃን ተራበች መልአኩ ፋኑኤል ኅብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ ይዞ መጣ ዘካርያስ ዛሬስ ክብሬን ባደባባይ ሊገልጽልኝ ነው ብሎ ሊቀበል ተነሣ ወደ ላይ ለቀቀበት /ራቀበት/ ሐና ልትቀበል ተነሣች ወደ ላይ ለቀቀባት /ራቀባት/ የጌታ ነገር አይታወቅም ይህችን ሕፃን ትታችኋት ፈቅ በሉ አላቸው፡፡ ትተዋት ፈቅ አሉ /ቢሉ/ አንድ ክንፉን አከናንቦ /አጎናጽፎ/ አንድ ክንፉን አንጥፎ አብልቷት አጠጥቷት ዓረገ፡፡ እኛ መጥቅዕ ይመታ ሕዝቡ ይሰብሰቡ ያልን ለምግቧ ነበር፡ ጌታ የማይጨርሰውን ይጀምራል? ምግቧ ሰማያዊ ከሆነ አግቡታችሁ ከቤተመቅደስ አኑሯት አለ፡፡ ፲፪ ዓመት ዕልተርቢዝ ዕልተግቢጥ /የዘመድ ፍቅርና ልማደ ሰብእ/ ጠፍቶላት ኖራለች፡፡ ጥንቱንም ኑሮባት አይደለም ከእናት ከአባቷ ቤት ፫ ዓመት ከቤተ

መቅደስ ፲፪ ዓመት ፲፭ ዓመት ሲሆናት ካህናቱ ተሰብስበው ልማደ አንስት አላት /ያለባት/ መስሏቸው ይህች ሕፃን አቅመ ሔዋን አደረሰች ቤተ መቅደስ ታስተራኩሳለች /ታሳድፋለች/ ብለው (ሳቲ ስብሐት) ሄደው ታገቢ በድንግልና ትኖሪ አሏት:: እንደእላችሁኝ አንጂ አለቻቸው /አለች/ እንዲህ ማለቷ እንኳን ገቢር ኀልዮ ኑሮባት አይደለም ፈጻሚተ ፈቃድ ናትና:: እነሱም እኛማ ከሕገ እንስሳ ሕገ ሰብእ ከሕገ ሰብእ ሕገ መላእክት እንዲበልጥ አናውቅ የለም? በንጽሕና ልትኖሪ /ብትኖሪ/ እንወዳለን አሏት:: ካላችሁስ ስንኳን ገቢር ኀልዮ የለብኝም አለቻቸው:: የዚች ሕፃን ነገር ከንቱ የሚቀር አይደለም ልብሰ ተክህኖ ለብሰህ ዕጣን አጥነህ ቃለ እግዚአብሔር ጠይቀህ ንገራት አሉት:: ዘካርያስም ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ዕጣን አጥኖ ቃለ እግዚአብሔር ቢጠይቅ ከቤተ ይሁዳ ሚስቱ የምትችበትን ሰው በትር ሰብስብ ከበትሩ ምልክት የተገኘበት ይጠብቅ አለው ለሁለት ሺህ አሥራ አምስት የጎደለው (አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አምስት) በትር ተሰበሰበ:: አራት ሺህም የሚል አለ:: በነረ ማርያም:: ሞተ አንስት የበዛበት ወራት ነውና /ነበርና/ ኋላ ከዮሴፍ በትር ዕቀባ ለማርያም ፍሕርትከ የሚል ጽሑፍ በግብር እምላካዊ ተጽፎ ተገኘ:: <u>አንድም</u> ርግብ ከበትሩ ወርዳ ከራሱ ላይ ተቀመጠችበት /ስትቀመጥ ታየች/:: አንድም እጣ ቢጣጣሉ ለእርሱ ደረሰ እንደ ሦስት ምስክር: ጠብቅ አሉት:: እኔ እናት የሌላቸው ልጆች የማሳድግ ነኝ ወዲያውስ ሞፈር ድግር ጠርቤ ያገኘ ሽሙ የማድር እንደምን አድርጎ ይሆንልኛል አላቸው:: የኛ ትእዛዝ አይደለም ትእዛዘ እግዚአብሔር ነው:: አይሆንም ብትል አንተ ለራስህ ታውቃለህ አሉት: ይዟት ሄደ ::

ወበሳድስ ወርኀ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አሐቲ ሀገር ዘገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት:: በስድስተኛው ወር ገብርኤል የገሊላ ክፍል የምትሆን ናዝሬት ወደምትባል አገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ:: ሳድስ ወርኀ ለኤልሳቤጥ ጽንስ ነው:: ወእምዝ ጸንሰት ኤልሳቤጥ ብእሲቱ ይላል:: ዮሐንስ የመስከረም እመ ፴ ተጸንሷል መጋቢትን ለመስከረም ሳድስ አለ:: ስለምን በስድስተኛው ወር ተላከ ቢሉ



በስድስተኛው ቀን የተፈጠረ አዳም በድሉ ነበርና እሱን ለማዳን በሱ የሄደችውን ልጅነት ለመመለስ እንደመጣ ለማጠየቅ:: ስለምን በዚህ ወራት ተላከ ቢሉ በዚያ ወራት የተፈጠረ አዳም በድሉ ነበርና እሱን ለማዳን በእሱ የሄደች ልጅነትን ለመመለስ እንደመጣ ለማጠየቅ:: <u>አንድም</u> በስድስተኛው ሺ ለምን ተላከ ቢሉ በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ያለው እንደደረሰ እንደተፈጸመ ለማጠየቅ:: ስለምን ሺሁን ወር አለው ቢሉ ዕለት ያለ ወርኀ ቢል ድንቅ ነው? ለማለት:: ስለም ገብርኤል ተላከ ቢሉ ሲላክ የለመደ ነው:: ከዘካርያስ ከኤልሳቤጥ ሲላክ የነበረ ነው:: ከቅዱሳን እያንዳንዱ የማይላክ የለም ብሎ ገብርኤል ማለት እምላክ ወሰብእ እግዚእ ወገብር ማለት ነው እምላክ ሰው ሰው እምላክ የሚሆንበት ጊዜ ደረሰ ሲል:: አንድም መጋቤ ሐዲስ ነውና ማን ይላክለት በዘመኑ:: አንድም በጥንተ ተፈጥሮ ጌታ መላእክትን ሕያዋን ለባውያን ነባብያን አድርጎ በጨለማ ፈጥሯቸው ተሠወረ:: መላእክትም ምንት ንሕነ እምኀበ አይቴ መጻእነ ወመኑ ፈጠረነ ወሚመ በበርእስነኑ ተፈጠርነ አሉ:: ያንጊዜ ዲያብሎስ ቅሩበ እግዚአብሔር አጋዜ መንጦላዕት ሆኖ ተፈጥሮ ነበር:: ከፍ ብሎ ቢያዳምጥ ድምፅ አጣ:: ዝቅ ብሎ ቢያዳምጥ እንዲህ ሲሉ ሰማ:: ዝም ብዬ መንግሥት እሰዳለሁ? እኔ ፈጠርኋችሁ ልበል ብሎ አሰበ: አስቦም አልቀረ:: እነ ፈጣሪሆሙ ለእሉ ፍጡራን ወእነ ገባሪሆሙ ለእሉ ግቡራን ብሎ ተናገረ:: ያን ጊዜ በመላእክት ከተማ ሽብር ጸና:: ወአኀድዮሙ መልአከ ሰላም ዘሰሙ ገብርኤል ይላል:: ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለእምላክነ ብሎ አጽንቷቸዋል:: ይህ ቅሉ ለብሥራት አብቅቶታል:: ወበእንተዝ ደለዎ ይጹር /ይሰብክ/ ዜናሃ ለማርያም እንዲል::

ኀበ ድንግል እንተ ተፍሕረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ:: ከዳዊት ወገን ለሚሆን ስሙን ዮሴፍ ለሚሉት ወደታጨች ወደ ድንግል ተላከ:: ዘእምቤተ ዳዊት አለ:: እስመ እምፍሬ ከርሥከ እነብር ዲበ መንበርከ ያለው እንደደረሰ እንደተፈጸመ ለማጠየቅ::

ወስማ ለይእቲ ድንግል ማርያም:: የዚያች ብላቴና /ሕፃን/ ስሟ ማርያም ይባል ነበር:: ቦአ መልአክ ኀቤሃ:: ወደሷ ገባ ከዚያ

ከቤተ ዮሴፍ ሳለች ቋንጤ ወንበሯን ዘርግታ ወእንዘ ትፌትል ወርቀ ወሜላተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ ይላል:: ወርቁን ከሐሩ ሐሩን ከወርቁ አስማምታ ስትፈትል መጥቶ ቃል ሥጋ ኮነ አላት:: ደንገጥ ብላ ወደ ቤቷ ገባች:: ተከትሎ ገባ ገብቶም ወቆመ ገሀደ በአንጻረ ዘትሬእዮ ይላል:: ፊት ለፊት ቆመ:: አንድም ቦአ: ወደሷ ባሕርይ ገባ:: በአምሳለ መልአክ የታየኂት እንደሆነ ትደነግጣለች ብሎ:: በአምሳለ ብእሲ ከዚያውም ዘንድ በአምሳለ ብእሲ ዘሰያብ /ሽበት የቀላቀለበት መካከለኛ ሰው መስሎ ታየ/ ለጊዜው እንዳትደነግጥ ነው:: ምስጢሩ ግን ብሉየ መዋዕል አምላክን ትጸንሻለሽ ሲል ነው::

ወይቤላ ተፈሥሒ ኦ ምልዕተጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ:: እግዚአብሔር ወልድ ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ቢሆን የእናትነትን ክብር ያገኘሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል:: ይህስ ጊዜው ገና ነው ብሎ እንደ ሐዋርያት በጸጋ ቢያድርብሽ የእናትነትን ክብር ያገኘሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል:: ይህም ጊዜው ገና ነው ብሎ እንደነቢያት በረድኤት ቢያድርብሽ የባለሟልነትን ክብር ያገኘሽ ማርያም ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻል::

ቡርክት አንቲ እምአንስት:: ከሴቶች ይልቅ ንዕድ ክብርት ነሽ:: ወርእያ ደንገጸት እምቃሉ:: ቃሉን ሰምታ ደነገጠች:: ርእየን ሰምዐ ይላል:: ወርእዮ ሕልመ አቡሁ ገብአ ማቱሳላ:: አጽንን ርእስከ /አጽምዕ/ እዝነከ ለርእየ ሕልመ አቡከ:: ስምዒ ወለትየ ወርእዩ: እንዲል:: አንድም ቃሉን ሰምታ መልኩን አይታ ደነገጠች:: ወኀለየት ወትቤ:: አሰበች እንዲህ አለች እፎኑ ከመዝ ኑ አምኃ ይትአምኑ:: እፎና ኑ አንድ ጊዜ /አንድነት/ አይተረጐምም ለሴት እንዲህ ያለ ለላምታ እንዴት ይሰጧታል:: እናቱ ሔዋንን ያሳተ ሰይጣን ነው እንጂ ሌላን ነው አለች::

ወይቤላ መልአክ ኢትፍርሒ ማርያም:: ማርያም አትፍሪ አንችም እንደ እናትሽ እንደ ሔዋን ስሕት አይደለሽም /ስሕተት የለብሽም::/ እኔም እናትሽ ሔዋንን እንዳሳተ ሰይጣን አይደለሁም አላት:: ኢትፍርሂ አላት ፍርሃቷን ካላራቀላት ነገሩን አትሰማውምና ማርያም ብሎ ጠራት:: አይወልዳትምና ዳዊት ግን



ይወልዳታልና ወለትየ ይላታል አለ:: እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር:: ከእግዚአብሔር ዘንድ የእናትነት ባለሟልነትን አግኝተሻልና ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ:: ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድን በድንግልና ጸንሰሽ በድንግልና ትወልጅዋለሽ አላት:: ኢሳይያስ አርቆ ትጸንስ ትወልድ ብሎ ነበር:: ፈከረ ላቷ ለድንግል ያስኘው ይህ ነው:: ራስ ቀርቶ ስም ጠርቶ እንደ መናገር::

ወትሰምዩዮ ስሞ ኢየሱስ:: ስሙን ኢየሱስ ትይዋለሽ:: ውእቱ ዓቢይ:: የአብ ዐቢይ ኃይሉ ነው:: ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል:: የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አለ በተዋሕዶ:: ወይሁቦ እግዚአብሔር መንበረ ዳዊት አቡሁ:: የዳዊትን መንግሥት ይሰጠዋል:: ለጊዜው ሰሎሞን ነው:: ፍጻሜው ግን ክርስቶስ ነው:: ምነው የዳዊት የጸጋ የጌታ የባሕርይ የዳዊት ሥጋዊ የጌታ መንፈሳዊ አይደለም? ቢሉ የጸጋውን የባሕርይ: የሥጋዊውን መንፈሳዊ: አድርጎ ገዝቷል: እንጂ መንግሥቱስ አንድ ነው:: አንድም የመስኮቱን ሥልጣን ይሰጠዋል:: መንበረ ዳዊት አለ:: መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም ብሎ ስለተናገረለት:: አንድም መስቀልን ይስጠዋል አለ እንዲሰቀል ያደርገዋል:: መንበረ ዳዊት አለ:: እርትዕ ተሠራህ ወንገሥ ብሎ ስለተናገረለት:: አንድም ምእመንን ይሰጠዋል አለ:: እንዲዋሐድ ያደርገዋል:: መንበረ ዳዊት አለ ስምዒ ወለትየ ብሎ በስመሰከረለት:: ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም:: ለዘላለሙ ለያዕቆብ ወገን ይነግሣል:: ምነው ለእሕዛብ አይነግሥምን ቢሉ እመቤታችንን ዮሴፍን ደስ ለማሰኘት:: የተሰፋ የሃይማኖት መሠረት ናቸውና:: አንድም ያመኑበትን ሁሉ ቤተ ያዕቆብ አለ:: አሕዛብ ቢሆኑ ካመኑ ቤተ ያዕቆብ ይባላሉ:: እስራኤል ቢሆኑ ካላመኑ ቤተ ያዕቆብ አይባሉም:: ወአልቦ ማሕለቅት ለመንግሥቱ:: ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም:: ዳዊት ሰሎሞን ፵:፵: ዘመን ነግሠው ገዝተው አልፈዋል:: እሱ ግን ቅድመ ዓለም ማዕከለ ዓለም ድኅረ ዓለም ነግሦ ይኖራልና:: ትቤሎ ማርያም ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢያአምር ብእሴ:: እሷም ይህ ወንድ ሳላውቅ እንዴት ይሆንልኛል: እምአይእቴ ረከብከ

ዘከመዝ ብሥራተ ዘእንበለ ዘርዐ እምድር እትወተ ወዘእንበለ ምት እምድንግል ጽንሰተ:: ምድር ያለዘር ታፈራ ዘንድ ሴት ያለወንድ ትጸንስ ዘንድ እንዲህ ያለ የምሰራች ከየት አገኘህ አለችው:: እንዲህ ማለቷ ነገሩን ሽታው አይደለም ጥንቱን እንደ ምን ይሆንልኛል ነገሩን አላደርገውም ስትል ነው:: ይህም እንደ ዘካርያስ ተጠራጥራ እንደ ኒቆዲሞስ ተከራክራ አይደለም ልረዳው ብላ ነው እንጅ:: መልካም ደቀመዝመር የጸነነውን ቀለም ከመምህሩ ተከራክሮ እንዲረዳ::

አውሥአ መልአክ ወይቤላ::

መለሰት እንዲህ አላት::

መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ:: ያንቺማ ነገር እንደሌሎች ሴቶች መሰለሽ? አላት::

ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ:: መንፈስቅዱስ ያለውን ኃይለ ልዑል:: ላዕሌኪ ያለውን ጸለለኪ ብሎ ደገመው:: ከኃጢአት ይጋርድሻል:: ይለብስ ሥጋ ዚአኪ የአብ ኃይሉ ወልድ ሥጋሽን ይዋሐዳል::

ዝኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ::

ይህ ካንቺ የሚወለደው ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው አላት:: ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል:: የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አለ፡ በተዋሕዶ:: ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተእምአዝማድኪ ይእቲኒ ጸንሰት ወረከበት ወልደ በልሕቃቲሃ ወበርሰዓቲሃ:: ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሳቤጥስ ስንኳን ካረጀች ከመከነች በኋላ ጸነሰች ወንድ ልጅን አገኘች:: ምነው በድንግልና ጸንሶ በድንግልና ከመውለድ ካረጁ ከመከኑ በኋላ መውለድ ይበልጣልና እንዲህ አለ ቢሉ እመቤታችን ከሙቀት ከልምላሜ ናት:: እሷ ግን ሙቀት ልምላሜ ተለይቷታልና:: ደግሞም መጽሐፍ የደረሰበትን ማጽናት ልማድ ነው:: እንድም ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሳቤጥም ካረጀች ከመከነች በኋላ ጸነሰች ወንድ ልጅን አገኘች:: እንተእምአዝማድኪ ያለኘው እንደምን ነው ቢሉ ሌዊ ማጣትን ይወልዳል:: ማጣት ሶፍያን ሐናን ማርያምን ይወልዳል:: ሶፍያ ኤልሳቤጥን ሐና እመቤታችንን ማርያም ስሎሜን ትወልዳለች::



ወናሁ ሳድስ ዝንቱ ወርኅ ለእንተ ይብልዋ መካን እስመ አልቦ ነገር ዘይሰእኖ ለእግዚአብሔር:: ካረጁ ከመከኑ በኋላ እንዲወልዱ ማድረግ ለእግዚአብሔር የሚሳነው አይደለምና እነሆ መካን ስሚሏት ለኤልሳቤጥ ከጸነሰች ስድስት ወሯ ነው አላት:: ገብርኤል ያየው ምሥጢር ያስኘው ይህ ነው:: እሷ ሠውራው ነበር:: እሷም እንጂ ከባሏ እንዳትወልድ በድንግልና ጸንሶ በድንግልና እንዲወልዱ ማድረግ ለእግዚአብሔር የሚሳነው አይደለም አኮን አለ:: አውሬ የፈራ ያጥራል ነገር የፈራ ቀን ይቀጥራል እንዲሉ እሷ እየጠየቀች እሱ እየመለሰ ነገር በዛ ነበርና::

እስመ አልቦ ነገር ዘይሰእኖ ለእግዚአብሔር:: ብሎ ነገሯን ወሰነባት:: ያን ጊዜ የደረቀ ዕፀ ዘይት ከፈተ ነበር አለምልሞ አሳይቷታል::

ትቤሎ ማርያም ለመልአክ ነየ ዓመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ:: እነሆ በነፍስ በሥጋ የማገለግለው ባሪያው አለሁለት እንደቃልህ /እንዳልኸው/ ይደረግልኝ አለችው:: ለእግዚአብሔርማ ይሳነዋል ብዬ ብል ክህደት ይሆንብኝ የለም? ብላ ይኩነኒ ብላለች:: እስካሁን አልተዋሐደም ነበር:: የኢአማኒት ሥጋ መዋሐድ በሆነበት ነበርና:: አሁን ግን ይኩነኒ ያለችው ቃሏን ምክንያት አድርጎ በምልዓት ያለ ቃለ እግዚአብሔር ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በአምጣነ ሕፃናት ተጸነሰ:: ስፍሐ ገብረ ዘእምጥንተ ሥጋሁ ለአዳም ወየአርፋ /ወየአርፍ/ አልባቢነ ዘበጥንተ እግዚአብሔር ነጽርኬ ኀበ ለዐሌ ሕፃናት ዘበጥንተ ሙላዱ ወጠነ ፍኖተ ነኪረ እሜሃ ተሰአለ በጥንተአካል ሥጋሁ ለወልደ ዕጓለ እመ ሕያው እንዘ ይትወሐድ ምስለ ቃል እንዲል::

ረቂቁ ግዙፍ፡ ግዙፉ ረቂቅ፡ ምሉዑ ውሱን፡ ውሱኑ ምሉዕ ሆነ:: የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆነ:: እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ እንዲል:: ተዋሕደ ፀና ምንታዌ ጠፋ:: እስመ ተዋሕዶ አስተታ ለምንታዌ እንዲል::

ሖረ ወኀለፈ እምኔሃ መልአክ::

ሖረ ከሷ ተለየ፡፡ ኀለፈ ከሷ አልፎ ተሰይቶ ብዙ ጎዳና ሄደ፡፡ ደርሼ የጠፋኋት እንደሆነ ትደነግጣለች ብሎ እያየችው ብዙ ጎዳና ሄዷል፡፡ አንድም ሖረ ከሷ ተሰይቶ ብዙ ጎዳና ሄደ ወኀለፈ ሄዶ ሄዶ ረቀቀ የርቀት ያይደለ የርሕቀት አሞራ ወጥቶ ወጥቶ እንዲረቅ፡፡

ወተንሥእት ማርያም ፍጡነ በውእቱ መዋዕል፡፡ በዚያ ወራት ፈጥና ተነሣች ፈጥኖ በጆሮ የሰሙትን በዓይን እስኪያዩት ያስቸኩላልና፡፡ ዘካርያስ ታሟልና እሱን ለመጠየቅ፡ ምስክር ሃብት ለማድረግ፡ ወሖረት ደወለ ዓይነ ከርም፡፡ የክረምት ግብር ባለበት ቦታ ሄደች አለ፡፡ ደመናው በሚረገረግበት ነፋስ በሚሳብበት፡፡ አንድም ለተክል የሚያጠጡት ምንጭ /ውሀ/ ባለበት ቦታ ዘይሰመይ ህጥሚ ይላል፡፡ ትብንት፡ ወበጽሐት ፍጡነ ሀገረ ዳዊት ዘያሁዳ፡፡ የይሁዳ ዕፃ ክፍል ወደምትሆን ወደ ዳዊት ሀገር ፈጥና ደረሰች፡፡ በቅርብ ጎዳና ሄዳ፡ ጸጋ እግዚአብሔር አድርሳታልና፡፡ አንድም ፍጡነን አይሻም፡፡ ወበጽሐት ኀበ ሀገረ ዳዊት ዘይሁዳ ይላል፡፡ ወቦአት ቤተ ዘካርያስ ወደ ዘካርያስ ቤት ገባች ወአምኃታ ለኤልሳቤጥ፡፡ ኤልሳቤጥን ቸር አለሽን? አለቻት፡፡

ወሰበ ሰምዐት ኤልሳቤጥ ቃለ አምኆታ ለማርያም፡፡ ቸር እሰሽን ስትላት በሰማች ጊዜ፡፡
እንፈርዐፀ ዕጓል በውስተ ከርሣ በፍሥሓ ወበሐሤት፡፡ በማሕፀኗ ያለ ጽንስ ደስ እያላት ደብ እያሰው ሰገደ፡፡ አንፈርዐፀን ሐዋርያት በሲኖዶስ ሰገደ ብለው ወስደውታል፡፡ ቅዱስ ያሬድም እምክርሠ እሙ አእሚሮ ሰገደ ወልደ መካን ለወልደ ድንግል ብሎ ወስዶታል /ተርጉሞታል/፡፡ በእመቤታችን ማኅፀን ያለ ጽንስ በኤልሳቤጥ ማኅፀን ባለው ጽንስ መንፈስ ቅዱስ አሳድሮበት ሰግዷል፡፡ ዮሐንስ ኤርምያስ በማሕፀን አግኝተዋል ደስ እያላት አለ፡፡ ሴቶች ሲነዋወጽ ያማችዋል ሲፈዝ ደስ ይላቸዋል ልማድ አፍርሶ ይህስ ሲነዋወጽ ደስ ይላቸዋል ብሎ ከወትሮው ደስታዋ ይልቅ ደስ እያላት፡፡ ወመልዐ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኤልሳቤጥ፡፡ መንፈስቅዱስ በኤልሳቤጥ መላባት ተሰይቷት አይደለም፡፡ ምስጢር ገልጾላት ትንቢት ቋንቋ አናገራት የሚል ነውና፡፡ ወከልሐት በዐቢይ ቃል፡፡ ቃሏን አሰምታ ተናገረች ሙሃ ተናግራ



አይደለም ሙሆ የተናገሩት ከሩቅ እንዲሰማ ነገሯ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ስለተሰማ፡፡
ወትቤ ቡርክት አንቲ እም አንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ፡፡ ተጸንሷልና ይህን አተረፈች የማኅጸንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቡር ምስጉን ነው፡፡ ወሀቤ በረከት ነው ርስሐተ ሕጻናት /ልማደ ሕፃናት/ የሌለበት ነው፡፡ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ በረከተ ነፍስን የሚያድል የባሕርይ አምላክ ነው፡፡

ምንትኑ አነ ከመ ትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ፡፡ የጌታዬ እናቱ ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድነኝ ገረድ ወደ እመቤቷ ትሄዳለች እንጂ እመቤት ወደ ገረዷ ትሄዳለች? አለች ይሄውም የሚያሰኝ ቃል ነው፡፡ ዳዊት ቢሄድበት ምንት አምጽዖ ለእግዚእየ ኀበ ገብሩ ብሏል፡፡ ዮሐንስም ጌታ አጥምቀኝ ብሎ ቢሄድበት አንሰ እፈቅድ እምኀቤከ እጠመቅ ወአንተኑ ትመጽእ ኀቤየ ብሏል፡፡ ጴጥሮስም ጌታ ሲያጥበው ቢሄድ አንተኑ ተሐፅበኒ እገርየ ብሏል፡፡

እስመ ናሁ ሶበ ሰማዕኩ ቃለ አምኆትኪ፡፡ አንፈርዐፀ ዕጓል በውስተ ከርሥየ በፍሥሓ ወበሐሤት፡፡ ቸር አሰሽን ስትይኝ በሰማሁ ጊዜ በማኅጸኔ ያለ ጽንስ ደስ እያለኝ ደስ እያሰው ሰግዷል፡፡ ወብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር፡፡ ከእግዚአብሔር ታዝዘው የነገሩሽ ቃል እንዲደረግ የምታምኚ፡፡

አንድም ቃለ፡፡ ከእግዚአብሔር አግኝተው የነገሩሽን ነገር እንዲደረግ የምታምኚ አንቺ ንዕድ ክብርት ነሽ፡፡ እንደ እኔ ባል ሳትከራከሪ /ተጠራጥረሽ/ መከራ ያላገኘሽ አለች፡፡ ምነው ዘነገሩኪ አለ አንድ መልአኩ አይደለም? ቢሉ መጽሐፍ ስም ካልጠራ አንድና ብዙ አይጠነቀቅም፡፡ በተአምኖ እመ ነገርዎ ለኖኅ፡፡ አየ ገቦ ረገዙ ሐራሁ ለጲላጦስ (ሐራ ጲላጦስ) እንዲል፡፡

ወትቤ ማርያም ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር፡፡ ከዚህም በአንድ መልአክ በአንዲት ባልቴት ቃል ብቻ ተመስግኜ አልቀርም፡፡ ትውልድ ዘይመጽእ ትውልድ ዘየኀልፍ ትውልደ ሴም ትውልደ ያፌት ትውልደ ካም ያመሰግኑኛል ስትል ታመጣዋለች፡፡

## ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር

ሰውነቴ እግዚአብሔርን ታገነዋለች ታከብረዋለች:: አሁን አመቤታችን ጌታን የምታገን የምታከብር ሆና አይደለም:: ልዕልናውን ትናገራለች ሲል ነው:: ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ እንዲል::

ወትትሐሠይ መንፈስየ በአምላኪየ ወመድኃንየ:: በፈጣሪዬ በመድኃኒቴ አምኜ ልቡናዬ ደስ ይላታል:: መድኃኒየ አለች ከምን አድኗታል ቢሉ ከርደተ ገሃነም አሉን ባትጸንስ እንደ አባቶቿ ርደተ ገሃነም ባልቀረላትም /ባገኛት/ ነበርና:: አንድም በዘርዕ በሩካቤ ከመውሰድ ከሰስሎተ ድንግልና:: ውእቱስ ንጹሕ እምነ ፫ቱ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርዕ ወሩካቤ ወሰስሎተ ድንግልና አለ ሥሩዓን በዕንለ እመሕያው ወእሙራን ቦሙ እንዲል::

እስመ ርእየ ሕማማ ለአመቱ::

የባሪያው የሔዋንን ኃዘን አይቷልና ኃዘኗን አይቶ ሰው ሆኗልና:: ትሕትናሃ ቢል በመንፀፈ ደይን መውደቋን በእግረ አጋንንት መጠቅጠቋን አይቶ:: አንድም የኔን ኀዘኔን አይቷልና ኃዘኔን አይቶ ሰው ሆኗልና:: ባባቶቿ ርደት ታዝን ነበርና:: ትሕትናየ ቢል ትሕትናዬን አይቶ:: ከዕለታት አንድ ቀን መጽሐፈ ኢሳይያስ ስትመለከት ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ከሚለው አንቀጽ ብትደርስ /ስትደርስ/ ወየው ከዚያ ሰዓት ደርሼ ውሀ ቀድቼ እንጨት ለቅሜ /ሰብሬ/ አገልግያት እያለች ትመኝ ነበር:: ይህ ትሕትናዋ ራሷ ለመሆን አብቅቷታል::

ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ:: እንግዲህ ወዲህ በአንድ መልአክ በአንዲት ባልቴት ቃል ተመስግኜ አልቀርም ብላለች:: ትውልድ ዘይመጽእ ትውልድ ዘየኀልፍ ትውልደ ሴም ትውልደ ያፌት ትውልደ ካም ያመሰግኑኛል:: አንድም ፍጥረት ሲል ነው:: አሪት ዘልደት እንዲል:: ፍጥረት ሁሉ ያመሰግኑኛል::

እስመ ገብረ ሊተ ኃይለ ዐቢያተ:: አብ ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠርቶልኛልና የባሕርይ ልጁን በባሕርዩ እንድወልደው አድርጎኛ ልና ወቅዱስ ስሙ:: ስሙ ልዩ ነው አለች:: አብ ቢባል እንጂ ወልድ መንፈስቅዱስ አይባልም::



አንድም እስመ ገብረ ሊተ ኀይለ ዐቢያተ:: ወልድ ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠርቶልኛልና በድንግልና ጸንሼ በድንግልና እንድወልደው አድርጎኛልና ወቅዱስ ስሙ ስሙ ልዩ ነው አለች:: ወልድ ቢባል እንጂ አብ መንፈስቅዱስ አይባልም::

አንድም እስመ ገብረ ሊተ ኀይለ ዐቢያተ:: መንፈስ ቅዱስ ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠርቶልኛልና አጽንቶኛልና ወቅዱስ ስሙ:: ስሙ ልዩ ነው አለች:: መንፈስ ቅዱስ ቢባል እንጂ አብ ወልድ አይባልም::

ወሣህሉኒ ለትውልደ ትውልድ ለእለ ይፈረሕዎ:: ለና ለ የተደራረበ ነው:: ለካህናት ለደቂቀ አሮን ለብእሲት ለመርዓተ በግዑ እንዲል:: ይቅርታው ለሚፈሩት ለሚያመልኩት ከትውልድ ለተወለዱ ትውልድ ነው::

ለእለ ይፈርሕዎ ያ ግን ለሚፈሩት ለሚያመልኩት ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም:: እንደ አባቷ እንደ ዳዊት:: ሣህሉ ለእግዚአብሔር እምዓለም ወእስከ ለዓለም ብሎ ዲበ እለይፈርሕዎ እንዲል::

ወገብረ ኀይለ በመዝራዕቱ:: ዛሬም ብቻ አይደለም በግብጽ በባቢሎን ታምራት አደረገ::

ወዘረዎሙ ለእለ የዐብዩ ኅሊና ልቦሙ:: ልቡናቸውን የሚያስታብዩ ግብጻውያንን ባቢሎናውንን በተናቸው::

<u>ወነሠቶሙ</u> ለኃያላን እመናብርቲሆሙ:: ኃያላን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ከሹመታቸው ሻራቸው::

አዕበዮሙ ለትሑታን:: በግብጽ ተዋርደው የነበሩ እስራኤልን ከፍ ከፍ አደረጋቸው:: አንድም ትሑታን ሐዋርያትን አሥራት በኵራት ሰጥቶ ትሑታን ነፍሳትን ልዕልና ነፍስን ሰጥቶ አከበራቸው::

ወአጽገቦሙ <u>እምበረከቱ</u> ለርኁባን:: በግብጽ ተርበው የነበሩ እስራኤልን አጠገባቸው:: መና ከደመና አውርዶ ውሀ ከደንጊያ አፍልቆ:: <u>አንድም</u> በባቢሎን ተርበው የነበሩ ትሩፋንን አጠገባቸው:: ፯ አህጉር ወግተው ብዕለ አሕዛብን ዘርፈው ወጥተዋልና::

ወፈነዎሙ ዕራቆሙ ለብዑላን:: ግብጻውያንን ባደዋቸውን አስናበታቸው:: በረድ መትቶባቸው አንበጣ በልቶባቸው ባቢሎናውያንን ባዷቸውን አሰናበታቸው:: የቂሮስ የዳርዮስ ጦር ዘርፏቸው::

ወተወከፎ ለእስራኤል ቍልዒሁ:: ወዳጁ እስራኤልን በረድኤት ተቀበለው::

ወተዘከረ ሣህሎ ዘይቤሎሙ ለአበዊነ:: ለአባቶቻችን የተናገረው ይቅርታውን አሰበ አለ ፈጸመ::

ለአብርሃም ወለዘርዑ እስከ ለዓለም:: ለአርብሃም የተናገረውን ደቂቅከኒ ይነብሩ ፈላሰያነ ውስተ ምድረ ነኪር፡ ፬ተ ፻ተ ዓመተ ያለውን::

ወለዘርዑ:: ለልጆቹ የተናገረውን:: ወኀሊቆ ፫ ዓም እትቤቀሎ ለንጉሠ ባቢሎን ወለኲሉ ሰብእ ያለውን:: እንድም ወገብረ ኃይለ አብ በወልድ ህልው ሆኖ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ታምራት አደረገ::

ወዘረዎሙ ለእለ የዐበዩ ኅሊና ልቦሙ:: ልቡናቸውን የሚያስታብዩ አይሁድን በተናቸው:: ወነሠቶሙ ለኃያላን:: ሐና ቀያፋን ከሹመታቸው ሻራቸው::

አዕበዮሙ ለትሑታን:: ልብደ ሠረ /መረብ ሠሪ/ ዓሣ አሥጋሪ /ወጋሪ/ የነበሩ ሐዋርያትን ከፍ ከፍ አደረጋቸው::

እንድም መልስ:: ወአጽገቦሙ እምበረከቱ ለርኁባን:: ከልጅነት ከትምህርት ተርበው ለነበሩ ለሐዋርያት ልጅነትን ትምህርትን አጠገባቸው::

ወፈነዎሙ ዕራቆሙ ለብዑላን:: አሥራቱን በኩራቱን ቀዳምያቱን ተቀብለው ከብረው ገነው ይኖሩ የነበሩ ሐና ቀያፋን ባዷቸውን አሰናበታቸው::

ወተወከፎ ለእስራኤል ቍልዒሁ:: ይህን ለማድረግ ልጁን እስራኤላዊ ሥጋን እንዲዋሐድ አደረገው:: ኅበ ያዕቆብ ኀድረ ወነበ እስራኤል ተዋረሲ እንዲል::

እንድም ወገብረ ኃይለ በመዝራዕቱ:: ወልድ በሥልጣኑ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ታምራት አደረገ::



ወዘረዎሙ ለእለ የዐበዩ ኅሊና ልቦሙ:: ልቡናቸውን የሚያስታብዩ አጋንንትን በተናቸው:: ሥጋትን በመቃብር አፍርሰን አበስብሰን ነፍሳትን በሲኦል /በገሀነም/ ተቆራኝተን እንኖራለን ይሉ የነበሩትን::

ወነሠቶሙ ለኃያላን እመናብርቲሆሙ:: ከሰው ልቡና አስወጣቸው ልቡናቸውን እንደ ዙፋን ሰውነታቸውን እንደ አዳራሽ እንደ ድንኳን አኩያት ፍትወታት ኃጣውእን እንደ አጥር እንደ ቅጥር አድርገው ይኖሩ የነበሩትን:: አዕበዮሙ ለትሑታን:: ነፍሳትን ከፍ ከፍ አደረጋቸው::

ወአጽገቦሙ እምበረከቱ ለርኁባን:: ከልጅነት ከክብር ተርበው የነበሩ ነፍሳትን ልጅነትን ክብርን አጠገባቸው::

ወፈነዎሙ ዕራቆሙ ለብዑላን:: አጋንንትን ባዷቸውን አሰናበታቸው::

ወተወከፎ ለእስራኤል:: ይህን ለማድረግ መጥቶ እስራኤላዊ ሥጋን ተዋሕዶ::

ወተዘከረ:: ለአዳምና ለሔዋን የተናገረውን ቃሉን አሰበ አለ:: በሐሙስ ዕለት ያለውን:: ለአብርሃም:: ለአብርሃም የተናገረውን በዘርዕከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዘበ ምድር ያለውን::

ወለዘርዑ:: ለልጆቹ የተናገረውን::

እስመ እምፍሬ ከርሥከ እንብር ዲበ መንበርከ ያለውን::

ወነበረት ማርያም ኀቤሃ መጠነ ፫ቱ አውራኅ ሰስት ወር ያህል ኖረች ወእምድኅረዝ አተወት ቤታ:: ከዚህ በኋላ ወደ ቤቷ ሄደች:: ስለምን ቢሉ መኖር ፈቃዷ ቢሆን ኖረች፡ መሄድ ፈቃዷ ቢሆን ሄደች:: እንድም ሰው ሁሉ በየሀገሩ ይኑር ተብሎ አዋጅ ተነግሮ ነበርና:: እመቤታችን ክብርት ቤተ መቅደስ ናት ክቡር ቤተ መቅደስ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስን ጸንሳለች:: ማስተራኮስ በሆነባት ነበርና:: ኤልሳቤጥ የምትወልድበት ጊዜ ደርሷል:: ተቀንዮ በሆነባት ነበርና:: ዮሐንስ ባልተወለደም ነበርና:: አንበሳ ከደደ አስረው አንበሳ ይፈታሉ? /ይፈቷል?/::

## ፲፬. ጸሎተ ዘካርያስ ካህን

ዘካርያስ ማለት ዝኩር ዝክረ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡

ወሀሎ አሐዱ ካህን ዘስሙ ዘካርያስ በመዋዕለ አብያ፡፡ በአብያ ዘመን ስሙን ዘካርያስ የሚሉት አንድ ካህን ነበረ፡፡ ዘካርያስ ሙሉዕ አብያ ዱግ ነው፡፡ /የበላይና የበታች/፡፡ ምነው ምስሉን በዱግ ዘመን ነበረ አለ ቢሉ ምሉው ቢስካክል ዱጉ የምሉውን ሥራ ያሠራዋልና፡፡ በአጢኑ ዕጣን በአብኦ መሥዋዕት ያፈራረቀዋልና፡፡ ወብእሲቱኒ እምአዋልደ አሮን ወስማ ኤልሳቤጥ፡፡ ሚስቱም ከአሮን ልጆች ወገን ነበረች፡ ስሟም ኤልሳቤጥ ይባል ነበር፡፡ ይህ አሮን የነአሶን ወልደ አሚናዳብ እኅት ኤልሳቤጥ ትባላለች እሷን አግብቶ አልዓዛርን ይወልዳል፡፡ የዚያች ልደቷ ከዚያች ነው፡፡ ይህን ለምን ይሻዋል ቢሉ የዮሐንስ ልደቱ ከቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት ነው ለማለት፡፡ የቀደመውን ሊቀ ካህናት የቀደመችውን ኤልሳቤጥ አነሳ፡፡ በቀደመው ሊቀ ካህናት በቀደመችው ኤልሳቤጥ ሕገ ሥጋ ኦሪት ተሠርታለች ለማለት፡፡ የኋለኛውን ሊቀ ካህናት የኋለኛዪቱን ኤልሳቤጥ አነሳ በኋለኛው ሊቀካህናት በኋለኛዪቱ ኤልሳቤጥ ሕገ ነፍስ ወንጌል ተሠርታለች ለማለት፡፡

ወክልኤሆሙ ጻድቃን እሙንቱ በቅድመ እግዚአብሔር፡፡ እግዚአብሔር ባወቀው ነገር ሁለቱ ደጎች ነበሩ፡፡

ወየሐውሩ በኵሉ ትእዛዙ፡፡ በኵሉ ትእዛዙ በኢታምልክ፡፡

ወሕጉ፡፡ በ፱ኙ

ወኲነኔሁ፡፡ በ፳፱፻ ወነበቦ፡፡ ጸንተው ይኖሩ ነበር፡፡ አንድም ያዘዋውራል፡፡ ብኩሉ ትእዛዙ፡፡ ፳፱፻ ወነበቦን፡፡

ወሕጉ፡፡ ፱ኙን

ወኲነኔሁ፡፡ ኢታምልክን ጠብቀው ይኖሩ ነበር፡፡

ወንጹሐን እሙንቱ ዘእንበለነውር፡፡ ነውር ነቀፋ የሌለባቸው ንጹሐን ነበሩ፡፡ ምግባራቸውን አበዛዝቶ ተናገረ፡፡ በደጎቹ ቃል አምላክነቱ ተመስክሯል ለማለት፡፡ ደግሞ ወባሕቱ አልቦሙ ውሉድ ብሎ የሚያመጣ ነውና፡፡ ልጅ አለመውለዳቸው በኃጢአታቸው እንዳይመስል፡፡ ወባሕቱ አልቦሙ ውሉድ፡፡ ነገር ግን ልጅ አልነበራቸውም ልጅ ባለመውለዳቸው እስመ መካን



ይእቲ ኤልሳቤጥ፡፡ ሚስቱ ኤልሳቤጥ የባሕርይ መካን ነበረችና፡፡ አነ እግዚአብሔር ዘእፈጥር መካነ ወዘአወልድ እንዲል፡፡ ይህስ ምክንትስ ኢተውህባ ለብእሲት ዳዕሙ ትማስን /ትመውት/ በግብረ እደዊሃ ዘእንበለ ውሉድ ይላል ብሎ እስከ ጊዜዋ ድረስ መካን አላት፡፡ ስለምን አዘገያት ቢሉ አዝና ታግኘው ብሎ፡፡ አዝነው ያገኙት ልጅ ይረባል ይጠቅማልና፡፡ ግሀሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ እንዲል፡፡ ያቅርታውን ያለጊዜው አያሠራውምና፡፡ ለወንጌል አምሳል መርገፍ ልትሆን እሷ ኖራ ኖራ እንደወለደች፡ ወንጌልም ሥራቷ በመልከጼዴቅ ታይቶ ኖራ ኖራ ተሠርታለች /የመሠራቷ ምሳሌ/፡፡

ወክልኤሆሙ ልሂቃን እሙንቱ ወሐለፈ መዋዕሊሆሙ፡፡ የሁለቱም ዘመናቸው ገፍቶ ነበር፡፡

ወእምዝ እመ ይገብር ግብረ ክህነት፡ በዕብራቱ ቅድመ እግዚአብሔር በከመ ይገብሩ ካህናት፡፡ በከመ ልማደ ካህናትም ይላል፡፡ እንደ ካህናቱ ልማድ ካህናት እንዲሠሩ፡፡ በስምኑ የክህነት ሥራ በሚሠራበት ወራት

በጽሐ ጊዜ የእጥን፡፡ የሚያጥንበት ጊዜ ደረሰ፡፡ በደረሰ ጊዜ ቦአ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር፡፡ ወደቤተ መቅደስ ገባ ይህስ ምን ቀን ነው ቢሉ ወአሕምምዋ ለነፍስክሙ ያላት ዕለተ ዮሴፍ ናት፡፡ በዚህ ቀን አባቶቻቸው ወንድማቸው ዮሴፍን ሸጠው አባታቸውን አሳዝነው ነበርና፡ ያን ዕዳ አታድርግባቸው ሲሉ፡ ካህናቱ በውስጥ ሕዝቡ በአፍኣ ሆነው ሲያለቅሱ /ሲጨነቁ/ ነበር፡፡ አንድ ቀን ባለቀሉት ዓመት ይጠበቁ ነበር /ይጠቀሙበታል/ አንድም ዕለተ ሮቤልም ናት ይላሉ፡፡ ከአባቱ ዕቅብት ደርሶ አባቱን አሳዝኖ ነበርና፡ እዳ አታድርግበት ሲሉ፡፡ ወገብሩ ላሕመ በኮሬብ እንዲል፡፡ ጣዖትም ያቆሙበት ቀን ነው ይላሉ፡፡

<u>ወሕዝብሰ</u> ሀለዉ ይጼልዩ በአፍኣ፡፡ ሕዝቡም በአፍኣ ሆነው ይጸልዩ ነበር፡፡ ምን ብለው ይጸልዩ ነበር ቢሉ የወትሮ ጸሎታቸውን ልጅ ስጠው ብለው በጎ ራእይ ግለጥለት ብለው፡፡ ስቡ ከእቅርንተ ምሥዋዕ እንዲመላለት አድርግ ብለው፡፡

<u>ወአስተርአዮ</u> መልአከ እግዚአብሔር ቀዊሞ መንገለ የማነ ምሥዋዕ ዘዕጣን፡፡

በዕጣኑ በምሥዋዑ ቀኝ በኩል ሆኖ ታየው ተነጋገረው:: ዘዕጣን አለ ዘመሥዋዕት ዘብርት አለና:: በቀኝ ሆኖ ታየው ተናገረው አለ የመልአክ ግብሩ የማናዊ ነውና:: ሰው ሁሉ ከግራ ወደቀኝ የሚያልፍበት ጊዜ ደረሰ ሲል:: አንድም መክሮ አስተምሮ ከግራ ወደ ቀኝ የሚመልስ ልጅ ትወልዳለሁ ሲል::

ወሰበ ርእዮ ደንገጸ ዘካርያስ:: ዘካርያስም መልአኩን ባየው ጊዜ ደነገጠ ፍርሃት ረዓድ አደረበት:: ድንጋጼ የናላ: ፍርሃት የልቡና: ረዓድ የጉልበት:: የመልአከ ራእዩ ግሩም ነውና:: ከቅድስተ ቅዱሳን ያለ እሱ የሚገባ የለምና ገብቶ ቢያየው ደነገጠ:: ናዳብ አብዩድን ባላወቁት ኃጢአት እንደቀሰፋቸው እኔንም ባላወቅሁት ኃጢአት ሊቀሥፈኝ መጣ ብሎ:: የአክዩ እሦር በዕብራውያን ወዕብራውያን የአክዩ በእሦር እንዲል::

በአፍአ ያሉትን ጨርሶ እኔን ሊያጠፋኝ መጣ ብሎ::

ወይቤሎ መልአክ ኢትፍራህ ዘካርያስ:: መልአኩም ዘካርያስን አትፍራ አለው:: ኢትፍራህ አለው ፍርሃቱን ካላራቀለት ነገሩን አይሰማውምና: ዘካርያስ ብሎ ጠራው ሥጋዊ ጠላት አይደለምና::

እስመ ናሁ ተሰምዐ ጸሎትከ ቅድመ እግዚአብሔር:: ጸሎትህ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሷልና ምን ብሎ ይጸልይ ነበር ቢሉ የወትሮ ጸሎቱን ልጅ ስጠኝ ብሎ በኅ ራእይ ግለጽልኝ ብሎ:: ስቡ እንዲመላ አድርግልኝ ብሎ:: ወብእሲትከኒ ኤልሳቤጥ ትወልድ ለከ ወልደ:: ሚስትህ ኤልሳቤጥም ጸንሳ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች:: ለከ አለው አርጅቶ ነበርና ከሌላ እንዳይመስለው: ልጅ ስጠኝ ብሎ ይጸልይ ነበር ብሎ ገለጠው:: ሌላ ጸሎት ይጸልይ ነበር ቢሉ ሁለተኛ ምልክት ይነግረዋል::

ወትሰምዮ ስሞ ዮሐንስ:: ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ትለዋለች:: ወይከውነከ ዐቢየ:: ደግ ደስታ ይሆንልሃል::

ወብዙኃን ይትፌሥሑ በልደቱ:: በመወለዱ ብዙ ሰዎች ደስ ይላቸዋል:: በሙያው በግብሩ:: መካን ዘመዳቸው ብትወልድ /ስትወልድ/::

እስመ ሀቢየ ይከውን ውእቱ በቅድመ እግዚአብሔር:: እግዚአብሔር ባወቀው ነገር ደግ ሰው ይሆናልና:: ኢይሰቲ ወይነ



ወሚሰ:: የማር ጠጅ የወይን ጠጅ አይጠጣም:: የማር ጠጅስ በአገራቸው የለም ብሎ ዘያሰክር: አረቂ አይጠጣም:: ወዘኢያለክር: ቀሀ /ቡና/ አይጠጣም::

አላ ይመልዕ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ እምከርሠ እሙ:: በእናቱ ማኅጸን ሳለ በወይኑ ባረቂው ቦታ መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል እንጂ:: ዮሐንስ ኤርምያስ በማኅጸን አግኝተዋል::

ወሰብዙኃን እምደቂቀ እስራኤል ይመይጦሙ ኀበ እግዚአብሔር አምላኮሙ::

ከእስራኤል ብዙዎቹን መክሮ አስተምሮ ወደ ፈጣሪያቸው ይመልሳቸዋል::

ውእቱሰ የሐውር ቅድሜሁ በመንፈስ ቅዱስ ወበኀይለ ኤልያስ:: በመንፈስ ቅዱስ በኤልያስ ግብር ጸንቶ ይናገራል:: ኤልያስን በምን ይመስለዋል ቢሉ ኤልያስ ጸዋሚ ተሐራሚ ዝጉሐዊ ባሕታዊ ድንግል ነው:: ዮሐንስም ጸዋሚ ተሐራሚ ዝጉሐዊ ባሕታዊ ድንግል ንጹሕ ነው:: ኤልያስ ጸጓር ነው:: ዮሐንስም ጸጓር ነውና:: ኤልያስ ቀይ ዓረብ ታጥቆ ነበር:: ደሚን በሰማዕትነት አፈሳሰሁ ሲል:: ዮሐንስም ቀይ ዓረብ ታጥቆ ነበር:: በሰማዕትነት እሞታለሁ ሲል:: ኤልያስ መገሥጸ አክአብ ወኤልዛቤል ነበር:: ዮሐንስም መገሥጸ ሄሮድስ ወሄሮድያዳ ነውና:: ኤልያስ ለደኃራዊ ምጽአቱ ፊታውራሪ /ግንባር ቀደም ሆኖ/ ይመጣል ዮሐንስም ለቀዳማዊ ምጽአቱ ፊታውራሪ ሆኖ መንፈቅ ቀድሞ መጥቷልና:: አንድም ዘውእቱ ኃይለ ኤልያስ ይላል:: የኤልያስ ኃይል በሚሆን በመንፈስቅዱስ እየተቃኘ በጌታ ፊት ይሄዳል አለ:: መንፈቅ ጽንስ መንፈቅ ማስተማር ይቀድመዋል:: ከመ ይሚጥ ልበ አበው ኀበ ውሉድ:: የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብን ዕውቀት ወደሐዋርያት ይመልስ ዘንድ::

ወኀሊና ከሐድያን ውስተ አእምሮ ጻድቃን:: የሐዋርያትን ልቡና ወደ አብርሃም ወደ ይስሐቅ ወደ ያዕቆብ ዕውቀት ይመልስ ዘንድ:: አንድም ከመ ይሚጥ የአይሁድን ዕውቀት ወደ ሐዋርያት ዕውቀት ይመልስ ዘንድ:: ወኀሊና ከሐድያን ውስተ አእምሮ ጻድቃን:: የከሐድያን የአይሁድን ልቡና ወደ ሐዋርያት ወደ ቀደመ ዕውቀታቸው ይመልስ ዘንድ:: ወደ ድንቁርና ማለት ነው::

ከመ ይሥራዕ ሕገ:: ሥርዓትን ይሠራ ዘንድ::

ወሕዝበ ዘድልው ለእግዚአብሔር:: ለእግዚአብሔር የተዘጋጀ ሕዝቡን ይሠራ ዘንድ:: ድልወ የተዘጋጀ አድርጎ ይሠራ ዘንድ

ወይቤሎ ዘካርያስ ለመልአክ በምንት አአምር ከመ ይከውን ዝንቱ እስመ አነሂ ልሕቁ ወለብእሲትየ ኀለፈ መዋዕሊሃ:: እኔ አርጅቻለሁ የሚስቴም ዘመኗ ገፍቷል ይህ እንዲደረግ በምን አውቃለሁ አለው:: ሣራ ካረጀች ከመከነች በኋላ እንደወለደች በኦሪት የተጻፈውን ገድፎ::

ወተሠጥዎ መልአክ ወይቤሎ አነ ውእቱ ገብርኤል ዘእቀውም ቅድመ እግዚአብሔር:: በእግዚአብሔር ፊት የምቆም እኔ ገብርኤል ነኝ:: በእግዚአብሔር ፊት የማይቆም ዲያብሎስ ሐሰት ይናገራል እንጂ እኔ ሐሰት እናገራለሁ?አለው እኔ ውእቱ አለው::በምን አውቆ ቢሉ መጽሐፈ ዳንኤልን ሲመለከት ያውቀው ነበርና:: ተፈኖኩ ንቤከ ዘንተ እንግርከ ወእዜንከ ዘንተ:: ጽንሱን ልደቱን እነግርህ ዘንድ ወዳንተ ተላክሁ::

ወናሁ ትከውን በሐመ:: እነሆ ድዳ ትሆናለህ:: ወትስዕን ነቢበ:: መናገር ይሳንሃል:: እስከ አመይከውን ዝንቱ:: ይህ እስኪደረግ ድረስ::

እስመ ኢአመንከኒ ነገርየ ዘይከውን ወይትፌጸም በጊዜሁ /በእድሜሁ/:: በጽንሱ የሚጀመር በልደቱ የሚፈጸም ነገሬን አላመንከኝምና /አላመንከምና/:: አንድም ኩን በሐመ ወስዐን ነቢበ ብሎ ረገመው:: እንደበቱ ታሠረ

ወሕዝብሰ ሀለዉ ይጸንሕዎ ለዘካርያስ:: ሕዝቡ ግን በእፍኣ ሆነው ዘካርያስን ደጅ ይጸኑት ነበር:: ዛሬ ስረዩ ቄስ ወጥቶ ካላሰናበታቸው እንዳይሄድ:: ወአንከሩ እስመ ጒንደየ ውስተ ቤተመቅደስ:: በቤተመቅደስ ዘግይቷልና ተጠራጣሩ ሽማግሌ ነውና፡ እቃ ሲያዘጋጅ ወድቆ ይሆን፡ ራዕይ በዝቶበት ይሆን ናዳብ እብዩድን እንደቀሠፋቸው ቀሥፎት ይሆን እያሉ ተጠራጠሩ::

ወወጺአ እፍአ ኅበሆሙ ስእነ ተናግሮቶሙ:: ወደ ውጭ በወጣ ጊዜ መነጋገር ተሳነው::



ወአእመሩ ከመ ቦ ዘአስተርአዮ በቤተመቅደስ:: በቤተመቅደስ ሳለ የታየው የተነጋገረው ነገር እንዳለ አወቁ፡ ጠቅሶ አሳይቷቸዋል:: እንደበቱ በመታሰሩ:: ወነበረ ከማሁ እንዘ በሐም ውእቱ:: እንዲሁ ድዳ ሆኖ ኖረ:: ወይኤምርሙ በእዴሁ በዚህ ውጡ በዚህ ግቡ እያለ በእጁ ሲያመላክታቸው ኖረ::

ወፈጺሞ መዋዕለ እብሬቱ አተወ ቤቶ:: ሰሞኑን ጨርሶ ወደቤቱ ሄደ በዓመት አንድ ቀን ነው ያሉ እንደሆነ ደብረዘይት ነው ቤቱ:: ሳምንት ነው ያሉ እንደሆነ የከተማ /ከከተማ/ ቤት ነበረው::

ወእምድኅረ ክልዔ መዋዕል ጸንሰት ኤልሳቤጥ ብእሲቱ:: ከሁለት ቀን በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጸነሰች ሰሰምን አስከዚያ ሰነበተ ቢሉ ስለ አክብሮተ ዕጣን:: ዛሬ ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ዕለቱን መድረስ እንዳይገባ ሲያጠይቅ:: ወከበተት ጽንሳ ሯተ አውራኃ እንዘትብል ከመዝ ኑ ረሰየኒ እግዚአብሔር አመ ሐውጻ ሐወጸኒ ያእትት ዝንጓጔየ እምሰብእ:: ከሰው ተግዳሮቴን ያርቅ ዘንድ በምሕረት በጎበኘኝ ጊዜ እንዲህ ያለ ሥራ ሠራልኝ እያለች አምስት ወር ያህል ጽንሷን ሰወረች:: ሴቶች ሦስት ወር መሠወር ልማዳቸው ነውና:: ትርፉ ሁለት ወር ነው:: በላች በላችና ሆዷ ቢከማች አረገዘች ትላለች:: ሲያረጁ አምባር ይዋጁ ያሉኝል ብላ፡እንድም ደግ ሰው ናትና ጊዜው ይግለጠው ብላ:: ምን እያሉ ይሰድቧት ነበር ቢሉ::

ዕፁተ ማሕፀን ይብለተ አጥባት ንጥእተ በረከት:: በቅሉ ከወሰዷት በኋላ ወልዳ አታውቅ እያሉ ይገደሯት ነበርና::

ወበጽሐ ወርኃ ለኤልሳቤጥ ከመ ትለድ:: ኤልሳቤጥ ትወልድ ዘንድ ወራቷ ደረሰ ወወለደት ወልደ:: ወንድ ልጅን ወለደች::

ወሰምዑ አዝማዲሃ ወአግዋሪሃ ከመ አዕበየ እግዚአብሔር ሣህሉ ላዕሌሃ:: ላቲ ሲል ነው:: ይቅርታውን እንዳበዛላት ሰሙ:: ወተፈሥሑ ምስሌሃ:: ከሷ ጋራ እንደሷ ደስ አላቸው በሙያው በግብሩ:: መካን ዘመዳቸው ብትወልድ::

ወእምዝ አመ ሰሙን ዕለት መጽኡ ከመ ይግዝርዎ ለሕፃን:: በስምንተኛው ቀን ዮሐንስን ይገዝሩት ዘንድ መጡ::

የሊቀ ካህናት ልጅ ነውና መጡ አሉ:: ጌታን ግን ወሰድዎ ይላል:: ይህንም ወሰድዎ ይላል::

ወሰመይዎ በስመ አቡሁ ዘካርያስ:: በአባቱ ስም ዘካርያስ አሉት በፋሲል ፋሲል በኢያሱ ኢያሱ እንዲሉ::

ወአውሥአት እሙ:: እናቱም መለሰች::

ወትቤ አልቦ አላ ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ:: ስሙ ዮሐንስ ይባል እንጂ አይሆንም አለች::

ወይቤልዋ አልቦ እምአዝማድኪ ዘዘሰመየ ስም:: ከዘመዶችሽ እንዲህ ያለ ስም ያለው ሰው የለምን? አሏት:: አንድም ከዘመዶችሽ እንዲህ ያለ ስም ያለው ሰው የለምና መልካም ነው አሏት::

ወቀጸብዎ ለአቡሁ ሴት ብታወት በወንድ ያልቅ እንዲሉ ዘካርያስን ጠየቁት::

መነ ትፈቅድ ይሰምይዎ:: ማን ይሉት /ይባል/ ዘንድ ትወዳለህ አሉት ወሰአለ ሰሌዳ ብራና ዳምጣችሁ ብዕር ቀርጻችሁ ስጡኝ ብሎ ለመነ /ጠየቀ/:: አልፋው: አ: ነው ያሉ እንደሆነ ለመነ:: ዐይኑ: ዐ: ነው ያሉ እንደሆነ ደመጸ ጻፈ::

ወጸሐፈ እንዘ ይብል ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ:: ስሙ ዮሐንስ ይባል ብሎ ጻፈ::

ወአንከሩ:: አደነቁ ቃሏና ቃሉ አንድ በመሆኑ::

አንድም የሚቀድመው ቀለም አለ:: ዮሐንስ ይሰመይ:: ስምንቱን ቀለም ጽፎ ሲጨርስ:: አንድም ዮሐንስ ይሰመይ ስሙ:: አሥሩን ቀለም ጽፎ ሲጨርስ አንደበቱን ፈትቶለታል:: የአሥሩ ቃላተ ኦሪት ምግብና (ሥርዓት) ሲፈጸም ሰው ሁሉ ከማዕሠረ ኃጢአት እንዲፈታ በሐዲስ ቋንቋ እንዲናገር ለማጠየቅ::

ተከሥተ አፉሁ ወነበበ ልሳኑ:: አንደበቱ ረትቶለት ተናገረ::

ወባረከ ለእግዚአብሔር:: እግዚአብሔርን አመሰገነው:: ከዚህ ሰዓት ያደረስከኝ ከደዌዬ የፈወስከኝ ልጅ የሰጠኸኝ ብሎ::

ወአንከሩ:: አደነቁ አንደበቱ በመፈታቱ::

ወኮነ ፍርሐት ላዕለ ሰብአ ውእቱ ብሔር:: በዚያ አገር ባሉ ሰዎች ፍርሐት አደረባቸው:: ወተናገርዎ ለዝንቱ ነገር ውስተ



ኵሉ ብሔረ ይሁዳ:: በይሁዳ አውራጃ ሁሉ ይህን ነገር ተጨዋወቱት::

ወዐቀብዎ ውስተ ልቦሙ:: በልቡናቸው አስተዋሉት::

ወይቤሉ ምንትኑ እንጋ ይከውን እምዝንቱ ሕፃን:: ከዚህ ሕፃን የተነሣ ምን ይሠራ ይሆን አሉ::

እስመ እግዚአብሔር ላዕሌሁ:: ሥልጣነ እግዚአብሔር አድሮበታልና:: ጌታ እንጂ ለነገሩ መስላል ይፈልግለታል ኖኅ አበ እንጋድ ሲሆን በመወልዲቱ ፊት ቆሞ አመሰገነ:: ዓይኑን ቢገልጠው በቤቱ ብርሃን መላ:: ሙሴ ሊቀ ነቢያት ሲሆን በፊቱ ብርሃን ተሰጦበት ተወለደ:: ዳዊት ሥርወ መንግሥት ሲሆን አንበሳ በርግጫ ነብር በጡጫ ይገድል ነበር:: ይህም ሲጸንስ ያባቱን አንደበት አሠረ:: ሲወለድ ያባቱን አንደበት ፈታ ብለሁ::

ወመልዐ መንፈስቅዱስ ላዕለ ዘካርያስ:: ተሰይቶት አይደለም ተናገረ የሚል ነውና::

ተነበየ ወይቤ:: ተነበየ ብሎ አንድ አርእስት: ይቤ ብሎ ሁለት አርእስት: ተናገረ: ለሁለቱም ያመጣል::

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል:: የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን:: ለቀረበው አመጣ:: ይቤ ላለው::

ዘተሣሀለነ ወገብረ መድኃኒተ ለሕዝበ ዚአሁ:: ይቅር ያለን ለወዳጆቹ /ለወገኖቹ/ ድኅነትን ያደረገልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን:: በኃላፊ ተናገረው ዕርቅ ተጀምሯልና::

አንሥአ ለነ ቀርነ መድኃኒትነ እምቤተ ዳዊት ገብሩ:: ከባርያው ከዳዊት ወገን የምንድንበትን ንጉሥ አስነስቶልናልና /ያስነሣልን/ ይትባረክ:: ቀርን: ንጉሥ ሥልጣን በቁሙ: ቀንድ ይሆናል:: ቀንድ ያለው እንስሳት በቀንዳቸው ከአራዊት እንዲጠበቁ እኛም የሱን ስም ጠርተን ከአጋንንት እንጠበቃለንና:: ብከ ንወግዖሙ ለኵሎሙ ፀርነ እንዲል::

በከመ ነበበ በአፈ ነቢያቲሁ ቅዱሳን እለእምዓለም:: በዚህ ዓለም ባሉ በነቢያት ቃል እንደተናገረ:: እለ እምአዳም ከአዳም ቢተወለዱ:: እለ እምቅድም /እምጥንት/ ከጥንት ጀምረው በነበሩ በነቢያት በካህናት እንደተናገረ::

ከመ ያድኅነነ እምእደጸርነ። ከሠራዊተ አጋንንት ያድነን ዘንድ ወእምእደኵሎሙ እለይጸልኡነ። ከሠራዊተ አጋንንት ከሊቃነ አጋንንት ያድነን ዘንድ።

ከመ ይግበር ሣህሎ ምስለ አበዊነ። ከአባቶቻችን ጋር እንደ አባቶቻችን ሳባቶቻችን አደርገዋለሁ ያለው ይቅርታውን ያደርግ ዘንድ።

ወከመይዘከር ኪዳኖ ቅዱስ፡ ክቡር መሐላውን ያስብ ዘንድ።

መሐላሁ ዘመሐለ ለአብርሃም አቡነ። ይኸውም ለአብርሃም የማለው መሐላ ነው። ክቡር መሐላውን ያስብ ዘንድ።

ከመ የሀበነ በዘኢንፈርሖ እምእደ ጸርነ። ከጠላቶቻችን እጅ በማንፈራ ገንዘብ አለመፍራትን ይሰጠን ዘንድ። አንድም በጠላቶቻችን እጅ የተወረወረ ፍላጻ ያገኘናል ብለን በማንፈራ ገንዘብ የማንፈራብትን ይሰጠን ዘንድ። አንድም የሀበነ መድኃኒተ ይላል። ከጠላቶቻችን ከአጋንንት እጅ አስሰቅቶ ሥጋውን ደሙን ይሰጠን ዘንድ።

ያድኅነነ ናምልኮ በጽድቅ ወበርትዕ። ያድነን ዘንድ በአራት በወንጌል ጸንተን እናገለግለው ዘንድ።

በቅድሜሁ ወበኵሉ መዋዕሊነ። ባለ በዘመናችን እሱ ባወቀው ነገር ጸንተን በአራት በወንጌል እናገለግለው ዘንድ። ከአጋንንት እጅ አስሰቅቶ ሥጋውን ደሙን ይሰጠን ዘንድ።

መሐላሁ ዘመሐለ ለአብርሃም አቡነ። ይኸውም ለአብርሃም የማለው መሐላ ነው። ክቡር መሐላውን ያስብ ዘንድ። ከሠራዊተ አጋንንት ያድነን ዘንድ። በዚህ ዓለም ባሉ በነቢያት ቃል እንደተናገረ። ከባሪያው ከዳዊት ወገን የምንድንበትን ንጉሥ ያስነሣልን ይቅር ይለን ዘንድ ለወገኖቹ ድኅነትን ያደረገ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።

ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ። ይቤ ያለውን ጨርሶ፡ ተነበየ ላለው አመጣ። አንተም ማም (ልጅ) ልዑል እግዚአብሔር የሾመህ መምህር ትባላለህ አለ።

እስመ ተሐውር ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ትጺሕ ፍኖቶ። ጎዳናውን ትጠርግ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ትሄዳለህና። ፍኖት



ልበ እስራኤል፡ መጥረግ ከእኩያት ከፍትወታት ከኃጣውእ። ቅድመእግዚአብሔር፡ መንፈቅ ዕንስ መንፈቅ ማስተማር ይቀድመዋል።

ከመተሀበሙ ለአሕዛብ ያእምሩ መድኀኒቶሙ። መድኃኒታቸው ክርስቶስን ሊያውቁ ታስተምራቸው ዘንድ። ወሀብከሞሙ ቃለ ዘወሀበከኒ እንዲል።

አንድም ነዋ በግዐ፡ ብለህ ትዳርጋቸው ዘንድ።

በዘያትኀድግ ሎሙ ኃጢአቶሙ። ኃጢአታቸው በሚሠረይበት (በሚሠረይላቸው) ገንዘብ ክርስቶስን ሊያውቁ።

በሣህሉ ወበምሕረቱ ለአምላክነ። በፈጣሪያችን በይቅርታው በቸርነቱ። ለዘሐወጸነ እምአርያም። ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በጎበኘን በፈጣሪያችን በይቅርታው በቸርነቱ።

ወሠረቀ ከመ ያርእዮሙ ብርሃና። ብርሃንነቱን ብርሃን መለኮቱን ይገልጥ ዘንድ።

ለእለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት በድንቁርና።

ወጽላሎተ ሞት። በቀቢጸ ተስፋ ለነበሩ ሰዎች ዕውቀትን ልጅነትን ይገልጥላቸው ዘንድ።

አንድም ውስተ ጽልመት። በራሳቸው ፍዳ የተያዙትን።

ወጽላሎተ ሞት። በራሳቸው ፍዳ ሳይ በእናት ባባታቸው ፍዳ ለተያዙት ሰዎች ብርሃንነቱን ብርሃን መለኮቱን ይገልጥላቸው ዘንድ።

ከመ ያርትዕ እገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም። እግረ ልቡናችንን ወደ ወንጌል ጎዳና ያቀና ዘንድ፡ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በጎበኘን በፈጣሪያችን በይቅርታው በቸርነቱ ኃጢአታቸው በሚሠርይላቸው ገንዘብ ይሠረይላቸው ዘንድ ክርስቶስን ሊያውቁ፡ ነዋ በግዑ ብለህ ትዳርጋቸው ዘንድ። ጎዳናውን ትጠርግ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ትሄዳለህና። አንተም እንጂ ማሞ /ብላቴና/ ልዑል እግዚአብሔር የሾመህ መምህር ትባላለህ።

## ፲፭. ጸሎተ ስምዖን ነቢይ

ስምዖን ማለት ሰምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነው።

ታሪክ በጥሊሞስ የሚባል የጽርዕ የፋርስ ንጉሥ ነበር። ልጅ አልነበረውም ከሞቱ በኋላ ስም የሚያስጠራ ምን አለ ብሎ ጠየቀ የአይሁድ ፶፻ቱ ብሉያት መጻሕፍት አሏቸው ያንን በጽርዕ ምላሽ አጽፈው አሉት። ጥበበ እግዚአብሔር ነው። አይሁድ ሥጋዌ ወልደ እግዚአብሔር አልደረሰም ብለው ቢፋቁት በጽርዕ ምላሽ እንዲገኝ መጻሕፍቱንም ጸሐፊቱንም ስደዱልኝ ብሎ ላከ። ንጉሥ ነገሥት ነውና ለደዱለት። ፸ ናቸው ቢሉ ፴፫ ድንኳን ፸፪ ናቸው ቢሉ ፴፮ ድንኳን ሰጣቸው። የሁለቱንም ቋንቋ የሚያውቅ አንድ ሰው በመካከላቸው አኖረ። በዕጣ (በክፍል) መጽሐፈ ኢሳይያስ ለስምዖን ደረሰ። አንድም መምህሩ ነውና የእነቱ ልጅ ነውና ያባትህን መጽሐፍ ማን ይጽፍልህ አሉት። ሲጽፍ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ ከሚለው ደረሰ። ይህን ንጉሥ ፈላስፋ ነው፡ ይነቅፈኛል ብሎ። ወለት ትጸንስ ብሎ ጻፈ። መልአኩ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ብሎ ጻፈበት ጸሐፊ የጻፈውን ዘወር ብሎ ማየት ልማድ ነው። ዞሮ ቢያይ ድንግል ትጸንስ ብሎ ጽፎበት አገኘው። ማነው እንዲህ የሚያደርግብኝ ብሎ ወቅለምቱን /ምላጩን ቢለዋውን/ እንሥቶ እፍቃለሁ ሲል እንደ እንቅልፍ ወደብ አደረገው። ይህን የተጠራጠርከውን ሳታየው አትቀርም /አትሞትም/ ተወው አለው። ከዚያ በፊት ፫፻ ዘመን ነበረው ቢሉ ከዚያ በኋላ ፫፻ ዘመን ከዚያ በፊት ፫፻ ዘመን ነበረው ቢሉ ከዚያ በኋላ ፫፻ ዘመን እንደ ትኋን ካልጋ ተጣብቆ ኖሯል። ጌታ በተወለደ በ፵ ቀን ዮሴፍ ሰሎሜ እመቤታችን ይዘውት ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ። ያ ሳታየው አትሞትም ያልኩህ ከቤተ መቅደስ አለልህ አለው። እንደ ትኋን ካልጋ ተጣብቆ የነበረ የ፴ ዘመን ጎልማሳ ሆኖ ተነሥቶ ፳ቱን ፮ቱን ቆመ ብእሲ መር መር እያለ /እየተራመደ/ መጥቶ ከእመቤታችን ክንድ ሕፃኑን ተቀብሎ ይህን ተናግሯል። ስምዖን የተናገረው ነገር ይህ ነው።



ይእዜ ትስዕሮ ለገብርከ። ሰዐሮ ሲል ነው። ወትገብራ ለደብተራ ያለውን ግበራ ብሎ እንደተረጐመው። እኔን ባርያህን በሞት አሰናብተኝ።

በሰላም እግዚእ በከመ አዘዝከ። መሬት አንተ ወትገብዕ ውስተ መሬት ብለህ እንዳዘዝክ በፍቅር ሳለሁ አሰናብተኝ። ከዋሉ ካደሩ ጸብ አይቀርምና /አይታጣምና/። አንድም ፃር ጋር ሳይበዛብኝ። ሸማግሌ ሆኖ ከዋሉ ካደሩ ፃር ጋር አይታጣምና። አንድም ሳታየው አትሞትም እንዳ ማለት የፍቅር አነጋገር ነው። ሳታየው አትሞትም ብለህ እንደተናገርህ።

እስመ ርእያ አዕይንትየ አድኅኖተከ። ዓይኖቼ ልጅህ ክርስቶስን አይተዋልና፡ አድኅኖት አለው በግብሩ።

ዘአስተዳሎከ ቅድመ ኩሉ ሕዝብከ። በኩረ ምእመናን አድርገህ ያዘጋጀኸውን።

አንድም እስመርእያ ቅድመ ኩሉ ሕዝብከ። በዮሴፍ በሰሎሜ በእመቤታችን ፊት አይተዋልና። አንድም እንግዲህ ወዲህም በሚነሡ ምእመናን ፊት አይተዋልና።

ከመ ትክሥት ብርሃነ ለአሕዛብ። ሃይማኖትን ለአሕዛብ።

ወክብረ ለሕዝብከ እስራኤል። ልጅነትን ለእስራኤል ትገልጥ ዘንድ። አንድም ከመ ትክሥት ብርሃነ ለአሕዛብ። እሪትን ለአሕዛብ።

ወክብረ ለሕዝብከ እስራኤል። ወንጌልን ለእስራኤል ትገልጥ ዘንድ። ይህ መለያየት አይደለም።

ከመ ትክሥት ብርሃነ ወክብረ ለአሕዛብ ወለእስራኤል ማለት ነው።

***ተፈጸመ ትርጓሜ መኃልየ ፲ቱ ወ፭ቱ ነቢያት በሰላመ እግዚአብሔር አሜን።***

## ከዚህ ቀጥሎ ከአንድምታው ትርጉም የወጡ ጥቅሶችን ይመልከቱ።

፩. ወእንዘ ቀዑ ተመሰጠ ሕፃኑ:- ልጁ ሕፃን ሳለ ፈጥኖ በሞት ተነጠቀ።
ወእንዘ በቆዑም ይላል:- ልጁ በሕፃንነቱ ሳለ በሞት ተነጠቀ ጥበብ ፲፬:፲፭-፲፮።

፪. ወይጼሊ ለከ እስመ ከመ ነቢይ ውእቱ። ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልይልሃል ትድናለህም ዘፍ ፳:፯።

፫. ቦ ዘወድቀ ውስተ አየር ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ወቦ ዘወድቀ ውስተ አንጦርጦስ /እንጦርጦስ/ ዘውእቱ መትሕተ ታሕቲት። በአየር ላይ ተንሳፎ የወደቀ አለ። በምድርም ላይ የወደቀ አለ በእንጦርጦስ ውስጥም የወደቀ አለ። ይህም የታች ታች ። /ከጥልቆች በታች ያለ ጥልቅ ነው/ እንዳለ አክሲማሮስ /ሥነ-ፍጥረት/።

፬. ወፈውስ ኵሉ ፍጡር ጊሜ። የሰው ሁሉ ሕይወቱ ዝናብ ፈጥኖ ቢዘንም ነው: ዝናብም ወደ ምድር በወረደ ጊዜ ደስ ያሰኛል: እንዳለ ሲራክ ፵፫:፳፪-፳፫።

፭. መልአክኒ ኢያእመረ ዕለተ ትስብእቱ ለቃል ወአልቦ ዘአእመረ እምእለ ሀለዉ ውስተ አርያም ዕለተ /ምሥጢረ/ ምጽአቱ ለቃል ወሥርዓተ ዘገብሮ እግዚእ። መልአክም ጌታ ሰው የሆነበትን ቀን ሰውንም ስለመውደዱ ጌታ ሰው ሆኖ የሠራውን ሥራ በአርያም ካሉ መላእክትም ማንም ሰው መሆኑን አላወቀም እንዳሉ ኤጲፋንዮስ እና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት /ዘእንዚናዙ/ በሃይማኖት አበው።

፮. ወይሜምዑ ፲ቱ፻ እምኔክሙ እምድምፀ አሐዱ። ከአንድ ሰው ድምፅ ወይም ዛቻ የተነሣ ሺህ ሰዎች ይሸሻሉ: ኢሳ ፴:፲፯።

፯. ሣህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ። አቤቱ በመልካሙ ጊዜ ጸሎቴ ወደ አንተ ነው እንዳለ ክቡር ዳዊት መዝ ፷፱:፲፫።



፰. ኢይባእ ሞዓባዊ ወአሞናዊ። አሞናዊና ሞዓባዊ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ ዘዳ ፳፫:፫-፬: ዘፍጥ ፲፱:፴፯-፴፰።

፱. እስመ ጉልቄ ሳብዕ (፯ቱ) ፍጹም ውእቱ በኀበ ዕብራውያን። በዕብራውያን ሰባት ቍጥር ፍጹም /መጨረሻ/ ነው: እንዳለ ሳዊሮስ: ዘአንጾኪያ በሃይማኖተ አበው።

፲. ዘያነሥኦ እምድር ለነዳይ ወያሌዕሎ እመሬት ለምስኪን። ችግረኛውን ከመሬት የሚያነሣ ምስኪኑንም (ጦም አዳሪ ደሀውን) ከፍ ከፍ የሚያደርግ እንዳለ ክቡር ዳዊት በመዝ ፻፲፪:፯-፰

፲፩. ኢይጠፍእ ምስፍና ወምልክና እምእባሉ ለይሁዳ። በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም ዘፍ ፵፱:፲

፲፪. እስከዝየ ብጽሒ ወኢትትዐደዊ እምወሰንኪ ዳዕሙ ይትከወስ ማዕበልኪ በውስቴትኪ። እስከዚህ ድረሺ አትለፊ ማዕበልሽ ገደብ ይሁን አልሁ: ለባሕርም ዳርቻዋን በወሰነ ጊዜ ውሃ ከትዛዙ እንዳያልፍ። ኢዮ ፴፰:፲፩-፲፪ ምሳሌ ፰:፳፱ ኤጲፋንዮስም: ይህንን ቃል በመጽሐፈ ቅዳሴው ወስዶታል።

፲፫. አነ ውእቱ ዘአሠርቅ ፀሐየ። ናቡከደነፆር ያለ እኔ ሌላ ንጉሥ የለም በዚህ ዓለምም ፀሐይን የማወጣ ፈጣሪ እኔ ነኝ ብሎ ኮራ ከትዕቢቱም ብዛት የተነሣ እንዲህ አለ። መጽ መቃ ቀዳ ፳:፫-፬።

፲፬. እምትጥስዮሙ ለእሉ ሕዝብከ ጠስየኒ ሲተ እመጽሐፈ ሕይወት። ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ: ዘጸአ ፴፪:፴፪-፴፫።

፲፭. አልቦ ዘገብረ በዓለ ዘከመ ገብረ ኢዮስያስ። ከነቢዩ ከሳሙኤል ዘመን ጀምሮ እንደ ኢዮስያስ ያለ ፋሲካን ያደረገ የለም መጽ: ዜና መዋ: ካልዕ ፴፭:፲፰-፲፱።

፲፮. አንስ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። እኔ እግዚአብሔር ባልኩ ጊዜ ስለ አብ

ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ እናገራለሁ እንዳለ ባስልዮስ በሃይማኖተአበው። ተናጋሪው ግን ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ነው።

፲፯. ነፍሶሙስ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፎሙ ሥቃየ /እሳተ/ ዝሀንም። የጻድቃን ሰዎች ነፍስ ግን በእግዚአብሔር እጅ ናት። የኃጢአተኞች መከራ አላገኛ ቸውም፡ ጥበ ፫:፩-፪።

፲፰. እስ ውስተ ሲኦል ጸእ ወእስ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ /ነጽሩ/። በሲኦል ውስጥ ያላችሁ ውጡ በጨለማ ውስጥ ያላችሁም ውጡ ተገለጡ። ኢሳ ፵፱:፱ እንዳለ ባስልዮስ ዘአንጾኪያና ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በሃይማኖተአበው።

፲፱. ወእሦጡ ቀሳውስቲሆሙ ዕራቆ። ታላላቆችም ብላቴናዎቻቸውን ወደ ውሃ ሰደዱ ወደ ጉድጓድ መጡ ውሃም አላገኙም እቃዎቻቸውንም ባዶውን ያዙ ተመለሱ እንዳለ÷ኤር ፲፬:፫።

፳. ወፍናሠርክ ይበርህ ብርሃን ፀሐይ። በዚያም ቀን በረዶና ውርጭ እንጂ ብርሃን አይሆንም አንድ ቀንም ይሆናል እርሱም በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ይሆናል ሌሊትም አይሆንም ሲመሽም ብርሃን ይሆናል። ዘካ ፲፬:፮-፯

፳፩. ሠረይን ሰብአ ወኢያሕየውን /ወኢያሕዮን/ ፈወስናሃ ለባቢሎን ወኢትፈወሰት። ባቢሎን በድንነት ወድቃ ጠፍታለች አልቅሱላት ትፈልግም እንደሆን ለቁስሏ መድኃኒት ውሰዱላት ባቢሎንን ፈወስናት እርሷ ግን አልተፈወሰችም ኤር ፶፩:፰-፲።

፳፪. ወትፈትዉ አሐተ ዕለተ እመዋዕሊሁ ለወልደዕጓለ እመሕያው። ከሰው ልጆች ቀኖች አንዱን ልታዩ የምትመኙበት ወራት ይመጣል አታዩትም ሉቃ ፲፯:፳፪

፳፫. ንሕነስ ንትዌለጥ በምዕር ከመ ቅጽበተዓይን ወኢንበጽሖሙ ለሞዉታን። የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገትእንደ ዓይን ጥቅሻ እንለወጣለን /እንነሣለን/ መለከት ይነፋልና።



ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን፡ ፩ ቆሮ ፲፭:፶፪-፶፫

፳፬. ወርእየ ሕልመ አቡሁ ነበሮ ማቴሳላ። ማቱሳላም የአባቱ የሄኖክን ነገር በሰማ ጊዜ ሥራውን ሁሉ በሥውር ገለጠለታልና ነገሩን ሰምቶ ተመለሰ። ሄኖ ፹፩:፳፩-፳፪።

፳፭. አጸምዕ /አጽንን/ ለዝንቱ ወልድየ ለርእየ ሕልመ አቡከ። ልጄ ማቱሳላ ነገሬን ስማኝ። የአባትህንም ህልም ለመስማት ጆሮህን አቅርብ ሄኖ ፹፪:፪-፬

፳፮. ነጸርኩ ኀበ ሰማይ ሕዋሳት ዘበምንት መላዱ ወጠን ፍናት ነበረ። ሕዋሳትን የፈጠረ ጌታ ትሕትናን የዕለት ጽንስ ዘመሆን እንደጀመረ አወቅ እንዳለ አረጋዊ መንፈሳዊ።

፳፯. ምንት አዕምጽአ ለእግዚእየ ኀበ ገብሩ። እርናም ጌታዬን ንጉሡን ወደ ባሪያው ያመጣው ምክንያት ምንድር ነው ፪ ሳሙ ፳፬:፳-፳፪

፳፰. ውእቱስ ንጹሕ እምነ ዕተ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርዕ ወሩካቤ ወሰስሎተ ድንግልና እስ ሥሩዓን በዕጓለ እመሕያው ወእሙራን ቦሙ። በሰው ዘንድ ከተሠሩ ከታወቁ ከሦስቱ ግብራት ንጹሕ ነው። እነዚህም ዘር ሩካቤ የድንግልና መለወጥ ናቸው እንዳለ ሱኑትዩ በሃ አበው።

፳፱. ወአሰሲቶ ፸ ዓም እትቤቀሎ ለንጉሠ ባቢሎን ወለኩሉ ሰብእ። ሰባው ዓመትም በተፈጸመ ጊዜ የባቢሎንን ንጉሥና ያንን ሕዝብ ስለ ኃጢአታቸው እቀጣለሁ ኤር ፳፭:፲፪-፲፭።

፴. ደቂቅከኒ ይነብሩ ፈላሰያን ውስተ ምድረ ነኪር ፬፻ ዓመተ። እግዚአብሔር አብርሃምን አለው። ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፡ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል። ዘፍ ፲፭:፲፫።

፴፩. ኀበ ያዕቆብ ኀድረ ወኀበ እስራኤል ተዋረሰ። የያዕቆብን ሥጋ ተዋሐዷ ከእስራኤልም በነሳሸው ሥጋ ሁሉን ግዢ አለኝ። ሲራክ ፳፬:፰-፱።

፴፪. በዘርዕከ ይትባረኩ ኩሉሙ አሕዛበ ምድር:: የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ:: ዘፍ: ፳፪:፲፰::

፴፫. እስመ እምፍሬ ከርሥከ እነብር ዲበ መንበርከ:: ከወገብህ የሚወጣው ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ መንግሥቱንም አጸናለሁ ፩ኛ ሳሙ ፯:፲፪-፲፯::

፴፬. እን እግዚአብሔር ዘእፈጥር መካነ ወዘአወልድ:: በሁኑ ወደ መውለድ የማደርስ እኔ አላስወልድምን? ማሕፀንን እኔ እዘጋለሁን? ኢሳ ፷፮:፱-፲::

፴፭. ምክንትለ ኢተውህባ ለብእሲት ዳዕሙ ትማስን /ትመውት/ በግብረ እደዊሃ ዘእንበለ ውሉድ:: በእጆዋ በሠራችው ሥራ ልጅ ሳትወልድ ትሞታለች እንጅ ለሴት ምክንት አልተሰጣትም ነበር: ሄኖክ ፴፮:፲፱-፳::

፴፮. ብከ ንወግዖሙ ለኩሎሙ ጸርነ:: በአንተ ጠላቶቻችንን እንዋጋቸዋለን መዝ ፵፫:፭

፴፯. ወሀብክዎሙ ቃለ ዘወሀብከኒ:: የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና እነርሱም ተቀበሉት: ዮሐ ፲፯:፰::

***ከአንድምታው ትርጓሜ በምዕራፍና በቍጥር የተዘጋጁ ጥቅሶች በዚህ ተጠቃለለዋል::***



# ክፍል ፪

<u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ አሜን</u>

<u>እዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ጽሒፈ ሐተታ መኃልየ</u>

<u>፲ቱ ወ፰ቱ ነቢያት</u>

<u>በአብ ስም አምኜ አብን ወላዲ ብዬ: በወልድ ስም አምኜ</u>

<u>ወልድን ተወላዲ ብዬ: በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ</u>

<u>መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብዬ:</u>

<u>የ፲፰ቱ ነቢያት መኃልይን ማብራሪያ መጻፍ እጀምራለሁ</u>

## መኃልየ ነቢያት ወጸሎቱ ለሙሴ
## አንቀጽ ፩
## ስለ መኃልይ

መኃልይ፡- ማለት ምስጋና ግጥም ቅኔ ማለት ነው። ምስጋናውም በሁለት ይከፈላል። በዜማ በግጥም /በስንኝ/ ምስጋናውንም የሚያቀርብ ሁሉም በየቋንቋው ነው። ሁሉም በየቋንቋው ስንል በእግዚአብሔር ምሳሌ ከተፈጠረው የሰው ዘር የመጀመሪያ አባት ከሆነው ከአዳም በፊት ቀድመው ከተፈጠሩ ከአዕዋፍ ዘሮች መጥቀስ ይቻላል። ዜማቸው /ድምጻቸው/ ምግረና ደስ የሚያሰኝ አዕዋፍ እንዳሉ መጻሕፍት ያስረዳሉ።

አዕዋፍ ዘሠናይ ዜማሆሙ እንዲል። ጥበ ፲፱:፲፰። በድጋሚም ዖፍ ዘይብልዎ አሮድዮን /እልአሮድዮን/ እንዲል።

ታሪክ አሮድዮን የሚባል ወፍ አለ። እጅግ ድምፀ መልካም ነው። ሰው ከሚኖርበት ወደ በረሀ ሔዶ ይኖራል። እሱም ከዜማው ደስ ማሰኘቱ የተነሣ ምግብ መልቀሙን እስኪዘነጋ ድረስ ድምፁን ያሰማል። መንገደኛውም ሁሉ የየራሱን መንገድ /ጉዞ/ ይዘነጋል። ማር ይሥ አንቀጽ ፳፰ ምዕ፫።

ነቢያትም ብዙዎች በዓለም የተወሰኑ ቢሆኑም ወይም በዓለም ተወስነው ልጆችን ወልደው ቢኖሩ እነሱ ከሰው ዘር ተገኝተው ዘርን /ልጅን/ ለዓለም ቢተኩ የዚህን ዓለም መንገድ ብቻ ሳያክተሉ ሰብአ ዓለም ከገቢረ ኀጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እንዲመለሱ ከእግዚአብሔር የታዘዙትን መልእክት ከመፈጸምና ትንቢትን ከመናገር ወደ ኋላ አላሉም።

በከመ ነበበ በአፈ ነቢያቲሁ ቅዱሳን እለ እምዓለም እንዲል። ሉቃ ፩:፸ ስለዚህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በየዘመናቸው በመንፈሳዊ ዜማ /ምስጋና/ እንዲሁም በግጥም እግዚአብሔርን አመስግነዋል። ለምሳሌ፡-

፩. እስራኤል ከባርነት ወደ ነፃነት ሲሸጋገሩ ንሴብሖ ብለው አመስግነዋል። ዘጸ ፲፭:፩-፳። ይህ በዘመነ መሳፍንት ነው። ከካህናት ሙሴና አሮን ሙሴ መስፍን ሲሆን አሮን ካህን ነው።



፪. በዘመነ መሳፍንት፡ ከመሳፍንት ባርቅና ነቢይት ዲቦራ በጠላቶቻቸው ላይ ድልን በተቀዳጁ ጊዜ የተቀኙት ቅኔ አለ። ነገሥታት ሆይ ስሙ፡ መኳንንት ሆይ አድምጡ፡ እኛ ለእግዚአብሔር እንቀኛለን። ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔርም እንዘምራለን ብለው በምስጋና ተቀኝተዋል። መሳ ፭:፩

፫. በዘመነ ነገሥት፡ ከነገሥታት ዳዊትና ልጁ ሰሎሞን አመስግነዋል። የእግዚአብሔርን ስም አመሰግናለሁ። በምስጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ። መዝ ፷፱:፴
ንጉሡ ሰሎሞንም ከፍ ያለ ምስጋናን አመስግኗል። መኃ ፩:፩
የመኃልይን ሐተታ ማብራሪያ በዚህ አጠቃለን ነቢይ የሚለውን እንቀጥላለን።

### ስለ ነቢይ /ነቢያት/

ነቢይ ማለት ቃልን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለንጉሥና ለሕዝብ የሚናገር ማለት ነው። ለዚህ ማስረጃ አንድ የእግዚአብሔር ሰው በዚች ከተማ አለ። እርሱም የተከበረ ሰው ነው። የሚናገረውም ሁሉ በእውነት ይፈጸማል ይህም ሳሙኤል ነው። ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ቃልን ተቀብሎ ለሳዖል ሲናገር የእግዚአብሔርን ሕዝብ ትመራ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶሃል ብሎ አነገሠው ፩ኛ ሳሙ ፱:፯። ፩ኛ ሳሙ ፲:፩-፪ ነቢያትም ትንቢት ሲናገሩ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እያሉ ነው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ማዳኔ ሊመጣ ጽድቄም ሊገለጽ ቀርቧልና ፍርድን ጠብቁ ጽድቅንም አድርጉ ኢሳ ፶፮:፩-፪።

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የነገርኩህን ቃል ሁሉ በመጽሐፍ ጻፍ። ኤር ፴፪:፫።

የሰው ልጅ ሆይ ይህን መጽሐፍ ብላ አለኝ። አፌንም ከፈትሁ መጽሐፉንም አጎረሰኝ። እኔም በላሁት መጽሐፉም እንደ ማር ጣፈጠኝ ሕዝ ፫:፩-፴።

## ስለ ጸሎት /ታት/
## የጸሎት ዝርዝርና ጥቅሙ

ጸሎት:- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እንደሚገልጸው ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ለእግዚአብሔር ስለተፈጠረ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መገናኘት ይገባዋል። መገናኛውም ጸሎት ስለሆነ ይጸልያል። የክርስቲያን ጸሎት ወደ ክርስቶስ ነው። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የመገናኛ ምልክትና ማጽኛ ነው።

ጸሎት:- ሁሉ ኅብረትን ምስጋናን ስግደትን ንስሐን ልመናን ምልጃን ያጠቃልላል። በጸሎተ ዕጣን ጊዜ ሕዝቡ ይጸልዩ እንደነበር ካህኑ ዘካርያስም ጸሎትህ ተሰማ የሚል መልካም መልስ ማግኘቱን እንረዳለን። ሉቃ ፩:፲-፲፬። ክርስቶስም በቃልና በሥራ የጸሎትን መንገድ አስተምሮናል። ለምሳሌ ክርስቶስ በአንድ ቦታ ይጸልይ በነበረበት ወቅት ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በጠየቀው መሠረት አባታችን ሆይ የሚለውን ጸሎት አስተማረ። ሉቃ ፲፩:፩-፲፫።

እግዚአብሔር የልጆቹን ጸሎት በደስታ ይሰማልና ጸሎት ብዙ ኃይል አለው። ፩ ጴጥ ፫: ፲፪። እርስ በእርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ። የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለች ብሎ የጸሎትን ጥቅም መጽሐፍ ያስረዳናል። ያዕ ፭:፲፮-፲፰።

አለመጸለይ ኃጢአት ነው። መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ ብሎ ነቢዩ ሳሙኤል ለሕዝቡ አስተማራቸው። ፩ኛ ሳሙ ፲፪:፳፫

## ስለ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ልደት መመረጥና የግብጽ ተልዕኮ

ሙሴ:- ለወላጆቹ ሦስተኛ /የመጨረሻ/ ልጅ ነው። አባቱ እንበረም እናቱ ዮካብድ ይባላሉ። በሶስት ሺሕ ሰባት መቶ ሰልሳ ሦስት ዓመተ ዓለም ሙሴ በግብፅ ተወለደ። ለ፹ ዘመንም ያህል



በግ ሲጠብቅ ከኖረ በኋላ ሙሴ እንደልማዱ በጎቹን ሲጠብቅ እግዚአብሔር ሙሴን መርጦ በሲና ተራራ /በኮሬብ/ ተገልጦ በግብጽ አገር በባርነት የሚሠቃዩት እስራኤልን እንዲያወጣ አዘዘው። ከብዙ መቅሠፍት በኋላም ፈርዖን እስራኤልን ለቀቀ። እስራኤል የኤርትራን ባሕር በደረቅ ምድር ተሻገሩ። እስራኤል ከግብጽ የወጡት ስድስት መቶ ሺሕ ሆነው ነው። ይህ ቁጥር ሕፃናትንና ሴቶችን አይጨምርም ዘጸ ፲፪:፴፯-፴፱።

እስራኤል በግብጽ የኖሩበት ዘመን ፬፻፴ ዓመት ነው። ዘጸ ፲፪:፵-፵፩። ይህም ቁጥር የእስራኤል ልጆች እነሱም አባቶቻቸውም /አብርሃም ከነቤተሰቡ/ በከነዓንና በግብፅ የኖሩበት ዘመን ነው።

በተጨማሪም እግዚአብሔር አብርሃምን ከተነጋገረበት ቀን ጀምሮ ያዕቆብ ወደ ግብፅ እስከ ወረደበት ዘመን ድረስ ፪፻፲፭ ዓመት ይሆናል። ያዕቆብ ከግብጽ ከወረደበት ቀን እስከ ሙሴ ልደት ፻፴፭ ዓመት ይሆናል።

ከሙሴ ልደት እስራኤል ከግብጽ እስከ ወጡበት ጊዜ ፹ ዓመት ይሆናል። በጠቅላላው ፬፻፴ ነው። ሙሴም ከእግዚአብሔር ጋር ፭፻፰ ቃላተ ሕግን ተነጋግሯል። ማለትም እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው የሚለው ቃል ፭፻፰ ይሆናል።

ወእምድኅረሁ በ፹ቱ ፻ ወ፴ ክረምት መጽአት ኦሪት እንዲል። አብርሃም ከሞተ በኋላ በ፬፻፴ ዘመን ኦሪት ተሠራች። ገላ ፫:፲፯

ሐተታ: አብርሃም ተስፋውን በሰማ በ፳፭ ዓመት ይስሐቅን ወልዷል። ይስሐቅ መስከረም ፴ ተጸንሶ ሰኔ ፳፭ ቀን ተወለደ። ይስሐቅ በተወለደ በ፷ ያዕቆብን ወልዷል። ፹፭ ይኾናል። ያዕቆብ በተወለደ በ፻፴ ርደተ ግብጽ ሆኗል። ይህንም ገብተው ይቆጥሩታል። ያዕቆብ በተወለደ በ፹፫ ሌዊን ይወልዳል። ሌዊ በተወለደ በ፵፮ ቀዓትን ይወልዳል። ቀዓት በተወለደ በ፫ ርደተ ግብጽ ሆኗል። ፪፻፲፭ ይኾናል። ርደተ ግብጽ በሆነ በ፷፭ ቀዓት እንበረምን ይወልዳል። እንበረም በተወለደ በ፸ ሙሴን ይወልዳል።

ሙሴ በተወለደ በ፹ እስራኤል ከግብጽ ወጥተዋል፡፡ ፪፻፲፭ና ፪፻፲፰ ፱፻፴ ያኽናል፡፡ በ፱፻፴ ዘመን አራት ተሠራች ያለኘው ይህ ነው፡፡

## ስለ እስራኤል ከግብፅ አወጣጥ

እስራኤል ከግብጽ የወጡበት ምክንያት ጌታ ለአብርሃም የነገረው ተስፋ ሲፈጸም ነው፡፡ ደቂቅከኒ ይነብሩ ፈላስያነ ውስተ ምድረ ነኪር ወይቀንይዎሙ ግብጽ ፬ተ ፻ተ ዓመተ ወእምዝ ይወጽኡ፡፡ /ልጆችህ በባዕድ አገር ይኖራሉ ግብጻውያንም አራት መቶ ዓመት ይገዟቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላም ይወጣሉ ባለው ቃል ኪዳን መሰረት ሲሆን አራት ነገሮችንም በመጠበቃቸው ነው፡፡

፩. ግዝረትን ስለአልተው
፪. ስማቸውን ስላልለወጡ
፫. ቋንቋቸውን ስላላጠፉ
፬. ተስፋቸውን ስላልገለጡ ነው

እስራኤል ከግብፅ የወጡበት ዘመን በሦስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሦስት ዓመተ ዓለም ነው፡፡ መጋቢት ፳፫ ረቡዕ ቀን እስራኤል በጉን በልተው መጋቢት ፳፬ ቀን ሐሙስ ከግብጽ ወጥተዋል፡፡ በዕብራውያን አቆጣጠር ሚያዚያ ፲፬ በጉን በልተው በ፲፭ ወጥተዋል፡፡

## ስለ ኤርትራ

ኤርትራ በግብጽና በዐረብ መካከል ያለ ባሕር ነው፡፡ ከብርቱካይድ እስከ ባብአልመንደብ ያለ ባሕር ቀይ እሳት የሚመስል ቀይነት /ቅላት/ ያለው ባሕር ነው፡፡ መሬቱ ቀይ ስለሆነ ቀይ ሰልባቦት ይንሳፈፍበታል፡፡ ቀያይ ዓሣ ይወለድበታል፡፡ በዙሪያውም ቀያይ ሣር ቅጠል ያበቅላልና ቀይ ያሰኘው ይህ ነው፡፡

ባሕርነቱ ከሜዲተራኒ እስከ ህንድ ውቅያኖስ ገጥሞ ተያይዞ በስተምሥራቅ እስያንና አፍሪካን ይለያል፡፡ ዘጸ ፲:፲፱:: ፲፫:፲፰:: ፲፭:፬::



## ስለ ፈርዖናውያን

ፈርዖን ማለት የኢትዮጵያ ነገሥታት አፄ ይባሉ እንደነበር ከጥንት ጀምሮ የድሮ ዘመን የግብጽ ነገሥታት ፈርዖን ይባሉ ነበር፡፡ የሮም ነገሥታት ቄሳር የገሊላ ሄሮድስ እንደሚባሉ በብሉይ ኪዳንም የተጠቀሱት ፈርዖኖች በመጠሪያ ስማቸው ሳይለዩ በዚህ ማረግ ይጠሩ ነበር፡፡

## የ፫ቱ ፈርዖኖች ልዩ ስም እንደሚከተለው ነው

፩. በአብርሃም ጊዜ /ዘመን/ የነበረው ፈርዖን ልዩ ስሙ ሳኖሪስት /ሴስስትሪስ/ ይባላል፡፡ አብርሃም በረሃብ ምክንያት ከሣራ ጋራ ወደ ግብጽ ወርዶ ያወቀው ፈርዖን ይህ ነው፡፡ ዘፍ ፲፪+፲፭-፳፡፡ በዚህ ጊዜ ፍቅር ጸንቷል፡፡
፪. በያዕቆብና በልጁ ዮሴፍ ዘመን የነበረው ፈርዖን የግብጽ ተወላጅ ነው፡፡ ልዩ ስሙ አህሞሲስ /አሜንሆቴፕን/ ይባላል፡፡ በዚህ ጊዜ ፍቅር ተከፍሏል፡፡
፫. ሙሴ በተወለደ ጊዜ የነበረው ፈርዖን እስራኤል በሥራ የደከሙበትና ነፃነት ያጡበት ሙሴም ያደገበት ዳግማዊ ራምሲስ ነው፡፡ ልዩ ስሙ መኔፕታህ /መሬንፕታህ/ ይባላል፡፡ እስራኤልን አልለቅም ብሉ በህገሩ ላይ መቅሠፍት እንዲወርድ ያደረገና ከነሠራዊቱ በኤርትራ ባሕር የሠጠመ ይህ ፈርዖን ነው፡፡ ሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስም በሐዲስ ኪዳን ዘመዶቻችንን ተንኮስ ያለው ይህን ፈርዖን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ፀብ ጸንቷል፡፡ የሐዋ. ፯+፲፯-፳፪፡፡

## አንቀጽ ፪
## ስለ ሰማይ /ያት/

የኪዳነ ወልድ ክፍሌ የግእዝ መዝገበ ቃላት እንደሚተነትነው ሰማይ /ያት/ ማለት ሰፊ ሆኖ የተዘረጋ መጥቆ የሚታይ የማየት መጨረሻ ወሰን ድንበር ከእርሱ በላይ ሌላ የማያሳይ መጋረጃ የምድር ባጥ /ጣራ/ መዋቅር ከእሳት ከውሃ

የተሠራ በነፋሳት ምሰሶዎች የቆመ ከበላዩ የውቅያኖስ ውሃ ሆኖስ የሰፈረበት ከበታቹ ታላላቅ ብርሃናት /ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት/ እንደፋኖስ የተሰቀሉበት ነው።

ሰማይ ሁለት ቃል ነው። ሰ:ማይ ትርጉሙ እሳትና ውሃ ማለት ነው። ከፍ ማለቱና ርቆ መታየቱ የጋራ ሆኖ ለጠፈርም ለላይኞቹ የብርሃን ሰማያት ለተባሉት ለጀቱ ሁሉ ይነገራል። እሳትና ውሃ ግን ለጠፈር ብቻ ነው።

## ስለ ምድር /ምድራት/

ምድር ምድራት እምዳር እምዳራት እምዳሮት ማለት፡ ሰፊ ዝርግ ደንዳና ወፍራም ከነ ባሕሩና ከነ የብሱ ከነ ልብሱ የብስ የባሕር ርቦ /፴ኛ/ ነው። ከየብስ የተፈጠሩ የዐርብ ፍጥረቶችም የሚኖሩበት ነው። ወሰመዮ ለየብስ ምድረ፡ ወለምእላደ ማይ ባሕረ። ለታብቍል ምድር ሐመልማለ ሣዕር፡ ለታውጽእ ምድር ዘመደ እንስሳ ወእራዊት እንዲል ዘፍ ፩:፲-፳፱

ምድር ርሒባት። ርሒብ ይላል። ምድሪቱም ሰፊና ጸጥተኛ ሰላም ያላት ነበረች። ፩ኛ ዜና ፬:፵፬። እድባር ወእምዳር። የምትገቡባት ምድር ኮረብታና ሸለቆ ያለባት አገር ናት ዘዳ ፲፩:፲፩። ወዘረውክምሙ በእምዳሮት። ወደአገሮችም በትኛቸዋለሁ። ሕዝ ፲፩:፲፮-፲፯። ይበውእ ውስተ እምዳሮት። ወደ መልካሚቱ ምድር ይገባል ዳን ፲፩:፵።

በተጨማሪም ምድር የሰው ባሕርይ ሥጋ ጠፈር መሬት የሚል ትርጉም አለው። ዘምድረ ሰብለ እንዲል። ኪዳ። ምድርንም በአራቱ እፍላጋት አጽንቷታል። ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ እንዲል። መዝ ፻፴፭:፮ ወይም ከውሃ ጋር እቀላቅሎ ፈጥሯታልና። ወበእፍላግኒ ውእቱ አጽንዓ። መዝ ፳፫:፪። በአራቱ ወንዞች አጽንቷታልና ውስጥ ለውስጥ ባያጠግቧት እንደረቅ እንደጎታ እንደ ጎተራ ሆና በፈረሰች ነበርና። ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ በል። መዝ ፻፫:፲፬።



## የአራቱ ወንዞች ስምና መነሻ መድረሻ

፩. ኤፌሶን /ፊሶን/፡- የወተት ወንዝ ነው። ርስትነቱም የሕፃናት ነው። ማቴዎስ ይመስልበታል። እስመ ኵሉ ዘይትወጋዕ ሐሊበ ሕፃን ውእቱ። ወተትን የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ፡ ወኮኑ ከመ ሕፃናት ወእፍቅሩ ሐሊበ ነባቤ። እሁንም እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ ዕብ ፭:፲፫። ፩ ጴጥ ፪:፪።

፪. ግዮን፡- የወይን ወንዝ ነው። ለሚጾሙ ለሚጸልዩ በመልካም ሥራቸውም ደስ ለሚላቸው ርስት ነው። በማርቆስ ይመሰላል።

፫. ጤግሮስ፡- የማር ወንዝ ነው። ርስትነቱ ነገርን መሸከም ለማይቻላቸው /ለትግሥተኞች/ ሰዎች ነው። ሉቃስ ይመስልበታል።

፬. ኤፍራጥስ። የዘይት ወንዝ ሲሆን ርስትነቱ የሰማዕታት ነው። ዮሐንስ ይመሰልበታል። በተጨማሪም የ፬ቱ ወንዞች መነሻንና መድረሻን በአጭሩ እንገልፃለን።

፩ኛው ኤፌሶን /ፊሶን/ ሲሆን ዘፍ:-፪፥፲፩-፲፪። በህንደኬ ያሉትን የወንዝ ውሃዎችን ሁሉ አሰባስቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ውቅያኖስ ይገባል።

፪ኛው ግዮን ሲሆን ። ዘፍ፪ ፲፪-፲፬ ። በኢትዮጵያና በግብፅ ያሉትን የወንዝ ውሃዎች ሁሉ ሰብስቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ኢያሪኮ ይገባል።

፫ኛው ጤግሮስ ሲሆን ዘፍ ፪፥፲፬-፲፭ ። በዮናናውያን ያሉትን የወንዝ ውሃዎች ሁሉ አሰባስቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ባሕረ ኤርትራ ይገባል።

፬ኛው ኤፍራጥስ ነው። ዘፍ ፪:፲፭-፲፮ በአውሮፖ በፋርስ በባቢሎን ያሉትን የወንዝ ውሃዎች ሁሉ አሰባስቦ ይዞ ሄዶ ገነትን አጠጥቶ ተመልሶ ባሕረ ኤርትራ ይገባል።

ሐተታ፡- ምድር ምንን ትመስላለች ቢሉ ሰውን ትመስላለች። እንደ ደሙ በውሃ፡ እንደ አጥንቱ በደንጊያ፡ እንደሥሩ በእንጨት፡ ጸንታ ትኖራለች። ሰማያትን የፈጠረ

ምድርንና በውስጧ ያለውን አጸና አለ። ኢሳ ፵፪:፭-፮። በመዝሙር ፻፩:፳፭ ሳይም አንተ እግዚኦ አቅደምከ ሣርሮታ ለምድር። አቤቱ አንተ ምድርን አስቀድመህ ፈጠርህ። ሰማያት ከጥንት ጀምረው ምድር በእግዚአብሔር ቃል ከውሃ ተጋጥማ በውሃ መካከል ነበረች፡ የሚል ይገኛል። ፪ኛ ጴጥ፡፫:፭

አቅደምከ አለ። ከማን ቢሉ ከሰማይ ምነው የሰማይና የምድርማ ተፈጥሯቸው በቀዳሚ ግብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ባለ ጊዜ አንድ ጊዜ አይደለምን ቢሉ በመታየት አቅደምከ አለ። ዛሬ ቅሉ ሰማይ አይታይምና። አንድ ወገን ለምድር ሰጥተህ ከመታየቱ መፈጠሯን ብቻ አቅደምከ በል። ከዚህ ብሩህ ሰማይ መልቶ ነበርና።

## አንቀጽ ፫
## ስለ እሳት /እሳውት/

እሳት፡- ከአራቱ ባሕርያት /ነፋስ እሳት ውሃ መሬት/ ከሲህ አንዱ በሁሉ የሚገኝ ነው በድርቀቱ ከነፋስ፡ ስሙቀቱ /በማቃጠሉ/ ከመሬት፡ በብርሃኑ ከውሃ፡ የሚስማማ ነው። በእምጣነ ዕፁ ለእሳት የዐቢንዱ። በእንጨቱ ልክ የእሳቱ ነዲድ ይበዛል። ሲራ ፳፰:፲

እሳት በላዒ ለዓማጽያን እንዲል። ቅዱ. ማር እሳተ እሳት የሰማይ እሳት። እሳተ ገሞራ እሳተ ገሃነም ብርቱ ቅጣት። አበራኤል ልጆቻቸውን ለሞሎህ /ሞሎህ/ ለተባለ ጣዖት/ ሠውተው ያቃጥሉበት የነበረ የሰማያዊ እሳት ምሳሌ ነው። በወንድሙ ላይ የተቆጣ ሁሉ የገሀነም ፍርድ ይገባዋል። እሳት ዘለዓለም፡ የማይጠፋ የማያልፍ፡ ሥቃይ ያለበት ማቴ ፲፰:፰-፲።

እሳተ ሕይወት። መንፈስ ቅዱስ፡ እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል። ማቴ ፫:፲፩-፲፫።



## ስለ ሲኦል

**ሲኦል**፡- ማለት ታች ዝቅተኛ መቃብር ማለት ሲሆን በዓመተ ፍዳ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ያህል ነፍሳት የኖሩበት ነው። ከዚህ በኋላም በሕገ እግዚአብሔር ያልሄዱና ሥርዓቱን ያልጠበቁ የከፉ ሥራ ከፉ ውጤት መኖሪያቸው ነው። ከምጽአት በኋላ ግን የኀጥአን የፍርድ ቦታ ገሃነም ነው። ሙታን ሰዎች ከውሃዎች በታች በውሃዎች ውስጥ ከሚኖሩ በታች ይንቀጠቀጣሉ። ሲኦልም በፊቱ ራቁትዋን ናት። ኢዮ ፵፩:፲፰-፲፱

## ስለ አራት አጻጻፍ

አራት አራት አይነት ነው/አራት ጊዜ ተጽፋለች፡፡

፩. በሙሴ ዘመን ነው። ይህ ኦሪት ዘሌዋውያን /ኦሪተ ሌዋውያን/ ይባላል።

፪. ኦሪት ዘሊቃውንት /ኦሪተ ሊቃውንት/ ይባላል። ይህ እንደምን ነው ቢሉ በግብጽ ንጉሥ በበጥሊሞስ ዘመን በአምስት ሺሕ ሁለት መቶ አርባ አምስት ዓመተ ዓለም ፸ ሊቃናትን ከኢየሩሳሌም አስመጥቶ ኦሪት ዘሌዋውያንና መጻሕፍተ ነቢያትን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ በተረጐመ ጊዜ ነው።

፫. ኦሪት ዘሳምራውያን /ኦሪተ ሳምራውያን/ ይባላል። በ፪ኛው ኢዮርብዓምና በአሰር ንጉሥ በስልምናሶር ዘመን ምናሴ የሚባል ካህን ኦሪትን አስተምሮ ስለጻፈላቸው ከላይ የተጠቀሰውን ሥያሜ ይዟል። ፪ ነገ ፲፯:፳፬-፳፱

፬. ኦሪት ዘአይሁድ /ኦሪተ አይሁድ/ ብሎ ይባላል። የዚህ ምክንያት ደግሞ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ የሄኖክ የትውልድ ሱባዔንና የኤርምያስን የዕለት ሱባዔ እየቆጠረ ለአይሁድ ሲያስተምር ባለማመናቸው ጊዜው አልደረሰም ሥጋ አልለበሰም እያሉ ከአዳም ፫ኛ ትውልድ ከሆነው ከሴት ዘመን ጀምረው እየቀነሱ እስከ አብርሃም ድረስ አንድ ሺሕ አምስት መቶ ዘመን አውጥተው ስለጻፉ ጊዜው አልደረሰም አሰኝቷቸዋልና ኦሪተ አይሁድ ተባለ።

## ስለ ሙሴ አገልግሎት

ሙሴ:- እስራኤልን በምድረ በዳ ለ፵ ዓመታት ያህል ሲመግብና ሲመራ ኖረ::

ታሪክ:- ከዕለታት አንድ ቀን እስራኤል ሙሴ ውሃ ሙሴ ውሃ እያሉ ዘበዘቡት:: ደክሞት ነበርና ንሴብሖን ዘጸ ፲፭:፩ ሳይደግም ለጣቸው እነርሱም ሳያመሰግኑ ጠጥተውታል:: እግዚአብሔር ሙሴን በእንተዝ ኢትበውእ ለኢየሩሳሌም በእንተ ዘኢቀደስከኒ:: ለዘርህ እሰጣታለሁ ያልኳት ምድር ይቺ ናት:: በዓይንህ እንድታያት አደረግሁህ:: ነገር ግን ወደዚያች አትሻገርም ብሎት ነበርና:: በዚህ ምክንያት ኢየሩሳሌም አልገባም: ምድረ ናባው ቀርቷል:: አገሩ ሞዓብ የተቀበረበት ተራራ ናባው ፍስጋ /ፒስጋ/ ይባላል:: ዘዳ ፴፬:፬-፯

## አንቀጽ ፬
## ስለ ነቢይት ሐና ዘመን

ሐና:- ማለት ሀብት መልካም ስጦታ ዕድል ፈንታ ማለት ነው:: የሕልቃና አንደኛ ሚስት ናት:: እምነቷም በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው:: መካንም ነበረች:: ሐና የተወለደችበት ዘመን በአራት ሺሕ ሦስት መቶ ዓመተ ዓለም ገደማ ነው::

## ስለ መካን /ናት/

መካን:- ማለት የማይወልድ /የማትወልድ/ የማያፈራ/ የማታፈራ ማለት ነው::

ወሶራሰ መካን ይእቲ ወኢትወልድ:: ሶራም መካን ነበረች ልጅ አልነበራትም:: ዘፍ ፲፩:፴/፲፱:፴፩-፴፪

እስመ መካን ይእቲ ኤልሳቤጥ:: ኤልሳቤጥም መካን ነበረች:: ሉቃ ፩:፮-፰

ብፁዓት መካናት እለ ኢወለዳ:: መካኖችና ያልወለዱ ማሕፀኖች ያላጠቡ ጡቶችም ብፁዓት ናቸው የሚሉበት ጊዜ እነሆ ይመጣልና ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ ሲል ክርስቶስ ለኢየሩሳሌም ልጆች ተናገረ:: ሉቃ ፳፫:፳፱-፴::



ነቢይት ሐናም ልጅ ባለመውለዷ ታዝን ነበር:: በእግዚአብሔር መቅደስ ፊት ጸለየች:: ወንድ ልጅ ብትሰጠኝ ዕድሜዉን ሁሉ ለአንተ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ ብላም ስእለትን ተሳለች ፩ኛ ሳሙ ፩:፳-፲፪::

## ስለ ስእለት /ስእለታት/

ስእለት:- የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስእለትን እንደሚከተለው ይተረጉማል:: ሰው በፈቃዱ አንድ ነገር ለእግዚአብሔር ለማድረግ ወይም ለመስጠት ቃል መግባት ነው:: ብዙ ጊዜ ሰው ወደፊት ከእግዚአብሔር በረከትን ለመቀበል ስእለትን ይሳላል:: ማስረጃ ያዕቆብም እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆንና ቢጠብቀኝ ከሰጠኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ከአሥር እጅ አንዱን እሰጣለሁ ብሎ ተሳለ:: ዘፍ ፳፰:፳-፳፪:: ዘሌዋ ፳፯:: ዘኁ ፳፩:፩-፫:: መሳ ፲፩:፴-፴፩::

ሰው ስእለቱን ባይፈጽም ኀጢአት ነውና በችኮላ መሳል አይገባም:: ዘዳ ፳፫:-፳፩:-፳፫:- ምሳ ፳:፳፭:: መክ ፭:፬-፭:: እግዚአብሔርም የሐናን ጸሎትና ስእለት ሰምቶ ወንድ ልጅ ወለደች ከእግዚአብሔር ለምኜ አግኝቸዋለሁ ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው:: ፩ኛ ሳሙ ፩:፳-፲፪::

ሕፃኑም ጡትን በተወ ጊዜ ሐና ወደ እግዚአብሔር ቤት ወሰደችው:: በእግዚአብሔርም ቤት አደገ:: ከዚህ በኋላም ሦስት ወንዶችንና ሁለት ሴቶችን ወለደች ፩ኛ ሳሙ ፪:፳፮::

አንቀጽ ፬ ተፈጸመ::

## አንቀጽ ፭
## ስለ ሕዝቅያስ ጸሎትና ዘመን

ሕዝቅያስ ማለት የስሙ ትርጉም እግዚአብሔር ኃይሌ ነው ማለት ነው:: በአራት ሺሕ ሰባት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ዓመተ ዓለም ተወለደ:: ፲፫ኛው የይሁዳ ንጉሥ ነው::

ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እሱን የሚመስል አልነበረም ፪ ነገ ፲፰:፭:: ባዕድ አምልኮትን አጠፋ:: ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰበረ ቤተ መቅደስንም አሠራ:: ታሞ ለሞት ከደረሰ በኋላ በዘመኖቹ ላይ ፲፭ ዓመት የተጨመረለት ጸሎቱም ቅድመ እግዚአብሔር የደረሰለትና የሠመረለት ንጉሥ ነው:: ይህም የሆነው በነቢዩ በኢሳይያስ ምክንያት ነው:: ምናሴንም የወለደ ከዚህ በኋላ ነበር:: ኢሳ ፴፰:፩-፯ በተወለደ በ፳፭ ዓመቱ ነገሠ የመንግሥቱ ዘመን ፳፱ ዓመት ሲሆን መላ ዘመኑ ፶፬ ዓመት ነው:: አንቀጽ ፭ ተፈጸመ::

## አንቀጽ ፮
## ስለ ንጉሡ ምናሴ በደልና ንስሐ

ምናሴ:- ማለት ማስረሻ ወይም መከራዬን አስረሳኝ ማለት ነው:: ከይሁዳ ነገሥታት አሥራ አራተኛው ንጉሥ የሕዝቅያስ ልጅ ነው:: ፪ ነገ ፳:፳፩::

በአራት ሺሕ ስምንት መቶ አንድ ዓመተ ዓለም ተወለደ:: በተወለደ በ፲፪ ዓመቱ ነገሠ:: ባዕድ አምልኮትን እየተከተለ ከአሞራውያን ይልቅ ክፉ ሥራ ሠራ:: በኢየሩሳሌም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዲመጣ አደረገ:: ፪ ነገ ፳፩:፩-፲፰:: ፪ ዜና ፴፫:፩-፲:: ኤር ፲፭:፬::

የአሦር ንጉሥ አስራዶን /ንዑስ ሰናክሬም/ ወደ ባቢሎን ማረከው:: በዚያም ጊዜ ጸለየ:: እግዚአብሔርም ምሕረትን አደረገለትና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ አዘዘ:: ፪ ዜና ፴፫:፲፩-፳



### ስለ ውቅያኖስ

ውቅያኖስ ውሃ የሚኖርበት የውሃ መኖሪያ ታላቅ ባሕር ሰፊ ጥልቅ ሲሆን ባራቱ ማዕዘን የሞላ ነው ውሃ የሌለበት ከደረቁ ምድር ፫ እጅ የሚበልጥ እንደየብሱ ፭ ክፍል ያለው ነው:: ባሕር ለታላቁ ለታናሹ ሲሆን ውቅያኖስ ግን ለታላቁ ብቻ ነው::

### ስለ ብሔሞት

ብሔሞት ጉማሬ የወንዝ አውሬ የባሕር ፈረስ በአፍሪቃ ወንዞች በሐይቆቿ የሚገኝ ከውሃ እየወጣ ሣርና ቅጠል የሚበላ ታላቅ ግዙፍ ቆርበተ ወፍራም አንገተ ደንዳና የባሕር የበረሃ ጉሽ ጠባዩ ያውሬ መልኩ የበሬ ነው:: ጉማሬ እንደ በሬ ሣር ይበላል ኢዮ ፵:፲፭

### ስለ ንስሐ

ንስሐ ማለት ኀዘን ጸጸት ቁጭት ምላሽ መቀጫ ቅጣትና ቀኖና የኀጢአት ካሳ ማለት ነው::

ምናሴ በኢየሩሳሌም የነገሠበት ዘመን ፶፭ ሲሆን መላ ዘመኑ ፷፯ ነው:: አንቀጽ ፮ ተፈጸመ::

## አንቀጽ ፯
## ስለ ነቢዩ ዮናስ የትውልድ ዘመን

ዮናስ ማለት የዋህ ሰላማዊ ገርና ንጹሕ ማለት ነው:: አባቱ አማቴ እናቱ ማቀሲ ይባላሉ:: በአራት ሺሕ ስድስት መቶ አርባ ዓመተ ዓለም ተወለደ:: ነቢዩ ኤልያስም ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ ከሞት ያስነሣው ነው:: ኤልያስንም ያገለግለው ነበር:: የትንቢት ጸጋ የተሰጠው ነው:: መኖሪያውም በገሊላ በጋትሔፌር ከተማ ነበር::

### ስለ ዐንበሪ /ዐናብርት/

ታላቅ ዓሣ እንደ ዘንዶ ያለ ዮና ፪:፩ ዐንበሪ ምሥጢሩ ታላቅነትና ነባርነት ያለው ማለት ሲሆን አምባ እንደማለት ነው::

## ስለ መልሕቅ /ቃት/ መላሕቅ/

የመርከብ ልጓም እንዳይሔድ እንዳይናወጥ የሚገታው እንደ አልጋ እግር አራት ሆኖ ሁለቱ በፊት ሁለቱ በኋላ ባራት ማለዘን የሚወርድ ታላቅ ዘናና ብረት ነው። ዮና ፪:፮

አስመ ዘውስተ መርሶ ያንቀለቅል። በወደብ የተጠጋ መርከብ ያነዋወጻልና። ወባሕቱ መርሶ ወመልሕቅ ኢየኀድግዎ ይትሀወክ።

ነገር ግን ወደብ መልሕቅ በታውን ለቆ እንዲሄድ አያደርጉትም እንዳለ ዮሐ.አፈ.ድር ፲፭።

## ስለ ነነዌ

ይህ ጥንታዊ ከተማ በጢሮስ ወንዝ ዳር በናምሩድ የተመሠረተ ነው። ዘፍ፡ ፲:፲፩-፲፪። ለአሶር መናገሻ ከተማ ሆነ። የነነዌ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ዮናስ ወደ ነነዌ ከተማ ተላከ። ንስሓም ገብተው ከመጥፋት /ከሞት/ ድነዋል። እንቀጽ ፮ ተፈጸመ።

## አንቀጽ ፯
## ስለ ነቢዩ ዳንኤል እና የትንቢቱ ፍጻሜ

ዳንኤል ማለት እግዚአብሔር የሚፈርድልኝ ፈራጂዬ ዳኛዬ ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ነው። አባቱ ዮአኪን፡ ይባላል እናቱ ሚሊናስ፡ ትባላለች።

በይሁዳ ክፍል ውስጥ በምትገኝ በኢየሩሳሌም በአራት ሺሕ ስምንት መቶ ሰባ አምስት ዓመተ ዓለም ተወለደ። በምርኮ ጊዜ ዳንኤል ወጣት ነበር። የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ሲማርክ ከተማረኩት ከአሥር ሺሕ ሰዎች ጋር አንዱ ዳንኤል ነበር። ፪ ነገ ፳፬:፲፬-፲፭። ሕልም ተርጓሚ መሆኑ የታወቀ ነው። ዳን ፪:፲፱-፴፱። ትንቢትም ሀብቱ ሆነ። ንጉሡ ናቡከደነፆር ከሰው ተሰይቶ ከአራዊት ጋር በዱር ፯ ዓመት እንደሚኖር እንደ እንስሳም ሣር እንደሚበላ ከ፯ ዓመትም በኋላ ወደ መንግሥቱ እንደሚመለስ ትንቢት ተናገረ። ትንቢቱም ተፈጸመ። ትንቢቱንና



የትንቢቱን ፍጻሜ ዳን ፬:፲-፴፯ ይመልከቱ። ማንም ያልተረጐመውን ተረጐመ። ማኔ ቴቄል ፋሬስ የሚለውን ማለት ነው። ዳን ፭:፳፭። የዚህ ትርጒምና የትንቢት ፍጻሜ በጊዜው ጊዜ ተፈጸመ።

ቤተ መቅደስም ከ፸ ዓመት ማለት ከባቢሎን ምርኮ በኋላ እስራኤል ሲመለሱ ዘሩባቤል በ፭፻፵፭ ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ቤተ መቅደስ እንደሚሠራ ተናገረ ተፈጸመ። ዕዝ ፫:፮-፲፫ ይህም እንደሚፈርስ /እንደሚቃጠል/ ተናገረ። በግሪክ መንግሥት በታላቁ እስክንድር ፈረሰ። ዳን ፰:፳፩። ትንቢቱም በ፫፴፩ ዓመት ከልደት በፊት ተፈጸመ። ትንቢቱም ከ፻፸፱-፻፷፯። ዓመት ከልደት በፊት የነገሠው የአሶር ንጉሥ አንጥያኮስም ቤተ መቅደስን እንደሚያረክስና እንደሚያጠፋ ተናገረ። ይህም ተፈጸመ። ዳን ፰:፳፱-፳፯። ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣና እንደሚገደል ተናገረ ተፈጸመ። ዳን ፱:፳፭-፳፯። ከክርስቶስ ስቅለት በኋላም ኢየሩሳሌም ተቃጠለች። ይህ የሆነው በ፸ ዓ.ም ነው። ቤተ መቅደሱን አስፋፍቶ ያሠራው ሄሮድስ አግሪጳ ከልደት በፊት በ፲፱ ዓመት ነበር። ያፈረሱትም ሮማውያን ናቸው። ዳንኤል ቤተ መቅደስ ትሠራለች ከዚህ በኋላም ትጠፋለች ብሎ ትንቢት የተናገረ ክርስቶስ ሲወለድ ፬፻፺ ዓመት ሲቀረው ነው።

## ስለ ኢየሩሳሌም

ኢየሩሳሌም ስመ ሀገር የዳዊት ከተማ መዲና የልጆች ሁሉ መናገሻ የሆነች በምድረ ይሁዳ ያለች ጥንታዊት ከተማ ናት ዘፍ ፲፬:፲፰።

የሩ፡ ሀገር ሳሌም ሰላም ሲናበብ ሀገረ ሰላም ማለት ነው። ሳሌም ከመባሏ በፊት ሴዱ ስላቀናት ሳይዳ ቤተ ሳይዳ ትባል ነበር። ቤተ ጸጋ ወሣህል ማለት ነው። ዮሐ ፭:፪። ከሴዱ በኋላ ልጁ ሳሌም ስለነገሠባት ሳሌም ኢየሩሳሌም ተብላለች። ከዚያም በኋላ ስሟ አልተለወጠም መዝ ፸፭:፪ ኢያ ፲:፩። ከሳሌም በኋላም የነገሡት ንጉሥ ሳሌም በመባል ላይ መልከጼዴቅ አዶንጼዴቅ እየተባሉ በምሳሌ ስም ተጠርተዋል። ኢያ ፲:፩-፴ ይኸውም የእውነት ንጉሥና ጌታ ማለት ነው። እማናዊው

ንጉሠ ጽድቅና እግዚአ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሰውነቱ ንጉሠ አይሁድ ተብሎ በመካከሏ ተሰቅሎ ደቂቀ አዳምን ከአብ፡ ሕዝብን ከአሕዛብ፡ ሰውን ከመላእክት፡ ነፍሳትን ከሥጋት አንድ የሚያደርግባት /የሚያስታርቅባት/ ስለሆነች ስሟ እንደ ትንቢት ሆኖ ከነቢያት በፊት በዘመነ አበው ተነግሯል። ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባምና ዛሬና ነገ ልሄድ ያስፈልገኛል አለ ክርስቶስ። ሉቃ ፲፫:፴፫-፴፭።

ነቢያት ግን በእስራኤል ከፋት ሰዶም ገሞራ ብለዋታል። ከሰዶምም ያከፏትና ያበለሏት አሉ። እናንተ የሰዶም አለቆች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፡ ኢሳ ፩:፲። ነቢዩ ሕዝቅኤልም ስለ ኢየሩሳሌም ሲናገር ኢየሩሳሌም ሆይ ወዮልሽ ከክፋትሽ ሁሉ በኋላ የምንዝርናን ስፍራ በየአደባባዩ ከፍ ያለ ቦታ ሰራስሽ ሠራሽ አለ። ሕዝ ፲፮:፵፮-፶፱። እንቀጽ ፰ ተፈጸመ።

## እንቀጽ ፱

### ስለ አናንያ አዛርያ ሚሳኤል ምርኮና ዘለዓለማዊ ምስጋና

አባታቸው ኢዮአቄም (ሴምዩ፡ ሴንዩ) ይባላል፡ እናታቸው ሐና ትባላለች። ኢዮአቄም ማለት እግዚአብሔር አቆመ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በመናቅ የነቢዩ ኤርምያስን መጽሐፍ አቃጠለ። ኤር ፴፮:፳፫-፳፱ በዚህ ምክንያት ኢየሩሳሌም እንደምትማረክ ኤርምያስ ትንቢት ተናገረ። የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄምን እንዲህ በለው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የባቢሎን ንጉሥ በእርግጥ ይመጣል ይህችንም ከተማ ያፈርሳታል ከሰውና ከእንስሳም ባዶ ያደርጋታል ሲል። ኤር ፴፮:፳፱-፴፩ ነቢዩ ኢሳይያስም ከኤርምያስ አስቀድሞ በኢየሩሳሌም ላይ ምርኮ እንደሚመጣ ተናግሮ ስለነበር። ኢሳ ፳፱:፩-፰ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ኢየሩሳሌም ተማረከች። ስትማረክም አናንያ አዛርያ ሚሳኤልም በወጣትነታቸው ተማርከው ወደ ባቢሎን ወረዱ። ንጉሡ ናቡከደነፆር በቤቱ ውስጥ አሳድጎ በባቢሎን ሀገሮች ውስጥ ሾማቸው። በእሳቱ ውስጥም የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤልም ፬ተኛ ሰው መስሎ ታየ። የእግዚአብሔር



መልአክም የእሳቱን ነበልባል ከ፫ቱ ደቂቅ ላይ አጥፍቶ አዳናቸው እንደ ጧት ጤዛም ሆነ። ንጉሡም በፊታቸው ሰገደ።

በዚያን ጊዜም ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ። የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን እያሉ በ፫ ቃላት ምስጋናን አቀረቡ። በዚያም ጊዜ ከ፭፻ ዓመት በኋላ ክርስቶስ እንደሚወለድ ትንቢት ተናገሩ። እንቀጽ ፱ ተፈጸመ።

## እንቀጽ ፲

ከዚህ በመቀጠልም ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር። የጌታ እግዚአብሔር ሥራዎቹ ሁሉ ያመሰግኑታል። እርሱ ለዘላለሙ ምስጉን ልዑልም ነው። እያሉ ፴፫ ጊዜ አመሰገኑት።

ይባርክዎ ብለው ያመሰገኑትን ምስጋና መሥመር ቢቆጥሩት ፴፫ ይሆናል። የ፫ቱ ደቂቅ ጸሎት በዘመናቸው በታሪክነት ብቻ ተጽፎ ሳይቀር ከአንድ ሺሕ አንድ መቶ ሃያ ዓመት በኋላ በቅዱስ ያሬድ ድርሰት በሰማያዊ ዜማ እንደገና ተቃኝቷል። ከላይ እንደጠቀስነው ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነንና ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር የሚለውን የ፫ቱ ደቂቅን ጸሎት ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከ፫ቱ ጸዋትወ ዜማዎች /የዜማ ክፍሎች/ አንዱ በሆነው ምዕራፍ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ በዘወትርና በዓበይት በዓላት ስብሐተ ነግህ /የጧት ምስጋና/ ተብሎ በሚጠራው ምስጋና ውስጥ በሦስት ዜማዎች ማለት ግእዝ ዕዝል ዓራራይ ተሰባስቦ ይገኛል።

ከዚህ ላይ ስብሐተ ነግህን ብቻ የጠቀስንበት ምክንያት ከዓመት እስከ ዓመት በታላላቅ አድባራት ሳይቋረጥ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ስለሆነ ለማለት እንጅ የይትባረክና የይባርክዎ ምስጋና ከላይ በተጠቀሰው ስብሐተ ነግህ ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን እናሳስባለን።

ቃሉ እንዴት ምዕራፍ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ተካተተ /ተዘጋጀ/ የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ የሚከተለው ይሆናል። ምዕራፍ በተባለው መጽሐፍም ውስጥ የሚገኘው ቃል በብዛት

ከመዝሙረ ዳዊት መሆኑ ለሊቃውንቱ ግልጽ ነው:: ሆኖም ምክንያቱ ዳዊት ይትባረክ ይባርክዎ የሚለውን ቃል በመዝሙሩ /በምስጋናው/ ውስጥ በብዛት ጠቅሶት ይገኛል /ተጠቅሶ ይገኛል/:: ነቢዩ ዳዊት ስለ ሕዝቅያስ ሲናገር እባርኮ ለእግዚአብሔር በኵሉ ጊዜ:: እግዚአብሔርን በ፯ቱ በ፳፬ቱ በ፷፬ቱ ጊዜያት አመሰግነዋለሁ ብሎ ተናግሮ ነበር:: መዝ ፴፫:፩::

፪ኛ ስለ ትሩፋቱንም ከ፸ ዘመን በኋላ እግዚአብሔር ያደረገውን ድንቅ ሥራ ትንቢት በተናገረበት በመዝ ፻፳፭:፩-፫ ወይትባረክ እግዚአብሔር:: ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን በማለት ተናግሮ ነበር::

፫ኛ በመዝ ፸፩:፲፰ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል: እስራኤልን የፈጠረ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብሎ ነበር::

፬ኛ በመዝ ፻፪:፳፩ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር ኵሉ ኃይሉ:: ሠራዊተ መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል:: ብሏል::

፭ኛ በመዝ ፻፴፬:፲፱-፳ ቤተ-እስራኤል ባርክዎ ለእግዚአብሔር:: የእስራኤል ወገኖች እግዚአብሔርን አመስግኑት:: ቤተ አሮን ባርክዎ ለእግዚአብሔር:: የአሮን ወገኖች ካህናትም እግዚአብሔርን አመስግኑት:: ቤተ ሌዊ ባርክዎ ለእግዚአብሔር:: የሌዊ ወገኖች እግዚአብሔርን አመስግኑት::

፮ኛ በመዝ ፻፵፫:፩ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኪየ:: ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብሎ የራሱን አመስጋኝነት ከላይ የተጠቀሱትንም እግዚአብሔርን እንደአመሰገኑና እንዲያመሰግኑ ገልጿል:: ይህን በማያያዝም ነቢዩ ዳንኤል በምዕ ፪:፳ ላይ ይትባረክ ስመ እግዚአብሔር: ካለ በኋላ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ የሚለውንም በምዕ ፫:፳፮ ላይ ተናግሯል:: ይህ በምዕ ፫:፳፮ ያለው ከአዛርያ ምስጋና ጋራ የተያያዘ ነው::

እግዚአብሔር ለአናንያ ለአዛርያ ለሚሳኤልም እውቀትንና ጥበብን መጻሕፍትን ከማንበብ ሁሉ ማስተዋልን ሰጥቷቸው ነበር:: ንጉሡም ናቡከደነፆር እንደ እራቱ ያለ ሰው አላገኘም::



ከዚህ በኋላም በሥጋ ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ በጸሎት ቤታቸው ማለት እስራኤል ጊዜና ነፃነት ስለሌላቸው ባሉበት ይጸልዩ ነበር::

ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ:: ምድርና መላዋ ለእግዚአብሔር ናት: ዓለምም በእርሷም የሚኖሩ ሁሉ:: መዝ ፳፫:፩-፪:: እየጸለዩ ሳሉ ለገደሉ ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጡ:: ወዲያው ንውጽውጽታ በባቢሎን አገር ሆነ:: ንጉሡም ፈርቶ ዳንኤልን ጠየቀው:: ነቢዩ ዳንኤልም ይህ የ፫ቱ ደቂቅ ስላረፉ ነው አለው:: ንጉሡም አዘዘ ፫ ሳጥኖችን እንዲሠሩላቸው በሐር ገምጃ ልብሶችም ገንዘው ቅዱሳኑን በሣጥኑ ውስጥ እንዲያኖሩአቸው አዘዘ:: ንጉሡም እንዳዘዘ አደረጉ:: ንጉሡም በሚሞትበት ጊዜ ሥጋውን በውስጡ አድርገው በነበሩ በሶስቱ ልጆች አፅም መካከል እንዲያኖሩት አዘዘ:: እንዲሁም አደረጉለት:: ከብዙ ዘመን በኋላ ማለት አንድ ሺሕ ዘመን ሲፈጸም አባ ቴዎፍሎስ በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስና በተሾመበት ወራት በ፫ቱ ደቂቅ ስም ቤተ ክርስቲያን ሠራ:: አባ ዮሐንስ ሐፂርን አፅማቸውን እንዲያመጣለት አዘዘ:: አባ ዮሐንስ ሐፂርም በታዘዘው መሠረት ባቢሎን ደረሰ:: ወንዞችንም ብቻ አየ:: በውስጧ ከቶ /ፈጽሞ/ ሰው አልነበረም: የወርቁ ምስል ብቻ ከዚያ ነበር:: አባ ዮሐንስ ሐፂርም አፅማቸው ባለበት ሰገደ:: እንዲህ ብሎ ጸለየ:: የከበራችሁ አባቶቼ ሆይ የከበረ አባት አባ ቴዎፍሎስ በስማችሁ ቤተ ክርስቲያንን ሠርቶ አፅማችሁን በውስጧ ሊያኖር እኔን ልኮኛልና ከእኔ ጋር ትሔዱ ዘንድ ፈቃዳችሁ ይሁን አለ:: በዚያን ጊዜ እንዲህ የሚል ቃል ከአፅማቸው ወጣ:: ስለሃይማኖት አባት ስለአባ ቴዎፍሎስ እንዲህ በለው: የድካምህን ዋጋ እግዚአብሔር ይስጥህ:: ነገር ግን እኛን እስከ ፍርድ ቀን /እስከ ዳግም ምጽአት/ ድረስ አፅማችን ከንጉሡ አፅም ጋራ እንዳይለይ እግዚአብሔር ስላዘዘን ከዚህ አንወጣም:: ድካሙንም ከንቱ እናደርግም ቤተ ክርስቲያኒቱ በምትከብርበት ዕለት በሌሊት መብራቶችን ይሰቅሉ ዘንድ እንዲያዝዝ በውስጣቸውም ዘይትና ፈትል እንዲያደርጉ በእሳት ግን እይለኩሷቸው: እኛም ከዚያ ደርሰን በእኛ የእግዚአብሔር ኃይል በዚያ ይገለጣል: ብለህ ንገረው

እሉት። አባ ዮሐንስ ሐዊርም እንደነገሩት ሁሉንም ለአባ ቴዎፍሎስ ነገረው እርሱም ፫ቱ ደቂቅ እንዳዘዙት አደረገ። በግንቦት ወር በ፲ኛው ቀን በግብጽ ሀገር ቤተክርስቲያኒቱ በምትከበርበት ሌሊት የከበሩ ፫ቱ ደቂቅ በተአምር ተገለጡ። ሊቀ ጳጳሱ አባ ቴዎፍሎስና ለዚህ ጸጋ የታደሉ ሁሉ በቤተክርስቲያኒቱ አርከን ላይ ሲዞሩ ፫ቱ ደቂቅን አዩአቸው በየዓይነቱ በሆነ ደዌ የታመሙ ብዙ በሽተኞችም ከቅዱሳን ፫ቱ ደቂቅ መገለጥ የተነሣ ያን ጊዜ ተፈወሱ።

## ታሪክ

የእስክንድርያ ፳፫ኛ ሊቀጳጳሳት የሆነው ቴዎፍሎስ በ፫፻፲፬ ዓ.ም በማርቆስ መንበር ተሾመ። ከዚህ በኋላ ቤተክርስቲያንን ለማሠራት ይተጋ ነበር። ቤተክርስቲያንን ለማሠራት የተነሣሣበት ምክንያት የእርሱ መምህር የነበረው ሐዋርያው የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት አትናቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ይመኝ ስለነበር፡ የመምህሩ የአትናቴዎስን መልካም ምኞት በተግባር ለመተርጎም ሲል፡ መበነ ለረድእ ከመ ሊቁ። ደቀመዝሙር እንደመምህሩ መሆኑ ይበቃዋል የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ በዚህም ላይ ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ እንዲሉ።

፩ኛ. በነቢዩ በኤልሳዕና በመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ስም፡

፪ኛ. በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፡

፫ኛ. በ፫ቱ ደቂቅ ስም በግብጽ አገር በ፬፻ ዓ.ም ገደማ ቤተክርስቲያንን አሠራ።

## ስለ አናንያ አዛርያ ሚሳኤል የስም መጠሪያ

አናንያ አዛርያ ሚሳኤል የመጀመሪያ ስማቸው ሲሆን ሲድራቅ ሚሳቅ አብደናጎ የሚለው ስም ደግሞ የንጉሡ ናቡከደነፆር የጃንደረቦቹ አለቃ የሆነው አስፋኔዝ /አስፋኔስ/ ያወጣላቸው ስም ነው። ዳን ፩፡፮-፯።

፩. ፫ቱ ሲል ቊጥራቸውን መናገር ነው።



፪. ደቂቅ ሲል በዕድሜ ታናናሽ ሆነው ከወጣትነት ጀምረው ለእግዚአብሔር አገልጋዮችና ታማኞች ሲሆኑ ቤተሰብና የአንድ ሰው ልጆችም /ወንድማማቾችም/ በመሆናቸው ነው።

፫. ፍቁራን አንበሙ ሲልም የተወደዱ የከበሩና የእግዚአብሔር ወዳጆች ባለሟሎች ማለቱ ሲሆን ወንድማማች መሆናቸውን የበለጠ ያስረዳል። በሥጋ ዝምድና በሃይማኖትም የተስማማ ስም ነው።

፬. ፫ቱ ስደው ሲል የጾታ ስም ማለት የወንድነት ተፈጥሮ መዓርግ ያላቸው መሆኑን ያበረዳል።

፭. ሰማዕት /ሰማዕታት/ የሥራ የተጋድሎ ስማቸው ነው። ከላይ የጠቀስናቸው ስሞች ሁሉ በቅዱስ ያሬድ ድርሰት ውስጥ የተገለጹ ናቸው።

## አንቀጽ ፲፩
## ስለ ነቢዩ ዕንባቆም

ዕንባቆም፡- ትውልዱ ከነገደ ስምዖንና ከነገደ ዮሴፍ ነው። አባቱ ዳዊር /ሳኪር/ ይባላል፡ እናቱ ሱራፋ ትባላለች። በአራት ሺሕ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ዓመተ ዓለም ገደማ ተወለደ። በአረሮና በሸመንስ ጊዜ የእስራኤል ልጆች ከተማረኩበት ስባቢሎን ተመልሰው ኢየሩሳሌም ገብተው በዘሩባቤል ዘመን ቤተ መቅደስን ሠሩ። ዕንባቆምም ኢየሩሳሌም ደርሶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ በታላቅ ደስታም ተቀበሉት ትንቢቱንም የሰሙ ወደእርሱ ተሰበሰቡ አፉንም ከፍቶ በመንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለ።

አቤቱ ድምፅህን ሰማሁ፡ ሰምቼም። ፈራሁ ሥራህንም አይቼ አደነቅሁ አለ። ስለ ጌታችን መድኃኒታችን መውረድና በይሁዳ ክፍል በሆነች በቤተልሔም ስለመወለዱ ሲናገር የተመሰገነ እግዚአብሔር ከፋራን ተራራ ከቴማን ከይሁዳ አውራጃ ይመጣል ብሎ እስከመጨረሻው ያለውን ቃል ተናገረ። ከነቢያት መጻሕፍትም ጋራ ቆጠሯት።

ከዚህ በኋላ ከእስራኤል ልጆች አንዲት ሴት ወደ እርሱ መጣች እያለቀሰችም እንዲህ አለችው። ሁለት ልጆች ነበሩኝ ጣዖት እንዲያመልኩ ፈለጉአቸው። እምቢ ባሉ ጊዜም ገደለው

በጎዳና ላይ ጣሏቸው:: ተገድለው ወደ አሱበትም አብሯት ሄደ:: ነፍሳቸውንም ያስነሣ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነ ልመናውንም ተቀብሎ በሕይወት አስነሣቸው:: ዕረፍቱም በቀረበ ጊዜ ዘመዶቹን ጠራቸው እንደሚሞትም ነገራቸው:: አንዲት ሰዓት ያህል ወደ ላይ እየተመለከተ ተቀመጠ:: እነሆ እንደለው ከንድ ያለች ታላቅ ከንድ የቤቱን ጣሪያ ሰንጥቃ ወረደች ወደ አፋም ተዘርግታ ነፍሱን ወሰደች::

### ስለ ቴማን

ቴማን:- የቦታ ክፍል ነው:: መጀመሪያውን ምሥራቅ ቢሉ አንጻሩ ምዕራብ ማለት ነው:: ስለዚህ ቴማን ማለት ዕንባ ፫:፲፫:: ናጌብ ደቡብ የደቡብ ነፋስ በደቡብ ያለ አገርና ሕዝብ ማለት ነው:: ሚያ ገጸከ መንገለ ቴማን ሲተረጐም ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም አቅና ማለት ሲሆን ቴማን ኢየሩሳሌም ተብሎ ተተርጉሟል:: ሕዝ ፳፩:፩-፪ ኤር ፵፱:፯-፳::

### ስለ ፋራን

ፋራን:- ከቤርሳቤህ በስተደቡብ በሲና ውስጥ የሚገኝ ምድረ በዳ ነው:: እስማኤል በፋራን ተቀመጠ:: ዘፍ ፳፩:፳፩ እስራኤላውያንም በዚህ ተጓዙ:: ዘኍ ፲:፲፪:: ፲፪:፲፮:: ፲፫:፳፮:: የፋራን ተራራ ኤልፋራን ተብሎአል:: ዘፍጥ ፲፬:፮:: ዕንባቆም ክርስቶስ ከፋራን እንደሚመጣ ተናገረ:: ዕን ፫:፫ ይህም ኤፍራታን ያመለክታል ሚክ ፭:፪

### <u>ስለ መብረቅ /መባርቅት/</u>

**መብረቅ:-** ማለት የእሳት ሰይፍ የእሳት ፍላጻ ማለት ሲሆን: በዝናም ጊዜ ከደመና አፎት የሚመዘዝ የሚወረወር ነው:: ራእ ፬:፭:: ሲራ ፵፭:፲:: ኤር ፲:፲፫ ማቴ ፳፰:፫::

<u>ሐተታ</u>:- የመብረቅ ተፈጥሮ እንደምን ነው ቢሉ ውሃው በደመና አይበት /በአቀማዳ: በሸራ/ ተቋጥሮ በነፋስ ወደል ጋዝ



/በጭነት እንስሳና በመጫኛ/ ተጭኖ ሲመጣ ደመናና ደመና በተጋጩ ጊዜ እንደ አረቄ ከውሃ ይወጣል:: ወተት ሲገፋ ቅቤ እንዲወጣው:: አንቀጽ ፲፩ ተፈጸመ::

### አንቀጽ ፲፪
### ስለ ነቢዩ ኢሳይያስ

ትውልዱ ከነገደ ስምዖን ነው:: አባቱ አሞጽ ይባላል: እናቱ ኑራንስ /ሰፍኒ/ ትባላለች:: በአራት ሺሕ ስድስት መቶ ሰማኒያ ሁለት ዓመተ ዓለም ገደማ እንደተወለደ በንጉሡ ዖዝያን እድሜ ያመለክታል::

ጌታ በዙፋኑ ላይ እያለ ሱራፌል ኪሩቤል እያመሰገኑት በክብሩ በመንበሩ ተገልጾለት አይቷል:: ኢሳ ፮:፩-፰::

ኢሳይያስም በያሁዳ በነገሡ በአምስቱ ነገሥታት ዘመን ትንቢት ተናገረ:: እሊህም ኦዝያን ኢዮአታም አካዝ ሕዝቅያስና ምናሴ ናቸው:: በአካዝ ዘመን እንዲህ ብሎ ትንቢት ተናገረ:: እነሆ እግዚአብሔር ምልክትን ይሰጣችኋል::

፩. እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከኛ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው:: ኢሳ ፯:፲፬-፲፭:: እርሱም በነቢያታቸው ከሚመጣባቸው ፍዳ ወገኖቹን የሚያድናቸው ወደሃይማኖቱም የሚመልሳቸው እንደሆነ የእስራኤልንም ልጆች መሥዋዕታቸውንና ክህነታቸውን /የኦሪቱን ሥርዓት/ እንደሚሽር ከሐዲስ ወገኖችም የሚያመሰግኑት ካህናትን /ሐዋርያትን/ እንደሚሾም ተናገረ::

፪. ስለ እስራኤል መማረክና ከምርኮ መመለሳቸውን ትንቢት ተናገረ:: ኢሳ ፳፱:፩-፮:: ኢሳ ፩:፯-፰::

፫. ክብር ይግባውና ስለ መድኃኒታችን ክርስቶስ መከራ ትንቢት ተናገረ:: ኢሳ ፶፫:፩-፲:: እንዲህም አለ:: እርሱም በመከራው ጊዜ ነገርን አልተናገረም: እንደ በግ ይታረድ ዘንድ መጣ በግ

በሚሸልተው ሰው ፊት እንደማይናገር እንዲሁ በመከራው ጊዜ ነገርን አልተናገረም ብሎ። የሐዋ ፰፥፴፪-፴፬።

በሕዝቅያስ ልጅ በንጉሡ ምናሴም ትንቢት ተናገረ። ጣዖትን ስለማቆሙና ስለማምለኩ ገሥጸው። ስለዚህም ንጉሡ ምናሴ ተቆጥቶ በእንጨት መሀንጠቂያ በመጋዝ በራሱና በእግሮቹ መካከል ሰንጠቀው። ምስክርነቱንም በዚህ ፈጸመ። እንቀጽ ፲፪ ተፈጸመ።

## እንቀጽ ፲፫
## ስለ ድንግል ማርያም ልደት

በአምስት ሺሕ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ዓመተ ዓለም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአባቷ ኢያቄም ከእናቷ ሐና ተወለደች። በተወለደች በ፲፭ ዓመቷ እግዚአብሔር በቃሉ እንደተናገረና እንደ ነቢያት ትንቢት በድንግልና ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድን አሑድ መጋቢት ፳፱ ቀን በ፫ ሰዓት ጸነሰችው። ወዲያው በዚሁ ወር ወደ ቅድስት ኤልሳቤጥ ቤት ሔዳ ሰላም ካለቻት በኋላ።

ተዐበዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር። ስውነቱ ጌታን ታከብረዋለች የሚለውን ምስጋና ተናገረች አመሰገነች። እንቀጽ ፲፫ ተፈጸመ።

## እንቀጽ ፲፬
## ስለ ካህኑ ዘካርያስ እና የልጁ ዮሐንስ ልደት

ዘካርያስ፦ ማለት እግዚአብሔር ያስባል ማለት ነው። ካህኑ ዘካርያስ በአምስት ሺ አራት መቶ ዓመተ ዓለም ተወለደ።

ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጸነሰች ስ፱ ወር ያህል ማለትም ከመስከረም ፳፯ - ሰኔ ፴ ቀን ዘካርያስ መናገር አልቻለም። ዮሐንስ ሲወለድ አንደበቱ ተከፈተ /ተናገረ/። ነቢዩ ዳዊትና ነቢዩ ዳንኤል እንዲሁም አናንያ አዛርያ ሚሳኤልም ያመሰገኑትን ምስጋናና ለፈጣሪያቸው ያቀረቡትን ጸሎት። ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል። የእስራኤል ጌታ አምላክ ይክበር



ይመስገን እያለ አመሰገነ። ሉቃ ፩፥፷ ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱንም ልትጠርግ በእግዚአብሔር ፊት ትሔዳለህ እያለ ትንቢት ተናገረ። አስቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስም ተነገር ስለነበር ኢሳ ፵፥፫ ሚል ፫፥፩-፪። ለልጁ ለዮሐንስ ተገልጾለት መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ እያለ ከማስተማሩም በላይ ማቴ ፫፥፩-፬። ለዮሐንስ ፴ ዓመት ከ፮ ወር ስጌታ ፴ ዓመት ሲሆነው ፈጣሪውን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀ። ማቴ ፫፥፲፭

## ስለ ልደቱ

ልጁ ዮሐንስ የ፪ ዓመት ሕፃን እያለ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፴፯ ዓመት የነገሠው የመጀመሪያው እንጦጦስ ሄሮድስ ሕፃናትን በሚያስገድልበት ጊዜ ዮሐንስን ይዛ እናቱ ኤልሳቤጥ ወደ በረሀ እንድትሸሽ ዘካርያስ አዝዞ ወደ በረሀ ይዛው ሄደች። በሄሮድስ የሚፈለገው ከሕፃናቱ አንዱ ዮሐንስ ነበርና ልጅህን አምጣ ቢሉት ልጁን ወደ ሌላ ቦታ እናቱ ይዛው ሔዳለች ቢላቸው በዚህ ምክንያት ገደሉት። እንዲህም የሚል ሌላ ታሪክ አለ። ዘካርያስ ልጁ ዮሐንስን ወደ ቤተ መቅደስ ወስዶ በመሠዊያው ጠርዝ /ጫፍ/ ላይ አኑሮ ጸለየበት፡ ሀብተ በረከት ለማሳደር። ያን ጊዜም የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ሕፃኑን ከእናቱ ጋራ ዚፋታ ወደሚባል በረሀ ነጥቆ ወስደው። ሕፃኑን ባላገኙት ጊዜ አባቱ ዘካርያስን ገደሉት። የዘካርያስንም ደም የሚበቀል እስኪመጣ ድረስ ስ፸ ዓመት ያህል ደሙ ስትፍላ ኖረች። በ፫ ዓ.ም ካህኑ ዘካርያስ በሰማዕትነት ተገደለ። ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ከተገደለ በኋላ ማቴ ፳፫፥፳፭-፳፯። ከብር ይግባውና እግዚአብሔር ሥጋውን ሠወረ። ደሙ ግን እንደ ደንጊያ ሆነች። ካህናቱና ሕዝቡ እንደልማዳቸው ለጸሎት በመጡ ጊዜ ስካህናት አንዱ ወደ ቤተመቅደስ ውስጥ ገባ። የረጋ ደምን አገኘ ከመሠዊያውም ውስጥ እንዲህ የሚል ቃልን ሰማ። እነሆ የበራክዩ ልጅ ካህኑ ዘካርያስ ተገደለ። ከተገደለ በኋላም የካህኑ

ዘካርያስ ደም ፸ ዘመን ሲፈላ ኖሯል። የሚበቀል እስኪመጣ ድረስ ደሙ ስትጮህ ትኖራለች የሚለውን ለመግለጽ የሚከተለውን ታሪክ እንመለከታለን።

## ታሪክ

ከክርስቶስ ስቅለት አስቀድሞ አይሁድ ፈጽመው ለሮም መንግሥት ተገዝተው ነበር። ነገር ግን ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ በ፴ ዓ.ም በሮም ግዛት ላይ ሸፈቱ ወይም ለሮም መንግሥት አንገዛም አሉ። በዚህ ምክንያት የሮም አገረ ገዢ ጥጦስ ኢየሩሳሌምን ለመክበብ ገሥግሦና ታላቅ የሚያስፈራ ጦርነት ሆነ። ወዲያው ሌሊቱን ከተማዋ /ኢየሩሳሌም/ ተያዘችና ተቃጠለች። ቤተ መቅደሱም በእሳት ነበልባል ተያያዘ። ዘጠና ስምንት ሺሕ አይሁድ ተማረኩ። ሌሎችም ምግብ እንዲሆኑ ለአራዊት ተወረወሩ። በሕይወት የተረፉትም ወደ ዓለም ሁሉ ተበተኑ። ይህ ሁሉ እንዲሆንና እንዲፈጸም ገና አስቀድሞ በነቢያት ትንቢት ተነግሮ ነበር። ከነቢያትም አንዱ ዳንኤል ነው። የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ፤ ፍጻሜውም በጎርፍ ይሆናል። እስከመጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል ጥፋትም ይቆጠራል። ዳን ፱፡፳፮-፳፯። ስለዚህ የሚበቀል እስኪመጣ ድረስ የሚለው ከላይ የታሪኩን ምንጭ እንደዘረዘርነው ሮማዊው ጥጦስም በ፸ ዓ.ም። የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ባፈራረሰ ጊዜ ደሙ ሲፈላ አግኝቶ ይህ ምንድን ነው ብሎ ጠየቀ። ደግ ሰው ነበር በግፍ /ያለ በደል/ የተገደለ ካህን ነው አሉት። ጥጦስም ከገዳዮቹ ወገን ፯ ሰዎችን አስመጥቶ ቢያስገድል ደሙ መፍላቱን ትቷል። የሚበቀል እስኪመጣ ያሰኘው ቃል ይህ ነው።

እንቀጽ ፲፱ ተፈጸመ።



## እንቀጽ ፳

## ስለ ነቢዩ /ካህኑ/ ስምዖን ትንቢትና ዕረፍት

ስምዖን፦ ማለት እግዚአብሔር ጸሎቴን ሰማ ማለት ነው። ካህኑ ስምዖን በአምስት ሺህ ዓመተ ዓለም ተወለደ።

## ታሪክ

እሱም በተፈጠረ በአምስት ሺሕ ሁለት መቶ አርባ አምስት ዓመተ ዓለም በቶለሚዎስ ንጉሥ። አባቱ አግለዋ ይባላል፤ እናቱ ሀሬኪት ትባላለች። በአገዛዙ በጣም የተመሰገነ ንጉሥ ነበር። ከእስራኤል ውስጥ ሊቃውንትን መርጦ መጻሕፍተ ኦሪትንና መጻሕፍተ ነቢያትን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ በሚያስተረጉምበት ጊዜ ከጸሐፊዎቹና ከተርጓሚዎቹ አንዱ ስምዖን ነው።

ጌታ በተወለደ በ፵ ቀን ሕጻኑን በቤተ መቅደስ ታቅፎ፤ ወዲያው ትንቢት ተገልጾለት ይህ ልጅሽ በእስራኤል ውስጥ ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ነው አለ። እያደገ በዕለተ ስቅለት ጊዜ በእመቤታችን ድንግል ማርያም በልቧ የሚደርስባትን ኀዘን አስረዳት እንዲህም አላት፤ ከልብሽ የሚዘፋፍል ፍላጻ ይገባል ብሎ በዕለተ ስቅለት የሚደርስባትን መራራ ኀዘን አመለከተ ትንቢቱም ተፈጸመ።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔርን አመስግኖ እንዲህ ሲል። ወይቤ ሥዐር ለገብርከ፤ ባሪያህን በሰላም አሰናብተው ብሎ በሰላም አረፈ። ሉቃ ፪፡፳፱-፴፭ እንቀጽ ፳ ተፈጸመ።

የ፲፭ቱ ነቢያት ምቅናይ ሐተታ በዚህ ተፈጸመ።

እንግሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

## ለ፲፮ቱ ነቢያት ምቅናይ ሐተታ ምንጭ የሆኑ መጻሕፍት


1. መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ኪዳን ወልድ ክፍሌ /አስቃ/ 1948 ዓ.ም
2. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 50 እና 51 ዓ.ም
3. መጽሐፍ ቅዱስ 81 ብርሃንና ሰላም 1980
4. ሃይማኖተ አበው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1986 ዓ.ም
5. መጽሐፈ ስንክሣር 1993/94 ዓ.ም
6. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 1996 ዓ.ም ንግድ ማተሚያ ቤት
7. የኢንተርኔት መረጃ